# ተግተህ አገልግል

## የማርቆስ ወንጌል

ከዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ
ትርጉም:- ግርማዊ
እርማት:- ኃይሌ ጀናይ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

Copyright © 2003 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE DILIGENT. Copyright © 1987 by SP Publications, Inc. Cook Communications Ministries, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, Colorado 80918 U.S.A. All rights reserved.

# ማውጫ

1. እነሆ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ (ማርቆስ 1) ................. 1
2. የባሪያው ገጸ በረከት (ማርቆስ 2:1-3:12)..................... 15
3. ባሪያው፣ ሕዝቡና መንግሥቱ (ማርቆስ 3:13-4:34)..... 28
4. ባሪያው ያሸንፋል! (ማርቆስ 4:35-5:43)....................... 41
5. የእግዚአብሔርን ባሪያ የሚያምን ሰው
ይኖር ይሆን? (ማርቆስ 6:1-56)................................. 55
6. ባሪያ -- አስተማሪ (ማርቆስ 7:1-8:26)........................ 68
7. የባሪያው ምሥጢራት (ማርቆስ 8:27-9:50).................. 82
8. የባሪያው አያዎዎች(ማርቆስ 10)................................... 97
9. የእግዚአብሔር ባሪያ በኢየሩሳሌም
(ማርቆስ 11:1-12:44)..................................................... 111
10. የእግዚአብሔር ባሪያ ወደ ፊት የሚሆነውን ገለጠ
(ማርቆስ 13)................................................................. 126
11. የእግዚአብሔር ባሪያ ሲሠቃይ (ማርቆስ 14:1-15:20).. 138
12. የእግዚአብሔር ባሪያ ሥራውን ፈጸመ
(ማርቆስ 15:21-16:20)................................................... 152
የማጥኛ ጥያቄዎች.......................................................... 164

# መግቢያ

የማርቆስ ወንጌል ያገኙትን አጋጣሚ በመጠቀም እግዚአብሔርን ለማገልገል ደፋ ቀና ለሚሉ ሰዎች የሚሆን መጽሐፍ ነው። ይህ ወንጌል ጌታችን የሰዎችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ለማሟላት የሚያደርገውን «መሯሯጥ» ፍንትው አድርጐ ያሳያል። ማርቆስ ጌታችን ሰዎች እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ራሱ ሰዎችን ለማገልገል የመጣ የእግዚአብሔር መከራ ተቀባይ አገልጋይ መሆኑን ያብራራል። አገልግሎቱም ሕይወቱን ለእኛ በመስቀል ላይ እስከ መስጠት የጠለቀ ነበር።

ዓለማችን በስሜት የተጐዱ ወገኖች የሞሉባት ናት። እነዚህ ወገኖች አገልግሎታችንን ይፈልጋሉ። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በምድር ላይ ያኖረው እርሱ የጀመረውን አገልግሎት እንድንቀጥል ነው። ይሁንና፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ከተሳታፊዎች ይልቅ ታዛቢዎች፣ ከአገልጋዮች ይልቅ ዝነኞች በዝተዋል ብዬ እፈራለሁ።

በዚህ መጽሐፍ አማካኝነት የማርቆስን ወንጌል ማጥናታችን ለሌሎች በምናበረክተው አገልግሎት ትጉ ሠራተኞች እንድንሆን ካነቃቃን፣ ጊዜያችንን አላባከንንም ማለት ነው። እግዚአብሔር ሁላችንም የክብሩ አገልጋዮች እንድንሆን ይርዳን።

ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ

# የማርቆስ ወንጌል አስተዋጽኦ

**ጭብጥ:** አገልጋዩ ኢየሱስ ክርስቶስ

**ቁልፍ ጥቅስ:** ማርቆስ 10:45

**ቁልፍ ቃል:** «ወዲያውኑ»

1. የባሪያው መሰደድ – 1:1-13
2. ባሪያው በገሊላ ያካሄደው አገልግሎት – 1:14-9:50
   - ሀ. ተወዳጅነት ያተረፈበት ጊዜ፣ 1:14–6:29
   - ለ. ከሕዝቡ ፈቀቅ ያለበት ጊዜ፣ 6:30-9:32
   - ሐ. የፍጻሜ ጊዜ፣ 9:33-50
3. ባሪያው ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ – 10
4. ባሪያው በኢየሩሳሌም ያካሄደው አገልግሎት – 11-16
   - ሀ. ለሕዝቡ የሰጠው ትምህርትና ያስከተለው ውዝግብ፣ 11:1-12:44
   - ለ. ለደቀ መዛሙርቱ ያቀረበው ትምህርትና አገልግሎት፣ 13:1-14:31
   - ሐ. መታሠሩ፣ መመርመሩና መሰቀሉ፣ 14:32-15:47
   - መ. ትንሣኤውና ዕርገቱ፣ 16

# 1

## እነሆ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ!

### ማርቆስ 1

ዶ/ር ፖል ኤስ. ሪስ እንደሚሉት፣ «ወንጌል ውይይትም ውዝግብም አይደለም:: ነገር ግን እወጃ ነው!»

ማርቆስ ጊዜ ሳያጠፋ ፈጠን ብሎ ይህንኑ እወጃ በመጽሐፉ መክፈቻ ቃላት አማካኝነት ገልጿል:: በቀዳሚነት ወንጌሉን ለአይሁዶች የጻፈው ማቴዎስ መጽሐፉን የጀመረው በዘር ሐረግ ትረካ ነበር:: ይህንንም ያደረገው ለአይሁዳውያን አንባቢዎች ክርስቶስ የዳዊት ዙፋን ትክክለኛ ወራሽ መሆኑን በመረጃ ማረጋገጥ ስለነበረበት ነው:: ሉቃስ በዋናነት አጽንኦት የሰጠው የሰው ልጅ ላካሄዳቸው የርኅራኄ አገልግሎት በመሆኑ፣ የወንጌሉን የመጀመሪያ ምዕራፎች የሠዋው ስለ ልደቱ በመተረክ ነው:: ሉቃስ ከአምላክነቱ ይልቅ ለክርስቶስ ሰብአዊነት ትኩረት ሰጥቷል:: ለዚህም ምክንያቱ ግሪካውያን አንባቢዎቹ ፍጹም ሰው ወደ መሆኑ ደረጃ ካደገው ፍጹም ሕፃን ጋር ራሳቸውን እንደሚያስተሳስሩ በመገንዘቡ ነው::

የዮሐንስ ወንጌል ስለ ዘላለማዊነቱ በመናገር ይጀምራል:: ለምን? ምክንያቱም ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ለዓለም ሰዎች ሁሉ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር (ዮሐ. 20:31):: የዮሐንስ ወንጌል ርእሰ ጉዳይ የክርስቶስ አምላክነት ሲሆን፣ ዓላማው አንባቢዎቹ በአዳኙ እንዲያምኑና የዘላለምን ሕይወት ስጦታ እንዲቀበሉ ማበረታታት ነው::

የማርቆስ ወንጌልስ? ማርቆስ የጻፈው ለሮማውያን ሲሆን፣ ጭብጡም ባሪያው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚል ነው:: ከዚህ ወንጌል ውስጥ ቁልፍ ጥቅስ መምረጥ ካለብን፣ ጥቅሱ፣ «የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» የሚል ይሆናል (10:45)::

ማርቆስ ለሮማውያን መጻፉ የአጻጻፍ ስልቱንና አቀራረቡን ለመረዳት ያስችለናል:: በዚህ ወንጌል ውስጥ ትኩረት የተሰጠው በእንቅስቃሴ ላይ ነው:: ማርቆስ ኢየሱስ በጥድፊያ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የሁሉንም ዓይነት ሰዎች ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ማሟላቱን ያብራራል:: ማርቆስ ከሚወዳቸው ቃላት አንዱ «ወዲያውኑ» የሚለው ሲሆን፣ አርባ አንድ ጊዜያት ጠቅሶታል:: ማርቆስ አጽንኦት የሰጠው ከጌታችን ንግግር ይልቅ ለተግባራቱ በመሆኑ፣ ከክርስቶስ ስብከቶች ብዙዎቹን አላካተተም:: ማርቆስ ክርስቶስን መከራ ለሚቀበሉ ሰዎች ለማገልገልና ለዓለም ኃጢአት ለመሞት እንደ ተላከ የእግዚአብሔር ባሪያ አድርጐ ይገልጸዋል:: በዚህ ወንጌል ውስጥ ስለ ክርስቶስ ልደትም ሆነ የዘር ሐረግ የተገለጸ ነገር የለም:: ይህ ለባሪያ አስፈላጊ አይሆንም::

በዚህ የመክፈቻ ምዕራፍ ውስጥ፣ ማርቆስ ስለ እግዚአብሔር አገልጋይ ሦስት ጠቃሚ እውነቶችን ይገልጻል::

## 1. የባሪያው ማንነት (ማርቆስ 1:1-11)

ማርቆስ ይህን ባሪያ ማን ይለዋል? ማርቆስ ክርስቶስ ስለ ራሱ የተናገረው ሁሉ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የአያሌ አስተማማኝ ምስክሮችን መረጃ ይመዘግባል::

ከእነዚህ ምስክሮች የመጀመሪያው የመጽሐፉ ደራሲ የሆነው *ዮሐንስ ማርቆስ* መሆኑን በድፍረት መስክሯል (ቁ.1):: ማርቆስ ከጻፋቸው ነገሮች አንዳንዶቹን በዓይኖቹ ሳይመለከት የቀረ አይመስልም:: ማርቆስ የኖረው ከእናቱ ማርያም ጋር በኢየሩሳሌም ከተማ ነበር:: የከተማይቱ አማኞች ተሰባስበው የሚያመልኩት በእነርሱ ቤት ውስጥ ነበር (የሐዋ. 12:1-19):: አያሌ ምሁራን ማርቆስ በማርቆስ 14:51-52 የተገለጸው ወጣት መሆኑን ያምናሉ:: ጴጥሮስ ማርቆስን «ልጄ» ብሎ መጥራቱ (1ኛ ጴጥ. 5:13)፣ ማርቆስን በክርስቶስ ወዳለው እምነት የመራው ጴጥሮስ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማርቆስ የጴጥሮስ አስተርጓሚ እንደነበረ ያስረዳል:: የማርቆስ ወንጌልም የስምዖን ጴጥሮስን ግላዊ ምስክርነት ገጠመኞች ያንጸባርቃል::

*ወንጌል* የሚለው ቃል «የምሥራች» ማለት ነው:: የማርቆስ አድምተኞች ለሆኑት ሮማውያን «ወንጌል» ማለት «ስለ ንጉሡ የሚነገር አስደሳች ዜና» ማለት ነበር:: «የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል» የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ዓለም መጥቶ ለኃጢአታችን መሞቱን የሚገልጽ መልካም የምሥራች ነው:: ኃጢአቶቻችን ይቅር ሊባሉ እንደሚችሉ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ልንሆንና ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ እንደምንሄድ የሚያስረዳ የምሥራች ነው:: ይህ በኃጢአት፣ በሞትና በሲዖል ላይ የታወጀ ድል ነው (1ኛ ቆሮ. 15:1-8፣ 51-52፤ ገላ. 1:1-9)::

ሁለተኛው ምስክርነት *ነቢያት* የሰጡት ነው (ማር. 1:2-3):: ማርቆስ ከብሉይ ኪዳን ሁለት ምንባቦችን ጠቅሷል፣ ሚል. 3:1 እና ኢሳ. 40:3:: (በተጨማሪም፣ ዘጸ. 23:20ን አንብብ::) *መልእክተኛና ድምፅ* የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ለልጁ መንገድ ለማዘጋጀት የላከውን ነቢይ (መጥምቁ ዮሐንስን) ያመለክታሉ (ማቴ. 3፤ ሉቃስ 3:1-18፤ ዮሐ. 1:19-34):: በጥንት ዘመን፣ አንድ ንጉሥ አንድን አካባቢ ከመጐብኘቱ በፊት መንገዱን የሚያዘጋጅ መልእክተኛ ቀደም ብሎ ይላክ ነበር:: ይህም መንገዱንና ሰዎችን ለንጉሡ ጉብኝት ማዘጋጀትን ይጨምር ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስ ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ በመጋበዝ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ አዘጋጅቷል:: ኢሳይያስና ሚልክያስ ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ አምላክ መሆኑን መስክረዋል::

ቀጣዩ ምስክር *መጥምቁ ዮሐንስ* ሲሆን (ማር. 1:4-8)፣ እርሱም ክርስቶስ ከነቢያት ሁሉ እንደሚበልጥ የተናገረው አገልጋይ ነው (ማቴ. 11:1-15):: መጥምቁ ዮሐንስ በአለባበሱ፣ በአኗኗሩና በንስሐ ስብከቱ ከኤልያስ ጋር ይመሳሰላል (2ኛ ነገ. 1:8፤ ሚል. 4:5፤ ማቴ. 17:10-13፤ ሉቃስ 1:13-17 አንብብ):: መጥምቁ ዮሐንስ ያገለገለበት «ምድረ በዳ» በምዕራባዊ የሙት ባሕር ዳርቻ የሚገኝ ጠፍ መሬት ነው:: መጥምቁ ዮሐንስ ሕዝቡ አያት ቅድመ አያቶቻቸው ለአርባ ዓመታት ከተቅበዘበዙበት መልክዓ ምድራዊ ምድረ በዳ በከፋ «መንፈሳዊ ምድረ በዳ» ውስጥ መሆናቸውን በተምሳሌት እየገለጸ ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስ ሕዝቡ በ«ኢያሱ»አቸው (በኢየሱስ) አምነው

ከመንፈሳዊ ምድረ በዳ ወጥተው ወደ ርስታቸው እንዲገቡ ጠራቸው::

ዮሐንስ ራሱን ሳይሆን ክርስቶስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጓል (ዮሐ. 3:25-30 አንብብ):: ዮሐንስ ንስሐ የሚገቡትን ሰዎች በውኃ ያጠምቃቸው የነበረ ሲሆን፣ «የሚመጣው» ክርስቶስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃቸዋል (የሐዋ. 1:4-5):: ይህ ግን የዮሐንስ ጥምቀት ተቀባይነት እንዳልነበረው (ማቴ. 21:23-27 አንብብ)፣ ወይም አንድ ቀን የውኃ ጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደሚተካ አያመለክትም (ማቴ. 28:19-20 አንብብ):: ነገር ግን የዮሐንስ መልእክትና ጥምቀት ሰዎች መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመገናኘትና ለመቀበል እንዲዘጋጁ የሚያስችሉ መሆናቸውን ያሳያል:: የጌታችን ሐዋርያት በዮሐንስ መጠመቃቸው አያጠራጥርም (ዮሐ. 4:1-2፤ የሐዋ. 1:21-26 አንብብ)::

በመጨረሻም፣ ማርቆስ የእግዚአብሔርን ባሪያ ማንነት ለማስመስከር *አብንና መንፈስ ቅዱስን* ዋቢ ጠቅሷል (ማር. 1:9-11):: ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ፣ ርግብ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል ወረደበት:: አብም ከሰማይ ድምፁን በማሰማት፣ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ:: በስፍራው የነበሩት ሰዎች ርግቧ ስትወርድ አላዩም:: የአብንም ድምፅ አልሰሙም:: ክርስቶስና ዮሐንስ ግን ይህንኑ ሁኔታ መስክረዋል (ዮሐ. 1:29-34 አንብብ):: *«የምወደው»* የሚለው ቃል ፍቅርን ብቻ ሳይሆን «አንድያነትንም» ያመለክታል:: አብ ከሰማይ ያሰማው ድምፅ መዝሙር 2:7ን እና ኢሳይያስ 42:1ን ያስታውሰናል::

በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚከተሉት ጥቅሶች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያስረዳሉ:– 1:1፣ 11፤ 3:11፤ 5:7፤ 9:7፤ 12:1-11፤ 13:32፤14:61-62፤ 15:39:: ማርቆስ የጻፈው ስለ አንድ ተራ አይሁዳዊ ባሪያ አልነበረም:: እርሱ የጻፈው ለዓለም ኃጢአቶች ለመሞት ከሰማይ ስለወረደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው::

እውነት ነው ክርስቶስ ባሪያ ነው:: ነገር ግን እርሱ በጣም የተለየ ባሪያ ነው:: ለሌሎች መንገድን የሚያዘጋጀውና

መምጣታቸውን የሚያውጀው ባሪያ ነው:: ነገር ግን ሌሎች ለክርስቶስ መንገድ አዘጋጅተው መምጣቱን አውጀዋል! ሰማይም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታዋለች! ይህ ባሪያ እግዚአብሔር ወልድ ነው::

## 2. የባሪያው ሥልጣን (ማርቆስ 1:12-28)

ባሪያ ከሌሎች ሥልጣን ሥር ሆኖ ትእዛዛትን እንደሚቀበል እንገነዘባለን:: የእግዚአብሔር ባሪያ ግን አጋንንትን ሳይቀር ያዝዛል:: እናም ይታዘዙለታል:: በዚህ ክፍል፣ ማርቆስ ጌታችን የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን የሚያሳዩ ሦስት ትዕይንቶችን ገልጿል::

*ትዕይንት አንድ – መፈተኑ* (1:12-13):: ማርቆስ፣ ማቴዎስ (4:1-11) እና ሉቃስ (4:1-13) እንዳደረጉት ስለ ክርስቶስ መፈተን የሚስረዳውን ሙሉ ታሪክ አላካተተም:: ዮሐንስ ደግሞ ሌሎች የተዉአቸውን አንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮች አካትቷል:: መንፈስ ወደ ምድረ በዳ *«አወጣው»*:: ይህ ማርቆስ አጋንንትን ስለማስወጣት አሥራ አንድ ጊዜያት ያህል የጠቀሰው ጠጣር ያለ ቃል ነው:: ይህ ቃል *በኒው አሜሪካን* የመጽሐፍ ቅዱስ እትም «ገፋፋው» ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፣ *ኒው ኢንተርናሽናል* እትም *«መራው»* ብሎታል:: ይህ ጌታችን ሰይጣንን ለመጋፈጥ ፈቃደኛ አለመሆኑን ወይም መፍራቱን አያሳይም:: ነገር ግን ማርቆስ የገጠመኙን ጥልቀት ለማሳየት የመረጠበት መንገድ ነው:: ጌታችን በሰማያዊ ድምፅና ርግብ ክብር እየተደሰተ ብዙ ጊዜ አላሳለፈም:: ባሪያው የሚፈጽመው ተግባር ስለነበረው በፍጥነት ይህንኑ ወደ ማድረግ አመራ::

ጠቅለል ባለ መልኩ፣ ማርቆስ ሁለት ተምሳሌታዊ ሥዕሎችን ያስጨብጠናል:: ጌታችን ለአርባ ቀናት መፈተኑ እስራኤላውያን ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ ውስጥ መቅበዝበዛቸውን ያስታውሰናል:: እስራኤላውያን ፈተናቸውን መቋቋም ተስኗቸው ቢወድቁም፣ ጌታችን ግን በድል ተወጥቷል:: ክርስቶስ ጠላትን ካሸነፈ በኋላ፣ አዲስ ሕዝብን መራ:: እነዚህም ሰዎች ወደ መንፈሳዊ ርስታቸው እንዲገቡ ጥሪ የተደረገላቸው ነበሩ:: *«ኢየሱስ»* የሚለው ስም የ*«ኢያሱ»* (ጆሹዋ) ግሪካዊ ቅርጽ

ስለሆነ፣ በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት መመልከት ይቻላል::

ሁለተኛው ሥዕል የ«ኋለኛው አዳም» ነው (1ኛ ቆሮ. 15:45):: የመጀመሪው አዳም በውብ የአትክልት ስፍራ ተፈትኖ ሲወድቅ፣ ሁለተኛው አዳም በአደገኛ ምድረ በዳ ውስጥ ተፈትኖ አሸንፏል:: አዳም ኃጢአት ከመሥራቱ የተነሣ በፍጥረታት ላይ «የመግዛት» ሥልጣኑን አጥቷል (ዘፍጥ. 1:28፤ መዝ. 8):: ነገር ግን ያ አገዛዝ በክርስቶስ በኩል ለሚያምኑበት ሁሉ ተመልሶላቸዋል (ዕብ. 2:6-8):: ኢየሱስ ከዱር አራዊት ጋር የቆየ ቢሆንም፣ አልጎዱትም:: ይህም ጌታችን ተመልሶ መንግሥቱን በሚመሠርትበት ጊዜ የሚገለጸውን የሰላምና የጽድቅ ዘመን የሚያሳይ ነው (ኢሳ. 11:9፤ 35:9):: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ክርስቶስ ሥልጣን ያለው ባሪያ ነው!

*ትእይንት ሁለት – ስብከቱ* (1:14-22):: እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን እውነት በሥልጣን የተናገረ ማንም የለም (ማቴ.7:28-29 አንብብ):: አንዳንዶች እንደሚሉት፣ ጸሐፍት የባለሥልጣናትን ድምፅ ሲያስተጋቡ፣ ክርስቶስ ግን በሥልጣን ተናግሯል:: ጌታችን ቀደም ሲል በሌሎች ስፍራዎች ስላገለገለ፣ ማርቆስ በዚህ ስፍራ የገለጸው የአገልግሎቱን ጅማሬ አይደለም (ዮሐ. 1:35-4:4):: ዮሐንስ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ክርስቶስ ለምን ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደ መጣ ነው:: ይኸውም ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ስላሰረው፣ ክርስቶስ ስፍራ ለመቀየር ጥበብን እንደ ተጠቀመ የሚያሳይ ነው:: በነገራችን ላይ፣ ክርስቶስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር የተነጋገረው በዚህ ጉዞው ወቅት ነበር (ዮሐ. 4:1-45)::

የጌታችን መልእክት የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል፣ ወይም አንዳንድ ምንባቦች እንደሚሉት «የእግዚአብሔር ወንጌል» ነበር:: አብዛኞቹ አይሁዶች «የእግዚአብሔር መንግሥት» የሚለውን ሐረግ «ፖለቲካዊ አብዮት» አድርገው ቢገነዘቡትም፣ ይህ የክርስቶስ አሳብ አልነበረም:: መንግሥቱ በሰዎች ልብ ውስጥ የመንገሡ ጉዳይ ነበር:: ይህ መንፈሳዊ እንጂ ፖለቲካዊ ጉዳይ አልነበረም:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት

የሚለው የምሥራቹን በማመንና ዳግም በመወለድ ብቻ ነው (ዮሐ. 3:1-7)::

ወንጌሉ «የእግዚአብሔር ወንጌል» የተባለው ከእግዚአብሔር በመምጣቱና እኛን ወደ እግዚአብሔር በማምጣቱ ምክንያት ነው:: በአዳኙ ማመን ሰዎችን ወደ መንግሥቱ ስለሚያመጣ «የመንግሥት ወንጌል» ተብሎ ተጠርቷል:: «የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል» የተባለውም ክርስቶስ የወንጌሉ እምብርት በመሆኑ ነው:: ያለ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ የምሥራች ሊኖር አይችልም:: ጳውሎስ እንደሚለው፣ ይህ «የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል» ነው (የሐዋ. 20:24):: ምክንያቱም ከጸጋ ውጭ ደኅንነት ሊኖር አይችልም (ኤፌ. 2:8-9):: አንድ ወንጌል ብቻ አለ (ገላ. 1:1-9):: ይህም ወንጌል ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ በፈጸመው ተግባር ላይ ያማከለ ነው (1ኛ ቆሮ. 15:1-11)::

ኢየሱስ ሰዎች ንስሐ ገብተው (አእምሯቸውን ለውጠው) እንዲያምኑ ሰብኳል (የሐዋ. 20:21 አንብብ):: እግዚአብሔር አማኞች ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ የሚጠብቅ ቢሆንም፣ ንስሐ መግባት ብቻውን ሊያድነን አይችልም:: በኢየሱስ ክርስቶስና በደኅንነት የተስፋ ቃሎቹ ማመንም ይጠበቅብናል:: እምነት ያልታከለበት ንስሐ ወደ ጸጸት ሊለወጥ ይችላል፣ ጸጸት ደግሞ የበደለኛነት ስሜት የሚያውካቸውን ሰዎች ሊያጠፋ ይችላል (2ኛ ቆሮ. 7:8-10፤ ማቴ. 27:3-5 አንብብ)::

ኢየሱስ በሥልጣን ከመስበኩ የተነሣ በተለያዩ ሙያዎች የተሠማሩትን ሰዎች ጠርቶ ደቀ መዛሙርቱ ሊያደርጋቸው ችሏል:: አራት ዓሣ አጥማጆችን ከሥራቸው ሊያስተጓጉልና መረቦቻቸውን ጥለው እንዲከተሉት ሊጠይቅ የሚችል ማን ነው? ከአያሌ ወራት በፊት ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ጋር ተገናኝቶ ነበር:: እነርሱም በእርሱ አምነዋል (ዮሐ. 1:35-49 አንብብ):: ይህ ለደቀ መዛሙርትነት እንጂ ለእምነትና ለደኅንነት መጠራታቸው አልነበረም:: ዘብዴዎስ ሠራተኞችን መቅጠሩ የዓሣ አጥማጅነት ሥራው የተሳካ መሆኑንና ግለሰቡም ሀብታም መሆኑን ያስረዳል:: በተጨማሪም ያዕቆብና ዮሐንስ ለክርስቶስ ጥሪ ምላሽ በመስጠታቸው አባታቸውን

አለመበደላቸውን ያሳያል:: ዘብዴዎስ በሠራተኞቹ እገዛ ሥራውን ሊያከናውን ይችል ነበር::

«ሰው አጥማጆች» የሚለው ሐረግ ኢየሱስ የፈጠረው ሳይሆን፣ በዚያን ጊዜ በማስተማርና በማግባባት «የሰዎችን አእምሮ የሚማርኩ» ፈላስፎችና መምህራን የሚጠሩበት የተለመደ ስያሜ ነበር:: ሰዎችን በትምህርታቸው ስበው ደቀ መዛሙርት ያደርጉ ነበር:: ከጌታችን ደቀ መዛሙርት መካከል እስከ አራት የሚደርሱት ዓሣ አጥማጆች ነበሩ (ዮሐ. 21:1-3):: የውጤታማ ዓሣ አጥማጆች መልካም ብቃቶች የጠፉትን ሰዎች በመማረኩ ከባድ አገልግሎት ወቅት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጉ ነበር:: ብርታት፣ አብሮ የመሥራት ችሎታ፣ ትዕግሥት፣ ጉልበት፣ ጽናት፣ እምነትና ቆራጥነት ለአገልግሎታቸው አስፈላጊዎች ነበሩ:: በዓሣ አጥማጅነት ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በቀላሉ ሥራቸውን የሚተዉ ወይም የሚያጉተመትሙ ሊሆኑ አይችሉም!

ኢየሱስ በሜዳ ላይ ብቻ ሳይሆን በምኩራብም ውስጥ አስተምሯል:: የአይሁድ ምኩራቦች የተሠሩት ቤተ መቅደሱ ከፈረሰና ሕዝቡ በምርኮ ወደ ባቢሎን ከሄደ በኋላ ነበር:: ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ የሆኑ አሥር አይሁዶች ባሉበት ስፍራ ሁሉ ምኩራቦች ይዘጋጁ ነበር:: በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚደረገው መሥዋዕት የማቅረብ ተግባር በምኩራብ ውስጥ አይካሄድም:: ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ፣ ጸሎትና አምልኮ ይከናወናል:: አገልግሎቶቹን የሚመሩት ካህናት ሳይሆኑ ተራ ሰዎች ነበሩ:: አገልግሎቱን የሚቆጣጠር የሽማግሌዎች ቦርድ የሚቋቋም ሲሆን፣ ይህ ቦርድ በአንድ የምኩራብ «አለቃ» ሊቀመንበርነት ይሰባሰባል (ማር. 5:22):: ከሌላ ስፍራ የመጡ መምህራን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንዲያነቡና እንዲያስተምሩ ይጋበዙ ነበር:: ኢየሱስ በምኩራቦች ውስጥ የማስተማር ነጻነት ያገኘው በዚሁ ምክንያት ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ሆኗል (የሐዋ. 13:14-16፤ 14:1፤ 17:1-4)::

ጌታችን ዋና የአገልግሎቱን ማዕከል ያቋቋመው በቅፍርናሆም ሲሆን፣ በጴጥሮስና እንድርያስ ቤት ውስጥ ወይም አካባቢም ሳይሆን አይቀርም (ማር. 1:29):: ዛሬ በቅድስቲቱ ከተማ ውስጥ

የቅፍርናሆም ምኲራብ ፍርስራሾችን መመልከት ይቻላል:: ይህ ምኲራብ ግን ኢየሱስ ያመለከበት ስፍራ አይደለም:: ሰዎች ቅዳሜ፣ ሰኞና ሐሙስ ለአምልኮ ይሰባሰቡ ነበር:: ኢየሱስ እንደ ታማኝ አይሁዳዊ ወደ ምኲራብ በመሄድ ሰንበትን አክብሯል:: ቃሉን ባስተማረ ጊዜም፣ ሰዎች በሥልጣኑ ተደነቁ::

የማርቆስን ወንጌል በምታነብበት ጊዜ የሕዝቡን የስሜት ምላሽ መመዝገብ እንደሚያስደስተው ልትመለከት ትችላለህ:: በምኲራቡ ውስጥ የነበረው ሕዝብ በትምህርቱና በመፈወስ ኃይሉ «ተደንቀዋል» (ቍ. 27፤ በተጨማሪም 2:12፤ 5:20፣42፤ 6:2፣51፤ 7:37፤ 10:26፤ 11:18 አንብብ):: ማርቆስ ጌታችን በናዝሬት በሰዎች አለማመን መደነቁን ሳይቀር ጽፎታል (6:6):: ይህም ትረካው የማይሰለች ጣፋጭ ለዛ እንዲኖረው አድርጓል::

*ትዕይንት ሦስት – ትእዛዙ* (1:23-28):: ይህ ሰው በአጋንንት መያዙን ሳያሳውቅ ምን ያህል የምኲራብ አገልግሎቶችን ተካፍሎ ይሆን? አጋንንቱን ያጋለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር:: ኢየሱስ አጋንንቱን ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን፣ ማንነቱን (የአዳኙን ማንነት) ሳይናገር ከሰውዬው እንዲወጣ አዝዞታል:: አዳኙ ማንነቱን ለሰዎች ለማሳወቅ የሰይጣንንና የሠራዊቱን እገዛ እንደማይፈልግ አመልክቷል (የሐዋ. 16:16-24)::

አጋንንቱ የኢየሱስን ማንነት (የሐዋ. 19:13-17) እና ከእርሱ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር እንደሌለ ያውቅ ነበር:: አጋንንቱ ብዙ ቁጥር መጠቀሙ በውስጡ ካደረበት ሰው ጋር ምን ያህል እንደ ተቀራረበ ያሳያል:: አጋንንቱ የክርስቶስን ሰብአዊነት («የናዝሬቱ ኢየሱስ») እና አምላክነት («የእግዚአብሔር ቅዱስ») ተረድቷል:: በተጨማሪም፣ ኢየሱስ በፍርድ ወደ ጥልቁ እንዳይልከው መፍራቱንም ተናዝዟል:: ዛሬም ይህንን አጋንንት ያደረበትን ግለሰብ የሚመስሉ ሰዎች አሉ:: እነዚህ ሰዎች በኃጢአታቸው ጠፍተው ሳሉ በመንፈሳዊ ስብሰባዎች ላይ የኢየሱስን ማንነት ለይተው ያውቃሉ፣ ይንቀጠቀጡለትማል! (ያዕ. 2:19 አንብብ::)

«ዝም በል» የሚለው እንዳይናገር መከልከሉን ያሳያል። ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ ባደረገ ጊዜ ይህንኑ ቃል ተጠቅሟል (ማር. 4:39)። አጋንንቱ የመጨረሻውን ጥቃት ከሰነዘረ በኋላ፣ ለእግዚአብሔር ባሪያ ሥልጣን ተገዝቶ ከሰውዬው ወጣ። በዚህም ጊዜ በምኩራቡ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተደነቁ፤ ደነገጡም። አንድ አዲስ ትምህርትና ኃይል እንደ ተከሰተ ተገነዘቡ። የጌታችን ቃላትና ሥራዎች ሁልጊዜም አብረው ይሄዳሉ (ዮሐ. 3:2)። ስለ ትምህርቱና ስለ ተአምራቱ አብዝቶ በመናገሩ፣ የኢየሱስ ዝና እየተሰራጨ ይሄድ ጀመር። ጌታችን ከአይሁዶችና ሮማውያን ጋር የሚፈጠረውን ግጭት ስለሚያውቅ፣ እንዲህ ዓይነቱን የወሬ መዛመት አያበረታታም ነበር። አይሁዶች ሊከተሉት የሚፈልጉት የፈውስ ኃይሉን በመሻት ሲሆን፣ ሮማውያን መንግሥታቸውን ለመጣል የሚያሤር አይሁዳዊ ዓማፂ አድርገው ይመለከቱት ነበር። ለዚህ ነበር ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ሕዝቡ ስለ ማንነቱ እንዳይናገሩ የሚጠይቃቸው (ማር. 1:44፤ 3:12፤ 5:43፤ 7:36-37፤8:26፣ 30፤ 9:9)። ሕዝቡ ግን ቃሉን ባለመታዘዝ ያዛመቱት ዜና ችግሮችን አስከትሎበታል።

## 3. የባሪያው ርኅራኄ (ማርቆስ 1:29-45)

በዚህ ክፍል፣ አዳኙ ለተቸገሩት ርኅሩኅ መሆኑን የሚያሳዩ ሁለት የፈውስ ተአምራት ተገልጸዋል። እንዲያውም፣ ለተቸገሩት የአዳኙ ፍቅር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ የሰንበት ጊዜ ካበቃ በኋላ ለብዙ ሕዝብ አገልግሏል።። ይህም ለዕርዳታ መምጣት የሚቻልበት ጊዜ ነበር። የእግዚአብሔር ባሪያ አጋንንት ያደሩባቸውንና ለምጻሞችን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ለመጥራትና የፍቅር አገልግሎቱን ለማበርከት ተዘጋጅቶ ነበር።

ኢየሱስና አራቱ ደቀ መዛሙርት ከምኩራብ ወጥተው የሰንበት ምሳ ይበሉ ዘንድ ወደ ጴጥሮስና እንድርያስ ቤት ሄዱ። ጴጥሮስ ሚስቱ ታማሚ እናቱን ለመንከባከብ በመገደዷ ምክንያት እንደተለመደው ልታስተናግዳቸው ባለመቻሏ እንግዶቹን ይቅርታ መጠየቅ ሳይኖርበት አልቀረም። ስለ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ባናውቅም፣ ጴጥሮስ ባለ ትዳር እንደነበረ ተገልጿል (1:30)።

ጴጥሮስና እንድርያስ ጓደኞቻቸው የሆኑትን ያዕቆብንና ዮሐንስን ብቻ ሳይሆን፣ ጌታንም ወደ ቤታቸው አምጥተዋል:: ይህ ልንከተለው የሚገባን መልካም አርአያነት ነው:: ኢየሱስ በረከቶቻችንንና ድካሞቻችንን ይካፈል ዘንድ ወደ ቤታችን ልንወስደው ይገባል:: ለጴጥሮስና ቤተሰቡ የእግዚአብሔርን ልጅ በደሳሳ ጎጆአቸው ውስጥ በእንግድነት ማስተናገድ ምንኛ ታላቅ ክብር ነበር:: ብዙም ሳይቆይ እንግዳው አስተናጋጅ ሆኖ ተገኘ:: በሌላ ጊዜም እንግዳው በጴጥሮስ ታንኳ ውስጥ የታንኳ ነጂ ሆኖ ተገኝቷል (ሉቃስ 5:1-11)::

ሰዎቹ ስለ ታመመችው ሴት ለኢየሱስ ነገሩት:: ይህንን ያደረጉት እንደሚፈውሳት በማመን ነበር:: እርሱም ይህንኑ አድርጓል:: ትኩሳቱ ወዲያውኑ ስለ ለቀቃት ተነሥታ የሰንበት ምግብ ልታቀርብላቸው ችላለች:: ኃይለኛ ትኩሳት ይዞህ የሚያውቅ ከሆነ፣ ምን ያህል እንደሚያሠቃይ ታውቃለህ:: ትኩሳቱ ከለቀቀ በኋላ እንኳን የቀድሞውን ብርታት መልሶ ለማግኘት ብዙ ጊዜ ይወስዳል:: በዚህ ጊዜ ግን እንደዚህ አልሆነም! ትኩሳቱ ከለቀቃት በኋላ ወዲያውኑ ጌታን ለማገልገል ችላለች:: ይህም ለጌታችን የምናበረክተው አገልግሎት እርሱን ከምናመሰግንባቸው ምርጥ መንገዶች አንዱ እንደሆነ ያሳያል::

የዚህ ተአምር ውጤት ምን ነበር? የፀሐይን መጥለቅ ተከትሎ የሰንበት ቀን ሲጠናቀቅ፣ የከተማዪቱ ነዋሪዎች በነቂስ ወጥተው ወደ ጴጥሮስ ቤት መጡ! የታመሙትንና የተጐዱትን ሁሉ ይዘው መጡ:: ጌታም (በድካም መዛሉ ባያጠራጥርም) ሁሉንም ፈወሳቸው:: የግሪኩ ግሥ እንደሚያመለክተው፣ ሰዎቹ በሽተኞችን ባለማቋረጥ ወደ እርሱ ያመጡ ነበር:: ይህም የመኝታ ጊዜውን ሳይሻሙ እንዳልቀሩ ያሳያል:: በማርቆስ 1:32 አጋንንት ያደረባቸው ከበሽተኞች ተለይተዋል:: ይህም ሰይጣን አካላዊ ጉዳት ሊያደርስ ቢችልም፣ የበሽታ ሁሉ ምንጩ ሰይጣን ነው ብለን እንዳናስብ ያስገነዝበናል::

ኢየሱስ በአገልግሎት ምክንያት አምሽቶ መተኛቱ ማለዳ በተወሰነው ሰዓት ከአባቱ ጋር እንዳይገናኝ አይከለክለውም:: የእግዚአብሔር ጻድቅ ባሪያ ማለዳ ማለዳ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገናኝ የሚያሳየውን ትንቢታዊ ገለጻ ከኢሳይያስ 50:4

አንብብ:: ይህ ልንከተለው የሚገባን ምንኛ ታላቅ ምሳሌ ነው! ፍጹም የተገራ የጸሎት ሕይወት የነበረው ኢየሱስ እንዲህ ባለ ኃይልና ሥልጣን ማገልገሉ የሚያስገርም አይሆንም (ማር. 9:28-29፤ 6:46፤ 14:32-38 አንብብ)::

ሕዝቡ ቃሉን ለመስማት ሳይሆን ፈውሱን ለማግኘትና ተአምራት ሲሠራ ለማየት በመሻታቸው ፣ እንደገና ተመልሰው ወደ እርሱ መጡ:: እርሱ ግን ከሕዝቡ ጋር ለመገናኘት ሳይጣደፍ ወንጌሉን ሊሰብክ ወደሚችልባቸው ሌሎች ከተሞች አመራ:: ይህም ጴጥሮስን አስደነቀው:: ጴጥሮስ የሕዝቡን ከንቱነት፣ አለማመንና ለእግዚአብሔር ቃል ፍላጐት ማጣታቸውን አልተገነዘበም ነበር:: ኢየሱስ እዚያ ሆኖ በሽተኞችን ከመፈወሱ ይልቅ በሌሎች ስፍራዎች ወንጌሉን መስበኩ የበለጠ ጠቃሚ መሆኑን ገልጾአል:: የሰዎች የአደባባይ እዩኝታ ቅድሚያ የሰጠውን ጉዳይ እንዲለውጥበት አልፈለገም::

ጌታችን ትኩሳት ያመማትን ሴት መፈወሱ ርኅራኄውን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ለምጻሙን መዳሰሱ ግን ከግንዛቤያችን በላይ ነው:: ሰዎችን ከርኩሰት ለመጠበቅ ሲባል ለምጻሞች ከአንድ ሰው ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ማንነታቸውን የመናገር ግዴታ ነበረባቸው (ዘሌዋ. 13:45-46):: ይህ ሰው ኢየሱስ ሊፈውሰው እንደሚችል ቢያውቅም፣ ፈቃደኛ ስለ መሆኑ እርግጠኛ አልነበረም:: ዛሬም በኃጢአታቸው የጠፉ ሰዎች ይህንን አላስፈላጊ ስጋት ያንጸባርቃሉ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እንጂ (1ኛ ጢሞ. 2:4)፣ ኃጢአተኞች እንዲጠፉ (2ኛ ጴጥ. 3:9) የማይፈልግ መሆኑን በግልጽ አመልክቷል::

በዘሌዋውያን 13 ለለምጽነት «መፈተሻ» የተሰጡትን ዝርዝሮች በምትመለከትበት ጊዜ፣ ይኼ በሽታ የኃጢአት መግለጫ መሆኑን ትገነዘባለህ:: እንደ ኃጢአት ሁሉ፣ ለምጽ ከቆዳ የጠለቀ (ቊ. 3)፣ ወደ ሌሎች የሚተላለፍ (ቊ. 5-8)፣ የሚያረክስና ከሰዎች የሚነጥል (ቊ. 44-46)፣ ነገሮችን ለእሳት የሚዳርግ (ቊ. 47-59) መሆኑ ተገልጿል:: በአዳኙ ያላመነ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ይኼ ግለሰብ ከነበረበት አካላዊ ሁኔታ በከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል::

ኢየሱስ ለዚህ ሰው በመራራቱ ፈውሶታል (6:34፣ 8:2፣ 9:22 አንብብ):: ይህንንም ያደረገው ግለሰቡን በመዳሰስና ቃል በመናገር ነበር:: ይህም ግለሰቡ ከረዥም ዘመናት በኋላ ያገኘው የፍቅር ዳሰሳ መሆኑ አያጠራጥርም:: እንደ ትኩሳቱ ሁሉ ለምጹም ከሰውዬው በፍጥነት ተወገደ!

ቀደም ሲል ለተጠቀሱት ምክንያቶች ሲል ኢየሱስ ሰውዬው የሆነውን ለሁሉም እንዳይናገር አዘዘው:: ነገር ግን ወደ ካህናት በመሄድ በዘሌዋውያን 14 የተሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲያደርግ ነገረው:: ይህም ግለሰቡ ከለምጹ እንደ ነጻ ታውቆ ወደ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት እንዲመለስ የሚያስችለው እርምጃ ነበር:: ሰውዬው ግን ኢየሱስ ለማንም እንዳይናገር የሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፍ፣ የመንጻቱን ዜና በሰፊው አሰራጨ:: እኛ ግን ኢየሱስ ተናገሩ እያለን ዝም ብለን እንቀመጣለን! ከኢየሱስ እርዳታ ለማግኘት የሚመጡ ሰዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ችግሮችን ፈጠረበት:: ይህ ምናልባትም እንደ ዕቅዱ ቃሉን እንዳያስተምር ሳያደናቅፈው አልቀረም (ማር. 1:38)::

በዘሌዋውያን 14 የተገለጸው ሥርዓት የደኅንነትን ሥራ የሚያንጸባርቅ ውብ ሥዕል ያሳያል:: ሁለቱ ወፎች የጌታችንን አገልግሎት ሁለት ገጽታዎች ያመለክታሉ:: እነዚህም ሥጋው መበስበሱና መሞቱ (ወፍ ማሰሮ ውስጥ ገብታ ትገደል ነበር)፣ እንዲሁም ትንሣኤውና ዕርገቱ (ወፏ ደም ውስጥ ተነክራ ትለቀቅ ነበር) ናቸው:: ደሙ የሰውዬው ቀኝ ጆሮ (የእግዚአብሔር ቃል)፣ ቀኝ የአውራ ጣት (የእግዚአብሔር ሥራ) እና ቀኝ የእግር አውራ ጣቱ (በእግዚአብሔር አረማመድ ላይ) ይደረግ ነበር:: ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተምሳሌት የሆነው ዘይት በደሙ ላይ ይጨመር ነበር:: መጀመሪያ ደሙ ካልተረጨበት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰው ሰውነት አይመጣም::

ከዚህ ምዕራፍ አንዳንድ ጠቃሚ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ማግኘት አለብን:: <u>በመጀመሪያ ደረጃ</u>፣ የሰው ልጅ ባሪያ ሆኖ መጥቷል:: ይህም ባሪያ መሆን ከጥሪዎች ሁሉ የላቀ መሆኑን ያሳያል:: ጌታ ኢየሱስን የምንመስልበት ዋንኛው መንገድ እንደ

እርሱ ሌሎችን ማገልገል ነው። ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ሥልጣኑን ለባሪያዎቹ ያጋራል። ሥልጣኑን የመጋራት መብት የሚኖራቸው ከሥልጣኑ ሥር የሚገኙ ሰዎች ብቻ ናቸው። በመጨረሻም፣ ባሪያ ለመሆን ከፈለግህ ርኅሩኅ መሆንህን አረጋግጥ። ምክንያቱም ሰዎች ዕርዳታ ለማግኘት ወደ አንተ ይመጣሉና ነው።

ይሁንና፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ በመከተልና ከእግዚአብሔር ርኅሩኅ አገልጋዮች አንዱ በመሆን የሰዎችን ፍላጐቶች አሟልቶ መገኘቱ ምንኛ ትልቅ ዕድል ነው።

# 2

# የባሪያው ገጸ በረከት

## ማርቆስ 2:1-3:12

ተአምር ሠሪ አስተማሪ ወደ ቅፍርናሆም መምጣቱን የሚያስረዳ ዜና በከፍተኛ ደረጃ በመዛመቱ፣ ጌታችን በሄደበት ስፍራ ሁሉ ብዙ ሕዝብ ይሰበሰብ ጀመር:: ሕዝቡ ጌታችን የታመሙትን ሲፈውስና አጋንንትን ከሰዎች ሲያስወጣ ለማየት ፈልገው ነበር:: በወንጌሉ መልእክት ተስበው ቢሆን ኖሮ፣ እነዚህ ሕዝብ ለኢየሱስ ታላቅ የመበረታቻ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን አብዛኞቹ የተበላሸ አስተሳሰብ ያላቸውና በራሳቸው ፍላጐት የታወሩ መሆናቸውን ያውቅ ነበር (ሉቃስ 5:15-16):: እያንዳንዱ የእግዚአብሔር አገልጋይ ይህንን ምሳሌነት ተከትሎ ከሰዎች በመነጠል ከአብ ጋር ሊገናኝ፣ በጸሎት ሊታደስና ሊነቃቃ ይገባል::

ኢየሱስ የአገልግሎቱን ምንነት ለሕዝቡ የሚያሳይበት ጊዜ ደረሰ:: እርሱ የመጣው የታማሚዎችንና አጋንንት ያደሩባቸውን ሰዎች ችግር ከማቃለል ይልቅ ለላቀ ዓላማ ነበር:: እነዚያ ተአምራት የሚደነቁ ቢሆኑም፣ ሰዎች ሊለማመዱት የሚገባቸው አንድ ታላቅ ነገር ነበር:: ይኸውም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገቡ መቻላቸው ነበር! ከሚፈጽማቸው አካላዊ ተአምራቶች በስተጀርባ ያሉትን መንፈሳዊ ትምህርቶች መረዳት ያስፈልጋቸው ነበር::

በዚህ ክፍል፣ ጌታችን በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሦስት ግሩም ገጸ በረከቶች ማምጣቱን ተናግሯል:: እነዚህም የኃጢአት ይቅርታ (ማር. 2:1-12)፣ ፍጸሜ (2:13-22) እና ነጻ መውጣት ናቸው (2:23-3:12)::

## 1. የኃጢአት ይቅርታ (ማርቆስ 2:1-12)

ይህ ክስተት የተፈጸመው በራሱ ቤት ወይም በጴጥሮስ ቤት ውስጥ መሆኑ ግልጽ አይደለም:: እንግዳ ተቀባይነት ከምሥራቃውያን ሕግጋት አንዱ በመሆኑ፣ የቅፍርናሆም ሰዎች

ግብዣ ሳይጠብቁ ኢየሱስ ወደነበረበት ቤት መጡ:: ይህም እውነተኛ ችግር ከነበረባቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ወደ ኢየሱስ ቀርበው ሊረዱ የማይችሉበትን ሁኔታ አስከተለ:: ነገር ግን የሽባው ወዳጆች የነበሩት አራት ሰዎች ጣሪያውን ቀድደው በሽተኛውን ለማስገባትና ፈውስን እንዲያገኝ ለማገዝ ወሰኑ:: ኢየሱስም ግለሰቡን ፈወሰው:: ይህ የፈውስ ተአምር ጌታችን ስለ ይቅርታ ጠቃሚ ትምህርት የሚያስተምርበትን ዕድል አመቻቸለት::

ይህንን ትዕይንት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይን ለማየት ሞክር:: ኢየሱስ ቀና ሲል አራቱን ሰዎችና የታመመ ጓደኛቸውን ተመለከተ:: ቤቶቹ ብዙውን ጊዜ በውጭ ደረጃዎች መግባት የሚያስችሉ ጠፍጣፋ ጣሪያዎች ነበሯቸው:: የቤቱን ጣሪያና ሣር ከፍቶ በሽተኛውን እስከነ አልጋው ማሳለፍ ከባድ ተግባር አልነበረም::

የእነዚህን ሰዎች አንዳንድ ባሕርያት ማድነቅ ይኖርብናል:: በእነዚህ ሰዎች ሕይወት እኛን «ሰው አጥማጆች» ሊያሰኙ የሚገቡ ብቃቶች ሊታዩብን ይገባል:: በአንድ በኩል፣ ለጓደኛቸው ከልባቸው በመራራት ዕርዳታ የሚያገኝበትን መንገድ ፈልገዋል:: ኢየሱስ ችግሩን እንደሚያስወግድለት አምነው ነበር:: ስለ ጉዳዩ መጸለይ ብቻ ሳይሆን ለጸሎታቸው የመፍትሔ እርምጃ ጭምር ወሰዱ:: አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተስፋ እንዲያስቆርጧቸው አልፈለጉም ነበር:: አብረው በመሥራት አንድ የተለየ ነገር ለማድረግ ፈለጉ:: ኢየሱስም ለጥረታቸው ሸለማቸው (ካሣቸው) «ዛሬ ኢየሱስን ለማግኘት መሞከሩ ዋጋ የለውም:: ምናልባት ነገ ተመልሰን ብንመጣ ይሻላል» ማለቱ ይቀላቸው ነበር:: በጥረታቸው መግፋታቸው ግን ጠቀማቸው::

ጌታችን ወደ ታች ሲመለከት፣ ሽባው ከአልጋው ላይ ተኝቶ አገኘው:: ወዲያውም ኢየሱስ ወደ ሰውዬው ዋና ችግር ወይም ኃጢአት ዘልቆ ገባ:: በሽታ ሁሉ የኃጢአት ውጤት ባይሆንም (ዮሐ. 9:1-3 አንብብ)፣ የዚህ ግለሰብ ሽባነት ግን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ምክንያት የደረሰበት በሽታ ነበር:: ኢየሱስ ሽባነቱን ከመፈወሱ በፊት ለልቡ ሰላምን በማወጅ ኃጢአቱ እንደተሰረየለት ገለጸለት:: የኃጢአት ይቅርታ ኢየሱስ ሊፈጽመው የሚችለው

ትልቁ ተአምር ነበር። ይህ ትልቁን ፍላጐት የሚያሟላ፣ ትልቁን ዋጋ የሚጠይቅ፣ እንዲሁም ትልቁን በረከትና እጅግ ዘላቂ ውጤቶችን የሚያስከትል ተአምር ነበር።

ከዚያም ኢየሱስ ዙሪያ-ገባውን በመመልከት፣ ሊሰልሉት የመጡ ተቺዎችን አየ (ሉቃስ 5፡17ን አንብብ)። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች የሕዝቡን ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚቆጣጠሩ በመሆናቸው የዚህን አዲስ መምህር አገልግሎት የመመርመር መብት ነበራቸው (ዘዳግ. 13)። ነገር ግን ኑፋቄን በሚያፈላልግ የትችት አሳብ ሳይሆን፣ እውነትን በሚሻ ግልጽ በሆነ አእምሮ መምጣት ይገባቸው ነበር። በይሁዳ ውስጥ የነበረው የተወሰነ አሉታዊ አመለካከት (ዮሐ. 4፡1-4) በዚህ ጊዜ ገሊላን ወርሯት ነበር። ይህም ጌታችንን ወደ እስራትና ሞት ያደረሱት ይፋዊ ተቃውሞዎች ጅማሬ ነበር። ዝናው እጅግ እየገነነ በመምጣቱ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ችላ ብለው ላያልፉት ወሰኑ። እነዚህ ሰዎች በጠዋት ተነሥተው በመምጣታቸው ልክ ድርጊቱ በሚታይበት ሰዓት በቦታው ተገኝተው ነበር። ወይም ኢየሱስ በቸርነቱ የፊት መቀመጫ ሰጥቷቸው ይሆናል? ማን ያውቃል!?

ጌታችን *ወደ ሰዎቹ ልብ* በተመለከተ ጊዜ፣ በልባቸው ውስጥ ያለውን የትችት መንፈስ አየ። እግዚአብሔርን ሰድበሃል ብለው እንደሚከሱትም አወቀ። ኃጢአትን ሊያስተሰርይ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ እየታወቀ፣ ኢየሱስ ሽባውን «ኃጢአትህ ተሰረየችልህ» ማለቱ የሃይማኖት መሪዎቹን አሳሰባቸው። ኢየሱስ አምላክ ነኝ ማለቱ እንደሆነ ገባቸው!

ወዲያውኑ ግን ልባቸውን በማንበብና አሳባቸውን በማጋለጥ አምላክነቱን አረጋገጠላቸው (ዮሐ. 2፡25፤ ዕብ. 3፡13 አንብብ)። «ምክንያታዊ» ክርክሮችን ይወዱ ስለነበር፣ የሚያስቡበትን ነገር ሰጣቸው። አንድን ሰው ከመፈወስና ኃጢአቱ እንደተሰረየለት ከመናገር የቱ ይቀልላል? ሲል ጠየቃቸው። በግልጽ እንደሚታወቀው፣ የአንድ ሰው ኃጢአት እንደተሰረየ መናገሩ ቀላል ነው። *ምክንያቱም መሰረይ አለመሰረዩን ሊያረጋግጥ የሚችል ሰው አይኖርም።* ስለሆነም፣ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ለማረጋገጥ ሰውዬውን ወዲያውኑ አድኖ ወደ ቤቱ ሰደደው።

የሰውዬው አካል መፈወስ የነፍሱን መፈወስ የሚያሳይ ማረጋገጫ ነበር [መዝ. (103):3]። ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ሰውዬውን መፈወስም ሆነ ኃጢአቱን ማስተሰረይ አይችሉም ነበር። ስለሆነም፣ በራሳቸው ወጥመድ ተጠምደውና በራሳቸው አሳብ ተኮንነው ተመለሱ።

ኢየሱስ የሰውዬውን ኃጢአት በማስተሰረይና አካላቱን በመፈወስ ብቻ ሳይሆን ራሱንም «የሰው ልጅ» ነኝ ብሎ በመጥራት፣ አምላክነቱን አረጋግጧል። ይህ ስያሜ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ አሥራ ሁለት ጊዜያት ተጠቅሷል። ከእነዚህም አሥራ ሁለቱ የተጠቀሱት ጴጥሮስ በ8:29 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅቡዕ (ክርስቶስ) መሆኑን ከመሰከረ በኋላ ነው (2:10፣ 28፤ 8:31፣ 38፤ 9:9፣ 12፣31፤ 10:33፣ 45፤ 13:26፣ 34፤ 14:21፣ 41፣ 62)። ይህ መሢሐዊ መጠሪያ በመሆኑ (ዳን. 7:13-14)፣ አይሁዶች በዚያ መልኩ መተርጐማቸው ግልጽ ነበር። ኢየሱስ በወንጌላት ውስጥ ሰማንያ ጊዜያት ያህል ይህንን ስያሜ ተጠቅሞበታል።

የሃይማኖት መሪዎቹ በዚያን ጊዜ ልባቸውን ለእውነት ቢከፍቱት ኖሮ፣ ምን ይማሩ ነበር? በአንድ በኩል፣ ኃጢአት እንደ በሽታ፣ ይቅርታን ማግኘት ደግሞ ከበሽታ እንደ መዳን መሆኑን ይማሩ ነበር። ይህ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተገለጸ በመሆኑ፣ አዲስ እውነት አልነበረም [ኢሳ. 1:5-6፣ 16:20፤ መዝ. (103):3 አንብብ]። ልዩነቱ በዚህ ጊዜ በዓይኖቻቸው ፊት በግልጽ መታየቱ ነበር። በተጨማሪም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን ያለው አዳኝ መሆኑን ሊገነዘቡ ይችሉ ነበር። ለፈጻሚቻቸውም ኃጢአቶች ይቅርታ ሊያገኙ ይችሉ ነበር። ከንስሐ ልብ ይልቅ ተቺ መንፈስ ይዘው በመምጣታቸው ምንኛ ታላቅ ዕድል አምልጧቸዋል።

## 2. ፍጻሜ (ማርቆስ 2:13-22)

ብዙም ሳይቆይ ኢየሱስ የአይሁድ ማኅበረሰብ ከሚያገልላቸው ሰዎች ጋር መተባበሩ በግልጽ እየታየ መጣ። ቀረጥ ሰብሳቢው ሳይቀር ከደቀ መዛሙርቱ መካከል እንዲቀላቀል ጠርቶታል። አብዛኞቹ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ታማኞች ባይሆኑም፣ ሌዊ እንደዚያ

ዓይነት ሰው መሆን አለመሆኑ አልተገለጸም:: ነገር ግን ሌዊ ለሄሮድስ አንቲጳስና ለሮማውያን ማገልገሉ ብቻ በታማኝ አይሁዶች ለመወገዝ ያበቃው ነበር:: ኢየሱስ በጠራው ጊዜ ግን ሌዊ አልተከራከረም፤ አልዘገየምም:: ሮማውያን ሥራውን መልሰው እንደማይሰጡት ቢያውቅም፣ ብድግ ብሎ ኢየሱስን ተከተለው:: የሚመለስበትን ድልድይ አፍርሶ በመሄድ (ሁሉንም ነገር ከኋላው ትቶ - ሉቃስ 5:28)፣ በአዲስ ስም ተጠራ- «ማቴዎስ ማለት የእግዚአብሔር ስጦታ» ማለት ነው:: ከ«ኃጢአተኛ» ጓደኞቹ አንዳንዶቹ ከጌታ ኢየሱስ ጋር እንዲገናኙም ጋበዛቸው:: እነዚህ ሰዎች እንደ እርሱው ሁሉ ሕጉን ያልተከተሉ ወይም ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች ትኩረት ያልሰጡ አይሁዳውያን ነበሩ:: ኢየሱስ የፈለገው እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች ነበር::

ተቺዎች በስፍራው መኖራቸው የማይቀር ነበር:: ነገር ግን ጌታችን ጥያቄያቸውን ተጠቅሞ ስለ ራሱና ሊያከናውን ስለመጣበት መንፈሳዊ ሥራ እንግዶቹን አስተምሯል:: ሦስት አስገራሚ ንጽጽሮችን በመጠቀም ተልዕኮውን አብራራ::

*ሐኪም* (2:16-17):: ምንም እንኳ በሃይማኖት መሪዎች የተወገዙ ቢሆኑም፣ ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች እንደተገለሉ አድርጎ አልቆጠረም:: የማቴዎስ ጓደኞች ሐኪም የሚያስፈልጋቸው በሽተኞች ሲሆኑ፣ ኢየሱስ ደግሞ ሐኪም ነበር:: ኃጢአት ከበሽታ፣ ይቅርታ ደግሞ ፈውስን ከማግኘት ጋር ሊነጻጸር እንደሚችል ቀደም ብለን ተመልክተናል:: አሁን አዳኛችን ከሐኪም ጋር ሊነጻጸር እንደሚችል እንረዳለን:: እርሱ በችግራችን ጊዜ ወደ እኛ መጥቶ ፍጹም የሆነ ምርመራ ያካሂዳል:: የማያዳግም የተሟላ መድኃኒት ይሰጠናል:: ይህም ሁሉ የሚከናወነው በራሱ አሳብ ነው:: ምንኛ አስደናቂ ሐኪም ነው::

ነገር ግን ኢየሱስ የኃጢአት በሽታቸውን የማይፈውስላቸው ሦስት ዓይነት «በሽተኞች» አሉ:: እነዚህም፣ (1) ስለ እርሱ የማያውቁ፣ (2) ስለ እርሱ እያወቁ ሊያምኑት የማይፈልጉና (3) እርሱ እንደሚያስፈልጋቸው የማያምኑ ናቸው:: ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሦስተኛው ምድብ ውስጥ ይገባሉ:: ዛሬ በራሳቸው ጽድቅ የሚተማመኑ ኃጢአተኞችም እንዲሁ ናቸው::

የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገባን ኃጢአተኞች መሆናችንን ካልተቀበልን፣ ደኅንነትን ልናገኝ አንችልም:: ኢየሱስ የሚያድነው ኃጢአተኞችን ብቻ ነው (ሉቃ. 19:10)::

እንደ ነቢያት ዘመን ሁሉ፣ በኢየሱስ ዘመን የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት እንፈውሳለን የሚሉ፣ ዳሩ ግን ውጤታማ መፍትሔ ሊያቀርቡ የማይችሉ ሰዎች ነበሩ:: ኤርምያስ በዘመኑ የነበሩት ካህናትና ነቢያት ለሕዝቡ የውሸት ተስፋ ከመስጠት ያለፈ ተግባር የማያከናውኑ ከንቱ ሐኪሞች በመሆናቸው፣ ገሥጿቸዋል:: «የሕዝቤንም ሴት ልጅ ስብራት በጥቂቱ ይፈውሳሉ፤ ሰላም ሳይሆን:- ሰላም ሰላም ይላሉ» (ኤር. 6:14፤ 8:11):: መሠረታዊ ችግር ወደ ሆነው የልብ ኃጢአት ጠልቀው ሳይገቡ ደካማ መድኃኒታቸውን ላይ ላዩን በሚታዩ ምልክቶች ላይ ይጨምሩ ነበር (ኤር. 17:9):: ዛሬ ከእንደዚህ ዓይነት ከንቱ ሐኪሞች መጠንቀቅ አለብን::

*ሙሽራው* (2:18-20):: የመጀመሪያው ጥያቄያቸው የኢየሱስን የጓደኝነት ዓይነት የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ኢየሱስ ለምን በገበታው ላይ ከነበሩት ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚመረምር ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስ ከሰዎች ተለይቶ የሚኖር ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን የምግብ ግብዣዎችን ይቀበል፣ ከልጆች ጋር ይጫወትና ከሰዎች ጋር መሰባሰብን ይወድ ነበር (ማቴ. 11:16-19):: የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን በግብዣው ላይ በመመልከታቸው ግራ ሳይገባቸው አልቀረም:: አክራሪዎቹ የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርትም (ማቴ. 23:15 አንብብ) በግራ መጋባቱ ተባበሯቸው::

ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለመለወጥ እንጂ በራሳቸው ጽድቅ የሚመጻደቁትን ሰዎች ለማበረታታት እንዳልመጣ ቀደም ሲል አስረድቷል:: አሁን ደግሞ ደስታን እንጂ ኃዘንን ለማምጣት አለመምጣቱን ይነግራቸዋል:: ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሕዝቡ ላይ ከጫኑት ሕግ አጥባቂነት የተነሣ፣ የአይሁዶች ሃይማኖት እንደ ከባድ ሸክም የሚያስጨንቅ ነገር ሆኖ ነበር:: ድሀው ኅብረተሰብ ለመታዘዝ በማይችላቸው ሕጎችና ደንቦች ሳቢያ ጉብጦ ለመኖር ተገድዶ ነበር (ማቴ. 23:4):: ኢየሱስ «ሕይወት መቃብር ቤት መሆን የለባትም»፣ እግዚአብሔር ሕይወት የሰርግ በዓል

እንድትሆን ይፈልጋል! እኔ ሙሽራው ነኝ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ዕድምተኞቼ ናቸው። የሰርግ ዕድምተኞች መደሰት የለባቸውምን?» ሲል ነገራቸው።

አይሁዶች በብሉይ ኪዳን እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ግንኙነት ለማብራራት ከተሰጡት ምሳሌዎች አንዱ ጋብቻ መሆኑን ያውቁ ነበር። «ከያህዌ ጋር ጋብቻ የፈጸሙ» በመሆናቸው የእርሱ ብቻ ነበሩ (ኢሳ. 54:5፤ ኤር. 31:32)። ሕዝቡ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ለባዕድ ጣዖታት በሚሰግዱበት ጊዜ፣ «መንፈሳዊ ዝሙት» ይፈጽሙ ነበር። ለባላቸው ታማኞች ባለመሆናቸው መቀጣት ነበረባቸው። የትንቢተ ሆሴዕ ዋንኛ ጭብጥ እግዚአብሔር ለዘማዊት ሚስቱ ያለውን ፍቅርና ሕዝቡን ወደ ሞገሱ ለመመለስ መፈለጉን የሚያመለክት ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ሙሽራ መሆኑን ቀደም ሲል ገልጿል (ዮሐ. 3:29)። ጌታችንም የመጀመሪያውን ተአምር ደስታ በሰፈነበት የጋብቻ ዓውድ ላይ ፈጽሟል (ዮሐ. 2:1-11)። አሁን ሕዝቡ ወደ ሰርጉ እንዲመጡ እየጋበዘ ነበር። ክርስቲያን መሆን የጋብቻ ግንኙነት ከመመሥረት ጋር የሚመሳሰል ነገር ነው (ሮሜ 7:1-4 አንብብ– «ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ»)። ሁለት ሰዎች በመተዋወቃቸው ወይም ጠንካራ የፍቅር ስሜት ስላላቸው ብቻ አይጋቡም። ለመጋባት ከፈለጉ፣ አንዱ ራሱን ለሌላው መስጠትና ይህንንም መሰጠት ይፋዊ ማድረግ አለባቸው። በአብዛኞቹ ማኅበረሰቦች፣ ወንዱና ሴቷ «አዎን» በማለት ይህንኑ መሰጠት በአደባባይ ይመሰክራሉ።

ከኃጢአት መዳን ስለ ክርስቶስ ከማወቅ ወይም ለክርስቶስ የፍቅር ስሜት ከማሳየት የጠለቀ ነው። ደኅንነት የሚመጣው አንድ ሰው ራሱን ለክርስቶስ «አዎን» ብሎ ሲሰጥ ነው። በዚህ ጊዜ አማኙ በክርስቶስ ስም በመጠራት፣ ሀብቱንና ኃይሉን በመካፈል፣ በፍቅሩና በጥበቃው ደስ በመሰኘትና አንድ ቀን በከበረው ሰማያዊ ቤቱ ውስጥ በመኖር፣ ከመቅጽበት ወደ መንፈሳዊ የጋብቻ ግንኙነት ይገባል። ከክርስቶስ ጋር ይህንን ግንኙነት በምትመሠርትበት ጊዜ ከችግሮችና መከራዎች ባሻገር፣ ሕይወት የሰርግ ደስታ ይሆንልሃል።

ቊጥር 20 ስለ መጭው የጌታችን ሞት፣ ትንሣኤና ወደ መንግሥተ ሰማይ መመለስ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ገና ከሥልጣናቸው መጀመሪያ ላይ የነበሩ ደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን አሳብ የተረዱት አይመስልም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ይህን ሲል ወደ ሰማይ በሚሄድበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ደስታን በኃዘን እንደሚተኩ መግለጹ አልነበረም፡፡ እርሱ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት አልፎ አልፎ መጾሙ ወደፊት ተገቢ እንደሚሆንና የአማኞች ተለምዷዊ ልምምድ የደስታ ሕይወት ሊሆን እንደሚገባ ነው፡፡

*ልብሱና አቁማዳው* (2:21-22)፡፡ ኢየሱስ ስለ አገልግሎቱ ሁለት ጠቃሚ ትምህርቶችን አስተምሮናል፡፡ (1) እርሱ የመጣው ኃጢአተኞችን ለማዳን እንጂ ሃይማኖተኞችን ለመጥራት አልነበረም፡፡ (2) እርሱ የመጣው ደስታን እንጂ ኃዘንን ለማምጣት አልነበረም፡፡ ሦስተኛው ትምህርቱ ደግሞ እርሱ የመጣው አዲሱን ለማስተዋወቅ እንጂ አሮጌውን ለመጠጋገን አይደለም፡፡

የሃይማኖት መሪዎች በጌታችን ትምህርት በመደነቃቸው፣ ምናልባትም አንዳንድ አሳቦቹን የሃይማኖታዊ ልማዳቸው አካላት ለማድረግ ሳይፈልጉ አልቀረም፡፡ ከፈሪሳውያን አይሁዳዊነትና ከኢየሱስ ክርስቶስ የተውጣጡ ምርጥ ምርጥ አሳቦችን አቻችለው ለመጠቀም ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ይህ የማያስኬድ መሆኑን ገለጸላቸው፡፡ ይህ ካልተቀደደ አዲስ ልብስ ላይ መጣፊያ አንሥቶ በአሮጌ ልብስ ላይ እንደ መለጠፍ ነበር፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አዲሱ ልብስ ይበላሻል፡፡ አሮጌው ልብስ በሚታጠብበት ጊዜም መጣፊያው ይቦጭቀዋል (ሉቃስ 5:36-39 አንብብ)፡፡ ወይም ደግሞ፣ የዚህ ዓይነቱ ተግባር አዲስን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ እንደ ማስቀመጥ ነበር፡፡ የወይን ጠጁ መብሰልና መፍላት ሲጀምር፣ አሮጌው አቁማዳ ይፈነዳል፡፡ ይህም ወይኑንም ሆነ አቁማዳውን ከጥቅም ውጭ ያደርገዋል፡፡

ኢየሱስ የመጣው አዲሱን ትምህርት ለመጀመር እንጂ ከአሮጌው ጋር ለማዋሐድ አልነበረም፡፡ የሙሴ ትምህርት ያረጀና ለመጥፋት የተዘጋጀ ነበር (ዕብ. 8:13)፡፡ ኢየሱስ በደሙ አዲስ ቃል ኪዳን ይመሠርት ነበር (ሉቃስ 22:19-20)፡፡ ሕጉ ጽላቶች

ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልብ ላይ ይጻፋል (ዕብ.10:15-18፤ 2ኛ ቆሮ.3:1-3 አንብብ)። በውስጣቸው የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሕጉን ጽድቅ እንዲያሟሉ ይረዳቸዋል (ሮሜ 8:1-4)።

ኢየሱስ ይህንን ማብራሪያ በመጠቀም በመቻቻል የሚመሠረተውን «የዓለም ሃይማኖት» ተወዳጅ አስተሳሰብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ውድቅ አድርጎታል። መልካም አስተሳሰብ የነበራቸውና ዳሩ ግን መንፈሳዊ ዕውርነት ያጠላባቸው መሪዎች ከእያንዳንዱ ሃይማኖት ምርጥ ምርጡን አሳብ በመውሰድና ከክርስትና እምነት ታላላቅ ትምህርቶች ጋር በማዋሐድ ሰዎች ሁሉ የሚቀበሉትን ሰው - ሠራሽ እምነት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው ነበር። የክርስትና እምነት ግን ባሕርዩ ሊቀየጥ የማይችል ነው። የትኛውንም ሌላ እምነት እንደ አቻው ወይም የበላዩ አድርጎ አይቀበልም። «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋ. 4:12)።

ደኅንነት የሰው ሕይወት በከፊል የሚጠገንበት ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ አዲስ የጽድቅ ልብስ የሚጐናጸፍበት ነው (ኢሳ. 61:10፤ 2ኛ ቆሮ. 5:21)። የክርስትና ሕይወት አዲሱና አሮጌው የሚቀላቀልበት ሳይሆን፣ አሮጌው በአዲሱ ተፈጻሚ የሚሆንበት ነው። አንድን ነገር በሁለት ነገሮች ማውደም ይቻላል። በማፍረስ ወይም የራሱን ዕድገት እንዲፈጽም በማድረግ። ለምሳሌ ያህል፣ የዋርካን ዛፍ ፍሬ በመደሻ ቀጥቅጠህ ልታጠፋ ትችላለህ። ወይም ተክለህ ወደ ዋርካ ዛፍነት ልትለውጠው ትችላለህ። በሁለቱም መንገድ ፍሬው ይጠፋል። በሁለተኛው መንገድ ግን ፍሬው የጠፋው ከፍጻሜ በመድረስ ነው- ወደ ዛፍ በመለወጡ።

ኢየሱስ የሙሴን ሕግ ትንቢቶች፣ አምሳያዎችና ግጼታዎች አሟልቷል። ፍጹም የሆነው መሥዋዕት ለዓለም ኃጢአት በተሠዋ ጊዜ ሕጉ በጎልጎታ ተፈጸመ (ዕብ. 8-10)። በኢየሱስ ክርስቶስ በምታምንበት ጊዜ፣ የአዲሱ ፍጥረት አካል ትሆናለህ (2ኛ ቆሮ. 5:17)። ይህም ሁልጊዜም አዳዲስ የጸጋና የክበረ ልምምዶችን ያስከትላል። ሰዎች ሕያው መንፈሳዊ እውነትን ሊከተሉ ሲችሉ፣ በሞተ ሃይማኖታዊ ልማድ ላይ የሙጥኝ

ማለታቸው አሳዛኝ ነገር ነው:: እውነተኛው ነገር ከተገለጠ በኋላ ለምን ጥላውን እንመርጣለን? (ዕብ. 10:ከ1 ጀምሮ):: በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ቃል የገባልን ነገሮች ሁሉ ተፈጽመዋል (2ኛ ቆሮ. 1:20)::

## 3. ነጻነት (ማርቆስ 2:23-3:12)

አይሁዶች ሰንበትን እንደ ቅዱስ ቀን ያከብሩት ነበር:: እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰንበትን ቀን የሰጠው ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ ነበር (ነህ. 9:14)፤ ዘጸ. 20:8-11):: ይህም በእስራኤላውያንና በያህዌ መካከል ልዩ ምልክት ነበር (ዘጸ. 31:13-17):: እግዚአብሔር ለሌላ ሕዝብ የሰንበትን ቀን እንደ ሰጠ የሚያመለክት አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም:: ስለሆነም፣ ኢየሱስ የሰንበት ልማዶችን በግልጽ መተላለፉ በሃይማኖቱ ላይ ጦርነትን እንደ መክፈት ነበር:: ዘመቻውን የጀመረው ለሠላሳ ስምንት ዓመታት ታሞ የቆየ ሰው በመፈወስ ሲሆን (ዮሐ. 5)፣ ከዚያ በኋላ በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ክስተቶች ተከትለዋል::

የአይሁድ ባሕል በሰንበት ቀን ሊከናወኑ የማይችሉትን ሠላሳ ዘጠኝ ተግባራት ይዘረዝራል:: ሙሴ በሰንበት ቀን መሥራት የተከለከለ መሆኑን ቢገልጽም፣ ሊሠሩ የማይችሉትን ነገሮች በሰፊው አልዘረዘረም (ዘጸ. 20:10):: ምግብ ለመሥራት እሳት ማቀጣጠል (ዘጸ. 35:3)፣ የማገዶ እንጨት መሰብሰብ (ዘኁል. 15: ከ32 ጀምሮ)፣ ዕቃ መሸከም (ኤር. 17: ከ21 ጀምሮ)፣ ወይም መነገድ (ነህ. 10:31፤ 13:15፣19) የተከለከለ መሆኑ ተገልጿል:: የአይሁድ ባሕል ግን ሰዎች በሰንበት ቀን ምን ያህል ርቀት እንደሚጓዙ ጭምር ደንግጓል (ሁለት ሺህ ክንድ፣ በኢያሱ 3:4 ላይ በመመሥረት):: በአጭሩ፣ የሰንበት ቀን በሕዝቡ ጫንቃ ላይ የወደቀ የከፍተኛ ሸክም ምልክት ወደ መሆኑ ደረጃ ደርሶ ነበር::

ጌታችን በቤተሳይዳ አንድ ሰው ከፈወሰ በኋላ በሰንበት ቀን በእርሻ ውስጥ እያለፈ እሸት በመቅጠፍ ደቀ መዛሙርቱም እሸት ቀጥፈው በእጆቻቸው እያሹ እንዲበሉ በመፍቀዱ፣ ቀጣዩን «ሰንበት የመተላለፍ» ተግባር ፈጽሟል:: አንድ ሰው የማከማቻ ወይም የማጨጃ መሣሪያ ሳይጠቀም በተራበ ጊዜ ከሰው እርሻ

ላይ ፍራፍሬ ወይም ጥራጥሬ መብላቱ የተከለከለ አልነበረም (ዘዳግ. 23:24-25)። ፈሪሳውያንን ያበሳጫቸው ይኼ አልነበረም። እነርሱን ያበሳጫቸው ደቀ መዛሙርቱ በሰንበት ቀን መሥራታቸው ነበር!

ማቴዎስ በዚህ ጉዳይ ላይ የጻፈውን ክፍል ስትመለከት፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመከላከል ሦስት የመከራከሪያ አሳቦችን እንዳቀረበ ትገነዘባለህ። እነዚህም፣ ዳዊት ያከናወነው ተግባር (12:3-4)፣ ካህናት የሚያደርጉት ( ቍ. 5-6) እና ነቢዩ ሆሴዕ የተናገረው ናቸው (ቍ. 7-8)። ሮማውያን የሆኑት የማርቆስ አንባቢዎች ለአይሁድ ነቢያትና ካህናት ፍላጐት ስለማይኖራቸው፣ ማርቆስ ሮማውያን በታላቅ ጀግንነቱና በንጉሥነቱ የሚያውቁትን ዳዊትን ለመጥቀስ መርጧል። ክርክሩ ትክክለኛ ነው። የተራበ ንጉሥና ጭፍሮቹ ከመገናኛ ድንኳን ውስጥ የተቀደሰ ዳቦ አንሥተው ሊበሉ ከቻሉ (1ኛ ሳሙ. 21:1-6)፣ የሰንበት ጌታም ደቀ መዛሙርቱ ከእርሻው እሸት እንዲቀጥፉ ማድረጉ ትክክል ነው። ዳቦው ለካህናት ብቻ የተፈቀደ በመሆኑ፣ ዳዊት በግልጽ የሰፈረ ሕግ ጥሷል (ዘሌዋ. 24:5-9)። ደቀ መዛሙርቱ የተላለፉት ግን ሰው ሠራሹን ልማድ ብቻ ነበር። የሰዎችን ፍላጐት ማሟላቱ ሃይማኖታዊ ልማዶችን ከመጠበቅ የበለጠ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል። የፈሪሳውያን ፍላጎት ቅደም ተከተል ግራ የተጋባ ነበር።

ኢየሱስ አብያታር ሊቀ ካህናት መሆኑን የጠቀሰው በስሕተት ይሆን? የአብያታር አባት የሆነው አቤሜሌክ በ1ኛ ሳሙኤል 21 ውስጥ ሊቀ ካህናት እንደሆነ ተገልጿል (1ኛ ሳሙ. 22:20)። ከዚህ አንጻር፣ የጌታችን ቃል በ1ኛ ሳሙኤል ውስጥ ከሰፈረው ጋር የሚቃረን ይመስላል። ነገር ግን ምንም የሚቃረን ነገር የለውም። አባትና ልጅ በሁለቱም ስሞች ሊጠሩ ይችላሉ (1ኛ ዜና 18:16 እና 24:6፤ 1ኛ ሳሙ. 22:20 እና 2ኛ ሳሙ. 8:17)። በተጨማሪም፣ ጌታችን «አብያታር» የሚለውን ስም የተጠቀመው ከግለሰቡ ይልቅ የብሉይ ኪዳን ምንባብን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። መዛግብቶቻቸው በአሁኑ መጽሐፍ ቅዱሶቻችን ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦችና ቁጥሮች የሚመስሉ

አከፋፈሎች ስላልነበሯቸው አይሁዶች የቃሉን ክፍሎች የሚለዩት በዚህ መንገድ ነበር (ማር. 12:26 አንብብ)::

በዚያኑ የሰንበት ዕለት፣ ጌታችን ለአምልኮ ወደ ምኩራብ ሄደ:: በዚያም፣ ሆን ብሎ አንድን ሰው ፈወሰ:: የሰንበት ቀን እስኪያልፍ ሊጠብቅ የሚችል ቢሆንም፣ የፈሪሳውያንን የሕግ አጥባቂነት ባሕል ለመፈታተን ፈልጐ ነበር:: በዚህ ጊዜ ፈሪሳውያኑ (ሉቃስ 6:7) ዓይኖቻቸውን በሰፊው ከፍተው ሲፈውስ ለመያዝ ይጠባበቁ ነበር:: ጌታችን በማርቆስ 3:4 ያነሣቸውን ጥያቄዎች ጠላቶቹ ሊመልሱለት አልቻሉም:: ክፋት የሰንበትን ዕለት ጨምሮ ሁልጊዜም እየሠራ፣ ደግነትስ ለምን ተግባሩን አያከናውንም? ሞት ሁል ጊዜም በሥራ ላይ ነው:: ነገር ግን ይህ ሕይወትን ለማዳን እንዳንጥር ሊያደናቅፈን አይገባም::

ኢየሱስ «የልባቸውን ድንዳኔ» መመልከት የቻለ ሲሆን፣ ኃጢአታቸው አስቆጥቶታል:: ጌታችን በቀራጮችና ኃጢአተኞች ላይ ቁጣውን ባይገልጽም፣ በራሳቸው ጽድቅ የሚመጻደቁትን ፈሪሳውያን ተቆጥቷል (ማቴ. 23):: ከሰውዬው መፈወስ ይልቅ ልማዳቸውን ለመጠበቅ ይመርጡ ነበር:: ሰውዬው ስለዚህ መንፈሳዊ ግጭት ብዙም የሚያውቀው አልነበረም:: የጌታችንን ትእዛዝ ሰምቶ እጁን በመዘርጋት ነበር የተፈወሰው::

ፈሪሳውያን ኢየሱስ የፈጸመው ተግባር እጅግ ስላበሳጫቸው ከሄሮድስ ደጋፊዎች (ሄሮዲያኖች) ጋር ተባብረው ሊያሳስሩትና ሊያጠፉት ዕቅዶችን ያወጡ ነበር:: ሄሮዲያኖች የሃይማኖት ፓሪቲዎች ሳይሆኑ፣ ንጉሥ ሄሮድስንና አገዛዙን የሚደግፉ ሰዎች ነበሩ:: አብዛኞቹ አይሁዶች ሄሮድስን ስለሚንቁት ሕግጋቱን የሚታዘዙት ከልባቸው አልነበረም:: ስለሆነም፣ አጥባቂዎቹ ፈሪሳውያን ታማኞች ካልሆኑ ፖለቲከኞች ጋር መተባበራቸው አስገራሚ ነው:: ነገር ግን ሁለቱን ወገኖች ያስተባበረው የጋራ ጠላታቸው የሆነው ኢየሱስ ነበር::

ይህ የትብብር ተቃውሞ በደረሰበት ጊዜ ኢየሱስ ከአካባቢው ራቀ:: ይህም ሆኖ፣ አሁንም ብዙ ሕዝብ ይከተሉት ነበር:: እነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ አስተሳሰብ ስላልነበራቸው፣ በኢየሱስ ላይ አደጋ

ሊያስከትሉበት ይችሉ ነበር። ባለሥልጣናቱ በሮማውያን ላይ የተቃውሞ ዓመፅ ይመራል ብለው ሊከሱት ይችሉ ነበር። ይህም ሆኖ፣ ኢየሱስ ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ ይፈውሳቸውና ከአጋንንት ነፃ ያወጣቸው ነበር። አሁንም አጋንንት ማንነቱን እንዳይናገሩ በድጋሚ አስጠንቅቋቸዋል (ማር. 1:23-26)።

ጌታችን አሁን በአገልግሎቱ ችግር ገጥሞታል። መንፈሳዊ ልብ የሌላቸው ብዙ ሕዝብ እየተከተሉት ነበር። የሃይማኖት መሪዎች ሊያጠፉት ይፈልጉ ነበር። ከሄሮድስ ወዳጆችም አንዳንዶቹ በዚህ ጉዳይ ውስጥ እየተሳተፉ ነበር። ቀጣይ እርምጃው ሌሊቱን በጸሎት ማሳለፍ (ሉቃስ 6:12)፣ በሐዋርያነት ያግዙት ዘንድ አሥራ ሁለት ሰዎችን መጥራትና የመንግሥቱን መንፈሳዊ መሠረት የሚገልጸውን ስብከት ማቅረብ ነበር።

እርሱ ይቅርታን፣ ፍጻሜንና ነጻነትን ቢሰጣቸውም፣ ሊቀበሉት አልፈለጉም።

አንተስ ስጦታውን ተቀብለኸዋልን?

# 3

# ባሪያው፣ ሕዝቡና መንግሥቱ

## ማርቆስ 3:13-4:34

የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነው ኢየሱስ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ በትምህርቱና በተአምራቱ የተደነቁ ብዙ ሕዝብ ይከተሉት ነበር (ማር. 3:7-9፣ 20፣ 32፤ 4:1)። ኢየሱስ ባሪያ ሳይሆን «ዝነኛ» ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ሕዝቡን ለማስደሰት ይሞክር ነበር (ማቴ. 11:7-15 አንብብ)። ነገር ግን ከሕዝቡ ፈቀቅ ብሎ በተለይ ደቀ መዛሙርቱን ያስተምር ጀመር። ወደ እርሱ ለመምጣት የሚጋፉት ሰዎች ከንቱዎችና ታማኝነት የጐደላቸው መሆናቸውን ያውቅ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህን አያውቁም ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ለዚህ «ስኬት» ትኩረት እንዳይሰጡ፣ ስለ ሕዝቡና ስለ መንግሥቱ እውነቱን ሊያስተምራቸው ፈለገ። በዚህ ክፍል፣ ጌታችን ለሕዝቡ ጫና የሰጣቸውን ሦስት ምላሾች እንመለከታለን።

## 1. አዲስ ሕዝብ አቋቋመ (ማርቆስ 3:13-19)

የእስራኤል ነገዶች አሥራ ሁለት በመሆናቸው፣ የደቀ መዛሙርቱ ቊጥር አሥራ ሁለት መሆን አስፈላጊ ነበር። በዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር የያዕቆብን አሥራ ሁለት ልጆች ከመረጠ በኋላ፣ በዘጸአት ታላቅ ሕዝብ አድርጐ መሠረታቸው። የምድር ነገዶች ሁሉ የሚመኩበትን መሢሕ ወደ ምድር ለማምጣት እግዚአብሔር እስራኤልን መረጠ (ዘፍጥ. 12:1-3)። ነገር ግን እስራኤል በመንፈሳዊ ሕይወቷ በመዝቀጥ የራሷን መሢሕ ላለመቀበል ተዘጋጀች። እግዚአብሔር አዲስ ሕዝብ፣ የተለየ (የተገዛ) ሕዝብ ለመመሥረት ፈልጐ ነበር (1ኛ ጴጥ. 2:9)። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የዚህ «መንፈሳዊ» ሕዝብ እምብርት ነበሩ (ማቴ. 21:43)።

ኢየሱስ እነዚህን አሥራ ሁለት ሰዎች ከመምረጡ በፊት ሌሊቱን ሲጸልይ አደረ (ሉቃስ 6:12)። አሥራ ሁለቱን የመረጣቸው ሦስት ዓላማዎችን በመያዝ ነበር። እነዚህም ዓላማዎች፣ (1) በራሱ ምሳሌና ትምህርት ማሠልጠን፣ (2)

ወንጌሉን እንዲሰብኩ መላክና (3) ሰዎችን እንዲፈውሱና አጋንንትን እንዲያስወጡ ሥልጣን መስጠት ነበሩ (ማር. 1:14-15፣ 38-39፤ 6:7-13 አንብብ):: እነዚህ አሥራ ሁለቱ እርሱ ወደ አብ ከተመለሰ በኋላ አገልግሎቱን የሚቀጥሉትን ሰዎች ያሠለጥኑ ነበር (2ኛ ጢሞ. 2:2)::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሦስት ሌሎች ስፍራዎችም የአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ስሞች ተዘርዝረዋል– ማቴ. 10:2-4፤ ሉቃስ 6:14-16፤ የሐዋ. 1:13:: ሉቃስ ጌታችን «ሐዋርያት» የሚል ልዩ ስም እንደሰጣቸው ይነግረናል:: ደቀ መዝሙር አንድን ተግባር እያከናወነ የሚማር ሰው ነው:: (በአገራችን የቆሎ ተማሪ የደቀ መዝሙር አቻ ሊሆን ይችላል::) «ሐዋርያ» ለይፋዊ አገልግሎት ተልዕኮ ተሰጥቶት የተላከ ማለት ነው:: ኢየሱስ ብዙ ደቀ መዛሙርት ቢኖሩትም፣ አሥራ ሁለት ሐዋርያት ብቻ ነበሩት:: እነዚህም ልዩ «አምባሳደሮቹ» ነበሩ::

ዝርዝሮቹን በምታነጻጽርበት ጊዜ፣ ሰዎቹ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ የተቀመጡ ይመስላል:: ጴጥሮስና እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ፣ ፊልጶስና በርተሎሜዎስ (ናትናኤል [ዮሐ. 1:45])፣ ቶማስና ማቴዎስ (ሌዊ)፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና ታዴዎስ (አስቆሮቱ ሳይሆን የያዕቆብ ልጅ የሆነው ይሁዳ [ዮሐ. 14:22])፣ ቀናተኛው ስምዖንና አስቆሮቱ ይሁዳ:: ኢየሱስ ሐዋርያቱን ጥንድ ጥንድ አድርጐ ስለላካቸው፣ ስማቸውን ለመዘርዘር ይኼ ምክንያታዊ መንገድ ነበር (ማር. 6:7)::

የስምዖን ስሙ ጴጥሮስ «ዓለቱ» (ዮሐ. 1:40-42)፣ የሌዊ ደግሞ ማቴዎስ «የእግዚአብሔር ስጦታ» ተብሎ ተቀይሯል:: ያዕቆብና ዮሐንስ «ቦአኔርጌስ – የነጎድጓድ ልጆች» የሚል ቅጽል ስም ተሰጣቸው:: ብዙውን ጊዜ ዮሐንስ የፍቅር ሐዋርያ እንደሆነ ብናስብም፣ ባሕርዩ ግን በመጀመሪያ እንደዚያ አልነበረም፣ ወንድሙ ያዕቆብም እንዲሁ (ማር. 9:38-41 እና 10:35-39፤ ሉቃስ 9:54-55):: ኢየሱስ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ሊታጩ የማይችሉ ከሚመስሉ የተለያዩ ሰዎች ጋር የሚያከናውነውን ተግባር መመልከቱ አበረታች ነገር ነው::

ማርቆስ የሚጽፈው ለሮማውያን አንባቢዎች በመሆኑ፣ «ቦአኔርጌስ» የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ፍች ሰጥቷል:: በዚህ ወንጌል ውስጥ እንዲህ ዓይነት «ለአሕዛብ የተጻፉትን ብዙ ማስታወሻዎች» እናገኛለን (ማር. 5:41፤ 7:11፣34፤ 11:9፤ 14:36፤ 15:22፣34):: በ3:18 «ከነዓናዊ» የሚለው ቃል ከዘር ወይም ከአገር ጉዳይ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ይህ «ቀጥተኛ» የሚል ፍች ከሚሰጥ ከዕብራይስጥ ቋንቋ የተገኘ ቃል ነው:: ቀናተኛ የሚባሉት የሮማውያንን አገዛዝ ለመገርሰስ የተደራጁ አይሁዳውያን አክራሪ ፖለቲከኞች ነበሩ:: እነዚህ ሰዎች ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ግድያንም ጨምሮ ሁሉንም መንገዶች ይጠቀሙ ነበር:: የታሪክ ጸሐፊው ጆሲፈስ «ተዋጊዎች» ይላቸዋል:: ቀናተኛው ስምዖን የሮማውያን የቀድሞ ሠራተኛ ከነበረው ማቴዎስ ጋር መጀመሪያ ሲገናኝ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጥቶ ይሆን?

የወንጌላትን ተመሳሳይ ምንባቦች በምታነጻጽርበት ጊዜ፣ በ3:19 እና 20 መካከል ኢየሱስ የተራራውን ስብከት (ማቴ. 5-7) እንደ ሰበከና በሉቃስ 7:1-8:3 በተገለጹት ክስተቶች ውስጥ እንደተሳተፈ ትገነዘባለህ:: ማርቆስ ትኩረት ያደረገው ኢየሱስ ከተናገረው ይልቅ ባደረገው ተግባር ላይ በመሆኑ፣ ይህንን ስብከት አላካተተም::

## 2. አዲስ ቤተሰብ መሠረተ (ማር. 3:20-21፣ 31-35)

የጌታችን ወዳጆች ኢየሱስ ግራ እንደተጋባና ምናልባትም አእምሮውን እንደ ሳተ እርግጠኞች ነበሩ:: በብዙ ሕዝብ ታጅቦ አስደናቂ ነገሮችን እያከናወነ ከቦታ ቦታ እንደሚዘዋወር በመስማታቸው የሆነ እርዳታ ሊደረግለት ይገባል ብለው አሰቡ:: በመሆኑም እንደ ማንኛውም ሰው ተራ ሕይወት የማይመራ መሆኑ ያሳሰባቸው ወዳጆቹ እንክብካቤ ሊያደርጉለት ወደ ቅፍርናሆም መጡ:: እናቱና ወንድሞቹም ከናዝሬት አርባ ስምንት ኪሎ ሜትር ተጉዘው በመምጣት ወደ ቤት መጥቶ ትንሽ እንዲያርፍ ለመኑት:: እርሱ ወዳለበት ቤት ግን ሊገቡ አልቻሉም:: በማርቆስ ወንጌል ማርያም የተገለጸችውና ሙከራዋ ውድቅ የሆነባት በዚህ ስፍራ ብቻ ነው::

የእግዚአብሔር ባሪያዎች ብዙውን ጊዜ በዘመናቸው ከነበሩት ሰዎች የተሳሳተ አስተያየት እንደሚሰነዘርባቸውና ቤተሰቦቻቸው እንደማይረዷቸው ታሪክ ያስረዳል:: ዲ. ኤል. ሙዲን በቺካጐ ብዙ ሰዎች «እብዱ ሙዲ» እያሉ ይጠሯቸው ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስም እብድ ተብሏል (የሐዋ. 26:24-25):: ከኤሚሊ ዲከንስ ጽሑፍ እንደምንመለከተው በአብዛኞቹ ስምምነት ሰዎች እንደ እብዶችና እንደ አደገኞች ይቆጠራሉ::

ጌታችን በነበረበት ቤት ውስጥ ተቀምጦ ከቤተሰቦቹ ጋር ለመገናኘት ያልቻለው ሊጨክንባቸው ስለፈለገ አልነበረም:: ልባቸው ትክክል እንደሆነና ዓላማቸው ግን የተሳሳተ መሆኑን ያውቅ ነበር:: ኢየሱስ የቤተሰቡን ጥያቄ ቢያሟላ ኖሮ፣ ለተቃዋሚዎቹ ትችት ይጋለጥ ነበር:: የሃይማኖት መሪዎች፣ «አያችሁ፣ ቤተሰቡ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ሲነግሩት አምኖ ተስማምቷል:: እብድነቱን ስለ ተቀበለ ትኩረት አትስጡት» ይሉ ነበር:: ኢየሱስ ለቤተሰቡ እጅ ከመስጠት ይልቅ አጋጣሚውን ተጠቅሞ መንፈሳዊ ትምህርት አስተምሯል:: ይኸውም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ሁሉ «ቤተሰቡ» እንደሆኑ የሚያስረዳ ነበር:: የጌታችን ወንድሞች (ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ይሁዳ፣ ስምዖን) አማኞች ባለመሆናቸው (ዮሐ. 7:1-5)፣ ኢየሱስ ከእነርሱ ይልቅ አማኝ ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን አቀረባቸው::

በዚህ እርምጃው፣ ጌታችን ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ቢኖር አማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማንኛውም ነገር ማስቀደም እንዳለባቸው እንጂ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል ቤተሰቦቻቸውን እንዲያገልሉ ወይም ቸል እንዲሉ አይደለም:: ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እጅግ ስለሚልቅ፣ ለቤተሰቦቻችን የሚኖረን ፍቅር የጥላቻ ያህል የወረደ ይሆናል (ሉቃስ 14:26):: ለቤተሰቦቻችን እንክብካቤ ማድረጋችንና የሚያስፈልጓቸውን ሁሉ ማሟላታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (1ኛ ጢሞ. 5:8 አንብብ):: ነገር ግን እጅግ የምንወዳቸው ሰዎች እንኳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ሊመልሱን አይገባም:: በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ ቤተሰብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ስትገነዘብ፣ የክርስቶስ ቃላት ለሰሟቸው ሰዎች ምን ያህል ከፍተኛ ድምፀት እንደነበሯቸው ልትረዳ ትችላለህ::

አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እንዴት ሊገባ ይችላል? አዲስ ልደት፣ ከላይ መንፈሳዊ ልደት በማግኘት (ዮሐ. 3:1-7፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22-25)። አንድ ኃጢአተኛ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙ አድርጎ በሚያምንበት ጊዜ ይህንኑ አዲስ ልደት በማግኘት ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ይገባል። የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ በመካፈል (2ኛ ጴጥ. 1:3-4)፣ «አባ» ብሎ ሊጠራው ይችላል (ሮሜ 8:15-16)። ይህ መንፈሳዊ ልደት እኛ ለራሳችን ወይም ለሌሎች ሰዎች የሚፈጽሙልን ተግባር አይደለም (ዮሐ. 1:11-13)። ይህ የእግዚአብሔር የጸጋ ሥራ ስለሆነ፣ በእምነት ልንቀበለው ይገባል (ኤፌ. 2:8-9)።

## 3. አዲስ መንግሥት አወጀ (ማርቆስ 3:22-30፤ 4:1-34)

ሕዝቡ ኢየሱስ ሮምን አሸንፎ አገሪቱን ከቅኝ ግዛት ነፃ ያወጣታል የሚል ተስፋ ነበራቸው። እርሱ ግን አሥራ ሁለት ተራ ሰዎችን ጠርቶ «አዲስ አገር» መሠረተ። እርሷም መንፈሳዊት አገር ስትሆን፣ የዜጐቿ ስሞች በሰማይ ተጽፈዋል (ሉቃስ 10:20፤ ፊልጵ. 3:20)። ሕዝቡ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም አይሁድ መልካም ባሕርይ እንዲያሳይና ቤተሰቡን እንዲያከብር ፈለጉ። እርሱ ግን «አዲሱ ቤተሰቡ» በእርሱ የሚያምኑና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ሁሉ የተካተቱበት መሆኑን ገለጸ። በተጨማሪም፣ ሕዝቡ የእስራኤልን መንግሥት በመመሥረት የእስራኤልን ክብር ይመልሳል ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር። የእርሱ ምላሽ ግን አዲስ መንፈሳዊ መንግሥት ማወጅ ነበር።

በዚህ ክፍል «መንግሥት» ቁልፍ ቃል ነው (ማር. 3:24፤ 4:11፣ 26፣ 30)። መጥምቁ ዮሐንስ የንጉሡ መምጫ እንደ ቀረበ በመግለጽ፣ ሕዝቡ ንጉሡን ለመገናኘት እንዲዘጋጁ አስጠንቅቋቸው ነበር (1:1-8)። ነገር ግን ይህ መንግሥት ምን ይመስላል? ጌታ እስራኤልን በማደስ ፖለቲካዊ መንግሥት የማይመሠርት ከሆነ፣ ምን ዓይነት መንግሥት ለመመሥረት ነበር ያቀደው?

በዚህ ነጥብ ላይ ማርቆስ – ምሳሌ የሚል አዲስ ቃል አስተዋውቋል (3:23፤ 4:2፣ 10-11፣ 13፣ 33-34 አንብብ)። ኢየሱስ

የመንግሥትን ጽንሰ አሳብ ያብራራው ሥነ መለኮታዊ ገለጻ በማቅረብ ሳይሆን፣ የሕዝቡን ቀልብ የሚስቡትንና ምናባቸውን በመጠቀም እንዲያስቡ የሚያስገድዷቸውን ሥዕላዊ ትረካዎች በመጠቀም ነው:: «ምሳሌ» የሚለው ቃል የተተረጐመው «አብሮ መወርወር» የሚል ፍች ከሚሰጡ ሁለት የግሪክ ቃላት ነው:: *(ፓራ- አጠገብ፣ ባሎ-መወርወር)::* ምሳሌ አንድን መልእክት መረዳት ይቻል ዘንድ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ታሪክ ወይም ገለጻ ነው:: ምሳሌ «ሰማያዊ ፍች ካለው ምድራዊ ታሪክ» ያለፈና አንድ ሰባኪ ለስብከቱ ማብራሪያነት ከሚጠቀመው መግለጫ ያለፈ ነው:: እውነተኛ ምሳሌ የአድማጩን ትኩረት በመጥለፍ ስለ እግዚአብሔር እውነትና ስለ ራሱ ሕይወት ከውሳኔ ላይ እንዲደርስ ያስገድደዋል:: የኢየሱስ ምሳሌዎች ወደ ሰዎች ልብ ጠልቀው የሚገቡና ግላዊ ዝምድና የሚፈጥሩ በመሆናቸው፣ የሃይማኖት መሪዎቹ አያሌ ምሳሌዎችን ከሰሙ በኋላ ጌታ ኢየሱስን ለመግደል ፈለጉ! (ማቴ. 21:45-46)::

ምሳሌው ትኩረትን እንደሚስብ ሥዕላዊ ትረካ እንደ ዋዛ ይጀምራል:: ነገር ግን ትረካውን እያነበብህ ስትሄድ፣ ራስህን የምትመለከትበት መስተዋት ሆኖ ታገኘዋለህ:: መስተዋቱን በእምነት መመልከታችንን ከቀጠልን፣ መስተዋቱ እግዚአብሔርንና እውነቱን የምንመለከትበት መስኮት ይሆናል:: እግዚአብሔር የሚያስተምረን ተጨማሪ እውነት የሚወሰነው ለዚያ እውነት በምንሰጠው ምላሽ ነው::

ኢየሱስ በምሳሌ የሚያስተምረው ለምን ነበር? ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ ጥያቄ ጠይቀውት ነበር (ማር. 4:10-12፤ ማቴ. 13:10-17 አንብብ):: ምላሹን በጥንቃቄ በምናጠናበት ጊዜ፣ ኢየሱስ እውነትን ለመደበቅና ለመግለጽ ምሳሌን ይጠቀማል:: ሕዝቡ በምሳሌዎቹ ላይ ሊፈርዱ አልቻሉም:: ምሳሌዎቹ ግን በሕዝቡ ላይ ፈርደዋል:: ሁሉንም አውቃለሁ ብሎ የሚያስብ ግድየለሽ አድማጭ በደንብ ያልተገነዘበውን ታሪክ ብቻ ይሰማል:: ይህም ፍርድን ያስከትልበታል (ማቴ. 11:25-30 አንብብ):: የእግዚአብሔርን እውነት የማወቅ ፍላጐት ያለው እውነተኛ አድማጭ ግን ስለ ምሳሌው በማሰላሰል፣ አለማወቁን በመገንዘብና

ለእግዚአብሔር ራሱን አሳልፎ በመስጠት፣ ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መንፈሳዊ ትምህርት ሊገነዘብ ይችላል።

ኢየሱስ *የእግዚአብሔርን ቃል በመስማቱ* ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። *«መስማት»* የሚለው ቃል በተለያዩ መስኮች በማርቆስ 4:1-34 ውስጥ *አሥራ ሦስት* ጊዜያት ተጠቅሷል። ጌታችን የሚናገረው ስለ አካላዊ መስማት ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ምርመራ ስለ መስማት መሆኑ ግልጽ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል «መስማት» ማለት ትርጉምን መረዳትና መታዘዝ ነው (ያዕ. 1:22-25 አንብብ)።

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ጨምሮ ሕዝቡ የመንግሥቱን ባሕርይ እንዲረዱ ለማገዝ ምሳሌዎችን ይናገር ነበር።

*ጠንካራው ሰው* (3:22-30)። ኢየሱስ አጋንንት ያደረበትን አንድ ዲዳና ዓይነ ስውር ግለሰብ በፈወሰው ጊዜ (ማቴ. 12:22-24)፣ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ይህንኑ ተአምር ተጠቅመው ኢየሱስን ይቃወሙት ጀመር። ሕዝቡ፣ «እውነትም ይኼ ሰውዬ የዳዊት ልጅ፣ መሲሑ ሳይሆን አይቀርም» ይሉ ነበር። የሃይማኖት መሪዎች ግን፣ «የለም፣ ብዔል ዜቡል አለበት! በእርሱ በኩል የሚሠራው የእግዚአብሔር ሳይሆን የሰይጣን ኃይል ነው» ሲሉ ተናገሩ።

«ብዔል ዜቡል» ማለት «የቤቱ ጌታ» ማለት ሲሆን፣ ዲያብሎስን የሚያመለክት ቃል ነበር። ኢየሱስ በዚህ ፍች ላይ በመመሥረት፣ ቤቱን ስለሚጠብቅ ጠንካራ ሰው ምሳሌ ተናገረ። ቤቱን ለመዝረፍ የሚፈልገው ሰው መጀመሪያ ጠንካራውን ሰውዬ ማሸነፍ ይኖርበታል።

በዚህ ንግግሩ ኢየሱስ የተበላሸ ሥነ መለኮታቸውንና የተሳሳተ አመክኒዮአቸውን አጋልጧል። አጋንንት ያስወጣው በሰይጣን ኃይል ከሆነ፣ ሰይጣን ከራሱ ጋር እየተዋጋ ነው ማለት ነው። ይህም የሰይጣን ቤትና መንግሥት እንደተከፋፈሉና ለውድቀት እንደ ተቃረቡ ያሳያል። ሰይጣን ከግዛቱ የትኛውንም ለማጣት ስለማይፈልግ፣ ያንን ግለሰብ በጥንቃቄ ሲጠብቀው ነበር። ኢየሱስ ሰውዬውን ከአጋንንት እስራት ነፃ ማውጣቱ ከሰይጣን

በላይ ጠንካራ መሆኑንና ሰይጣን ሊያስቆመው አለመቻሉን ያሳያል፡፡

ኢየሱስ ለሐሰተኛ ክሳቸው ምላሽ ከመስጠት ያለፈ ተግባር አከናውኗል፡፡ ምን ያህል የከፋ ቃል እንደ ተናገሩ ገለጸላቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የምንናገራቸው ቃላት የልባችንን አሳብ (ማቴ. 12:35)፣ የልባችን አሳብ ደግሞ ባሕርያችንን፣ ጠባያችንንና ፍጻሜያችንን የሚገልጥ መሆኑ ነው፡፡ ምዕራባውያን አንዳንድ ጊዜ፣ «ንግግር ርካሽ ነው!» ይላሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የምንናገራቸው ቃላት ብዙ ዋጋ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ኢየሱስ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ዘላለማዊና ይቅር የማይባል ኃጢአት በመሥራታቸው አደጋ ውስጥ መሆናቸውን ገለጸ (ማቴ. 12:32)፡፡

«ይቅርታ የማይደረግለት ኃጢአት ምንድን ነው?» ብለህ በምትጠይቃቸው ጊዜ ሰዎች ብዙውን ጊዜ፣ «መንፈስ ቅዱስን መስደብ» ወይም «መንፈስ ቅዱስ ያከናወነውን ተግባር የዲያብሎስ ነው ብሎ የመናገር ኃጢአት ነው» ብለው ይመልሱልሃል፡፡ በታሪካዊ አነጋገር፣ እነዚህ አሳቦች እውነተኛ ናቸው፡፡ ነገር ግን ለጥያቄው ምላሽ አይሆኑም፡፡ ዛሬ የእግዚአብሔርን መንፈስ የምንሰድበው እንዴት ነው? ዛሬ በግድየለሽነት ወይም ሆን ብለን ሰይጣን እንደ ሠራው የምንናገራቸው የመንፈስ ቅዱስ *ሥራዎች* ምን ምን ናቸው? አንድ ሰው ይህንን ኃጢአት እንዲፈጽም ተአምር ሲፈጸም ማየት አለበት?

ኢየሱስ እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአትና ስድብ ይቅር ሊል እንደሚችል በግልጽ አመልክቷል፡፡ ይህም *በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የሚሰነዘረውን ስድብ የሚጨምር ነው* (ማቴ 12:32)፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር ወልድ የመንፈስ ቅዱስን ያህል አስፈላጊ አይደለም ማለት ነውን? በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የሚሰነዘር ስድብ የሚሰረየውና በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሰነዘር ስድብ ግን የማይሰረየው ለምንድን ነው?

መልሱ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ባሕርይና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ከነበረው ትዕግሥትን የተሞላ ግንኙነት ነው፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመሢሐቸው መምጣት ለማዘጋጀት መጥምቁ ዮሐንስን ልኮት ነበር። ብዙዎቹ ተራ ሰዎች ለዮሐንስ ጥሪ ምላሽ በመስጠት ንስሐ ቢገቡም (ማቴ. 21:32)፣ የሃይማኖት መሪዎቹ ግን ዮሐንስን እንዲታሰርና የኋላ ኋላም እንዲሞት ፈቀዱ። የተስፋ ቃል በተሰጠው መሠረት፣ እግዚአብሔር ወልድ ሕዝቡ እንዲያምንበት ጥሪ ቢያደርግለትም፣ እነዚያው የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስ እንዲገደል ጠየቁ። ጌታችን በመስቀል ላይ፣ «አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ሲል ጸልዮአል (ሉቃስ 23:34)።

በበዓለ ኀምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ መጥቶ የእግዚአብሔርን ኃይል በብዙ ወቃሽ መንገዶች ገልጿል። በዚህ ጊዜ እነዚሁ የሃይማኖት መሪዎች ምን ዓይነት ምላሽ ሰጡ? ምላሻቸውን የገለጹት ሐዋርያትን በማሰር፣ ስለ ኢየሱስ እንዳይመሰክሩ በማዘዝና *እስጢፋኖስን በመግደል* ነበር። እስጢፋኖስ ኃጢአታቸው ምን እንደሆነ ተናግሯል። «እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ» (የሐዋ. 7:51)። ቀደም ሲል በአብና በወልድ ላይ ኃጢአት የፈጸሙ ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ይቅርታ አድርጐላቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአትን በፈጸሙ ጊዜ «ከቋፍ» ላይ ስለ ደረሱ፣ ተጨማሪ ይቅርታ ሊደረግላቸው አልተቻለም።

ዛሬ ሰዎች ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በአይሁዶች የተፈጸመውን ዓይነት መንፈስ ቅዱስን የመሳደብ ኃጢአት ሊፈጽሙ አይችሉም። ዛሬ እግዚአብሔር ይቅር የማይለው ኃጢአት በልጁ አለማመን ነው (ዮሐ. 3:16-21፣ 31)። የእግዚአብሔር መንፈስ ኃጢአተኛውን በመውቀስ አዳኙን በሚገልጥለት ጊዜ፣ ኃጢአተኛው የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳና የእግዚአብሔርን ቃል ምስክርነት ችላ ሊል ይችላል። ይህ ማለት ግን የመዳን ዕድሎቹን ሁሉ አጥቷል ማለት አይደለም። ንስሐ ገብቶ በኢየሱስ ካመነ፣ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው ይችላል። ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ጥሪዎች ሁሉ የማይሰማ እስኪመስል ድረስ ልቡን ቢያደነድን እንኳ ሕይወቱ እስካለ ድረስ ተስፋ አለው። ዕድሉ የሚያበቃበ`ን ጊዜና ሁኔታ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኔና አንተ የትኛውም ኃጢአተኛ

የማይሰረይ ኃጢአት ፈጽሟል ብለን መጨነቅ የለብንም (1ኛ ጢሞ. 2:4፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9)።

*ዘሪውና መሬቶቹ* (ማር. 4:1-20)። ይህ ምሳሌ ደቀ መዛሙርቱ፣ ኢየሱስ በሚከተሉት ብዙ ሕዝብ የማይደነቅበትን ምክንያት እንዲገነዘቡ አድርጓል። የሚያስተምራቸው ቃል ለም ባልሆነ መሬት ላይ እንደ ተዘራ ዘር በመሆኑ፣ በተለወጠ ሕይወት ፍሬ ሊሰጡ እንደማይችሉ ያውቅ ነበር።

ዘሩ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያመለክት ሲሆን (ሉቃስ 8:11)፣ ዘሪው ቃሉን ለሌሎች የሚያካፍለው የእግዚአብሔር ባሪያ ነው (1ኛ ቆሮ. 3:5-9 አንብብ)። የሰው ልብ እንደ መሬት ነው። ዘሩ ሥር ሰድዶ ፍሬ ይሰጥ ዘንድ መሬቱ መዘጋጀት አለበት። ቃሉ እንደ ዘሩ ሕያውና መንፈሳዊ ፍሬ ሊሰጥ የሚችል ነው። ነገር ግን ከመከሩ በፊት ዘሩ መዘራትና እንክብካቤ ማግኘ ት አለበት።

እንደዚያን ዘመኑ ሁሉ፣ ዛሬም አራት ዓይነት ልቦች አሉ። እነዚህ ልቦች ለእግዚአብሔር መልእክት በአራት መንገዶች ምላሽ ይሰጣሉ። *ደንዳናው ልብ* (ማር. 4:14፣15) የእግዚአብሔርን ቃል ባለመቀበል ሰይጣን (ወፎች) እንዲነጥቀው ያደርጋል። መሬት የሚጠነከረው ብዙ ከተረገጠ ነው። ለሁሉም ዓይነት ሰዎችና ተጽዕኖዎች በግድየለሽነት «ልባቸውን የሚከፍቱ» ሰዎች ለልብ ድንዳኔ ሊጋለጡ ይችላሉ (ምሳሌ 4:23 አንብብ)። ደንዳና ልቦች ቃሉን ከመቀበላቸው በፊት «መታረስ» አለባቸው። ይህ ደግሞ ሥቃይን የሚያስከትል ልምምድ ሊሆን ይችላል (ኤር. 4:3፤ ሆሴዕ 10:12)።

*ጭንጫ ልብ* (ማር. 4:5-6፣ 16-17) በድንጋይ ላይ እንደሚገኝ ስስ መሬት ነው። የዚህ ዓይነቱ መሬት በፍልስጥኤም በስፋት ይገኛል። መሬቱ ጥልቀት ስለሌለው የተዘራው ዘር ሥር መስደድ ይሳነውና በፍጥነት ይጠወልጋል። ይህ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆን የሚከፈለውን ዋጋ በአግባቡ ሳይረዱ የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ የሚቀበሉትን «ስሜታዊ አድማጮች» ያመለክታል። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ለአያሌ ቀናት ወይም ሳምንታት የተነቃቃ ሕይወት ሊመሩ ቢችሉም፣

ስደትና ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ መነቃቃታቸው ይቀዘቅዛል፤ ደስታቸውም ይወገዳል። ለወደቀው የሰው ልጅ ባሕርይ አስመሳይ «ሃይማኖታዊ ስሜት» ማንጸባርቅና ሐሰተኛ የመተማመን ሁኔታ ማሳየት ከባድ አይደለም።

*የተጨናነቀ ልብ* (ማር. 4:7፣ 18-19) *ቃሉን* ቢቀበልም በእውነተኛ ንስሐ «*አረሞችን*» ከልቡ የማያስወግደውን ሰው *ያመለክታል*። በዚህ ሰው ልብ ውስጥ እንደ ዓለማዊ ፍላጐቶች፣ የብልጽግናና የቁሳቁሶች ምኞት ያሉ የተለያዩ «ዘሮች» ሲያድጉ ይቆያሉ። ይህም መልካሙ የቃሉ ዘር የሚያድግበትን ቦታ ያጣብበዋል። ሁኔታውን ለመለወጥ ሰውዬው በተመሳሳይ ጊዜ «በሰፊው» እና «በጠባቡ» መንገድ ላይ ለመጓዝ ይፈልጋል (ማቴ. 7:13-14)። ይኼ ደግሞ ሊሞከር አይችልም።

*ፍሬያማ ልብ* (ማር. 4:8፣ 20) እውነተኛውን አማኝ *ያመለክታል*። ምክንያቱም ፍሬው፣ ማለትም የተለወጠ ሕይወት የእውነተኛ ደኅንነት ምልክት ነው (2ኛ ቆሮ. 5:17፤ ገላ. 5:19-23)። ሦስቱ ዓይነት ልቦች ፍሬ ስላልሰጡ፣ ደኅንነት ያላገኙትን ሰዎች ልቦች ያመለክታሉ ብለን እንገምታለን። ሁሉም እውነተኛ አማኞች በእኩል ደረጃ ፍሬያማ አይሆኑም። ነገር ግን ከእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት የተወሰነ የመንፈሳዊ ፍሬ ማረጋገጫ ይታያል።

ፍሬ ያልተገኘባቸው ሦስቱም ልቦች በተለያዩ ጠላቶች የሚጠቁ ናቸው። ከጠንካራው ልብ ዲያብሎስ ዘሩን ይነጥቃል። ከጭንጫው ልብ– *ሥጋ* አስመሳይ ሃይማኖታዊ ስሜቶችን ያሳያል። ከተጨናነቀ ልብ – የዓለም ነገሮች ዘሩ እንዳያድግና እንዳያፈራ ያንቃሉ። እነዚህ ሦስቱ የክርስቲያን ኃይለኛ ጠላቶች ናቸው– ዓለም፣ *ሥጋ*ና ሰይጣን (ኤፌ. 2:1-3)።

*መብራት* (ማር. 4:21-25)። በዚህ ምሳሌ፣ ጌታችን ሁሉም በሚያውቁት ትዕይንት (ቤት) ውስጥ የሚታየውን የተለመደ ነገር (*መብራት*) ተጠቅሟል። መብራቱ ዘይት የተሞላበት የሸክላ ዕቃ ሲሆን፣ በዘይቱ ውስጥ እሳቱን የሚያቀጣጥል ክር የተጨመረበት ነበር። ብርሃን ማግኘት የሚቻለው ሸክላው ከፍ ብሎ የተቀመጠ እንደሆነ ነው። ዘይቱ በጐደለ ጊዜ እንደገና

ይሞላል። መብራቱ ካልተቀጣጠለ ወይም በሆነ ነገር ከተሸፈነ ለቤቱ ጥቅም ሊሰጥ አይችልም ነበር።

ሐዋርያትም እንደዚያው ብርሃን ነበሩ። የእግዚአብሔርን ብርሃን እንዲያሰራጩና እውነቱን እንዲገልጡ ነበር። ብርሃኑን ለሌሎች «መስጠት» የሚችሉት ግን መጀመሪያ ራሳቸው «ከተቀበሉት» በኋላ ነበር። የቍጥር 24-25 ምክርም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ በሰማን ቍጥር፣ የበለጠ ለሌሎች የማካፈል ብቃት ይኖረናል። ሁሉንም እናውቃለን ብለን በምናስብበት ጊዜ፣ እናውቃለን የምንለው ሁሉ ይወሰድብናል። ምን እንደምንሰማ (ቍ. 24) እና እንዴት እንደምንሰማ (ሉቃስ 8:18) መጠንቀቅ አለብን። መንፈሳዊ መስማታችን ለሌሎች ምን ያህል መስጠት እንዳለብን ይወስናል። እግዚአብሔር አንድ ቀን ሁሉንም ስለሚገልጥ ነገሮችን «ለመሸፋፈን» መሞከሩ ፋይዳ የለውም።

*የዘሩ ዕድገት* (ማር. 4:26-34)። የመጀመሪያው ምሳሌ ዘሩ እንዲያድግ ልናደርግ አለመቻላችንን ያሳያል። እንዴት እንደሚያድግም ልናብራራ አንችልም። ዘሩ አድጎ ፍሬ የሚሰጥበት ሂደት ምሥጢራዊ ነው። የግብርና ባለሙያ የሆነ ሰው ብዙ እምነትና ትዕግሥት ሊኖረው ይገባል። ጌታችን በዘሪውና መሬቶቹ ምሳሌ ውስጥ ከተዘራው ዘር አብዛኞቹ ለም ባልሆነ መሬት ላይ እንደሚወድቁ አመልክቷል። ይህ ግን ሠራተኞቹን ተስፋ ማስቆረጥ የለበትም። በዚህ ምሳሌ፣ ባይዝሉ በጊዜው የሚያጭዱ መሆናቸውን አረጋግጦላቸዋል (ገላ. 6:9)።

ሁለተኛው ምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ ማስጠንቀቂያና ማበረታቻ የሚሰጥ ነው። ማበረታቻው፣ መንግሥቱ ከአነስተኛ ጅማሬ ተነሥታ በስፋቷ መጠንና በምታሳድረው ተጽዕኖ ከላቀ ደረጃ እንደምትደርስ ያሳያል። የሰናፍጭ ዘር በዓለም ከሁሉም ዘሮች ያነሰች ባትሆንም አይሁዶች በማሳቸው ውስጥ የሚዘሯት አነስተኛዋ ዘር ነበረች። ሰናፍጭ በአይሁዶች ባሕል የትንሽ ነገር ሁሉ ምልክት ነበረች። ጌታችን አገልግሎቱን የጀመረው በአሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ቢሆንም፣ በኋላ ወደ 500 የሚደርሱ አማኞች ሊከተሉት ችለዋል (1ኛ ቆር. 15:6)። በበዓለ ኀምሳ ዕለት ጴጥሮስ 3,000 ሰዎችን ወደ ጌታ አምጥቷል። በሐዋርያት

ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሁሉ ይኼ ቊጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ ሄዷል (4:4፤5:14፤ 6:1፣7)። ከቤተ ክርስቲያን ኃጢአቶችና ድክመቶች ባሻገር፣ መልእክቱ ወደ ሌሎች አገሮች ተሰራጭቷል። አንድ ቀን ደግሞ ከሁሉም አገሮች የተውጣጡ ቅዱሳን ከዙፋኑ ፊት ይሰግዳሉ (ራእይ 5:9)።

የዘሩ ማደግ ግን የታሪኩ አንድ ክፍል ብቻ ነው። በዛፉ ቅርንጫፎች ውስጥም ወፎች ያርፋሉ። በዘሪውና መሬቶቹ ምሳሌ ውስጥ፣ ወፎች ዘሩን የሚነጥቀውን ሰይጣንን ያመለክታሉ (ማር. 4:15)። ሁለቱም ምሳሌዎች የተነገሩት በተመሳሳይ ቀን በመሆኑ፣ ተያያዥነት እንዲኖረው ከተፈለገ፣ ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን። የመንግሥቱ መስፋፋት የዓለምን ሕዝብ በሙሉ አይለውጠውም። እንዲያውም፣ ከመንግሥቱ ዕድገት አንዳንዱ ለሰይጣን አሠራር ዕድል ሊሰጥ ይችላል። ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ይሁዳ ነበረ። ከኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሐናንያና ሰጲራ ነበሩ (የሐዋ. 5:1-11)። ሲሞን ማጉስ የሰማርያ ቤተ ክርስቲያን አካል የነበረ ሲሆን (የሐዋ. 8:1-24)፣ የሰይጣን አገልጋዮች የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን በድፍረት ወርረው ነበረ (2ኛ ቆሮ. 11:13-15)። መረቡ በሰፋ መጠን ጥሩና መጥፎ ዓሣ የመያዝ ዕድሉ እየጨመረ ይሄዳል (ማቴ. 13:47-50)።

በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፣ የሰማያዊ አገር ዜጐች፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ እንዲሁም የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ጭፍሮች እንሆናለን። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቁ እንዴት ያለ መልካም ዕድል ነው!

# 4

# ባሪያው ያሸንፋል!

## ማርቆስ 4:35-5:43

የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የየትኛውም ሁኔታ ጌታና የየትኛውም ጠላት አሸናፊ ነው:: እርሱን ካመንንና ትእዛዛቱን ከተከተልን፣ በፍጹም መፍራት የለብንም:: ድል የተሰኘው ጭብጥ ይህንን ረዥም ክፍል ያስተሳስራል:: ማርቆስ ኢየሱስ የፈጸማቸውን አራት ተአምራት የመዘገበ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ተአምር ዛሬ ለእኛም ሳይቀር የጠላትን ሽንፈት ያውጃል::

## 1. ድል በአደጋ ላይ (ማርቆስ 4:35-41)

«በዚያም ቀን» የሚለው ኢየሱስ «የመንግሥቱን ምሳሌዎች» የተናገረበትን ዕለት ያመለክታል:: እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ ቃሉን ሲያስተምር የቆየ ሲሆን፣ አሁን ምን ያህል እንደ ተገነዘቡ በተግባራዊ መንገድ ሊፈትናቸው ፈለገ:: ምክንያቱም አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰማበት ጊዜ በሕይወቱ ውስጥ እምነት መፈጠር አለበት (ሮሜ 10:17):: እምነት ደግሞ ሁል ጊዜም መፈተን አለበት:: አስፈላጊው ነገር አንድ ትምህርት መማር ወይም ትምህርቱን ደግሞ ለመናገር መቻል ብቻ አይደለም:: በተጨማሪም፣ የተማርነውን በእምነት ተግባራዊ ልናደርግ ይገባል:: እግዚአብሔር መከራ ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ ከሚፈቅድባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኼ ነው::

ኢየሱስ ማዕበል እንደሚነሣባቸው አውቆ ነበርን? በሚገባ ያውቅ ነበር! ማዕበሉ የዚያን ዕለቱ ሥርዓተ ትምህርት አንዱ ክፍል ነበር:: ይህም ደቀ መዛሙርቱ አስፈላጊነቱን ያልተገነዘቡትን ትምህርት እንዲረዱ አስችሏቸዋል:: ይኸውም በሕይወት ማዕበሎች ውስጥ በኢየሱስ ሊታመኑ እንደሚችሉ ነው:: ብዙ ሰዎች ማዕበሎች ወደ ሕይወታቸው የሚመጡት እግዚአብሔርን በማይታዘዙበት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይመስላቸዋል:: ይህ ግን ሁል ጊዜም እውነት አይደለም:: ዮናስ

ማዕበል የገጠመው እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ ሲሆን፣ ደቀ መዛሙርቱ ግን እግዚአብሔርን በመታዘዛቸው ማዕበል ገጥሟቸዋል::

ከገሊላ ባሕር መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የተነሣ የኃይለኛ ማዕበሎች መነሣት ያልተለመደ ክስተት አልነበረም:: በአንድ የበጋ ወቅት ከሰዓት በኋላ፣ ይህንኑ ባሕር በማቋርጥበት ጊዜ እስራኤላዊ አስጐብኚዬን፣ እንዲህ ዓይነት ማዕበል አጋጥሞት ያውቅ እንደሆነ ጠየቅሁት:: እርሱም እጆቹን እያወራጨ፣ ራሱንም እየነቀነቀ፣ «አዎ አጋጥሞኛል! ሁለተኛ ግን እንዲያጋጥመኝ አልፈልግም!» ሲል መለሰልኝ::

እንደ ደቀ መዛሙርቱ የካበተ ዓሣ የማጥመድ ልምድ ያላቸውን ሰዎች ካሰጋቸው በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ማዕበል አደገኛ መሆን አለበት:: ሁኔታው አደገኛ ቢመስልም እንኳ በመርከቢቱ ከነበሩት ሰዎች አንዳቸውም መፍራት እንዳልነበረባቸው የሚያስረዱ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶች አሉ::

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከባሕር ማዶ እንደሚሻገሩ ኢየሱስ ቃል ገብቶላቸው ነበር (ማር. 4:35):: ትእዛዛቱ ሁልጊዜም ማስቻያዎቹ በመሆናቸው ዕቅዶቹ ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚያግድ ምንም ነገር አልነበረም:: ጌታ መንገዱ ቀላል እንደሚሆን ሳይሆን፣ ከታቀደ መድረሻ መገኘታቸው እንደ ማይቀር ዋስትና ሰጥቷቸው ነበር::

ሁለተኛ፣ ጌታ ራሱ ከእነርሱ ጋር እስካለ ድረስ ምን ያስፈራቸዋል? ቀደም ሲል በተአምራቱ አማካኝነት ኃይሉ ሲገለጥ ስለተመለከቱ፣ ሁኔታውን ሊቆጣጠር እንደሚችል ሙሉ በሙሉ ሊተማመኑበት ይገባ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የሁሉም ሁኔታዎች ጌታ መሆኑን አልተገነዘቡም ነበር::

በመጨረሻም፣ በዚያው ማዕበል ውስጥ ኢየሱስ ሳይረበሽ በሰላማዊ ሁኔታ መገኘቱን ሊመለከቱ ይችሉ ነበር:: ይኼ እውነት ብቻ ሊያበረታታቸው ይገባ ነበር:: ኢየሱስ በእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ አብ እንደሚጠነቀቅላቸው ያውቅ ነበር:: ስለሆነም፣ የሽልብታ እንቅልፍ ተኛ:: ዮናስ ከእግዚአብሔር እየኰበለለ ሳለ ያንቀላፋው እውነተኛ ያልሆነ የዋስትና ስሜት ስለነበረው ነበር::

ኢየሱስ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እውነተኛ ዋስትና ስለነበረው አንቀላፋ:: «በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁም፤ አቤቱ፣ አንተ ብቻህን በእምነት አሳድረኸኛልና» (መዝ. 4:8)::

እኛም የሕይወት መከራ ሲገጥመን እምነት የሌላቸውን ደቀ መዛሙርት ለመምሰል ምን ያህል ጊዜ አስበን ይሆን፣ «ጌታ ሆይ፣ ስንጠፋ አይገድህምን?» ብለን የጮኽነው? በእርግጥ ይገደዋል! ከተኛበት ተነሥቶ ማዕበሉን ገሠጸው:: ወዲያውም ጸጥታ ሰፈነ:: ነገር ግን ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ በማሰኘት ብቻ አላበቃም:: ምክንያቱም ትልቁ አደጋ የደቀ መዛሙርቱ አለማመን እንጂ ነፋስ ወይም ማዕበል አልነበረም:: አደገኞቹ ችግሮቻችን በውስጣችን እንጂ በአካባቢያችን የሚገኙ አይደሉም:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመጠኑ ገሥጾ «እንዴትስ እምነት የላችሁም?» ያለውም ለዚሁ ነው:: ምንም እንኳ ቃሉን ሲያስተምር የሰሙና ተአምራት ሲሠራ የተመለከቱ ቢሆኑም፣ እምነት አልነበራቸውም:: ፍርሃት ያስከተለባቸው እምነተ ቢስነታቸው ነበር:: ፍርሃታቸው ኢየሱስ ለእነርሱ ግድ ይኖረው እንደሆነ እንዲጠራጠሩ አደረጋቸው:: እኛም ልባችን ባለማመን እንዳይሞላ መጠንቀቅ አለብን (ዕብ. 3:12)::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በለመዱት የገሊላ ባሕር አካባቢ ካስተማራቸው በርካታ ትምህርቶች አንዱ ይኼ ነበር:: እያንዳንዱ ትምህርት ደግሞ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳዲስና ግሩም እውነቶችን ይገልጥ ነበር:: ኢየሱስ ኃጢአትን የማስተሰረይ፣ አጋንንትን የማስወጣትና በሽታን የመፈወስ ሥልጣን እንደነበረው ቀደም ብለው ያውቁ ነበር:: አሁን ደግሞ በነፋስና በማዕበል ላይ ሥልጣን እንደነበረው ተገነዘቡ:: በመሆኑም፣ ከእንግዲህ የሚፈሩበት ምክንያት አይኖራቸውም ማለት ነው:: ጌታቸው ሁሉንም ሁኔታ ባለማቋረጥ ይቆጣጠር ነበርና ነው::

## 2. ድል በአጋንንት ላይ (ማርቆስ 5:1-20)

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከባሕር ማዶ ሲደርሱ፣ አጋንንት ያደሩባቸውን ሁለት ሰዎች አገኙ (ማቴ. 8:28 አንብብ):: በተለይ አንደኛው ግለሰብ በጣም ይጮኽና ይረብሽ ነበር:: ይህ ትዕይንት «ዘመናዊ ሥልጣኔ» ላይ ደርሰዋል በሚባሉት የምዕራባውያን

አገሮች ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሊታመን የማይችል ቢመስልም፣ ሚሲዮናውያን በአገልግሎት በሚሄዱባቸው አገሮች የሚያጋጥማቸው ዓይነት ነው:: እንዲያውም፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች በዛሬው «ዘመናዊ ማኅበረሰብ» ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በብዛት በአጋንንት እየተያዙ መሆኑን ያስረዳሉ::

በዚህ ትዕይንት ውስጥ ሦስት የተለያዩ ኃይሎች በሥራ ላይ ተሰማርተው እንመለከታለን:: እነዚህም ሰይጣን፣ ማኅበረሰቡና አዳኙ ናቸው:: እነዚህ ሦስት ኃይላት ዛሬም የሰዎችን ሕይወት ለመቆጣጠር እየጣሩ በዓለማችን ውስጥ በመሥራት ላይ ናቸው::

በመጀመሪያ፣ *ሰይጣን* በሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ችግር እንመለከታለን:: ሰይጣን የማጥፋት ዓላማ ያለው ሌባ ነው (ዮሐ. 10:10፤ በተለይ ራእይ 9:11ን አንብብ):: አጋንንት እንዴት ወደ እነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ገብተው እንደ ተቆጣጠሯቸው አልተገለጠም:: ምናልባትም ራሳቸውን ለኃጢአት አሳልፈው በመስጠታቸው ይሆናል:: አጋንንት «ርኩሳን መናፍስት» በመሆናቸው፣ ኃጢአትን መሥራት ወደሚያዘወትሩ ሰዎች ሕይወት በቀላሉ ሊዘልቁ ይችላሉ::

እነዚህ ሁለት ሰዎች ራሳቸውን ለሌባው ሰይጣን አሳልፈው በመስጠታቸው ሁሉንም ነገር አጥተዋል:: ቤቶቻቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውንና የወዳጆቻቸውን ኅብረት አጥተዋል:: ዕርቃናቸውን በመቃብር አካባቢዎች እየሮጡ ክብራቸውን አጥተዋል:: ራሳቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው እየጮኹና ሰውነቶቻቸውን እየቆራረጡና የአካባቢውን ነዋሪዎች እያስበረገጉ እንደ እንስሳት ይበራሉ:: ሰላማቸውንና የኑሮ ዓላማቸውን አጥተዋል:: ኢየሱስ ሊያድናቸው በማዕበል ውስጥ ባይመጣ ኖሮ በዚሁ ሁኔታ ይቀጥሉ ነበር::

የሰይጣንን አጥፊ ኃይል ማናናቅ የለብንም:: ጠላታችን ስለሆነ፣ ከተቻለው ሁላችንንም ሊያጠፋን ይፈልጋል:: እንደሚያገሣ አንበሳ፣ ሊውጠን ይሻል (1ኛ ጴጥ. 5:8-9):: በሚያምኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ አድሮ «የዓመፃ ልጆች» የሚያደርጋቸው ሰይጣን ነው (ኤፌ. 2:1-3):: በጌርጌሴኖን

መቃብር አካባቢ የነበሩት ሁለት ሰዎች ሰይጣን በሰዎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ከፍተኛ አደጋ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሰይጣንን ለመቃወምና ከእርሱ ለመራቅ የእነርሱን ባሕርይ መመልከቱ በቂ ነው፡፡

ብዙ ተግባር ለማከናወን ባይችልም፣ በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ይሠራ የነበረው ሁለተኛው ኃይል *ማኅበረሰቡ* ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ማኅበረሰቡ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሰዎቹን ለብቻቸው መነጠል፣ ማስጠበቅና ካስፈለገም ማሰር ነበር (ሉቃስ 8:29)፡፡ ሕዝቡ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ሰዎች ቢያስሩም፣ ሰይጣን ሰንሰለቶቻቸውን የሚበጣጥሱበትን ኃይል ሰጥቷቸዋል፡፡ ሰዎቹን ለመግራት የተደረገው ጥረት ሁሉ ሊሠራ አልቻለም፡፡ ግሩም ሳይንሳዊ ውጤቶችን ያስመዘገበው ማኅበረሰብ ዛሬም ሰይጣንና ኃጢአት የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ሊቋቋም አይችልም፡፡ ማኅበረሰቡ የተወሰነ የመቋቋምና የጥበቃ ጥረቶችን በማድረጉ እግዚአብሔርን ብናመሰግንም፣ ማኅበረሰቡ ለዘለቄታው ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ በመስጠት ሰይጣን ያሸበራቸውን ሰለባዎች ነፃ ሊያወጣ እንደማይችል እንገነዘባለን፡፡

ይህም ሦስተኛው ኃይል ወደ ሆነው *አዳኙ* ያመጣናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነዚህ ሰዎች ምን አደረገላቸው? በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከፍቅሩ የተነሣ በማዕበል ውስጥ አልፎ መጣላቸው፡፡ አንዳንዶች ማዕበሉን ያስነሣው ሰይጣን መሰላቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ ለማሰኘትና አጋንንትን ለማስወጣት ተመሳሳይ ቃላት በመጠቀሙ ነው (ማርቆስ 1:25ን ከ4:39 ጋር አነጻጽር)፡፡ ምናልባት ሰይጣን ኢየሱስን ለማጥፋት ወይም የእርሱን አገልግሎት ወደሚፈልጉት ሰዎች እንዳይደርስ ለመቋቋም እየሞከረ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ጌታ ወደ መቃብሩ ስፍራ መጥቶ ሰዎቹን ነፃ እንዳያወጣ የሚከለክለው ኃይል ሊገኝ አልቻለም፡፡

ኢየሱስ ወደ ሰዎቹ መምጣት ብቻ ሳይሆን፣ ቃልን በመናገር እነርሱም እንዲናገሩ ፈቅዶላቸዋል፡፡ የአካባቢው ሰዎች ሁለቱን ሰዎች ያገለሏቸው ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን በፍቅርና በአክብሮት ተቀብሏቸዋል፡፡ እርሱ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነበር የመጣው (ሉቃስ 19:10)፡፡

አጋንንቱ በግለሰቡ በኩል በተናገሩ ጊዜ፣ የሚያምኑበትን ነገር መናገራቸው አስገራሚ ነው:: አጋንንት እምነት አላቸው:: ለሚያምኑበትም ነገር ይንቀጠቀጣሉ (ያዕ. 2:19):: ነገር ግን እምነታቸውም ሆነ ፍርሃታቸው ሊያድናቸው አይችልም:: አጋንንት፣ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያለው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያምናሉ:: አንድ ቀን ወደ ሲዖል የሚወርዱ በመሆናቸውና በፍርድ እውነታ ያምናሉ (ማቴ. 8:29 አንብብ):: ይህ ዛሬ ብዙ ሃይማኖተኞች ከሚያምኑት የበለጠ ነው!

መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ በአጋንንት ስለ መያዝ ሥነ ልቡናዊም ሆነ አካላዊ ማብራሪያ አይሰጥም:: ከኢየሱስ ጋር የተነጋገረው ግለሰብ በአጋንንት ሌጌዎን (ጭፍራ) ቁጥጥር ሥር ነበር:: በሮም መንግሥት አንድ ሌጌዎን እስከ 6,000 ሰዎችን ይይዝ ነበር:: ግለሰቡ በሺዎች የሚቆጠሩ ርኩሳን መናፍስት ቀንና ሌሊት እያሠቃዩት ያሳለፈውን የሰቀቀን ሕይወት ማሰቡ አስፈሪ ነው:: ሌላኛውም አጋንንት ያደሩበት ግለሰብ ተመሳሳይ ሥቃይ እንደ ደረሰበት ጥርጥር የለውም::

ሰይጣን እነዚህን ሰዎች ለማጥፋት ሲሞክር፣ ኢየሱስ ግን ነፃ ሊያወጣቸው መጣ:: አጋንንት በጸሎትም ያምናሉ:: ምክንያቱም የሥቃይ ስፍራ ወደ ሆነው ወደ ጥልቁ እንዳይልካቸው ኢየሱስን ለምነውታል (ማር. 5:7፤ ሉቃስ 8:31):: አጋንንት የኢየሱስን ዕቅድ አለማወቃቸው የሚያበረታታ ነገር ነው:: ይህም እግዚአብሔር እስካልገለጠለት ድረስ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ሊያውቅ እንደማይችል ያሳያል:: እንዲያውም፣ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ይቅርና የአማኙን አእምሮ ሊያነብ እንደሚችል የሚያመለክት አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም::

ማርቆስ 5 ስለ ሦስት ጥያቄዎች ይናገራል:: እነዚህም፣ አጋንንት ኢየሱስ ወደ እርያዎቹ እንዲሰዳቸው መጠየቃቸው (ቍ. 12)፣ ሕዝቡ ኢየሱስ አካባቢውን ለቅቆ እንዲሄድ መጠየቃቸው (ቍ. 17) እና ከአጋንንት እስራት ነፃ ከወጡት ሰዎች አንደኛው ኢየሱስን ለመከተል መጠየቁ (ቍ. 18) ናቸው:: ጌታችን የመጀመሪያዎቹን ሁለት ጥያቄዎች ቢያሟላም፣ ሦስተኛ ውን ግን ውድቅ አድርጓል::

ኢየሱስ 2,000 እርያዎችን የማጥፋትና የእርያዎቹ ባለቤቶች ምናልባትም ለኪሣራ እንዲዳረጉ የመፍቀድ መብት አለውን? ሰዎቹ አይሁዶች ከሆኑ፣ ንጹሐን ካልሆኑ እንስሳት ምድብ ውስጥ የሚገኙትን እሪያዎች የማሳደግና የመሸጥ መብት አልነበራቸውም:: ነገር ግን አካባቢው የአሕዛብ ግዛት ስለሆነ፣ ሰዎቹ አሕዛብ ሳይሆኑ አይቀሩም::

ኢየሱስ አጋንንቱን ወደ ጥልቁ፣ ወደ እርያዎቹ ወይም ወደ ፈለገው ሌላ ስፍራ የመላክ ነጻነት አለው:: ነገር ግን ለምን ወደ እርያዎቹ ሰደዳቸው? ይህንን በማድረጉ፣ በስፍራው የነበሩት ሰዎች ሁለቱ ግለሰቦች በተአምር ከአጋንንት እስራት መፈታታቸውን ይመለከቱ ነበር:: የእርያዎቹ መጥፋት የአጋንንቱን መወገድ ለሁለቱ ሰዎችም ያረጋግጥ ነበር:: ከሁሉም በላይ ግን፣ ለእነዚህ ክርስቶስን ላልተቀበሉት ሰዎች የ2,000 እርያዎች በባሕር ውስጥ መስጠም ለሰይጣን እርያዎች እንደ ሰዎች ሁሉ ተስማሚዎች መሆናቸውን ያረጋግጥላቸዋል:: እንዲያውም፣ ሰይጣን ሰውን ወደ እርያነት ሊለውጠው ይችላል! ጌታ ሕዝቡን ሰይጣንና ኃጢአት ከሚያደርሱባቸው አደጋዎች እንዲጠነቀቁ እያሳሰበ ነበር:: ይህ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት» መሆኑን የሚያሳይ ሥዕላዊ ስብከት ነበር::

የእርያዎቹ እረኞች ለደረሰው ጥፋት ሊጠየቁ ስላልፈለጉ፣ በፍጥነት ሮጠው በመሄድ ለእርያዎቹ ባለቤቶች ስለተከሰተው ሁኔታ አስረዱ:: ባለቤቶቹ በደረሱ ጊዜ የሁለቱን ሰዎች መለወጥ አይተው ፈሩ:: ዕርቃናቸውን ወዲያ ወዲህ በመሯሯጥ ፈንታ ሰዎቹ በጤነኛ አእምሮ ልብስ ለብሰው ተቀምጠው ነበር:: አዲስ ፍጥረት ሆነው ነበር (2ኛ ቆሮ. 5:17)::

የእርያዎቹ ባለቤቶች ኢየሱስ ከአካባቢያቸው ለቅቆ እንዲወጣ የጠየቁት ለምን ነበር? እዚያው ሆኖ ሌሎች ችግረኞችን እንዲረዳ ለምን አልጠየቁትም? የባለቤቶቹ ዋንኛ ፍላጐት ንግድ ብቻ ነበር:: በመሆኑም፣ ኢየሱስ ብዙ ከቆየ በአካባቢው ኢኮኖሚ ላይ ተጨማሪ ውድመት እንዳያስከትል ሰግተው ነበር:: ጌታችን ባልተፈለገበት ስፍራ የመቆየት ፍላጎት ስላልነበረው፣ አካባቢያቸውን ለቅቆ ሄደ:: እነዚህ ሰዎች ያጡት ዕድል ምንኛ ታላቅ ነበር!

ኢየሱስ ነፃ የወጣው ግለሰብ እንዳይከተለው የፈለገው ለምን ነበር? ግለሰቡ ጥያቄውን ያነሣው ለጌታችን ከነበረው ፍቅር ሳቢያ ሲሆን፣ ይህም ታላቅ ምስክርነት ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ሰውዬው በወዳጆቹና በቤተሰቡ አካባቢ ስለ አዳኙ መመስከሩ የበለጠ ጠቃሚ መሆኑን ያውቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም ውጤታማ ክርስቲያናዊ ሕይወት መጀመር ያለበት ሰዎች በጣም በሚያውቁን አካባቢ ነበር፡፡ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን ካከበርን፣ በሌላ ስፍራ ለማገልገል ልናስብ እንችላለን፡፡ ይህ ሰው ለአሕዛብ ካገለገሉት ቀደምት ሚሲዮናውያን አንዱ ሲሆን በቅቷል፡፡ ኢየሱስ አካባቢውን ለቅቆ ለመውጣት ቢገደድም፣ የተፈወሰው ሰውዬ እዚያው ቀርቶ ለኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ኃይል እውነተኛ ምስክርነት ሰጥቷል፡፡ በዚህ ግለሰብ ምስክርነት ከአሕዛብ ብዙዎቹ በአዳኙ አምነዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

## 3. ድል በበሽታ ላይ (ማርቆስ 5:21-34)

የአንድ አካባቢ ሕዝብ በኢየሱስ መሄድ እፎይታ ሲሰማው፣ የሌላ አካባቢ ሕዝብ ግን ወደ አገሩ ወደ ቅፍርናሆም ሲመለስ ለመቀበል እየተጠባበቀ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል በተለይ ሁለት ሰዎች ሊያገኙት ቸኩለው ነበር፡፡ እነርሱም ልጁ ልትሞት የምታጣጥርበት ኢያኢሮስ የተባለ ሰውና በስሟ ያልተጠቀሰችው በማይድን በሽታ የተለከፈች ሴት ነበሩ፡፡ መጀመሪያ ወደ ኢየሱስ የቀረበው ኢያኢሮስ ቢሆንም፣ ኢየሱስ ግን መጀመሪያ የረዳው ሴቲቱን ነበር፡፡ ስለሆነም፣ ከእርሷ እንጀምራለን፡፡

በእነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል የነበረው ልዩነት በጣም የተራራቀ ሲሆን፣ የክርስቶስን ፍቅርና ምሕረት ስፋት ያሳያል፡፡ ኢያኢሮስ ትልቅ ሰውና የምኵራብ አለቃ ሲሆን፣ ሴቲቱ ግን «ተራ ሰው» ነበረች፡፡ ኢየሱስ ግን ሁለቱንም ተቀብሎ ረድቷቸዋል፡፡ ኢያኢሮስ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ደስታ ስትመግበው የኖረች ልጁን ሊያጣ ተቃርቦ ነበር (ቊ. 42)፣ ሴቲቱ ደግሞ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ሲያሠቃያት ከነበረው በሽታ የተነሣ የመኖር ተስፋዋ የመነመነ ነበር፡፡ ኢያኢሮስ የምኵራብ አለቃ በመሆኑ ሀብታም ሳይሆን አልቀረም፡፡ ሀብቱ ግን ልጁን ከሞት ሊታደግለት አልቻለም ነበር፡፡ ሴቲቱ ቀድሞውን ለጉስቊልና ተዳርጋለች፡፡ ገንዘቧን ሁሉ ለሐኪሞች

ብትከስክስም ማናቸውም ሊረዷት አልቻሉም። ኢያኢሮስም ሆነ ሴቲቱ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ያገኙት ከኢየሱስ እግር ሥር ነበር (ቍ. 22 እና 33)።

ሴቲቱ መድኃኒት በሌለው የደም መፍሰስ በሽታ ተይዛ ከቀን ወደ ቀን እየከሰሰች ትሄድ ነበር። በየዕለቱ ብርታቷን ሲመጥ የኖረው ይህ በሽታ ምን ያህል አሠቃቂና አስጨናቂ እንደነበረ መገመት አያዳግትም። ለሐኪሞች ገንዘቧን ከፍላ መጨረሷ ያሳደረባትን ቅያሜና ድህነት ስትመለከት፣ እስከዚያን ጊዜ ድረስ እንዴት ጸንታ እንደቆየች ማሰቡ አስገራሚ ነው። በዚህች ሴት ላይ ሌላም ጭነት ነበር። ይኸውም፣ በሕጉ መሠረት ይህች ሴት ርኩስ ስለሆነች፣ ከሃይማኖታዊም ሆነ ከማኅበራዊ ግንኙነቶች የተገለለች ነበረች (ዘሌዋ፣ 15 ከ19 ጀምሮ)። ሸክሟ ምንኛ ብርቱ ነበር!

ነገር ግን የከበቡትን ሰዎች እየሰነጣጠቀች ወደ ኢየሱስ በምትመጣበት ጊዜ በመንገዷ ላይ ምንም ዓይነት መሰናክል እንዲኖር አልፈቀደችም። ወደ እርሱ ላለመቅረብ ብዙ ማመኻኛ ዎች ልትደረድር ትችል ነበር። ኢየሱስ እንዲረዳኝ ለመጠየቅ የሚያስችል ክብር የለኝም። ወይም «አሁን ከኢያኢሮስ ጋር እየሄደ ስለሆነ ላስቸግረው አልፈልግም» ልትል ትችል ነበር። እስከ አሁን ያደረገችው ጥረት ሁሉ እንዳልተሳካላት በማሰብ አሁንም መሞከሩ ዋጋ እንደማይኖረው ልትናገር ትችል ነበር። ወደ እነዚያ ሐኪሞች ሁሉ ከሄደች በኋላ በመጨረሻው ላይ ወደ ኢየሱስ መምጣቱ «ባጣ ቆየኝ» ዓይነት ይሆንብኛል ልትልም ትችል ነበር። ነገር ግን ሁሉንም ማመኻኛዎች ወደ ጐን ትታ በእምነት ወደ ኢየሱስ መጣች።

የዚህች ሴት እምነት እንዴት ያለ ነበር? ደካማ፣ ዓይነ አፋርና ምናልባትም አጉል እምነት ነበር። ለመዳን ልብሱን መንካት እንዳለባትም ደጋግማ ስታሰላስል ነበር (3:10፤6:56 አንብብ)። ሌሎች በኢየሱስ መፈወሳቸውን ሲናገሩ ስለሰማች (5:27)፣ ወደ አዳኙ ለመድረስ ታላቅ ጥረት አደረገች። ኢየሱስም አላስቀየማትም። ምንም እንኳ እምነቷ ደካማ ቢሆንም፣ ኢየሱስ እምነቷን በማክበር ከሕመሟ ፈወሳት።

እዚህ ጋ ለሁላችንም የሚጠቅም ትልቅ ትምህርት አለ:: ሁሉም ሰው እኩል የእምነት ደረጃ ባይኖረውም፣ ኢየሱስ እምነታችን ምንም ያህል ደካማ ቢሆንም ምላሽ ይሰጣል:: በእርሱ በምናምንበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ኃይሉን ለእኛ ስለሚያካፍል አንድ ነገር ይከሰታል:: በዚያ ሕዝብ መካከል ከኢየሱስ ጋር እየተጓዙ ሲያልፉ ቆይተው ምንም ዓይነት ተአምር ያልደረሰላቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ:: ለምን? ምክንያቱም እምነት አልነበራቸውም? ኢየሱስን ማጀብ ሌላ፣ በእርሱ ማመን ደግሞ ሌላ ነገር ነው::

ሴቲቱ ከተፈወሰች በኋላ በሕዝቡ መካከል ተደብቃ ልትሰወር ስትሞክር፣ ኢየሱስ መለሳት:: ፍቅርን በተሞላ ሁኔታ ሴቲቱ እግዚአብሔር ስላደረገላት ተአምር ግሩም ምስክርነት እንድትሰጥ አደረገ:: ኢየሱስ በሰዎች ፊት ያነጋገራት ለምን ነበር? ማንም ሳያውቅ ለምን ወደ ቤቷ እንድትመለስ አላደረገም?

በአንድ በኩል፣ ይህንን ያደረገው ለራሷ በማሰብ ነበር:: እርሱ ለእርሷ ከፈዋሽ ሊበልጥላት ፈለገ:: አዳኛና ጓደኛዋ ሊሆን ወደደ:: ፊቱን ቀና ብላ እንድትመለከት፣ ፍቅሩን እንድትሞቅና ፍቅር የተሞላባቸውን የማረጋገጫ ቃላት እንድትሰማ ፈለገ:: ከእርሷ ጋር ተነጋግሮ በጨረሰ ጊዜ፣ ከሥጋዊ ፈውስ የበለጠ ነገር አገኘች:: «ልጄ ሆይ፣» ብሎ በመጥራት በሰላም ቡራኬ አሰናበታት (ቍ. 34):: «እምነትሽ አድኖሻል» የሚለው ዓረፍተ ነገር ሥጋዊ ፈውስ ከማግኘት ያለፈ መልእክት ያስተላልፋል:: ኢየሱስ መንፈሳዊ ፈውስም ሰጥቷታል::

በሕዝብ ፊት ያነጋገራት ለኢያኢሮስም ጭምር በማሰብ ነበር:: ልጁ ለሞት ታጣጥር ስለነበር ሊያበረታታው ፈለገ:: ሕዝቡ እያጨናነቀ ሳለ ይህች ሴት ጣልቃ ገብታ ወደ ኢያኢሮስ ቤት ፈጥነው እንዳይሄዱ አግዳቸው ነበር:: ከወዳጆቹ አንዱ መጥቶ የልጅቱን መሞት ባረዳው ጊዜ፣ ኢያኢሮስ ነገረ ዓለሙ እንደ ጨለመ ሳያስብ አልቀረም:: ጌታ ስለ እምነትና ሰላም ለሴቲቱ የተናገራቸው ቃላት እንደ ሴቲቱ ሁሉ ኢያኢሮስንም ሳያበረታቱት አልቀሩም::

በመጨረሻም ኢየሱስ ሴቲቱን በአደባባይ ያነጋገራት ምስክርነቷን ለሰዎች የማካፈልና እግዚአብሔርን የማክበርን

ዕድል እንድታገኝ በማሰብ ነበር። «እግዚአብሔር ያዳናቸው፣ ከጠላቶች እጅ ያዳናቸው ይናገሩ።. . . ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፣ ከጥፋታቸውም አዳናቸው። ለሰው ልጆች ስላደረገው ተአምራት ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ» [መዝ. (107)፡2፣ 20-21]። ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶቹ የሴቲቱን ምስክርነት ሰምተው በአዳኙ እንዳመኑ አይጠረጠርም። ወደ ቤቷ በደረሰች ጊዜም ለክርስቶስ መመስከር ምን እንደሆነ አውቃ ነበር።

## 4. ድል በሞት ላይ (ማርቆስ 5፡35-43)

ለኢያኢሮስ ወደ ኢየሱስ መጥቶ በአደባባይ እርዳታ መጠየቁ ቀላል ነገር አልነበረም። ኢየሱስን የሚቃወሙ የሃይማኖት መሪዎችም ሆኑ አንዳንድ የምኵራብ አለቆች የዚህ ዓይነቱን ተግባር አይደግፉም ነበር። ኢየሱስ በምኵራቦች ውስጥ ያስተማራቸውና ያደረጋቸው ነገሮች ጸሐፍትንና ፈሪሳውያንን አስቆጥተዋቸው ነበር። ከእነዚህም አንዳንዶቹ የኢያኢሮስ ወዳጆች ሊሆኑ ይችላሉ። ኢያኢሮስ ግን ከአጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ ምክንያት ወደ ኢየሱስ ለመምጣት ተገደደ። ብዙዎችም ወደ ኢየሱስ የሚመጡት እንዲህ ዓይነት የጭንቅ ጊዜ ሲደርስባቸው ነው። የወዳጆቹን ዝምድና አጥቶ ውድ ልጁን ለማዳን መረጠ።

ኢየሱስም ለኢያኢሮስ ጥያቄ ምላሽ በመስጠት በደስታ ወደ ተሞላ ድል መምራቱ ግሩም ትዕይንት ነው። በዚህ ሁሉ ክስተት ውስጥ ነገሮችን የሚለውጡት የጌታችን ቃላት ናቸው። እስኪ ጌታ የተናገራቸውን ሦስት ነገሮች እንመልከት።

1) *የእምነት ቃል* (5፡36)። በዚህ ነጥብ ላይ ኢያኢሮስ ጓደኛውን ወይም ጌታ ኢየሱስን ማመን ነበረበት። የሚወዳት ልጁ እንደ ሞተች በሰማ ጊዜ ሁለመናው በኃዘን እንደ ተመታ የሚያጠራጥር አይሆንም። ኢየሱስ ግን፣ «አትፍራ። በእምነትህ ጽና» አለው (ቀጥተኛ ትርጉም)። በሌላ አገላለጽ፣ ኢየሱስ ይህን ሲል፣ «ወደ እኔ በመጣህ ጊዜ የተወሰነ እምነት ነበረህ። ለሴቲቱ ተአምራት ሳደርግ ባየህ ጊዜ ደግሞ እምነትህ ጨምሮ ነበር። አሁንም ተስፋ አትቁረጥ! ማመንህን ቀጥል!» ማለቱ ነበር።

ለኢያኢሮስ ልጁ በሕይወት ሳለችና ጌታም አብሮት ወደ ቤቱ እየሄደ ሳለ ማመን ይቀልለው ነበር:: ነገር ግን ኢየሱስ ሴቲቱን ለመፈወስ ሲቆምና ጓደኛው መርዶ ይዞ ሲመጣ፣ ኢያኢሮስ እምነቱን ሊያጣ ተቃረበ:: በኢያኢሮስ ላይ ብዙም ባንፈርድበት መልካም ነው:: ሁኔታዎችና ስሜቶች ባጉበጡን ጊዜ እኛም ለጥርጣሬ በር ከፍተን ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሲዘገይ ለምን ይሆን ብለን አስበናል:: ይህ ልዩ የእምነት ቃል የሚያስፈልገን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በምንገኝበት ጊዜ ነው:: ይህንንም ከጌታ ዘንድ የምናገኘው ቃሉን ለማጥናት ጊዜ ስንሰጥ ነው::

2) *የተስፋ ቃል* (5:39):: ኢየሱስና ኢያኢሮስ ከቤቱ በደረሱ ጊዜ አይሁዳውያን አስለቃሾችን ተመለከቱ:: እነዚህ የተካኑ (የታወቁ) አስለቃሾች ሰው በሞተበት ስፍራ ሁሉ ይገኙ ነበር:: ሥራቸውም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማልቀስ የሟቹን ዘመዶችና ወዳጆች መቀስቀስ ነበር:: የእነዚህ አስለቃሾቹ ከቤቱ ውስጥ መገኘት ልጅቱ በትክክል ለመሞቷ ማረጋገጫ ነበር:: ምክንያቱም የልጅቱ መሞት ባይረጋገጥ ኖሮ አስለቃሾቹ አይጠሩም ነበር::

ጌታችንም:- «ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም» ሲል ለኢያኢሮስና ለባለቤቱ የተስፋ ቃል ሰጣቸው:: ለአማኝ ሞት እንቅልፍን የመተኛት ያህል ነው:: ምክንያቱም ሰውነቱ እስከ ትንሣኤ ቀን ያርፋልና (1ኛ ተሰ. 4:13-18):: መንፈስ ግን አይተኛም:: አንድ አማኝ በሚሞትበት ጊዜ መንፈሱ ከሥጋው ተለይቶ (ያዕ. 2:26) ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ይሄዳል (ፊልጵ. 1:20-23):: የጌታን መመለስና ትንሣኤ እየተጠባበቀ የሚያንቀላፋው ሥጋችን ነው (1ኛ ቆሮ. 15:51-58):: ይህ ክርስቲያን ወዳጆቻችንንና ዘመዶቻችንን በሞት ላጣን ወገኖች ትልቅ መጽናኛ ነው:: ይህ እርሱ ለእኛ የሰጠን የተስፋ ቃል ነው::

3) *የፍቅርና የኃይል ቃል* (5:41):: አለማመን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሲስቅ፣ እምነት ግን ቃሉን በመያዝ ኃይሉን ይለማመዳል:: ኢየሱስ በዚህ ተአምር የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ እየሞከረ አልነበረም:: የልጅቱ ወላጆች ስሜት እንዳይጐዳ

ከመጠንቀቁም ባሻገር፣ በአስለቃሾቹ ምፀታዊ ባሕርይ አዝኖ ነበር። *«ጣሊታ ቁሚ»* የሚለው ዓረፍተ ነገር በአረማይክ ቋንቋ፣ «አንቺ ብላቴና ተነሽ» የሚል ፍች ነበረው። ከዚያም ኢየሱስ «እኔ» በሚለው ቃል ላይ አጽንኦት በመስጠት «እኔ እልሻለሁ» ሲል ተናገረ። ይህንንም ያደረገው መንፈሷ ወደ ሥጋዋ የተመለሰው በእርሱ ሥልጣን በመሆኑ ነበር (ሉቃስ 8:55)። እነዚህ ቃላት ሰው ሙታንን ለማስነሣት ሊጠቀም የሚችላቸው ምትሐታዊ ቀመሮች አልነበሩም።

ልጅቱ ከሞት ወደ ሕይወት መመለስ ብቻ ሳይሆን፣ ከበሽታዋም ተፈወሰች። ምክንያቱም ከአልጋዋ ተነሥታ በቤቱ ውስጥ ተመላለሰች። አፍቃሪው ሐኪም በሁኔታው የተደነቁት ወላጆቿ የምትበላውን እንዲሰጧት ነገራቸው። ይህም በሽታዋ እንዳያገረሽባት በማሰብ የተናገረው ነበር። መለኮታዊ ተአምራት ምን ጊዜም የተለመዱትን ሰብአዊ እንክብካቤዎች ፍጹም ሊተኩ ባይችሉም ማድረግ ያለብንን አለማድረጋችን እግዚአብሔርን መፈታተን ይሆናል።

እንደ ቀደሙት ተአምራት ሁሉ፣ ኢየሱስ በዚህም ጊዜ የልጅቱን ከሞት መነሣት ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው (ማር. 1:44፤ 3:12)። ምናልባትም አስለቃሾቹ ልጅቱ ራሷን ስታ እንደነበረና ሙሉ ለሙሉ እንዳልሞተች የሚያመለክት ቃል ሳይናገሩ አልቀሩም። በእነርሱ አስተሳሰብ ምንም ዓይነት ተአምር አልተደረገም ነበር። አንድ ነገር እውነት መሆኑን ለማወቅ በሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ይረጋገጥ ይላል ሕጉ (ዘዳግ. 17:6፤ 19:15)፤ ይሁን እንጂ ይህ ተአምር ለመፈጸሙ አምስት ምስክሮች ነበሩ! ምንም እንኳ በወንጌላት ውስጥ ስለ እነርሱ የተጠቀሰ ተጨማሪ ዘገባ ባይኖርም፣ ኢያኢሮስና ባለቤቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመናቸውን የሚያመለክት ምክንያት አለን። በሕይወት ዘመኗ ሁሉ ልጅቱ የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይል የምታሳይ ምስክር ነበረች።

በእርግጥ የእግዚአብሔር ባሪያ አደጋን፣ አጋንንትን፣ በሽታንና ሞትን ያሸንፋል። እነዚህ ተከታታይ ተአምራት ኢየሱስ ከራሱ ደቀ መዛሙርት ጀምሮ አጋንንት እስካደሩባቸው ግለሰቦች ድረስ

ሁሉንም ዓይነት ሰዎች እንዳገኘና እንደረዳ ያሳያሉ፤ ዛሬም እኛን ሲረዳ የሚችል አምላክ መሆኑን ያረጋግጡልናል::

ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ሁልጊዜም ሕዝቡን ከአደጋ ማዳን (የሐዋ. 12 አንብብ) ወይም ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች መፈወስ አለበት ማለት አይደለም (2ኛ ቆሮ. 12:1-10 አንብብ):: ነገር ግን የመጨረሻው ሥልጣን በእርሱ እጅ እንደሆነና ምንም ነገር መፍራት እንደሌለብን ያሳያል:: «በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ 8:37)::

# 5

# የእግዚአብሔርን ባሪያ የሚያምን ሰው ይኖር ይሆን?

## ማርቆስ 6:1-56

ቻርለስ ዳርዊን፣ «ሰውን ከሌሎች እንስሳት ከሚለዩት ነገሮች ሁሉ ምልዓት ያለው እምነት ብቻ ነው» ብሏል:: ይህ አስተሳሰብ እውነት ከሆነ፣ እምነት የሌለው ሰው ከእንስሳት ጋር እኩል ነው ማለት ነው:: የአግኖስቲክ ሰባኪ የሆነው ሮበርት ኢንገርሶል ከዚህ የተለየ አቋም በመያዝ አማኝ «በሳጥን ውስጥ እንደሚኖር ዝማሬ የሌለው ወፍ» መሆኑን ገልጿል:: የዚህ ግለሰብ ቃላት ከሚያምን ይልቅ የማያምነውን ሰው በተሻለ ሁኔታ ይገልጻሉ::

በዚህኛው የማርቆስ ወንጌል ክፍል ከሚገኙት ጭብጦች አንዱ ወደ እግዚአብሔር ባሪያ የመጡት ሰዎች አለማመን ነው:: የራሱን ደቀ መዛሙርት ጨምሮ፣ እነዚህ ሁሉ ሰዎች ኢየሱስን ለማመን የሚያስችሉ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሯቸውም፣ ይህንኑ ከማድረግ ተቆጥበዋል:: ይህንን ክፍል በምታጠናበት ጊዜ የዕብራውያን 3:12ን ጽኑ ምክር ልብ ብለህ አስተውል:: «ወንድሞች ሆይ፣ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ::» እግዚአብሔር አለማመንን በጽኑ ስለሚጠላ፣ እኛም በዚህ ጉዳይ ላይ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል::

## 1. በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች አለማመን (ማርቆስ 6:1-6)

ኢየሱስ ከአንድ ዓመት በፊት ሕዝቡ ተቀባይነት ወደነፈጉትና ከምኩራብ ወደተባረረበት የናዝሬት ከተማ ተመልሶ መጣ (ሉቃስ 4:16-30):: ጌታ ለሕዝቡ ቃሉን በመስማት አምነው የሚድኑበትን ሌላ ዕድል መስጠቱ የጸጋ ሥራ ነበር:: ይሁንና፣ የሕዝቡ ልብ አሁንም እንደ ጠጠረ ነበር:: በዚህ ጊዜ ባያባርሩትም፣ ከቁም ነገር አልቆጠሩትም::

የጌታችን ዝና ከእርሱ ቀድሞ ስለናኘ፣ አሁንም በምኩራብ ውስጥ እንዲያስተምር ተፈቀደለት:: ናዝሬት «የገዛ አገሩ» ስለነበረች፣ የሚያስተምረው በሚገባ ለሚያውቁት ሰዎች ነበር:: እነዚህ ትውውቆች ግን መንፈሳዊ ግንዛቤዎችን አላሳደጉም:: እንዲያውም ኢየሱስ፣ ነቢይ በአገሩና በሕዝቡ ዘንድ እንደማይከበር በመጀመሪያው ታላቅ ጉብኝቱ የነገራቸውን እንደገና አስታውሷቸዋል (ማር. 6:4፤ ሉቃስ 4:24፤ ዮሐ. 4:44)::

እነዚህ ሰዎች በሁለት ነገሮች ተደንቀው ነበር:: እነዚህም ታላላቅ *ሥራዎቹ*ና ግሩም ጥበቡ ነበሩ:: ጌታችን በዚያ ስፍራ ታላላቅ *ሥራዎች*ን ስላልሠራ፣ ከሌሎች የሰሟቸውን መጥቀሳቸው ይሆናል (ማር. 1:28፣45፤3:7-8፤ 5:20-21):: እንዲያውም፣ ባለማመናቸው ምክንያት ኢየሱስ በመካከላቸው ብዙ አገልግሎት ሊያበረክት አልቻለም ነበር::

ችግራቸው ምን ነበር? እርሱን ለማመንና እንደ ሌሎቹ የጸጋውንና የኃይሉን ድንቅ ክስተት ሊለማመዱ ያልቻሉት ለምን ነበር? *እናውቀዋለን ብለው አስበው ነበር!* ምክንያቱም ለሠላሳ ዓመታት ያህል ጐረቤታቸው ስለነበር፣ በአናጢነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ ያዩት ነበር:: ከሌሎች የናዝሬት ሰዎች የተለየ አልመሰላቸውም ነበር:: «ተራ ሰው» ስለመሰላቸው፣ ራሳቸውን ለእርሱ አሳልፈው የሚሰጡበት ምክንያት አልታያቸውም::

በ2 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት (ዓክልበ) ይኖር የነበረ አንድ ሶሪያዊ እንደተናገረው፣ «መተዋወቅ ያናንቃል»:: ኤሶፕም ይህንኑ እውነታ የሚያረጋግጥ ተረት ጽፏል:: ተረቱ እንደሚለው፣ አንድ አንበሳ አይቶ የማያውቅ ቀበሮ ነበር:: ለመጀመሪያ ጊዜ ቀበሮው ከእንስሳት ንጉሥ ጋር በተገናኘ ጊዜ፣ እጅግ ከመፍራቱ የተነሣ ተንቀጠቀጠ:: ለሁለተኛ ጊዜ ሲገናኙ ብዙም አልፈራም:: ለሦስተኛ ጊዜ በተገናኙበት ወቅት ቀበሮው ደፍሮ ሊያነጋግረው ቻለ! ኤሶፕ ተረቱን ሲያጠቃልል፣ «መቀራረብ እጅግ አስፈሪው ነገር እንኳ ጉጂ እንዳልሆነ ያስመስለዋል» ብሏል::

ይህም ሆኖ፣ ይህ አባባል በጥንቃቄ ሊወሰድ የሚገባው ነው:: ለምሳሌ፣ የሚዋደዱ ባልና ሚስት በጣም ስለሚተዋወቁ ይናናቃሉ ማለት ይቻላልን? በዓመታት ውስጥ ወዳጅነታቸው እየጠለቀ ከመሄዱ የተነሣ የሚዋደዱ ጓደኞች ሊናናቁ ይችላሉን? ፊልፕስ ብሩክስ ይህንን በግሩም ሁኔታ ገልጸውታል:: «ትውውቅ መናናቅን የሚያስከትለው በተናቁ ነገሮች ወይም ሰዎች መካከል ብቻ ነው::» የናዝሬት ሰዎች ንቀት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ የሚያስከትለው መልእክት ባይኖርም፣ ስለ ራሳቸው ድክመት ሰፊ ትምህርት ይሰጣል::

በሥነ ጥበብ አዳራሹ (ጋለሪው) ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ለመመልከት የጓጓ አንድ ጐብኚ ከአንዱ ሥዕል ወደ ሌላው እየዘለለ ሲቆይ በማዕቀፎቹ ውስጥ የነበሩትን ነገሮች በቅጡ አላጤናቸውም ነበር:: ከአዳራሹ በሚወጣበት ጊዜም፣ «እዚህ ምንም የተለየ ነገር አላየሁም» ሲል ከዘበኞቹ ለአንዱ ተናገረ:: ዘበኛውም፣ «እዚህ የጥራት ምርምር የሚካሄደው በሥዕሎቹ ላይ ሳይሆን በተመልካቹ ላይ ነው» ሲል መለሰ::

አናጢነት በዚያን ዘመን የተከበረ ሙያ ቢሆንም፣ አናጢ ተአምራትን ሲያደርግ ወይም በምኩራብ ውስጥ ጥልቅ እውነቶችን ሲያስተምር መመልከቱ አስገራሚ ነበር:: ይህን ሁሉ ኃይልና ጥበብ ከየት አመጣው? ከእግዚአብሔር ወይስ ከሰይጣን? (3:22 አንብብ):: እኅቶቹና ወንድሞቹስ ለምን እንዲህ ዓይነት ኃይልና ጥበብ ሊኖራቸው አልቻለም? ከዚህም በላይ ደግሞ፣ ወንድሞቹና እኅቶቹ ለምን አያምኑበትም? «የማርያም ልጅ» እያሉ የሚጠሩት ሰዎች የስድብ ቃል በመሰንዘር ላይ ነበሩ:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ሰው ተለይቶ የሚታወቀው በአባቱ እንጂ በእናቱ ስም አልነበረም::

የናዝሬት ሰዎች በእርሱ ተሰናከሉ:: ቅሌትን የሚያመለክተው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘው (scandalize) መሰናከላቸውን ከሚያስረዳው የግሪክ ቃል ነው:: "Wuest's Word Studies" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ውዬስት እንደ ገለጹት፣ «ስለ እርሱ የሚያቀርቡት ማብራሪያ ስላልነበራቸው፣ ሊቀበሉት አልፈለጉም::» ኢየሱስ ባለማመናቸው ምክንያት የማሰናከያ ዓለት ሆነባቸው (ኢሳ. 8:14፤ ሮሜ 9:32-33፤ 1ኛ ጴጥ. 2:8)::

በዚህ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ሁለት ጊዜ ሲደነቅ ታየዋለህ:: ይህ ምንባብ እንደሚያመለክተው፣ ኢየሱስ በአይሁዶቹ አለማመንና አሕዛብ በሆነው የሮም መቶ አለቃ ታላቅ እምነት ተደንቋል (ሉቃስ 7:9):: ኢየሱስ ከናዝሬት ወጥቶ ወደ ገሊላ ከተሞችና መንደሮች አመራ:: በሕዝቡ አሳዛኝ ሁኔታ ልቡ ስለ ተሰበረ (ማቴ. 9:35-38)፣ ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ ሥልጣንና ኃይል እንዲያገለግሏቸው ላካቸው::

## 2. የጠላቶቹ አለማመን (ማርቆስ 6:7-29)

ጌታ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መጀመሪያ ሲጠራ፣ ዓላማው እነርሱን ማስተማርና ማሠልጠን ነበር:: ይህም ያስፈለገው በአገልግሎት እንዲያግዙትና በመጨረሻም ወደ አብ በሚመለስበት ጊዜ እንዲተኩት ነበር (3:13-15):: ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ከመላኩ በፊት አጋንንትን የማስወጣትና በሽተኞችን የመፈወስ ሥልጣን እንዳላቸው በድጋሚ አረጋገጠላቸው (ቍ.7):: አንዳንድ መመሪያዎችንም ሰጣቸው (የዚህን ስብከት ዝርዝር ከማቴዎስ 10 አንብብ)::

ለተንቀሳቃሽ አገልግሎታቸው ተጨማሪ ዕቃዎችን ሳይገዙ ያሏቸውን ብቻ ይዘው እንዲወጡ ነገራቸው:: በተጨማሪ የዕቃዎች ሸክም መጨናነቅ አያስፈልጋቸውም ነበር:: (በዚህ «የተልዕኮ ስብከት» ውስጥ ምን ያህል የጥድፊያ ስሜት እንደሚንጸባረቅ ልትመለከት ትችላለህ::) ኢየሱስ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እንዲይዙ ቢነግራቸውም፣ በእምነት ለመኖር በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገኙ ግን አልፈለገም ነበር:: «ከረጢት» የሚለው ቃል «የለማኝን ከረጢት» ያመለክታል:: ምግብም ሆነ ገንዘብ መለመን አያስፈልጋቸውም ነበር::

ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በሚያገለግሉበት ወቅት ተቀባይነትና ጥላቻ፣ ወዳጅነትና ጠላትነት ያጋጥማቸው ነበር:: ወደ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በሚሄዱበት ጊዜ ምግብና መጠለያ ሳይመርጡ በአንድ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ አስጠንቅቋቸዋል:: ምክንያቱም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ሞልቃቃ እንግዶች ሳይሆኑ ጠቃሚ አገልጋዮች መሆን ያስፈልጋቸው ነበር:: አንድ ቤት

ወይም መንደር በማይቀበላቸው ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዲያውጁ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል:: አይሁዶች ከአሕዛብ ክልል በሚወጡበት ጊዜ ትቢያቸውን ከእግራቸው የማራገፍ ልማድ ነበራቸው:: በራሳቸው አይሁዳውያን ሕዝቦች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ ግን አዲስ ነገር ነው (ሉቃስ 10:10-11፤ የሐዋ. 13:51)::

በቊ. 7 «ላከ» ተብሎ የተተረጐመው ቃል፣ በግሪኩ «አፖስቴሎ» (apostello) የሚል ነው:: ሐዋርያ (በእንግሊዝኛው «አፖስትል») የመጣው ከዚሁ ቃል ነው:: ፍችውም፣ «ሌላውን ሰው በመወከል ተግባሩን ለማከናወን በልዩ ተልዕኮ የተላከ» ማለት ነው:: ኢየሱስ ለእነዚህ አሥራ ሁለት ሰዎች ሐዋርያዊ ሥልጣንና የላካቸውን ተግባር የሚያከናውኑበትን መለኮታዊ ብቃት ሰጥቷቸዋል:: የሚናገሩና የሚያደርጉት ሁሉ የራሳቸውን ሳይሆን የወከላቸውን ጌታ የሚያንጸባርቅ ነበር::

የሐዋርያት ስሞች ጥንድ ጥንድ ሆነው መጠቀሳቸው ቀደም ሲል ተገልጿል (ማር. 3:16-19):: ጴጥሮስና እንድርያስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ፣ ፊልጶስና በርተሎሜዎስ፣ ወዘተ. . .ኢየሱስ ጥንድ ጥንድ አድርጐ የላካቸው ሁልጊዜም ለአገልጋዮች አብሮ መጓዙና መሥራቱ ቀለል የሚልና ከአደጋም የሚጠብቃቸው በመሆኑ ነው:: «ሁለቱ ከአንድ ይሻላሉ» (መክ. 4:9):: ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው፣ አንዱን ጉዳይ ለማረጋገጥ የሁለት ምስክሮች መኖር ሕግ የሚጠይቀው መስፈርት ነበር (ዘዳግ. 17:6፤ 19:15፤ 2ኛ ቆሮ. 13:1):: አብረው በመሆናቸው እርስ በርሳቸው ይተጋገዙና ይማማሩ ነበር::

ሰዎቹ ጉዟቸውን ጀምረው ኢየሱስ ያዘዛቸውን አደረጉ:: ጥቂት ተራ ሰዎች በዚህ ዓይነት ታላቁን አምላክ ወክለው መውጣታቸውና ተአምራትን በመሥራት ሥልጣናቸውን ማሳየታቸው አስገራሚ ነገር ነው:: ሁልጊዜም እግዚአብሔር የሚያዘንን ተግባር የምንፈጽምበትን ኃይል ይሰጠናል (2ኛ ቆሮ. 3:5-6):: የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች በማወጅ፣ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ በመጥራትና የታመሙትን በመፈወስ አገልግሎታቸውን አካሂደዋል (ማር. 6:12-13፤ ሉቃስ 9:6)::

በደቀ መዛሙርቱ የታገዘው የክርስቶስ አገልግሎት ታሪክ እስከ ሄሮድስ አንቲጳስ ቤተ መንግሥት ድረስ ተሰማ (ሉቃስ 9:7)። ማርቆስ ሄሮድስ እንደሚፈልገው «ንጉሥ» ብሎ ጠርቶታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ፈሪሀ እግዚአብሔር የራቀው ሄሮድስ ከአገሪቱ አንድ አራተኛውን ክፍል ብቻ ነበር የሚገዛው። ታላቁ ሄሮድስ ሲሞት፣ ሮማውያን ግዛቱን ለሦስት ልጆቹ አካፈሉ። በዚህም መሠረት፣ አንቲጳስ የጼርያና ገሊላ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ።

ሄሮድስ አንቲጳስ የንጉሥ አሬታስ 4ኛን ልጅ አግብቶ ነበር። ነገር ግን የወንድሙ ሄሮድስ ፊልጶስ ሚስት የሆነችውን ሄሮድያዳን ለማግባት ይችል ዘንድ ሚስቱን ፈታት። ይህ የሙሴን ሕግ የሚጻረር ተግባር በመሆኑ (ዘሌዋ. 18:16፤20:21)፣ ፍርሃት የማይመክተው መጥምቁ ዮሐንስ ንጉሡን ስለ ኃጢአቱ አወገዘው። ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ አስደናቂ ሥራዎች ሲሰማ፣ እርሱ ያስገደለው መጥምቁ ዮሐንስ ሊኮንነው ከሞት ተነሥቶ የመጣ መሰለው። የሄሮድስ ሕሊና በበደለኛነት ስሜት እየታመሰ ቢሆንም፣ በታማኝነት ኃጢአቶቹን ተጋፍጦ ንስሐ ሊገባ አልፈቀደም ነበር።

በዚህ ነጥብ ላይ፣ ማርቆስ ምልክትን በመጠቀም መጥምቁ ዮሐንስ እንዴት ፍትሐዊነት በጐደለው መንገድ በጭካኔ እንደ ታሰረና እንደ ተገደለ ያብራራል። በዚህ አጭር ዘገባ እንኳ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የነበረውን ውጥረት ልንመለከት እንችላለን። ሄሮድስ ዮሐንስን ፈራው፣ ስብከቱን ለብቻ ከሰማ በኋላ ለሚወስደው እርምጃ ጥርት ያለ አቋም አልነበረውም። በሌላ በኩል፣ «ንግሥት» ሄሮድያዳ ዮሐንስን ትጠላው፣ ልትገድለው ትፈልግና አመቺ ጊዜ ትጠባበቅ ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች በክፉ ባሕርያቸውና ሕገ - ወጥ ድርጊታቸው አክዓብንና ኤልዛቤልን ያስታውሱናል (1ኛ ነገ. 18-21)።

ሄሮድያዳ ዕቅዷን ከሥራ ላይ የምታውልበት «ስትራቴጂያዊ ቀን» ደረሰ (ማር. 6:21)። ይህም የሄሮድስ የልደት ቀን ነበር። ነገሥታት ሀብታምነታቸውን ለማሳወቅና በምቾት ራሳቸውን ለማስደሰት ሲሉ የተጋነኑ ድግሶችን ያዘጋጁ ነበር። አይሁዶችም ሴት ልጅ በወንዶች ፊት እንድትደንስ አይፈቅዱም ነበር።

አብዛኞቹ የአሕዛብ እናቶችም እንደ ሄሮድያዳ እንዲህ ዓይነት ተግባር እንድትፈጽም ልጃቸውን አይገፋፉም ነበር:: (የልጅቱ ስም ሰሎሜ እንደነበረ ታሪክ ይናገራል::) ሰሎሜ እናቷ መጥምቁ ዮሐንስን ለማጥፋት የወጠነችው ዕቅድ አካል በመሆኗ፣ የድርሻዋን በጥሩ ሁኔታ ተወጣች::

ሄሮድስ ልጅቱ ያቀረበችውን አሰቃቂ ጥያቄ ሲሰማ «እጅግ አዘነ» (ኢየሱስ በ14:34 ላይ ተመሳሳይ ግሥ እንደ ተጠቀመ ልብ በል):: ነገር ግን የገባውን ቃል መጠበቅ ነበረበት ወይም ተደማጭነት የነበራቸው ሰዎች በተገኙበት ስፍራ «ዓይንህ ለአፈር» እንደሚባል ማወቅ ነበረበት:: በቁጥር 26 «መሐላው» የሚለው ብዙ መሐላዎችን የሚያመለክት ነው:: ምክያቱም ሄሮድስ ለልጅቱ ሽልማት እንደሚሰጥ ደጋግሞ ቃል ሲገባላት ነበርና:: እንግዶቹን ከሚያስደንቅባቸው መንገዶች አንዱ ይኼ ነበር:: ነገር ግን የወሰደው እርምጃ በራሱ ላይ ችግር አስከተለ:: የዮሐንስን ቃል ለመታዘዝ ያልደፈረው ሄሮድስ የራሱን ቃል ለመታዘዝ ተገደደ! ይህም የንጹሕ ሰው ደም እንዲያፈስስ አደረገው::

መጥምቁ ዮሐንስ ከታሰረ በኋላ ማናቸውም የአይሁድ መሪዎች ሊያድኑት አለመሞከራቸው አስገራሚ ነገር ነው:: ተራ ሰዎች ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ እንደሆነ ቢያምኑም፣ የሃይማኖት መሪዎች መልእክቱን አልታዘዙም (ማር. 11:27-33):: የዮሐንስ ሞት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከተፈጸሙት ሦስት ጭካኔ የተሞላባቸው ግድያዎች አንዱ ነው:: ሌሎች ሁለቱ የክርስቶስ ስቅላትና የእስጢፋኖስ መወገር ናቸው (የሐዋ. 7):: የእነዚህን ክስተቶች ጠቀሜታ በማርቆስ 3:22-30 ላይ ከተሰጠው አስተያየት አንብብ:: ሄሮድስ የዮሐንስ መልእክት ሕዝቡን ለዓመፅ ይቀሰቅሳል የሚል ፍርሃት አድሮበት ነበር:: ምንም እንኳ ይህ የእግዚአብሔርን ሰው መግደልን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ሚስቱን ለማስደሰት ፈለገ::

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የመሪያቸውን ሬሳ ወስደው እንዲቀብሩ ተፈቀደላቸው:: ይህንኑም ካደረጉ በኋላ ስለተፈጸመው ሁኔታ ለመናገር ወደ ኢየሱስ ሄዱ (ማቴ. 14:12):: ጌታችን አንድ ቀን ራሱም እንደሚገደል ያውቅ ስለነበር፣ የዮሐንስን

መሞት የሚያስረዳው መርዶ ጥልቅ ኃዘን ሳያሳድርበት እንዳልቀረ የሚያጠራጥር አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በወንጌላት ውስጥ ሄሮድስ አንቲጳስ ኢየሱስን «እየመረመረ» ጌታችን ተአምር ሲሠራ ለማየት ተስፋ ሲያደርግ እንመለከታለን (ሉቃስ 23:6-12)። ኢየሱስ ተአምር አድርጐ ሊያስደስተው ቀርቶ ከዚህ ዘማዊና ነፍሰ ገዳይ ጋር ሊነጋገር እንኳ አልፈለገም። ኢየሱስ ሄሮድስን «ቀበሮ» ሲል ጠርቶታል (ሉቃስ. 13:31-35)። ይህም ለዚህ ብልጣ ብልጥ ግለሰብ ተስማሚ ስያሜ ነበር። በ39 ዓ.ም የሄሮድስ አንቲጳስ የወንድሙ ልጅ የሆነው ሄሮድስ አግሪጳ (የሐዋ. 12:1) አጐቱን ለሮማው ንጉሠ ነገሥት በማሳጣቱ አንቲጳስ ከሹመቱ ተነሥቶ እንዲሰደድ ተደርጓል። «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?» (ማር. 8:36)።

## 3. የደቀ መዛሙርቱ አለማመን (ማርቆስ 6:30-56)

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ከሥራ በኋላ ያርፉ ዘንድ ለብቻቸው ዕረፍት ወደሚያገኙበት ስፍራ ወሰዳቸው። ስለ አገልግሎታቸው ሊያወያያቸውና ለቀጣዩ ተልእኳቸው ሊያዘጋጃቸው ፈልጐ ነበር። ቫንስ ሃቭነር እንደተናገሩት፣ «ከሥራህ ተለይተህ የማታርፍ ከሆነ፣ ራስህ ትገነጣጠላለህ።» የእግዚአብሔር ባሪያ ልጅ እንኳን ማረፍ፣ ከጓደኞቹ ጋር ኅብረት ማድረግና ከአብ ጋር የተቀደሰ ግንኙነት ማድረግ ያስፈልገው ነበር።

ሌላው ምክንያት እያደገ የመጣው የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች ተቃውሞ ነበር። ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን መግደሉ ሁኔታው እንደ ተለወጠና ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መጠንቀቅ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነበር። በቀጣዩ ምዕራፍ ውስጥ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችን ጥላቻ እናገኛለን። የሕዝቡ ፖለቲካዊ ፍላጐት በበኩሉ ሁልጊዜም ችግር ሲያስከትል ቆይቷል (ዮሐ. 6: ከ 15 ጀምሮ)። ለዚህ ሁሉ አማራጩ ገለል ማለቱ ነበር።

ነገር ግን ሕዝቡ በሄደበት ሁሉ መከተላቸው አልቀረም። ተአምራዊ ፈውሶችን ሲያካሂድ ለመመልከት ተስፋ አድርገው ከቤተሳይዳ አቅራቢያ እስከሚገኘው አካባቢ ድረስ ተከተሉት

(ሉቃስ 9:10-11፤ ዮሐ. 6: ከ1 ጀምሮ):: ዕቅዱ ቢስተጓጐልበትም፣ ጌታ የታመሙትን በመፈወስና ቃሉን በማስተማር አገልግሏቸዋል:: በራሴ አገልግሎትና ሕይወት ብዙ ጣልቃ ገብ ጉዳዮች ስላጋጠሙኝ፣ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ኢየሱስ የሚያሳየው ትዕግሥትና ጸጋ ይደንቀኛል:: ይህ ልንከተለው የሚገባን ምንኛ ታላቅ ምሳሌ ነው!

ማርቆስ ኢየሱስ ከፈጸማቸው ተአምራት ሁለቱን ጠቅሷቸዋል::

1) *አምስት ሺህ ሕዝብ መመገቡ* (6:33-44):: ኢየሱስ ለድሆቹ ሕዝቦች ስለ ራራላቸው አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት እንዲያገለግሏቸው ላከ (ማቴ. 9:36-38):: በዚህ ጊዜ ድሆቹ ሕዝቦች ወደ እነርሱ ሲመጡ ደቀ መዛሙርቱ ሊመልሷቸው ፈለጉ:: ገና ሕይወትን በጌታቸው ዓይን ማየት አልጀመሩም ነበር:: ለእነርሱ ሕዝቡ ችግር፣ ከዚያም በላይ የሚያበሳጩ ነገሮች ነበሩ:: ለኢየሱስ ግን እረኛ እንደ ሌላቸው በጐች ነበሩ::

ዲ. ኤል. ሙዲ በቺካጎ ታላቅ የሰንበት ትምህርት ቤት በሚገነቡበት ወቅት ልጆች ከየአቅጣጫው መጡ:: ልጆች ብዙውን ጊዜ ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናትና የሰንበት ትምህርት ቤቶችን አልፈው ወደ ሙዲ ይመጡ ነበር:: አንድ ልጅ ለምን ይህን ያህል ርቀት ተጉዞ ወደ ሙዲ የሰንበት ትምህርት ቤት እንደሚመጣ በተጠየቀ ጊዜ፣ «ምክንያቱም እነርሱ ልጆችን ይወዳሉ» ነበር ያለው:: ልጆች ልዩነቱን ያውቁ ነበር::

ደቀ መዛሙርቱ የድሆችን ችግር ለመቅረፍ ሁለት አማራጮችን አቅርበው ነበር:: አንድም ሕዝቡ ለራሳቸው ምግብ ፈልገው እንዲበሉ ወደየፊናቸው እንዲሄዱ ማድረግ፣ አሊያም እያንዳንዱ ሰው ትንሽ እንጀራ እንዲቀምስ በቂ ገንዘብ ማሰባሰብ:: ደቀ መዛሙርቱ የሚያስቡት ምንም ሊደረግ በማይችልበት ስፍራና ጊዜ ላይ መገኘታቸውን ነበር:: በዚህ አስተሳሰባቸው፣ ትክክለኛ የኮሚቴ አባላት ሊሆኑ ይችሉ ነበር:: አንድ ሰው እንደተናገረው፣ ኮሚቴ ማለት በግል ደረጃ ምንም ነገር የማያደርጉና በአንድነትም ምንም ነገር ሊደረግ እንደማይችል የሚወስኑ የሰዎች ስብስብ ነው::

ኢየሱስ ሁኔታውን የተመለከተው እንደ ችግር ሳይሆን፣ አብን ለመተማመንና ስሙን ለማስከበር እንደሚያስችል አጋጣሚ ነበር:: ውጤታማ መሪ በችግሮች ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉትን ተግባራት የሚመለከትና በእምነት እርምጃ የሚወስድ ሰው ነው:: በሰብአዊ ጥበብ በመመራታቸው ደቀ መዛሙርቱ ችግሩን እንጂ በችግሩ ውስጥ ሊከናወን የሚችለውን ተግባር አልተመለከቱም:: ብዙ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ «በቂ ገንዘብ ቢኖረን አንድ ነገር ልናደርግ እንችል ነበር!» ሲሉ አማርረዋል! ሁለት መቶ ዲናር አንድ ተራ የጉልበት ሠራተኛ በዓመት የሚያገኘው ደመወዝን ያህል ነው:: የመጀመሪያው እርምጃ ሀብታችንን ሳንለካ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ፍላጐታችንን እንደሚያሟላ መተማመን ነው::

ምግብ የያዘ ልጅ ያገኘው እንድርያስ ነበር (ዮሐ. 6:8-9):: ጌታ ሕዝቡ ከሣር ላይ እንዲቀመጡ አደረገ [መዝ. (23):2፤ (78):19 አንብብ]:: ይህ ከሄሮድስ አንጸባራቂ ድግሦች የተለየ ነበር:: ኢየሱስ ትንሿን ምሳ ወስዶ በመባረክ ቆርሶ ለተራቡት ሕዝብ ያከፋፍሉ ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው:: ተአምሩ የተፈጸመው በእርሱ እንጂ በእነርሱ እጆች ውስጥ አልነበረም:: እርሱ የምንሰጠውን ነገር ሁሉ ሊባርክና ሊያበዛ ይችላልና:: እኛ አምራቾች ሳንሆን አከፋፋዮች ነን::

ዮሐንስ ኢየሱስ ይህንን ተአምር በመጠቀም ስለ «የሕይወት እንጀራ» እንደ ሰበከ ያስረዳል (ዮሐ. 6:ከ22 ጀምሮ):: መታወቅ ያለበት ኢየሱስ ተአምራትን የሚፈጽመው የሰውን ልጅ ፍላጐቶች ለማሟላት ብቻ አልነበረም፤ ምንም እንኳ ይህም አስፈላጊ ቢሆንም:: እያንዳንዱ ተአምር ስለ እርሱ የሚገልጥ ተግባራዊ ስብከት እንዲሆን ይፈልጋል:: አብዛኛውን ጊዜ ሕዝቡ በተአምራቱ በመደሰትና ስላበረከተላቸው እገዛ በማመስገን ምላሽ ቢሰጡም፣ መንፈሳዊውን መልእክት ለመገንዘብ ይቸገሩ ነበር (ዮሐ. 12:37):: የፈለጉት ስጦታውን እንጂ ሰጪውን አልነበረም:: መንፈሳዊ በረከቶችን ሳይሆን ሥጋዊ በረከቶችን ፈለጉ::

*(2.) የማዕበሉ ጸጥ ማለት* (6:45-56):: በዚህ ክስተት ውስጥ ተከታታይ ተአምራት ታይተዋል፡- ኢየሱስ በውኃ ላይ

ሲረማመድ፣ ጴጥሮስም እርሱን ተከትሎ በውኃ ላይ ሲረማመድ (ማርቆስ ይህን አልጻፈም:: ማቴ. 14:28-34 አንብብ):: ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ ሲያደርግና እርሱ በገባበት ጊዜ ጀልባዋም ከባሕሩ ዳርቻ ስትደርስ እንመለከታለን (ዮሐ. 6:21):: ይህ ለአሥራ ሁለቱ «አስደናቂ ሌሊት» ነበር::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሄዱ ግድ ያላቸው ለምን ነበር? ምክንያቱም ሕዝቡ እየተቅበጠበጡ በመሆናቸው ኢየሱስን ለማንገሥ ቅስቀሳ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር (ዮሐ. 6:14-15):: አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የዚህ ዓይነቱን ፈተና ለመጋፈጥ ገና አልተዘጋጁም ነበር:: ምክንያቱም ስለ መንግሥቱ የነበራቸው አስተሳሰብ ወደ ብሔራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ያዘነበለ ነበር::

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እርሱ ከሄደ በኋላ እንዲያከናውኑት ላቀደው ሥራ የሚያዘጋጃቸውን የእምነት ትምህርት ሊያስተምራቸው መፈለጉ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ የታመሙትን በመፈወስና ወንጌሉን በመስበክ ፍሬያማ አገልግሎት አበርክተው መነሣታቸው ነበር:: ኢየሱስ 5,000 ሰዎችን የመገበበት ተአምርም ተካፋይ ነበሩ:: በአጠቃላይ «መንፈሳዊ የበላይነት» ተሰምቷቸው ነበር:: ይህም ራሱ አደገኛ ነገር ነበር:: ግድየለሽ ሆነህ ወደ ገደል የማትወድቅ ከሆነ ከተራራ ጫፍ ላይ መሆኑ መልካም ነው!

መንፈሳዊ በረከት ከሸክሞችና ጦርነቶች ጋር መመጣጠን አለበት:: አለዚያ ብስለትን አጥተን ሞልቃቃ ልጆች ልንሆን እንችላለን:: ቀደም ሲል ኢየሱስ ከአስደሳች የማስተማር አገልግሎት በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ማዕበሉ መርቷቸዋል (ማር. 4:35-41):: አሁን ደግሞ ከተአምራዊ አገልግሎት በኋላ፣ እንደገና ወደ ማዕበል መርቷቸዋል:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ 5,000 ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ካመጡ በኋላ የይፋዊ ስደት «ማዕበል» መነሣቱ አስገራሚ ነው (የሐዋ. 4:1-4):: ሐዋርያቱ ታስረው በነበሩበት ጊዜ 5,000 ሰዎች እንጀራ ከተመገቡ በኋላ የተከሰተውን ማዕበል አስታውሰው፣ ጌታ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንደሚረዳቸው ሳይገነዘቡ አልቀሩም::

እያንዳንዱ አዲስ ፈተና ተጨማሪ እምነትና ብርታት ይጠይቀናል። በዚያው የመጀመሪያው የማዕበል ገጠመኝ፣ ኢየሱስ በታንኳይቱ ውስጥ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር። በዚህ ጊዜ ግን በተራራ ላይ ሆኖ ስለ እነርሱ በመጸለይ ላይ ነበር። በእምነት እንዲኖሩ እያስተማራቸው ነበር። (ለነገሩ በታንኳይቱ ውስጥ አብሯቸው ሳለ እንኳ ፈርተው ነበር!) ትዕይንቱ ዛሬ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚገኝበትን ሁኔታ ያብራራል። እኛ በዚህ ማዕበልማ ዓለም ውስጥ ላለመስመጥ እየታገልን አለን። እርሱ በክብሩ ሆኖ እያማለደልን ነው። ጊዜያቱ ጨለማ በሚመስልበት ጊዜ እርሱ ይመጣልናል፣ እኛም ወደ ባሕሩ ዳርቻ እንደርሳለን።

ዓሣ አጥማጆች የሚገኙበትን የደቀ መዛሙርት ቡድን ያስደነገጠው ማዕበል ጌታ ኢየሱስን ወደ እነርሱ የሚያመጣ መሰላል ነበር። ራሳቸው ለማድረግ የሚወስዱትን እርምጃ አጥተው እስኪጠበቡ ድረስ ጠበቃቸው። ነገር ግን አልፎ ተጓዥ መስሎ የቀረበው ለምን ነበር? ምክንያቱም ደቀ መዛሙርቱ ለይተው እንዲያውቁት፣ እንዲተማመኑበትና ወደ መርከቡ እንዲጋብዙት ነበርና ነው። እነርሱ ግን ለይተው አላወቁትም። ነገር ግን መንፈስ መስሏቸው ፈሩና ጮኹ!

ኢየሱስም በቃሉ፣ «አይዞአችሁ፣ እኔ ነኝ አትፍሩ» (ማር. 6፡50) ሲል ማንነቱን አረጋገጠላቸው። በዚህ ነጥብ ላይ ጴጥሮስ ኢየሱስን በውኃ ላይ እንዲሄድ እንዲፈቅድለት ጠየቀው። ማርቆስ ግን ይህንን አልጻፈም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማርቆስ የጴጥሮስ ቃል አቀባይ ሆኖ መልእክቱን እንደ ጻፈና ጴጥሮስ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳያሳድር በማሰብ ይህንን ክስተት እንዳልጠቀሰው ይናገራል። ጴጥሮስ ለምን ሰመጠ? ብሎ መተቸቱ ቀላል ነው። ነገር ግን አንተ ራስህ የእርሱን ያህል ሞክረሃል?

ደቀ መዛሙርቱ መንፈሳዊ አጥልቆ የማየት ዓቅምና ተቀባይ ልብ በማጣታቸው ፈተናቸውን ወድቀዋል። የእንጀራውና የዓሣው ተአምር ዘላቂ መልእክት አልሰጣቸውም። ምክንያቱም ኢየሱስ ምግብን ለመግዛትና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ለመመገብ ከቻለ፣ ከማዕበሉ ሊታደጋቸው ይችል ነበር። የኢየሱስ

ክርስቶስ ደቀ መዝሙር እንኳ ከሕይወቱና ከአገልግሎቱ ሊማር የሚገባውን ትምህርቶች ካልተማረ፣ ከማመን ሊዘገይ ይችላል።

እነዚህን ሁለት ተአምራት ስትከልስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ችሮታንና ጥበቃን እንደሚሰጥ ትገነዘባለህ። «እግዚአብሔር እረኛ ዬ ነው። የሚያሳጣኝም የለም. . . ክፉውን አልፈራም» [መዝ. (23)፡1-4]። በእርሱ ከተማመንን፣ ሁኔታው የፈለገውን መልክ ቢይዝም እንኳ ሁልጊዜም ዋስትናና ብቃት ይኖረናል። ዋናው ነገር በእርሱ መታመናችን ነው።

ማርቆስ ፈውስን ፈልገው ወደ ኢየሱስ ስለመጡት ሰዎች በመግለጽ ይህንን ክፍል በአዎንታዊ መልኩ ፈጽሞታል። እነዚያ ሰዎች እምነት ነበራቸው። ጌታም ለእምነታቸው ሸልሞአቸዋል። ይህ በናዝሬት ከሕዝቡ እምነት ማጣት የተነሣ ብዙዎቹ ካልተፈወሱበት ሁኔታ ጋር የሚቃረን ነው።

«ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» (1ኛ ዮሐ. 5፡4)። በባሪያው ተማመን! እርሱም ከቶ አይተውህም።

# 6

# ባሪያ -- አስተማሪ

## ማርቆስ 7:1-8:26

በዚህ ወንጌል ውስጥ ማርቆስ ያተኮረው ኢየሱስ ባከናወነው ተግባር ላይ ነው:: በዚህ ክፍል ውስጥ ግን ማርቆስ ከጌታ ጠቃሚ ትምህርቶች አንዳንዶቹን ጽፎ እናገኛለን:: ማርቆስ በተጨማሪም ኢየሱስ በሕዝብ መካከል ስላከናወነው አገልግሎት ገልጿል:: ይህም ለሮማውያን አንባቢዎች ልዩ ፍላጎት ይቀሰቅስ ነበር:: በዚህ ክፍል ውስጥ ባሪያ - መምህር የሆነው ኢየሱስ ያበረከታቸውን ሦስት አገልግሎቶች እንመለከታለን::

## 1. አይሁዶችን ማስተማር (ማርቆስ 7:1-23)

በዚህ ተውኔት ውስጥ አራት ክፍሎች አሉ:: ከእነዚህም የመጀመሪያው በኢየሱስ ላይ የቀረበው *ክስ* ነው (ቊ. 1-5):: የዚህ ጊዜ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች በጌታና በአገልግሎቱ ላይ ያላቸውን ጥላቻ በግልጥ ማሳየት ጀምረዋል:: የሚከስሱበትን ነገር ለማግኘት ሲሉ ወደሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ይከተሉት ነበር:: በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የአይሁዶችን ሥርዓታዊ መተጣጠብ ባለመፈጸማቸው ነበር የከሰሷቸው:: እነዚህ የመተጣጠብ ሥርዓቶች ከግል ንጽሕና ጋር የሚያያዙ ወይም ሕጉ የደነገጋቸው አልነበሩም:: እነዚህ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሕዝቡ ሸክም ላይ የጨመሯቸው ነበሩ (ማቴ. 23:4)::

ጌታችን ሁልጊዜም የሰንበት ልማዶቻቸውን ይተላለፍ ነበር (ማር. 2:23-3:5):: ስለሆነም፣ ደቀ መዛሙርቱ የመተጣጠብ ሥርዓት ሳያካሂዱ በተመገቡበት ሰዓት ኢየሱስን ይከስሱት ጀመር:: እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች በእንዲህ ዓይነቱ አነስተኛ ጉዳይ የሚበሳጩት ለምን ይሆን? ሥርዓታዊ መተጣጠቦችን የመከላከል ግዴታ አለብን ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው? በአንድ በኩል፣ እነዚህ መሪዎች ጌታችን ሥልጣናቸውን በይፋ መቃወሙን አልወደዱትም ነበር:: ምክንያቱም እነዚህ ልማዶች ከአባቶች የመጡና የዘመናት ሥልጣን ያላቸው ነበሩ:: አይሁዶች

ልማዶችን «የሕጉ አጥር» ብለው ይጠሩ ነበር:: ልማዶችን የሚጠብቃቸው ሕጉ ሳይሆን፣ ሕጉን የሚጠብቁት ልማዶቹ ነበሩ!

ሌላም ከዚህ የበለጠ ነገር ነበር:: አይሁዶች እነዚህን የመተጣጠብ ሥርዓቶች በሚፈጽሙበት ጊዜ ሁሉ፣ እነርሱ «ልዩ»፣ ሌሎች ሰዎች ግን «ርኩስ» መሆናቸውን ያውጁ ነበር:: አንድ አይሁዳዊ ምግብ ሊገዛ ወደ ገበያ ቢወጣ በአሕዛብ ወይም (አያድርገውና!) በሰማርያዊ ሰው ተነክቶ ሊረክስ ይችል ነበር:: ይህ ልማድ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት አይሁዶች የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ መሆናቸው ከሌሎች መለየት እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነበር የተሰጣቸው:: ነገር ግን ይህ መልካም የማስገንዘቢያ ነጥብ ወደ ባዶ መረዳትነት ተለወጠ:: ኩራትንና ሃይማኖታዊ መነጠልንም አስከተለ::

እነዚህ የመተጣጠብ ሥርዓቶች በሰዎች ላይ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ከመስንዘራቸውም በላይ፣ ስለ ኃጢአትና የግል ቅድስና ባሕርይም የሚያስተላልፉት መልእክት የተዛባ ነው:: ኢየሱስ እውነተኛ ቅድስና ውስጣዊ ፍቅርና አመለካከት እንጂ ውጫዊ ተግባር እንዳልሆነ በተራራው ስብከት ላይ ገልጿል:: አክራሪ ፈሪሳውያን ሕጉን በመታዘዛቸውና የሚያረክሷቸውን ውጫዊ ነገሮች በማራቃቸው የተቀደሱ ይመስላቸው ነበር:: ኢየሱስ በውጫዊ ገጽታው ሕግን የሚጠብቅ ሰው በልቡ ሊተላለፍ እንደሚችልና ውጫዊ «ርኩሰት» ከውስጣዊ ማንነት ጋር ብዙም ግንኙነት እንደሌለው አስረድቷል::

ስለሆነም፣ ግጭቱ የተጧጧፈው በእግዚአብሔር እውነትና በሰው ልማድ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በሁለቱ የተለያዩ የኃጢአትና የቅድስና አመለካከቶች መካከል ጭምር ነበር:: ይኼ ተጋፍጦ በአጋጣሚ የተከሰተ ሳይሆን፣ ወደ እውነተኛ ሃይማኖታዊ እምነት እምብርት የዘለቀ ነበር:: ሰብአዊ ተፈጥሮ በነተቡ ሰው ሠራሽ ልማዶች ላይ በመንተራስ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል የመተላለፍ ወይም ችላ የማለት ዝንባሌ ስላለው፣ እያንዳንዱ ትውልድ በተመሳሳይ ግጭት ውስጥ ማለፉ የማይቀር ነው:: አንዳንድ ልማዶች የበለጸገ ውርሳችንን በማስታወስ ወይም ትውልዶችን እንደ «ሲሚንቶ» በማያያዝ

ቢያገለግሉም፣ ልማዶች የእውነትን ስፍራ እንዳይሻሙ መጠንቀቅ አለብን:: የቤተ ክርስቲያን ልማዶቻችንን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መመርመርና ለውጦችን ለማድረግ መበርታት ጠቃሚ ነው:: (በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:15 «ወግ» የሚለው ቃል ከሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተላለፈውን የአስተምህሯዊ እውነት አካል እንደሚመለከት ልብ በል:: በተጨማሪም፣2ኛ ጢሞቴዎስ 2:2ን አንብብ::)

ቀጣዩ ክፍል *ትንኔ* ሊባል ይችላል (ማር. 7:6-13):: ይህም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በመቆም የከሳሾቻቸውን ግብዝነት ባጋለጠበት ጊዜ የተከሰተ ነው:: *መጀመሪያ* ያደረገው ነገር ቢኖር ከትንቢተ ኢሳይያስ መጥቀሱ (29:13) እና ከዚያም የሙሴን ሕግ ማስከተል ነበር (ዘጸ. 20:12፤ 21:17፤ ዘሌዋ. 20:9):: ፈሪሳውያን ከሕግና ከነቢያት ጋር የተከራከሩት እንዴት ነበር?

ፈሪሳውያን ልማዳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የራሳቸውንና የእግዚአብሔርን ቃል ባሕርይ ሸራርፈዋል:: እነዚህ ሰዎች ከንቱ ሃይማኖታዊ አምልኮ የሚያካሄዱ ግብዞች (ተዋንያን) ነበሩ:: እውነተኛ አምልኮ ከልብ ሊመነጭ፣ በሰው የግል አሳቦች ሳይሆን በእግዚአብሔር እውነት ሊመራ ይገባል:: የሃይማኖት ሰዎች ሃይማኖታቸውን ሳያውቁት መከተላቸው አሳዛኝ ነገር ነው::

እነዚህ ሰዎች ከራሳቸው ባሕርይ በተጨማሪ እንጠብቀዋለን የሚሉትን የእግዚአብሔርን ቃል ባሕርይ ጭምር ነበር ያበላሹት:: እስኪ ይህንን አሳዛኝ ቅደም ተከተል ተመልከት:: የራሳቸውን አስተምህሮዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል በማስተማር (ማር. 7:7)፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመተው (ቍ. 8)፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመናቅ (ቍ. 9)፣ በመጨረሻም፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመሻር (ቍ. 13) በድለውታል:: ሰው - ሠራሽ ልማዶችን ከእግዚአብሔር ቃል የሚያስበልጡ ሰዎች የኋላ ኋላ በሕይወታቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ኃይል ያጣሉ:: ምንም ያህል የተሰጡ ቢመስሉም፣ ልባቸው ከእግዚአብሔር የራቀ ነው::

አይሁዶች ልማዶቻቸውንና ወጎቻቸውን ከእግዚአብሔር ቃል አልቀው ማየታቸውን ታሪክ ይመሰክራል:: የአይሁድ የሃይማኖት

መምህር (ራባይ) የሆኑት ኤልዔዘር፣ «ቅድሳት መጻሕፍትን ከልማዶች በተፈታ መንገድ የሚተረጉም ሰው በመጭው ዓለም ውስጥ ዕድል ፈንታ የለውም» ብለዋል፡፡ *በታልሙድ* ውስጥ የሚገኘው የአይሁዶች ልማዶች ስብስብ (ሚሽና) እንደሚለው፣ «የአይሁድ የሃይማኖት መምህራንን ድምፅ የሚቃረን አንዳች ነገር ማስተማር ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመቃረን የበለጠ አስከፊ ነገር ነው፡፡» ነገር ግን አይሁዳውያን ወዳጆቻችንን ከመተቸታችን በፊት «የቤተ ክርስቲያን አባቶች» በራሳችን አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚያሳድሯቸውን ተጽዕኖዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ እኛም የእግዚአብሔር እውነት በሰው ሠራሽ ልማዶች የመተካት ጥፋት ፈጽመን ሊሆን ይችላል?

ኢየሱስ ግብዝነታቸውን ካጋለጠ በኋላ፣ ወደ ሙሴ ሕግ በመመለስ አምስተኛውን ትእዛዝ እንደ ጣሱ ይከስሳቸዋል፡፡ ሕጉን እየጣሱ የበደለኛነት ስሜት እንዳይሰማቸው የማድረግ ብልሃት ነበራቸው፡፡ ፈሪሳውያን በሀብታቸው ወላጆቻቸውን እንደ መደገፍ፣ ንብረታቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ከሰጡ በኋላ («ቊርባን» ማለት «ምጽዋት፣ ስጦታ» ማለት ነው፡፡ ዘኍልቁ 30 አንብብ) «ለመንፈሳዊ ዓላማዎች» ብቻ እንደሚውል ይናገሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ሀብቱ የእግዚአብሔር ነው ቢሉም ለራሳቸው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንወደዋለን ቢሉም፣ ለወላጆቻቸው ፍቅር አልነበራቸውም፡፡

ሦስተኛው ክፍል *እወጃ* ነው (ማር. 7:14-16)፡፡ ኢየሱስ ለሁሉም ሕዝብ የቅድስና አኗኗር ምንጩ ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ሕይወት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ኢየሱስ ሙሴ ስለ «ንጹሕ» እና «ርኩስ» ምግቦች ያስተማረው ሁሉ ባዶና ከንቱ እንደሆነ እየገለጸ ነበረ፡፡ በዚያን ጊዜ ይህን ሥር ነቀል እውነት ለሕዝቡ በግልጽ ባያብራራም፣ ለደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው አብራርቶላቸዋል፡፡

ዳሩ ግን ጠላቶቹ ይህን አሳብ በግልጽ ተረድተው ነበር፡፡ አይሁዶችን ከአሕዛብ ከሚለዩት «ግድግዳዎች» አንደኛውን እየናደ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ሕግ ከጥቅም ላይ መዋሉን ቢቀጥልም (ኤፌ. 2:14-15፤ ቈላ. 2:14)፣ ኢየሱስ የተናገረው መርህ በዘመናት ሁሉ

እውነት ነበር። በሁሉም የታሪክ ወቅቶች፣ እውነተኛ ቅድስና የልብ፣ ማለትም በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የማድረግ ጉዳይ ነበር። ሥርዓታዊ መንጻት ይህንኑ እምነት የሚያመለክት ውጫዊ ታዛዥነት ብቻ ነበር [መዝ. (51):6፣ 10፣ 16-17]። ሙሴ እግዚአብሔር ለደንቦች የመታዘዝን ውጫዊ ክስተት ብቻ ሳይሆን፣ ከልብ የሚመነጭ ፍቅርና ታዛዥነት እንደሚፈልግ ገልጿል (ዘዳግ.6:4-5፤10:12፤30:6፣20 አንብብ)።

የጌታችን *ማብራሪያ* (ማቴ. 7:17-23)። ይህ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው በጠየቁት ጊዜ ለብቻቸው የሰጣቸው ትምህርት ነው። ማብራሪያው ለእኛ ግልጽ ቢመስልም፣ እነዚህ ደቀ መዛሙርት ምግቦችን ሁሉ «ንጹሕ» እና «ርኩስ» እያለ በሚከፋፍል የአይሁዶች ጥብቅ የምግብ ሥርዓት ውስጥ ማደጋቸውን መዘንጋት የለብንም (ዘሌዋ. 11)። እንዲያውም፣ ጴጥሮስ ይህን እውነት ከሰማ በኋላም እንኳ ቢሆን ለዓመታት የሚበሉ ንጹሕ የእንስሳት ዓይነት ዘር ጠብቆ ይዟል (የሐዋ. 10:14)። ለብዙ መቶ ዓመታት የተማሩትንና የተለማመዱትን ሃይማኖታዊ ልማድ መለወጡ ቀላል አይደለም።

የሰው ልብ በኃጢአት የተሞላ በመሆኑ ሁሉንም ዓይነት ክፉ አሳቦችን፣ ፍላጎቶችን፣ ተግባራትንና በአጠቃላይም ከግድያ እስከ ቅንዓት ያሉትን ነገሮች ያመለክታል። በዘመናችን ያሉ አንዳንድ ለዘብተኛ የሥነ መለኮት ምሁራንና የሰብአዊነት መምህራን ሰብአዊ ባሕርይን በተመለከተ እንዳላቸው ዓይነት ልዩ ስሜት ኢየሱስ አልነበረውም፤ እርሱ የሰውን ልጅ ባሕርይ ጥርት አድርጎ ያውቅ ነበር። ሰው ኃጢአተኛና የራሱን ባሕርይ ለመለወጥ ወይም ለመቆጣጠር የማይችል መሆኑን ያውቅ ነበር። *ወደ ምድር የመጣውም ለጠፉት ኃጢአተኞች ለመሞት ነበር።*

እግዚአብሔር ለአይሁዶች የአመጋገብን ሕግጋት የሰጠው የተመረጡት ሕዝቡ ንጹሕ የሆነውን ነገር ንጹሕ ካልሆነው ለይተው እንዲያውቁ ለማገዝ ነበር። (የጤንነት ንጽሕናን የሚመለከቱ አንዳንድ ተግባራዊ ጉዳዮችም ለዚህ ሕግ መሰጠት ጠቃሚ ድርሻ እንደነበራቸው አይጠረጠርም)። እነዚህን ሕግጋት መተላለፍ ሥርዓታዊ ርኩሰትን ያስከትል ነበር። ይህ ደግሞ ውጫዊ ጉዳይ ነበር። ምግብ ሆድ ውስጥ ይጠናቀቃል። ኃጢአት

ግን ከልብ ይጀምራል:: የምንበላው ምግብ ከሰውነታችን ጋር ከተዋሃደ በኋላ ቀሪው በእዳሪ መልክ ይወገዳል:: ኃጢአት ግን በልባችን ውስጥ ሠርጾ ርኵሰትንና ሞትን ያፈራል::

ይህ «በእውነትና ወግ» መካከል የቀረበው ታላቅ ትምህርት የአይሁድ የሃይማኖት መምህራንን የበለጠ በማበሳጨት ኢየሱስን ዝም ለማሰኘት እንዲነሣሡ አደረጋቸው:: በሕዝቡ ከተጨናነቀው ስፍራ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደ አሕዛብ ግዛት የሄደውም በዚሁ ተቃውሞ ምክንያት ነበር::

ይህን ክፍል ከመልቀቃችን በፊት፣ የእግዚአብሔርን እውነት ከሰዎች ወግ ወይም ልማድ ጋር ማነጻጸሩ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም::

| *የሰው ወጐች* | *የእግዚአብሔር እውነት* |
|---|---|
| ውጫዊ ቅርጾች– | ውስጣዊ እምነት– |
| እስራት | ነጻነት |
| የማይረቡ ሕግጋት | መሠረታዊ መርሖች |
| ውጫዊ ቅድስና | እውነተኛ ውስጣዊ ቅድስና |
| ቃሉን ችላ ማለትና በወጐች መተካት | የእግዚአብሔርን እውነት ከፍ ከፍ ያደርጋል |

## 2. አሕዛብን መርዳት (ማርቆስ 7:24-8:9)

ኢየሱስ በጢሮስና ሲዶና አካባቢ አሕዛብን በሚያገለግልበት ጊዜ ሦስት ተአምራት መሥራቱን ማርቆስ መዝግቧል:: ጌታችን ከፍልስጥኤም ሲመጣ የምንመለከትበት ክፍል ይኼ ብቻ ነው:: ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረውን ተግባራዊ እያደረገ ነበር:: ይኸውም ሁሉም አዳኝ የሚያስፈልጓቸው ኃጢአተኞች በመሆናቸው፣ በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌለ የሚያስረዳ ነበር::

*(1) አጋንንትን አወጣ* (7:24-30):: በወንጌላት ውስጥ ከተመዘገቡት ሠላሳ አምስት ተአምራት መካከል፣ ስድስቱ ሴቶችን ያካትታሉ:: እነዚህም፣ የጴጥሮስ አማት መፈወስ (1:30-

31)፣ የመበለቷ ከሞት መነሣት (ዮሐ. 11)፣ የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት መነሣትና ደም የሚፈስሳት ሴት መፈወስ (ማቴ. 9:18-26)፣ እንዲሁም እዚሁ በማርቆስ 7 ውስጥ እንደተመለከተው የአጋንንት መውጣት ናቸው::

ኢየሱስ ከቅፍርናሆም ስድሳ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ወደሚገኘው ወደዚሁ አካባቢ የመጣው ከሕዝቡ ፈቀቅ ብሎ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለማሳለፍ ነበር:: ነገር ግን የልጇ ሁኔታ ያሳሰባት እናት እርዳታውን ፈልጋ በእምነት ወደ እርሱ መጣች:: በመጀመሪያ ደረጃ ይህችን ሴት የብሔሯ ማንነት ያሳጣት ጀመር:: ኢየሱስ አይሁዳዊ ሲሆን፣ እርሷ አሕዛብ ነበረች:: ከዚህም በላይ የወንዶች አምባገነንነት በገዘፈበት ዘመን ውስጥ የምትኖር ሴት ነበረች:: ከአጋንንቶቹ አንዱ የልጇን ሕይወት በመቆጣጠሩ ምክንያት ሰይጣንም ተነሥቶባት ነበር:: ደቀ መዛሙርቱም አልፈለጓትም ነበር:: ኢየሱስ እንዲያሰናብታትና የዕረፍት ጊዜያቸውን ከማወክ እንዲቆጠብ ጠየቁ:: ለአፍታ ያህል፣ ራሱ ኢየሱስም የተቃወማት ይመስል ነበር! ሁኔታው ቀላል አልነበረም:: ነገር ግን ከታላቅ እምነቷ የተነሣ ልታሸንፍ ችላለች::

ለክርስቶስ ብዙ መከራ የተቀበሉ የስኮትላንድ አገልጋይ ሳሙኤል ሩዘርፎርድ አንድ ጊዜ ለጓደኛቸው፣ «ከእግዚአብሔር ሸካራ ጉሸማዎች ሁሉ ፍቅር የተሞላበትን በጐነት ፈልፍሎ ማውጣት የእምነት ተግባር ነው» ሲሉ ጽፈዋል:: ይህች የአሕዛብ ሴት ያደረገችውም ይህንኑ ነበር:: እኛም ዛሬ ከእርሷ ብዙ ልንማር እንችላለን::

መጀመሪያ እንዲረዳት በጠየቀችው ጊዜ ኢየሱስ መልስ እንኳ አልሰጣትም! ዝምታው የልብ ልብ የሰጣቸው ደቀ መዛሙርት እንዲያሰናብታት ወተወቱት:: ኢየሱስ መናገር ሲጀምር መልስ የሰጠው ለሴቲቱ ሳይሆን ለደቀ መዛሙርቱ ነበር:: ቃላቱም እርሷን ሙሉ በሙሉ የሚያገልሉ ይመስሉ ነበር:: «ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጐች በቀር አልተላክሁም አለ» (ማቴ. 15:24):: ይህ ሁሉ ግን ጸንታ ልመናዋን እንዳታቀርብ አልከለከላትም::

መጀመሪያ እንዲረዳት ስትለምን ኢየሱስን በአይሁዳዊ መጠሪያ «የዳዊት ልጅ» ብላ ነበር የጠራችው። ሁለተኛ ጊዜ ስትለምነው ግን ፣ «ጌታ ሆይ፣ እርዳኝ» አለችው (ማቴ. 15:25)። በዚህ ጊዜ ነበር ኢየሱስ መጀመሪያ ልጆችን (እስራኤላውያንን) መመገብ እንደሚያስፈልግና ምግባቸውን ለውሾች መወርወር እንደማይገባ የተናገረው። ኢየሱስ እንደ ብዙዎቹ ኩሩ አይሁዳውያን አሕዛብን «ቆሻሻ ጥንብ–አንሳ ውሾች» ማለቱ አልነበረም። ተስፋ እየሰጣት ነበር። እርሷም ከተስፋው ላይ ተንጠላጠለች።

ምላሿ የእምነትን ማሸነፍ ያሳያል። ሴቲቱ «ልጆች» (አይሁዶች) በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የነበራቸውን ስፍራ አልካደችም። የእነርሱንም ስፍራ ለመውሰድ አልፈለገችም። እርሷ የፈለገችው ከማዕዱ የሚወድቀውን ትንሽ የበረከት እንጥፍጣፊ ብቻ ነበር። ምክንያቱም «መዳን ለአይሁድ ነውና» (የሐዋ. 4:22)። እርሱ በተናገረው ቃል ላይ ተመሥርታ መለመኗ ደስ ሳያሰኘው አይቀርም። ስፍራዋን በመቀበልና ቃሉን በማመን ነበር በልመናዋ የጸናችው። ኢየሱስም ጥያቄዋን ከሟሟላት አልፎ ለጠንካራ እምነቷ አመስግኗታል።

በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ «ለታላቅ እምነታቸው» ያመሰገናቸው ሁለት ሰዎች አይሁዶች ሳይሆኑ አሕዛብ መሆናቸው አስገራሚ ነገር ነው። ይህን ምስጋና የተቀበሉት ይህች የሲሮፊኒሺያ (ከናናዊት) ሴትና ሮማዊው የመቶ አለቃ ነበሩ (ማቴ. 8:5-13)። በተጨማሪም፣ በሁለቱም ሁኔታዎች ኢየሱስ ፈውስን የሰጠው ወደ በሽተኞቹ ሳይቀርብ ነበር። ይህም በዚያን ጊዜ በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል የነበረውን መንፈሳዊ ርቀት ያመለክታል (ኤፌ. 2:11-22)። በመጨረሻም፣ የጢሮስና ሲዶና ሰዎች በእምነታቸው የማይታወቁ ሰዎች ሆነው ሳሉ (ማቴ. 11:21-22)፣ ይህች ሴት ኢየሱስ ልጇን እንደሚፈውስ አምናለች።

ታላቅ እምነት ማለት በቃሉ አማካኝነት እግዚአብሔርን በመለመን ጥያቄው እስኪሟላ ድረስ በመማጸን መቀጠል ማለት ነው። ታላቅ እምነት እጅግ አነስተኛ በሆነ ማበረታቻ ላይ

በመንተራስ ተፈጻሚነትን ወዳገኘ የተስፋ ቃልነት ይለውጠዋል:: «ጌታ ሆይ፣ እምነትን ጨምርልን::»

2. *የደንቆሮው መፈወስ* (7:31-37):: የዴካፖሊስ («አሥር ከተሞች») አካባቢም የአሕዛብ ክልል ነበር:: ነገር ግን ኢየሱስ ከአካባቢው ከመውጣቱ በፊት ሕዝቡ የእስራኤልን አምላክ እያከበረ ነበር (ማቴ. 15:30-31):: ወደ ኢየሱስ ያመጡት ሰውዬ ዲዳና ደንቆሮ ነበርና ኢየሱስ ፈወሰው:: ይህ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ የተመዘገበው ተአምር በተለይ የማርቆስ ተደራስያን ለነበሩት ሮማውያን የተለየ ትርጉም ይሰጥ ነበር:: ምክንያቱም የአሥር ከተማ አካባቢ «ከሮም ፈቀቅ ያለ ሮም» ነበር::

የፈውሱ ዜና እንዳይስፋፋና ሰዎች በተፈወሰው ሰውዬ ላይ ዓይናቸውን እንዳይጥሉ በማሰብ ኢየሱስ ከሕዝቡ ለይቶ ወሰደው:: ሰውዬው ደንቆሮ በመሆኑ ምክንያት የጌታችንን ንግግሮች ሊሰማ ባይችልም፣ ጌታችን በጆሮዎቹ ጣቶቹን ሲያስገባና እንትፍ ብሎ ምላሱን ሲዳስስ ይሰማው ነበር:: ጌታችን የቃተተው ኃጢአት ወደዚህ ዓለም ባመጣው ሥቃይና ኃዘን ምክንያት በሰውዬው ላይ ለደረሰው ችግር በመራራት ነበር:: በተጨማሪም፣ ይህ የአካል ጉዳት በደረሰበት ሰውዬ ፋንታ ለአብ ያቀረበው ጸሎት ነበር:: (ይኸው ቃል ከጸሎት ጋር በተያያዘ በሮሜ 8:23 እና 8:26 ውስጥ ተጠቅሷል::)

ኤፍታህ «ተከፈት፣ ተለቀቅ» የሚል ፍች ያለው የአረማይክ ቃል ነው:: ሰውየው የኢየሱስን ንግግር ባይሰማም፣ ፍጥረት የፈጠረውን ትእዛዝ በመስማቱ ግለሰቡ ሊፈወስ ችሏል:: ምላሱና ጆሮዎቹ እንደገና በትክክል መሥራት ጀመሩ:: ሕዝቡ ስለ ተአምራቱ ለማንም ትንፍሽ እንዳይሉ የተነገራቸውን ጥብቅ ትእዛዝ ጥሰው በየስፍራው ዜናውን በማሰራጨታቸው (ማር. 1:34፣ 44፤3:12፤5:43)፣ ሌሎች ብዙ ሰዎች የታመሙባቸውንና ለአካል ጉዳተኝነት የተዳረጉ ዘመዶቻቸውን እየያዙ ወደ ኢየሱስ ይጎርፉ ጀመር:: ኢየሱስ ትንሽ ለማረፍ ቢፈልግም ጊዜውን ሠውቶ ፈወሳቸው:: የዚህ አገልግሎት ውጤት ምን ነበር? እነዚህ አሕዛብ «የእስራኤልን አምላክ አከበሩ» (ማቴ. 15:31)::

*(3). የ 4,000 ሕዝብ መመገብ (8:1-9)::* ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይቃረናል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚጣደፉ ሰዎች ይህንን ተአምር በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ከተመዘገበው የ5,000 ሰዎች መመገብ ተአምር ጋር ያምታቱታል:: ይህንን ክስተት የመዘገቡት ማቴዎስና ማርቆስ ብቻ ሲሆኑ፣ ይህንን ተአምር 5,000 ሰዎች እንጀራና ዓሣ ከተመገቡበት ተአምር መለየቱ አስቸጋሪ አይደለም:: የመጀመሪያው ተአምር የተፈጸመው አይሁዶች በሚበዙባትና ከቤተሳይዳ አቅራቢያ በምትገኝ ገሊላ ውስጥ ነበር:: ይኼኛው ተአምር የተፈጸመው አሕዛብ በሚበዙባት ዴካፖሊስ (አሥር ከተማ) ነው:: የመጀመሪያው ተአምር የተሠራው በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሦች ሲሆን፣ ይኼኛው ተአምር የተሠራው በሰባት እንጀራ «በጥቂት ዓሦች» ነበር:: 5,000ዎቹ ከእርሱ ጋር የቆዩት ለአንድ ቀን ብቻ ሲሆን፣ 4,000ዎቹ ግን ለሦስት ቀናት አብረውት ነበሩ:: ከ5,000ዎቹ የተረፈው ምግብ አሥራ ሁለት ቅርጫት ሲሆን፣ ከ4,000 ዎቹ የተረፈው ሰባት ቅርጫት ብቻ ነበር:: የቅርጫቶቹም ዓይነት የተለያየ ነበር:: የ5,000ዎቹ ትርፍራፊ የተሰበሰበው በትናንሽ ቅርጫቶች ሲሆን፣ የ4,000ዎቹ ትርፍራፊ የተሰበሰበው ሰውን ሊይዙ በሚችሉ ትላልቅ ቅርጫቶች ነበር (የሐዋ. 9:25 አንብብ)::

አሁንም የጌታን ርኅራኄና ሁኔታዎችን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር መቻሉን በመመልከት እንበረታታለን:: ነገር ግን የደቀ መዛሙርቱ ዕውርነትና አለማመን ተስፋ ያስቆርጠናል:: የበፊቱን ተአምር ሙሉ በሙሉ ረስተው ነበር ማለት ነው? እስኪ ብዙም አንጫናቸው:: እኛስ ስንት ጊዜያት የጌታን ምሕረቶች ዘንግተናል? ዛሬም ኢየሱስ እንዳልተለወጠና ለችግሮች ሁሉ መፍትሔ እንዳለው ልንገነዘብ ይገባል:: ከእኛ የሚፈለገው በእርሱ መተማመን፣ ሁለንተናችንን ለእርሱ መስጠትና መታዘዝ ብቻ ነው::

## 4. ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ማርቆስ 8:10-26)

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የገሊላን ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ተሻግረው ከፈሪሳውያን ጋር ተገናኙ:: ፈሪሳውያኑ ኢየሱስ ቀደም ሲል ከሰነዘረባቸው ክስ ገና አላገገሙም ነበር (7:1-23):: በዚህም ጊዜ ከሰማይ ምልክትን እንዲያሳያቸው በመጠየቅ ፈተኑት:: የበሽተኞችን መፈወስ የመሳሰሉትን ምድራዊ ተአምራት ንቀው ነበር:: ከሰማይ እሳት ወይም መና እንደማውረድ ያለ ታላቅ ምልክት ነበር የፈለጉት (ዮሐ. 6:30-31):: ይህም በርግጥ ከእግዚአብሔር ለመላኩ ማረጋገጫ ይሆናል ብለው አሰቡ::

ጌታችን በዚህ ጥያቄ አዘነ (ማር. 7:34 አንብብ):: የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ሃይማኖታዊ መሪዎች ልበ-ደንዳናና መንፈሳዊ ዕውራን እስኪሆኑ ድረስ የሚሳሳቱት እንዴት ነው! ከሰማይ ምልክትን መጠየቃቸው ያለማመናቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ነበር:: ምክንያቱም እምነት ምልክትን አይጠይቅምና:: እውነተኛ እምነት የእግዚአብሔርን ቃል ይቀበላል፤ በመንፈስ ቅዱስም ውስጣዊ ምስክርነት ይረካል::

ማርቆስ የሚጽፈው በቀዳሚነት ለአሕዛብ ተደራስያን በመሆኑ፣ ጌታችን ስለ ነቢዩ ዮናስ ምልክት የሰጠውን ምላሽ አላካተተም (ማቴ. 16:4፤ ማቴ. 12:38-41ን አንብብ):: «የዮናስ ምልክት» ምን ነበር? ሞት፣ መቀበርና ትንሣኤ:: ኢየሱስ የተናገረውን ሆኖ መገኘቱ የተረጋገጠው በራሱ ሞት፣ መቀበርና ትንሣኤ ነበር (የሐዋ. 2:22-36፤ 3:12-26)::

ኢየሱስ ከሕዝቡ ተለይቶ ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅ ወዳለው አካባቢ ሄደ:: በጕዞውም ወቅት ለደቀ መዛሙርቱ ጠቃሚ መንፈሳዊ ትምህርት አስተምሯል:: ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሳይይዙ በመምጣታቸው እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ነበር:: ምግቡን ይዞ ባለመምጣቱ ጥፋት የፈጸመው ማን ይሆን?

በጥንቃቄ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርቱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዘገምተኞች ሆነው መገኘታቸው ኢየሱስን ሳያሳዝነው አይቀርም:: በሁለት አጋጣሚዎች እንጀራን ከ10,000

የሚበልጡ ሰዎችን መመገቡ ወደ ልባቸው የዘለቀ አይመስልም! ኢየሱስ በጀልባይቱ ውስጥ አብሯቸው እያለ ስለሚበሉት እንጀራ መከራከር ለምን አስፈለጋቸው? ምክንያቱም አእምሯቸው የደነዘዘ ሲሆን፣ ልባቸውም ደንድኖ ነበር (ማር. 6:52 አንብብ):: ዓይኖቻቸው ከመታወራቸውም በላይ፣ ጆሮዎቻቸውም ደንቁረው ነበር (4:11-12 አንብብ)::

ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተቀበሏቸውን በረከቶች የመርሳት ዝንባሌ ይታይባቸዋል [መዝ. (103):1-2]:: እርሱ ፍላጐቶቻችንን እያሟላ ሳለ አንድ ችግር ሲገጥመን እናጉረመርማለን ወይም እንፈራለን:: ከእርሱ ጋር እስካለን ድረስ የሚያስፈልገንን እንደሚያሟላልን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን:: ስለሆነም፣ ለአፍታ ቆም ብለን ለእኛ ያሳያቸውን በጐነቶችና ታማኝነቶች ልናስታውስ ይገባል::

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር የፈለገው ስለ እርሾ እንጂ ስለ እንጀራ አልነበረም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እርሾ የክፉ ነገር ምልክት ሆኖ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል:: የፋሲካ በዓል በመጣ ቁጥር አይሁዶች እርሾን ከቤታቸው ማስወገድ ነበረባቸው (ዘጸ. 12:18-20):: ለመሥዋዕትነት በሚቀርብ ምግብ ውስጥ እርሾ መጨመር አይቻልም ነበር (ዘጸ. 23:18፤ 34:25፤ ዘሌዋ. 2:11 እና 6:17):: ክፋት እንደ እርሾ ሁሉ አነስተኛና ድብቅ ሲሆን፣ በፍጥነት የመስፋፋትና ሁሉንም ነገር የማበላሸት ብቃት አለው (ገላ. 5:9)::

እርሾ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሐሰተኛ ትምህርት (ገላ. 5:1-9)፣ በቤተ ክርስቲያን ብይን ያልተሰጠው ኃጢአት (1ኛ ቆሮ. 5)፣ እንዲሁም የግብዝነት መግለጫ ሆኖ አገልግሏል (ሉቃስ 12:1):: በዚህ ዓውድ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያስጠነቀቀው ከፈሪሳውያን ሐሰተኛ ትምህርትና ከሄሮድስ ተከታዮች እንዲጠበቁ ነበር:: በሌላ አገላለጽ፣ ግብዝነትን ይለማመዱና ያስፋፉ ነበር (ማር. 7:6ን ተመልከት):: የሄሮድስ ተከታዮች ሄሮድስን የሚደግፉ፣ የሮማውያንን አኗኗር የተቀበሉ፣ ሄሮድስና አገዛዙ ለአይሁዶች ተስፋ የተገባውን መንግሥት እንደሚመሠርቱ የሚያስቡ ሰዎች ነበሩ:: ይህ ሐሰተኛ ትምህርት በደቀ መዛሙርቱ ልብና አእምሮ ውስጥ ከሠረፀ በሕይወታቸው

ውስጥ ተጽዕኖ በማሳደር፣ ኢየሱስ ስለ ራሱና ስለ መንግሥቱ እንዲያስፋፉ የሰጣቸውን እውነት ይበርዝ ነበር::

ሐሰተኛ ትምህርትን ለመለየትና ለማስወገድ የምናደርገው ጥንቃቄ ምንጊዜም በቂ ሊሆን አይችልም:: አንድ ግለሰብ ወይም ቤተ ክርስቲያን ትንሽ ዝንፍ ያሉ እንደሆነ ብዙም ሳይቆይ ሁሉም ነገር ሊበላሽ ይችላል:: ጌታችን ብዙውን ጊዜ የማስጠንቀቂያ ቃል ባይሰነዝርም፣ ይህንኑ የሚያደርገው ጉዳዩ በጣም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው::

በዚህ ክፍል ማርቆስ በሌሎች ወንጌላት ውስጥ የማይገኙትን ሁለት ነገሮች ጠቅሷል:: እነዚህም የደንቆሮው (7:31-37) እና ከቤተ ሳይዳ ውጭ የነበረው የዓይነ ስውሩ መፈወስ ናቸው (8:22-26):: የእነዚህ ሁለት ሰዎች ታሪክ በ8:18 የተገለጠውን የደቀ መዛሙርቱን መንፈሳዊ ሁኔታ የሚያብራራ ይመስላል:: አይሁዳውያን አንባቢዎች እነዚህን ሁለት ተአምራት በኢሳይያስ 35 ውስጥ ከተገለጹት የመሢሑ የተስፋ ቃሎች ጋር ያዛምዳሉ::

በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ሰዎቹን ወደ ኢየሱስ ያመጡት ወዳጆቻቸው ነበሩ:: በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ኢየሱስ ሰዎቹን ከሕዝቡ ለይቶ አስወጥቷቸዋል:: እንዲያውም ሁለተኛውን ግለሰብ ከከተማዪቱ ውጭ ይዞት ወጥቷል:: ለምን? ይህንን ያደረገው ምናልባትም የቤተሳይዳ ከተማ ቀደም ሲል ባለማመኗ ምክንያት ፍርድ ስለተበየነባት ይሆናል (ማቴ. 11:21-24):: ለቤተ ሳይዳ ነዋሪዎች የሚሰጥ ተጨማሪ መረጃ አልነበረም::

ስለዚህ ተአምር ለየት ያለው ነገር ወዲያውኑ ሳይሆን ቀስ በቀስ መከሰቱ ነው:: በወንጌላት ውስጥ ቢያንስ ሰባት ዓይነ ስውራን ተፈውሰዋል:: ጌታም ሰዎቹን የፈወሰው በተለያዩ መንገዶች ነው:: ፈውሱ ቅጽበታዊ እንዳይሆን ያገደው የቤተሳይዳ እምነተ-ቢስነት መንፈስ (ማር. 6:5-6 አንብብ) ወይም የግለሰቡ መንፈሳዊ ሁኔታ ሊሆን ይችላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተገለጸ ምክንያት ሳቢያ ግለሰቡ ለቅጽበታዊ ፈውስ ባለመዘጋጀቱ፣ ኢየሱስ ቀስ በቀስ ዓይኖቹን አብርቶለታል:: ሰውዬው ሰዎችንና ዛፎችን ለይቶ ማወቁ ዕውር ሆኖ

እንዳልተወለደና ነገር ግን በበሽታ ወይም በአደጋ ብርሃኑን እንዳጣ ያስረዳል::

ኢየሱስ ሰውዬውን ወደ ቤቱ በሚያሰናብትበት ጊዜ ወደዚያች ከተማ እንዳይገባ ማስጠንቀቁ፣ ግለሰቡ የቤተሳይዳ ሰው አለመሆኑን ያሳያል:: በኢየሱስ ካመነ በኋላ ክርስቶስን ለመቀበል ወዳልፈለጉት የቤተሳይዳ ሰዎች መሄድ ለምን አስፈለገ? ከእንግዲህ ወዲህ ሥራው ወደ አገሩ በመሄድ የክርስቶስን መንግሥት የምሥራች ቃል ማስፋፋትና የተደረገለትን ለሌሎች በማሳየት የዚህን መንግሥት ኃይል ማንጸባረቅ ነበር (2:11፤ 5:34፤10:52 አንብብ):: ለቤተሳይዳ ሰዎች ተጨማሪ ዕድል መስጠት አይገባውም ነበርን? ኢየሱስ ዓይኖቹን እንዴት እንደ ፈወሰ ቢሰሙ ያምኑ ይሆን? የቤተሳይዳ ሰዎች ብዙ ዕድሎች ቢሰጧቸውም ሊጠቀሙ አልቻሉም:: ለማንኛውም ሰው ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል ላለመስማት ልቡን ማደንደኑ አደገኛ ነገር ነው::

ደቀ መዛሙርቱ በዚህ የጉዞ ወቅት ጠቃሚ ትምህርቶችን ገብይተዋል:: እነዚህም ለወደፊት የአገልግሎት ጊዜዎቻቸው የሚያስፈልጓቸው ትምህርቶች ነበሩ:: ዛሬ እኛም እነዚህኑ እውነቶች መማር ይኖርብናል:: (1) ሌሎችን ምልክቶች ሳትፈልግ በቃሉ ኑር:: (2) ኢየሱስ የሚያስፈልግህን እንደሚያሟላልህ ተማመን:: (3) የሐሰተኛ ትምህርትን እርሾ አስወግድ:: (4) ኢየሱስ እንደ ፈቃዱ በተለያዩ መንገዶች እንዲሠራ ፍቀድለት::

ማርቆስ በእግዚአብሔር ባሪያ አገልግሎት ውስጥ የታዩትን አንዳንድ ክስተቶች መዝግቧል:: ከዚህ በኋላ ደግሞ ከመጋረጃው በስተጀርባ ወደሚከናወኑ ድርጊቶች ይወስደናል:: በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ባሪያ ደቀ መዛሙርቱን ሲያስተምርና ለመስቀል ላይ ሞቱ ሲያዘጋጃቸው እንመለከታለን::

# 7

# የባሪያው ምሥጢራት

## ማርቆስ 8:27-9:50

ምሥጢር «በአንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ብቻ የምትናገረው ነገር ነው» ይባላል:: ኢየሱስ በተለያዩ ጊዜያት ልዩ «ምሥጢራትን» ለደቀ መዛሙርቱ አካፍሏል:: በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ሦስት ምሥጢራት ቀርበዋል:: ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ሕይወት ለመኖር ከፈለጉ እነዚህን መንፈሳዊ ምሥጢራት ተረድተው ከሕይወታቸው ጋር ማዛመድ ይኖርባቸዋል::

## 1. መከራን መቀበል ወደ ክብር ይመራል (ማር. 8:27-9:13)

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለዚህ ግላዊ ስብሰባ ሲያዘጋጃቸው ቆይቷል:: ይህም በኢየሩሳሌም ምን እንደሚገጥመው የሚናገርበት ጊዜ ነበር:: ቀደም ሲል ጫፍ ጫፉን የነገራቸው ሲሆን፣ አሁን ሙሉ በሙሉ በግልጽ ሊነግራቸው ፈልጓል:: ለስብሰባው ማካሄጃ ከቤተሳይዳ በስተ ሰሜን አርባ ኪሎ ሜትሮች ርቃ የምትገኘውን የቂሣሪያ ፊልጵስዩስ ከተማን ነበር የመረጠው:: ይህች ከተማ ከውቧ የሄርሞን ከተማ ሥር ትገኝ ነበር:: ከተማዩቱ ስያሜዋን ያገኘችው ከአውግስጦስ ቄሣርና ሄሮድስ ፊልጶስ ሲሆን፣ በውስጧ ለአውግስጦስ መታሰቢያነት የተበረከተ የእምነበረድ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ ነበር:: ይህ ለሮም ክብር የተበረከተ ስፍራ ነበር:: አሁን ያ ክብር በስፍራው የለም:: የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ግን ለዘላለም ይኖራል::

ሀ) *ምስክርነት* (8:27-30):: ወደ ጓደኞችህ በመሄድ፣ «ሰዎች ስለ እኔ ምን ይላሉ?» እያልህ ብትጠይቅ በትዕቢት የተወጠርህ መስሎ ሊሰማቸው ይችላል:: ሰዎች ስለ እኛ የሚያስቡት ወይም የሚናገሩት ነገር ምን ለውጥ ያመጣል? ነገር ግን ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትና የሚያስቡት ነገር በጣም አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅና የኃጢአተኞች አዳኝ ነውና::

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለህ ምስክርነት የሕይወት ወይም የሞት ጉዳይ ነው (ዮሐ. 8:21፣24፤ 1ኛ ዮሐ. 2:22-27፤ 4:1-3)። የቂሣሪያ ዜጎች « ፈጣሪ ጌታ ነው!» ይሉ ነበር። ይህ ምስክርነት ታማኝ የሮም ዜጎች መሆናቸውን ቢያረጋግጥም፣ ከኃጢአታቸውና ከዘላለማዊ ሞት ሊታደጋቸው አይችልም ነበር። ሊያድነን የሚችለው «ኢየሱስ ጌታ ነው!» የሚለው ምስክርነት ብቻ ነው! (1ኛ ቆሮ. 12:1-3)። ይህም ምስክርነት ከልብ በመነጨ እምነት ሊታጀብ ይገባል (ሮሜ 10:9-10)።

ሰዎች ስለ ኢየሱስ የተለያዩ አስተሳሰቦችን መያዛቸው አስገራሚ ነገር ነው። ዛሬም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል። አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ ነው ማለታቸው ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። ምክንያቱም ዮሐንስና ኢየሱስ በየአደባባዩ አብረው ይታዩ ነበር። አገልግሎታቸውም ሆነ ባሕርያቸው የተለያየ ነበር (ማቴ. 11:16-19)፣ ኢየሱስን ከዮሐንስ ለመለየት መቸገራቸው እንግዳ ነገር ይመስላል።

መጥምቁ ዮሐንስ «በኤልያስ መንፈስና ኃይል መጥቶ» (ሉቃስ 1:17) የፍርድ አገልግሎትን ነበር የሰጠው። ኢየሱስ ግን በትሕትናና በአገልጋይነት መንፈስ መጣ። ዮሐንስ ምንም ተአምር አልሠራም (ዮሐ. 10:41)። ኢየሱስ ግን ተአምራት ሠሪ ነበር። የዮሐንስ አለባበስ የነቢዩ ኤልያስን ይመስል ነበር (2ኛ ነገ. 1:8፤ ማር. 1:6)። ሕዝቡ ኢየሱስን ከዮሐንስ ለመለየት እንዴት ተቸገሩ?

አንዳንዶች ኢየሱስ ከነቢያት አንዱ፣ በተለይም ኤርምያስ ሳይሆን እንደማይቀር ገመቱ (ማቴ. 16:14)። ኤርምያስ «አልቃሻው ነቢይ» ሲሆን፣ ኢየሱስ የኃዘን ሰው ነበር። ይህም በሁለቱ መካከል ሁነኛ ተመሳሳይነት እንደነበረ ያሳያል። ኤርምያስ እንደ ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ እውነተኛ ንስሐ ይጠራ ነበር። በተጨማሪም፣ ኤርምያስና ኢየሱስ ከሕዝባቸው ተቀባይነት ያጡና ሰዎች ያልተረዷቸው፣ ሐሰተኛ የሃይማኖት መሪዎችንና የግብዝነት አምልኮ የኮነኑ፣ እንዲሁም ከባለሥልጣናት ስደት የደረሰባቸው በመሆናቸው ይመሳሰላሉ።

ኢየሱስ በሥራውና በቃላቱ ሁሉ እርሱ መሢሑና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጡ መረጃዎችን አሳይቷል:: ይህም ሆኖ፣ ሕዝቡ ማንነቱን ሊረዱ አልቻሉም:: ሕዝቡ በትጋት እውነትን መሻት ሲገባቸው፣ ሁሉም የሚለውን ተወዳጅ አስተሳሰብ ለመከተል መረጡ:: ይህም ዛሬ ብዙ ሰዎች የሚፈጽሙት ስሕተት ነው:: ወደ ጥፋት የመራቸውም ከእምነት ይልቅ አስተሳሰቦችን መከተላቸው ነበር:: ሄልበርት ሁባርድ የተባሉ የሕዝብ አስተያየትን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል:- «የመለየት ስጦታ ያላቸው ጥቂቶቹ ፍርድን መስጠት በሚሳናቸው ብዙኃን ተቃውሞ ሲሰነዘርባቸው ይስተዋላል::» ይሁን እንጂ ጥቂቶች ቢሆኑም የመለየት ስጦታ ያላቸውን ሰዎች የሰጠን ጌታ ምስጋና ይግባው!

የጴጥሮስ ምስክርነት ድፍረት የተሞላበትና የማያወላውል ነበር:: የእኛም ምስክርነት እንዲሁ የጠነከረ ሊሆን ይገባል:: «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» (ማቴ. 16:16):: ክርስቶስ የሚለው ስም፣ «የተቀባ፣ ተስፋ የተገባው መሢሕ» የሚል ፍች ይሰጣል:: ነቢያት፣ ካህናትና ነገሥታት አገልግሎታቸውን በሚጀምሩበት ጊዜ ይቀቡ ነበር:: ጌታችንም እነዚህን ሁሉ ሥልጣናት ይዞ ነበር::

ኢየሱስ ስለ እርሱ እንዳይናገሩ ያስጠነቀቃቸው ለምን ነበር? በአንድ በኩል፣ ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸው ስለ እርሱና እርሱን ስለ መከተል ገና ብዙ መማር ያስፈልጋቸው ነበር:: የሃይማኖት መሪዎቹ ስለ ክርስቶስ ግትር አቋም ስለ ወሰዱ፣ መሢሕነቱን ማወጁ የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ከማጓተት የተሻለ ሚና አይኖረውም ነበር:: ተራ ሰዎች፣ የሚሠራቸውን ተአምራት ለመመልከት ቢፈልጉም፣ ለመልእክቱ ለመገዛት ግን አይፈልጉም:: መሢሕነቱን ማወጁ ፖለቲካዊ ዓመፅ በመቀስቀስ ብዙ ጉዳት ሊያስከትል ይችል ነበር::

ለ) *ግራ መጋባት* (8:31-38):: ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ጊዜ በክርስቶስ ማመናቸውን ስለ መሰከሩ (ነገር ግን ዮሐንስ 6:66-71 አንብብ)፣ ኢየሱስ ለሚያካፍላቸው «ምሥጢር» ዝግጁዎች ነበሩ:: ይኸውም በመስቀል ላይ ይሞት ዘንድ ከእነርሱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ነበር:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፣ ማርቆስ ወደ

ኢየሩሳሌም ስለሚያደርጉት ጉዞ በሰፊው ይተርካል:: በዋነኛነት የሚያተኩረውም እየቀረበ ስላለው የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ነበር (9:30-32፤ 10:32-34)::

ይህ እወጃ ወይም ማስታወቂያ ደቀ መዛሙርቱን አስደነገጣቸው:: እነርሱ እንደ መሰከሩት እርሱ በእርግጥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መሢሕ ከሆነ፣ የሃይማኖት መሪዎች ለምን አልተቀበሉትም? ለምንስ ይሰቅሉታል፣ መሢሑ ጠላቶቹን ሁሉ አሸንፎ ለእስራኤል የከበረ መንግሥት እንደሚመሠርት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አልተነበዩም ነበርን? የሆነ ቦታ የሆነ ነገር በመበላሸቱ ደቀ መዛሙርቱ ግራ ተጋብተው ነበር::

እውነተኛ ስሜቱን ከመግለጽ የማይቆጠበው ጴጥሮስ ነበር ያሳሰባቸውን ጉዳይ ይፋ ያወጣው:: ከአንድ ደቂቃ በፊት በእግዚአብሔር ተመርቶ በኢየሱስ ማመኑን የመሰከረው ጴጥሮስ (ማቴ. 16:17)፣ በቀጣዩ ደቂቃ እንደማያምን ሰው የሰይጣንን አሳብ ያንጸባርቅ ጀመር! ይህም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በምንሟገትበት ጊዜ ለሰይጣን ውሸት በር እንደምንከፍት ያሳያል:: ጴጥሮስ ጌታውን መገሠጽ ጀመረ:: ማርቆስ ጌታችን አጋንንትን ለመገሠጽ ይህንኑ የጴጥሮስን የተግሣጽ ቃል እንደ ተጠቀመ ጠቅሷል (ማር. 1:25፤ 3:12)::

የጴጥሮስ ተቃውሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካለማወቁና ለጌታው ከነበረው ጥልቅ ፍቅር የመነጨ ነበር:: ከአንድ ደቂቃ በፊት «ዓለት» የነበረው ጴጥሮስ ወዲያው ደግሞ የማሰናከያ ድንጋይ ሆነ:: ዶክተር ካምፕቤል ሞርጋን እንዳሉት፣ «ኢየሱስን የሚወድና ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን የአሠራር መንገድ የሚቃወም ሰው ለእግዚአብሔር የማሰናከያ ድንጋይ ነው::» ጴጥሮስ በመከራና በክብር መካከል ያለውን ግንኙነት ገና አልተረዳም ነበር:: የኋላ ኋላ ግን ይህንኑ ትምህርት ይማርና በመልእክቱ ውስጥ ያተኩርበት ነበረ (1ኛ ጴጥ. 1:6-8፤ 4:13-5:10 አንብብ)::

ጌታችን ጴጥሮስን በገሠጸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱንም እንደገረመማቸው መገንዘቡ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም በጴጥሮስ አሳብ ተስማምተው ነበር:: በአይሁዶች ልማዳዊ አተረጓጐም

በመጠመዳቸው ምክንያት መሢሐቸው መከራ የሚቀበልበትንና የሚሞትበትን ሁኔታ ለመረዳት አልቻሉም ነበር:: አንዳንድ ነቢያት መሢሑ መከራ እንደሚቀበል የተነበዩ ሲሆን፣ ስለ ክብሩ የጻፉት ግን ብዙዎች ነበሩ:: አንዳንድ የአይሁድ መምህራን መከራ የሚቀበለውና የሚነግሠው መሢሕ የተለያዩ ናቸው ብለው ያስቡ ነበር (1ኛ ጴጥ. 1:10-12 አንብብ):: የደቀ መዛሙርቱ ግራ መጋባት አለምክንያት አልነበረም ለካ::

ችግሩ ግን ሥነ መለኮታዊ ብቻ ሳይሆን፣ ተግባራዊም ጭምር ነበር:: ኢየሱስ እነዚህን ደቀ መዛሙርት ስለ ጠራቸው በእርሱ ላይ የሚደርሰው ሁሉ በእነርሱም ላይ ይደርስ ነበር:: እርሱ የመስቀሉን ሕይወት የሚጋፈጥ ከሆነ፣ ለእነርሱም እንዲህ ያለ ዕጣ ሊገጥማቸው ይችላል:: ይህ ብቻ ከእርሱ ጋር ላለመስማማት በቂ ምክንያት ነበር:: ለእርሱ ራሳቸውን አሳልፈው ቢሰጡም እንኳ ደቀ መዛሙርቱ በመስቀሉና በአክሊሉ መካከል ያለውን ግንኙነት አያውቁም ነበር:: መከራ ወደ ክብር እንደሚለወጥ ከሚያሳየው የእግዚአብሔር አሳብ ይልቅ ያለ መከራ ወደ ክብር እንደሚደርስ የሚያስረዳውን የሰይጣን ፍልስፍና እየተከተሉ ነበር:: ከእነዚህ አሳቦች መካከል ከልብህ የምትቀበለው የምትኖርበትንና የምታገለግልበትን መንገድ ይወስነዋል::

ማርቆስ 8:34 እንደሚያሳየው፣ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ቢነጋገሩም ከሕዝቡ አልራቁም ነበር:: ኢየሱስ ለሕዝቡ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረውን አሳብ አስተማረ:: ይኸውም *እውነተኛ ደቀ መዝሙር ለመሆን የሚፈልግ ሰው ዋጋ መክፈል እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነበር::* አብዛኛው ሕዝብ የሚከተለው ተአምራትን ለመመልከት እንደሆነና የደቀ መዝሙርነትን ዋጋ ለመክፈል እንደማይፈልጉ ያውቅ ነበር::

ኢየሱስ ለእውነተኛ ደቀ መዝሙርነት ሦስት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጧል:: (1) ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን መስጠት አለብን:: (2) በመከራውና በሞቱ ልንተባበረው ይገባል:: (3) ወደሚመራን ስፍራ ሁሉ በታዛዥነት ልንከተለው ይገባል:: ለራሳችን የምንኖር ከሆነ ራሳችንን እናጣዋለን:: ነገር

ግን ለእርሱና ለወንጌሉ ብለን ራሳችንን ብናጣ ራሳችንን እናገኛለን።

ራሳችንን የምንክደው ራሳችንን ለክርስቶስ አሳልፈን ሰንሰጥና ፈቃዱን ለመታዘዝ ስንቆርጥ ነው። ይህ ለአንዴና ለዘለዓለም የምናደርገው ራስን የመካድ ውሳኔ በየዕለቱ መስቀሉን ተሸክመን እርሱን እንድንከተል ያነሣሣል። ይህ ከሰብአዊ እይታ አንጻር ራስን ማጣት ቢሆንም፣ ከመለኮታዊ እይታ አንጻር ራስን ማግኘት ነው። ለክርስቶስ በምንኖርበት ጊዜ የበለጠ እራሱን እየመሰልን እንሄዳለን። ይህም ልዩ ግለሰባዊ ማንነታችንን ፍንትው አድርጐ ያወጣዋል።

ነገር ግን እውነተኛ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት እንድንኖር የሚያነሣሣን የክርስቶስና የወንጌሉ ጉዳይ ነው (ቍ. 35)። ራስን ማጣት ራስን የመስጠት እንጂ ተስፋ የመቁረጥ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን ታሪኩ ራስን በመስጠት ብቻ አያበቃም። ግላዊ ራስን የመስጠት ውሳኔ ወደ ተግባራዊ እርምጃ ሊመራን ይገባል። ይህም ወንጌሉን ለጠፋው ዓለም የማካፈል ኃላፊነት ነው። «ለእኔ» የሚለው ወደ ራስ ወዳድ ሃይማኖታዊ ገለልተኝነት ሊወስድ ስለሚችል፣ «እና ለወንጌሉ» በሚለው አሳብ ሚዛኑን መጠበቅ አለበት። ምክንያቱም የምንኖረው ለእርሱና ለሌሎችም ነውና።

ደቀ መዝሙርነት የትርፍና የኪሳራ ጉዳይ ነው። ይህም ሕይወታችንን የማባከን ወይም በሌሎች ሕይወት የማትረፍ ጥያቄ ነው። እዚህ ላይ ኢየሱስ የሰጠውን ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ አጢን። ሕይወታችንን በአንድ ጉዳይ ላይ ካዋልን በኋላ መልሰን የራሳችን ልናደርገው አንችልም። የሚያስተምረው ቀደም ሲል የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው የመሰከሩለትን ደቀ መዛሙርት መሆኑን አስተውል። የሚነግራቸው እንዴት ደኅንነትን አግኝተው ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄዱ ሳይሆን፣ እንዴት ሕይወታቸውን እንደሚያድኑና በምድር ላይ ቆይታቸው ዕድሎቻቸውን በሚገባ መጠቀም እንዳለባቸው ነው። «ነፍስ ማጣት» ሕይወትን ከማባከን፣ እግዚአብሔር ሕይወትህ ትርጉም ይኖረው ዘንድ የሚሰጥህን ታላላቅ ዕድሎች ካለመጠቀም ጋር ተመጣጣኝ ነው። «ዓለሙን ሁሉ አትርፈህ»

በሰዎች ፊት ስኬታማ ልትሆንና በእግዚአብሔር ፊት በምትቆይበት ጊዜ ግን ባዶ ልትሆን ትችላለህ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ከተከሰተ፣ ዓለሙን ሁሉ መግዛትህ ለእግዚአብሔር ታላቅ ቁም ነገር ሆኖ በሕይወትህ ሌላ ዕድል እንድትገዛ አያስችልህም።

እውነተኛ ደቀ መዝሙር የሆነ ሰው የሚያገኘው ሽልማት አለን? አዎን፣ አለ። ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰለ በመሄድ አንድ ቀን የክብሩ ተካፋይ ይሆናል። ሰይጣን ክብርን እንደሚሰጥህ የተስፋ ቃል ቢገባልህም፣ የኋላ ኋላ መከራን ታጭዳለህ። እግዚአብሔር መከራን እንደምትቀበል ቢናገርም፣ የኋላ ኋላ መከራህ ወደ ክብር ይለወጣል። ክርስቶስን አምነን ለእርሱ ብንኖር፣ አንድ ቀን ለእኛ እውቅና በመስጠት ክብሩን ያጋራናል።

(ሐ) *ማረጋገጫ* (9:1-8)። ይህንን የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ እምነትን ይጠይቃል። ስለሆነም፣ ከስድስት ቀናት በኋላ ጌታ እግዚአብሔር መከራን ወደ ክብር እንደሚለውጥ የሚያሳይ ማረጋገጫ ሰጠ። (ሉቃስ «ስምንት ቀን» የሚለው ትምህርቱ የተሰጠበትንና ጌታ የከበረበትን ቀን በመቍጠር ነው፤ ሉቃስ 9:28።) ጌታ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ወደ ተራራ (የሄርሞን ተራራ ሳይሆን አይቀርም) ወጣ፤ በዚያም ክብሩን አሳያቸው። ይህ ክስተት በማርቆስ 8:38 እንደተገለጸው ቃሉን በግልጽ የሚያጠናክርና የወደፊቱን መንግሥት ክብር የሚያሳይ ነበር (9:1፤ ዮሐ. 1:14፤ 2ኛ ጴጥ. 1:12-21)። መልእክቱም በግልጽ የሚታይ ነበር። ይኸውም ከመከራ በኋላ ክብር እንደሚከተል የሚያሳይ ነበር።

ሙሴ ሕግን፣ ኤልያስ ደግሞ ነቢያትን ይወክላል፤ ሁለቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜያቸውን ያገኛሉ (ዕብ. 1:1-2፤ ሉቃስ 24:25-27)። ሙሴ ሞቶ የተቀበረ ሲሆን፣ ኤልያስ ግን ወደ ሰማይ ዐርጐ ነበር (2ኛ ነገሥ. 2:11)። ኢየሱስ ደግሞ በሚመለስበት ጊዜ የሞቱትን ቅዱሳን ሰውነት ያስነሣል። በሕይወት ያሉትንም ወደ ሰማይ ይወስዳቸዋል (1ኛ ተሰሎ. 4:13-18)። ኢየሱስ አንድ ቀን የከበረ መንግሥቱን በመመሥረት በነቢያት በኩል የተሰጡትን ብዙ ትንቢቶች ይፈጽማል። የክርስቶስ መከራ መቀበልና ሞት እግዚአብሔር መንግሥቱን እንዳይመሠርት አይከለክለውም። ይልቁንም መስቀሉ

እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ውስጥ ያለውን የኃጢአት ችግር በማስወገድ መንግሥቱን እውን ያደርጋል::

ስለ ክርስቶስ በተራራው ላይ መለወጥ የሚናገረው ቃል በውስጥ ተከስቶ ከውጭ ስለሚታይ ለውጥ ያስረዳል:: ይህ ከልብ ሳይመነጭ ከውጭ ከሚታይ ለውጥ የሚቃረን ነው:: ኢየሱስ ክብሩ በሁለንተናው ላይ እንዲንጸባረቅ በመፍቀዱ የተራራው ጫፍ ቅድስተ ቅዱሳን ሆነ! ስለዚህ ክስተት በምታስብበት ጊዜ፣ ክርስቶስ ይህንን ክብር እንዳካፈለንና ለዘላለም የምንኖርበትን የከበረ ቤት ለመስጠት ቃል እንደገባልን አስታውስ (ዮሐ. 17:22-24):: ሮሜ 12:1-2 እና 2ኛ ቆሮ. 3:18 እንደሚያስረዱት፣ ዛሬ አማኞች ይህንን የመለወጥ ክብር ሊለማመዱ ይችላሉ::

ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ጌታ እየጸለየ ሳለ አንቀላፉ (ሉቃስ 9:29፣32):: ይህም በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራም የሚደግሙት ጥፋት ነው (ማር. 14:32-42):: ሙሴን፣ ኤልያስንና ኢየሱስን በክብሩ ማየታቸውን ሊዘነጉ ተቃርበው ነበር! ጴጥሮስ ያቀረበው አሳብ የእግዚአብሔርን ጥበብ ሳይሆን የሰውን አሳብ ያንጸባርቃል:: ከተራራ ጫፍ ሆኖ በክብሩ መፈንጨት ምን ያህል አስደሳች ነበር! ነገር ግን ደቀ መዝሙርነት ማለት ራስን መካድና መስቀሉን ተሸክሞ እርሱን መከተል ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከከበረው የተራራ ጫፍ ላይ ተቀምጠው የሚያከናውኑት ተግባር አይደለም:: ከታች ከሸለቆ መሟላት የሚገባቸው ፍላጎቶች አሉ:: ከተራራው ጫፍ ላይ የክርስቶስን ክብር ለመጋራት ከፈለግን፣ የክርስቶስን የሸለቆ መከራ ለመካፈል መፍቀድ አለብን::

እግዚአብሔር አብ የጴጥሮስን ንግግር አቋርጦ ትኩረታቸውን ከራእዩ ላይ አንሥቶ ወደ ቃሉ ወሰደው:: «እርሱን ስሙት!» ነበር ያላቸው:: የራእዮች ትውስታ የሚደበዝዝ ሲሆን፣ የማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል:: የከበረው ራእይ እግዚአብሔር ቃሉን ያረጋገጠበት መንገድ እንጂ ፍጻሜ አልነበረም (2ኛ ጴጥ. 1:12-21 አንብብ):: ደቀ መዝሙርነት የሚመሠረተው በአስደናቂ ራእዮች ላይ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ በሆነው በማይለወጠው ቃሉ ላይ ነው:: ጴጥሮስ ፍንጭ እንደ ሰጠው ሙሴን፣ ኤልያስንና ኢየሱስን እኩል አድርገን ልንመለከት አንችልም:: አጽንኦት

የምንሰጠው «ለኢየሱስ ብቻ» ነው — ለቃሉ፣ ለፈቃዱ፣ ለመንግሥቱና ለክብሩ።

ሦስቱ ሰዎች በተራራው ላይ የተመለከቱትን ነገር ለተቀሩት ደቀ መዛሙርት እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም። ምናልባት ይህ ማን ከማን ይበልጣል ለሚለው «የወዳጅነት ውድድር» አስተዋጽኦ አድርጎ ይሆናል። ከጌታ ትንሣኤ በኋላ ስለዚሁ ጉዳይ የሰጡት ማብራሪያ ለስሙ መከራንና ሞትን ለሚጋፈጡት አማኞች ከፍተኛ መበረታታትን እንዳስከተለ አያጠራጥርም።

(መ) *እርማት* (9:11-13)። ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ የተሻለ ግንዛቤ አግኝተው ነበር። ነገር ግን ኤልያስ ለመሢሑ መንገድ ሊያዘጋጅ እንደሚመጣ የተነገረው ትንቢት ጥርት ብሎ አልታያቸውም ነበር። መምህሮቻቸው በሚልክያስ 3:1 እና 4:5-6 የተነገሩት ትንቢቶች መሢሑ ከመምጣቱ በፊት መፈጸም እንዳለባቸው አስተምረዋቸው ነበር (ዮሐ. 1:21)። ኤልያስ ቀደም ሲል መጥቶ ሳያዩት ቀሩ ወይስ ገና አልመጣም ነበር? ምናልባት ኤልያስ በተራራው ላይ የተገለጸው ይህንን ትንቢት ለመፈጸም ይሆናል።

ኢየሱስ ሁለት እውነቶችን በግልጽ ተናግሯል። በመጀመሪያ፣ በእርሱ ለሚያምኑት ይህ ኤልያስ የተባለው አገልጋይ መጥምቁ ዮሐንስ ነበር። ምክንያቱም ዮሐንስ የጌታን መንገድ አዘጋጅቷልና። ዮሐንስ ኤልያስ ከሞት ተነሥቶ በእርሱ አምሳል መምጣቱን ባይቀበልም (ዮሐ. 1:21፣25)፣ በኤልያስ መንፈስና ኃይል አገልግሏል (ሉቃስ 1:16-17)። ሁለተኛ፣ ኤልያስ ሚልክያስ እንደተነበየው ወደፊት ከታላቁ መከራ ጊዜ በፊት ይመጣል (ማቴ. 17:11)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህንን ከራእይ 11:2-12 ጋር ያያይዙታል። እስራኤል የዮሐንስን አገልግሎት አልተቀበለችም ነበር። ተቀብለውት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር እንደላከው ኤልያስ ያገለግላቸው ነበር። ኢየሱስንም በተቀበሉት ነበር። ነገር ግን ሁለቱንም አገልጋዮች ባለመቀበል ለሞት አሳልፈው ሰጧቸው።

## 2. ኃይል ከእምነት ይመጣል (ማር. 9:14-29)

የክርስትና ሕይወት ዓቀበትና ቊልቊለት የበዛበት መልክዓ ምድር ነው (ዘዳግ. 11:11)። በአንድ ቀን ውስጥ አንድ ደቀ መዝሙር ከሰማይ ክብር ወደ ሲዖል ሊወርድ ይችላል። ጌታችንና ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ዘጠኙ ደቀ መዛሙርት በተመለሱ ጊዜ፣ በሁለት ችግሮች ውስጥ ተዘፍቀው አገኟቸው፦ አጋንንት ያደሩበትን ልጅ ለመፈወስ ካለመቻላቸውም በላይ፣ ጸሐፍት እየሞገቷቸው ነበር። ምናልባትም ልጁን ከአጋንንት ነፃ ሊያወጡ ባለመቻላቸው ተሳልቀውባቸው ይሆናል።

ልጁ ዲዳና ደንቆሮ ሲሆን (ማር. 9:17፣ 25)፣ ጋኔኑ ሊያጠፋው እየተጣጣረ ነበር። ልጁን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ይሞክር ለነበረው አባቱ ሁኔታው ምን ያህል ከባድ እንደነበረ እስቲ አስቡት! ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አጋንንትን እንዲያወጡ ሥልጣን የሰጣቸው ቢሆንም (6:7፣13)፣ ለልጁ ያበረከቱት አገልግሎት ግን ውጤታማ አልነበረም። በዚህ ጊዜ ጌታችን እምነት በማጣታቸው ማዘኑ አስገራሚ አይሆንም! እኛስ በልግስና ለሕዝቡ የሰጣቸውን መንፈሳዊ ሀብቶች ባለመጠቀማችን ምን ያህል ጊዜ አዝኖብን ይሆን!

ደቀ መዛሙርቱ ከልጁ ጋኔኑን ሊያወጡ እንዳልቻሉ የተመለከተው መከረኛው አባት ኢየሱስም ይሳካለት እንደሆነ እርግጠኛ አልነበረም። ለዚህ ነበር «ቢቻልህስ» ያለው (9:22)። ነገር ግን የልጁ አባት አለማመኑን ተገንዝቦ ጌታ ራሱንና ልጁን እንዲረዳ ጠይቋል። ኢየሱስም ጋኔኑን አውጥቶ ልጁን ለአባቱ ሰጠው።

የዚህ ተአምር ዋንኛ ትምህርት እምነት ጠላትን የማሸነፍ ኃይል እንዳለው ማሳየት ነው (ቊ. 19፣23-24፣ እንዲሁም ማቴ. 17:20 አንብብ)። ዘጠኙ ደቀ መዛሙርቱ ያልተሳካላቸው ለምን ነበር? ምክንያቱም በግል መንፈሳዊ ጕዟቸው ቸልተኞች በመሆን ከጸምና ጸሎት ስለ ራቁ ነው (ቊ. 29)። ኢየሱስ የሰጣቸው ሥልጣን የሚሠራው እምነት የታከለበት እንደሆነ ብቻ ነበር። ነገር ግን እምነታቸውን በመንፈሳዊ ራስን የመግዛት ልምምድና በጽሞና ማሳደግ ይኖርባቸው ነበር። ምናልባትም መንፈሳዊ

መነቃቃታቸውን የቀነሰውና እምነታቸውን ያዳከመው የጌታቸው አለመኖር ወይም እነርሱን ትቶ ሦስቱን ደቀ መዛሙርት መውሰዱ ሊሆን ይችላል:: ጉድለታቸው እነርሱን ከማሳፈር አልፎ የጌታን ክብር ለመጉዳትና ጠላቶቹ የሚተቹበትን ምክንያት አስገኝቶላቸዋል:: እግዚአብሔርን የሚያስከብረው በእርሱ ላይ ያለን እምነታችን ነው (ሮሜ 4:20)::

## 3. አገልግሎት ወደ ክብር ይመራል (ማርቆስ 9:30-50)

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ሳለ ስለሚደርስበት መከራ ነገራቸው:: ምንም እንኳ ጌታችን ስለ ትንሣኤውም ጨምሮ የነገራቸው ቢሆንም፣ እነርሱ ግን ሊረዱት አልቻሉም (ማቴ. 17:9 አንብብ):: በመሆኑም፣ እጅግ አዘኑ (ማቴ. 17:23)::

ማዘናቸው ግን ከመካከላችን ታላቁ ማን ነው? በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ከመከራከር አላቀባቸውም? ኢየሱስ ስለሚቀበለው መከራና ሞት የነገራቸውን ከሰሙ በኋላ የራስ ወዳድነት ዕቅዶቻቸውን ዘንግተው በዚሁ ጉዳይ ላይ ማሰላሰል ነበረባቸው:: ምናልባትም ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ከጌታ ጋር መሄዳቸው ለእኔ እበልጣ ውድድር ማቀጣጠያ ተጨማሪ ነዳጅ ሆኖ ይሆናል::

ጌታ ለእነርሱ (እና ለእኛ) ስለ ክብር ጠቃሚ ትምህርት ለመስጠት በማሰብ፣ ሕፃን ልጅ በመካከላቸው አቁሞ የመጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ ሰው የመጨረሻ መሆን እንዳለበት፣ የመጨረሻም ለመሆን የሚፈልግ ሰው የሁሉ አገልጋይ መሆን እንዳለበት አስተማረ:: ሕፃን ልጅ ሕፃንነቱን በማወቅ እንደ ሕፃን ልጅ የሚሆነውን ሁሉ ይሆናል:: ይህም የሰዎችን ፍቅርና እንክብካቤ ወደ ራሱ እንዲስብ ያስችለዋል:: እንደ ትልቅ ሰው ለመሆን በመሞከር ሰዎችን ለማስደነቅ የሚሞክር ልጅ ብዙም ትኩረት አያገኝም::

እውነተኛ ትሕትና ማለት ራስህን ማወቅ፣ ራስህን መቀበል፣ ራስህን መሆንና ራስህን ለሌሎች አሳልፈህ መስጠት ነው:: ይህም የምትችለውን ሁሉ ያጠቃልላል:: የዓለም ፍልስፍና ሌሎች ለአንተ የሚሠሩልህ ከሆነ አንተ ታላቅ ነህ ይላል:: የክርስቶስ

መልእክት ግን ታላቅነት ሌሎችን በማገልገል የምናገኘው በረከት እንደሆነ ያስተምራል:: በአረማይክ ቋንቋ «ልጅ» እና «ባሪያ» የሚሉት ቃላት አንድ ስለሆኑ፣ ኢየሱስ ሁለቱን ያገናኘበትን ምክንያት መረዳቱ አስቸጋሪ አይሆንም:: የሕፃን ልጅ ልብ ካለን ሌሎችን ማገልገል ብዙም አይከብደንም:: የባርነት አመለካከት ካለን ደግሞ ልጆችን የኢየሱስ ክርስቶስና የእግዚአብሔር አብ ተወካዮች አድርገን እንቀበላለን::

በዚህ ነጥብ ላይ ዮሐንስ ቀናዒነታቸውን በመግለጽ ደቀ መዛሙርቱን ለመከለል ሞክሯል (ማር. 9:38-41):: ዘጠኙ ደቀ መዛሙርት ዲዳውንና ደንቆሮውን ልጅ ከሰይጣን መዳፍ ሊያላቅቁት ባልቻሉበት ሰዓት አንድ ሰው ከልጁ አጋንንት እንዳያስወጣ መናገር ምን እንደሚመስል አስብ:: የኢየሱስን ስም መጠቀም ከሥልጣኑ ሥር እንደ መሥራት በመሆኑ፣ ደቀ መዛሙርቱ ሰውዬውን የመከልከል መብት አልነበራቸውም:: ሰውዬው ለጌታው ይቆማል ወይም ይወድቃል (ሮሜ 14:4)::

ማርቆስ 9:40ን «ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል» ከሚለው ከማቴዎስ 12:30 ጋር ማነጻጸሩ ጠቃሚ ነው:: ሁለቱም አንድ ሰው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ገለልተኛ አቋም ሊይዝ እንደማይችል ያስረዳሉ:: ስለሆነም፣ እርሱን ካልደገፍን ተቃውመነዋል ማለት ነው:: ካልተቃወምነው ደግሞ ደግፈነዋል ማለት ነው:: በስሙ ያልተጠቀሰው አገልጋይ ለክርስቶስ ክብር እያመጣ በመሆኑ፣ የአዳኙ ደጋፊ እንጂ ተቃዋሚ ሊሆን አይችልም::

ነገር ግን ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር ለማረጋገጥ የግድ ታላላቅ ተአምራትን መፈጸም የለብንም:: አንድን ልጅ በፍቅር ስንቀበል ወይም በርኅራኄ አንድ ብርጭቆ ውኃ ስናካፍል ትሑት የባሪያ ልብ እንዳለን ይታወቃል:: ምክንያቱም ክርስቶስን እያገለገልን ነውና:: በዓለም ደግሞ ይህን የሚያህል ታላቅ አገልግሎት የለም (ማቴ. 25: 31-46)::

ኢየሱስ የዮሐንስን ንግግር እንደ ዋዛ አላየውም:: እንዲያውም ከዚሁ አሳብ ተነሥቶ ሌሎችን ማሰናከልና ከዚህም የተነሣ ጌታን አለማገልገል ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ አብራርቷል (ማር. 9:42-50):: «ከእነዚህ ከታናናሾች» የሚለው ክርስቶስን

የሚከተሉትንና ሊያገለግሉት የሚፈልጉትን የእግዚአብሔርን ልጆች ሁሉ ያመለክታል:: አማኞች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች አማኞች የሚያስተናግዱበት መንገድ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው:: እግዚአብሔር እርስ በርሳችን እንድንስማማ ይፈልጋል (ቍ. 50):: ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌሎች አማኞች ጋር አይስማሙም ነበር!

ይህ ስለ ሲዖል የተነገረው ጠንካራ መልእክት ሁላችንም ለኃጢአት ትልቅ ትኩረት እንድንሰጥ ያስጠነቅቀናል:: ራሳችንንና ሌሎችን የሚያሰናክል ማንኛውም ነገር ከሕይወታችን ተቆርጦ መወገድ አለበት:: እጅ፣ እግርና ዓይን ጠቃሚ የሰውነት ክፍሎች ቢሆኑም፣ ኃጢአትን የሚጋብዙ ከሆኑ መወገድ አለባቸው:: በመሠረቱ፣ ጌታ ቀደም ሲል ኃጢአት ከልብ እንደሚመነጭ ስላስተማረ (7:20-23)፣ ስለ ትክክለኛው (ቀጥተኛው) የአካል መቆረጥ አልነበረም የሚናገረው:: እርሱ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት የካንሰር በሽታ ውጫዊ አካልን እንደሚያሠቃይ ሁሉ ኃጢአት ውስጣዊ ማንነታችንን አጥብቆ እንደሚጐዳና ከዚህም የተነሣ መወገድ ያለበት መሆኑን ነው::

አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ስለ ሲዖል እንዲህ ጠንከር ያሉ ቃላት ሲናገር በመስማታቸው ደንግጠዋል (ኢሳ. 66:24 አንብብ):: ኢየሱስ ዘላለማዊ ሥቃይና የጽድቅ ቅጣት የሚሰጥበት ሲዖል የተባለ ስፍራ እንዳለ ያምን ነበር (ሉቃስ 16:ከ19 ጀምሮ አንብብ):: አንድ የጦር ሠራዊት ወንጌል አገልጋይ በሲዖል እንደማያምን ሲናገር፣ ከወታደሮቹ አንዳንዶቹ የእርሱ አገልግሎት አስፈላጊ እንዳልሆነ ገልጸውለታል:: ምክንያቱም ሲዖል ከሌለ ሞት ምን ያስፈራል? ሲዖል ካለ ግን አገልጋዩ ወደ ጥፋት እየመራቸው ነው:: በሁለቱም መንገድ የእርሱ አገልግሎት ቢቀርባቸው ይሻላል::

በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ሲዖል» ተብሎ የተተረጐመው ቃል «ገሃና» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ነው (በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በቀጥታ «ገሃነም» ተብሏል::) የዕብራይስጥ ምንጩ «የሂኖን ሸለቆ» ነው:: ይህም በኃጢአት የተሞላው ንጉሥ አካዝ ከኢየሩሳሌም ውጭ ሞሎክ

ለተባለ የእሳት ጣዖት የሰገደበትና ልጆቹን የሠዋበት ስፍራ ነው (2ኛ ዜና 28: 1-3፤ ኤር. 7:31፤ 32:35)።

አንዳንድ መዛግብት ኢሳይያስ 66:24ን በማርቆስ 9:44 እና 46 ውስጥ አይጠቅሱም። ነገር ግን በቍ. 48 የተጠቀሰው አንድ ዓረፍተ ነገር ራሱ በቂ ነው። ሲዖል ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው (ራእይ 20:10)። ለኃጢአተኞች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ከዘላለማዊ ሲዖል መትረፋቸው ምን ያህል ጠቃሚ ነው። ለአማኞችስ ለጠፋው ዓለም መልእክቱን ማስተላለፋቸው ምን ያህል አስፈላጊ ነው!

ይህ ከባድ መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ አይደለምን? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። «ኃጢአትን በጽኑ መዋጋት ብዙ ዋጋ ይጠይቅብናል!» በማርቆስ 9:49-50 ኢየሱስ አሳቡን ለማብራራት «የሕያው መሥዋዕትነትን» ጽንሰ አሳብ ተጠቅሟል (ሮሜ 12:1-2 አንብብ)። መሥዋዕት ከመሠዊያው ላይ ተጥዶ በእሳት ተቃጥሎ ያልቃል። በኃጢአትህ ጠፍተህ የሲዖልን እሳት ከምትጋፈጥና ለክብሩ ተሠውተህ የእግዚአብሔርን የሚያነጻ እሳት ከምትታገሥ የትኛው ይሻላል? ሰይጣን አሁን የክብርን ተስፋ እንደሚሰጥህና ሥቃዩ በኋላ እንደሚደርስብህ አስታውስ። ኢየሱስ አሁን ለመከራ ይጠራናል፣ በኋላ ግን በክብሩ ደስ ይለናል።

አይሁዶች በመሥዋዕቶቻቸው ውስጥ እርሾ ወይም ማር መጨመር አይችሉም ነበር። ነገር ግን ጨው እንዲጠቀሙ ይነገራቸዋል ((ዘሌዋ. 2:11፣13)። ጨው ንጽሕናንና ሳይበላሽ መቆየትን ያመለክታል። ጨው በብሉይ ኪዳን ዘመን ቃል ኪዳንን ለመመሥረት ያገለግል ነበር። ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔር ጨው ነበሩ (ማቴ. 5:13)። ነገር ግን ጨውነታቸው ዋጋ ቢስ ሊሆን ተቃርቦ ነበር። በዘመናችን ያለው ጨው የጠራ በመሆኑ ጣዕሙን አያጣም። በዚያን ጊዜ የነበረው ጨው ግን ቆሻሻ ነገሮች የነበሩበት በመሆኑ ጣዕሙን ሊያጣ ይችል ነበር። ይህንን ግሩም ክርስቲያናዊ ባሕርይ ካጣህ በኋላ እንዴት መልሰህ ልታገኘው ትችላለህ?

ደቀ መዛሙርቱ ሌሎችን ከሚገሥጹ ይልቅ የራሳቸውን ልብ ሊመረምሩ ይገባቸው ነበር:: በቀላሉ ጨውነታችንን አጥተን ለእግዚአብሔር የማንጠቅም ሰዎች ልንሆን እንችላለን:: ክርስቲያኖች የመከራና ስደት እሳት የሚደርስባቸው ቢሆንም እኔ እበልጥ ማለታቸውን ትተው በኅብረት ሊጸኑ ይገባል:: እርሱን ልናስከብርና እርስ በርሳችን ልንስማማ የምንችለው ለጌታ ራሳችንን ከሰጠንና መልካም ባሕርይ ካለን ብቻ ነው::

ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ ያስተማራቸው ሦስት ትምህርቶች ዛሬ ለክርስቲያናዊ አኗኗር መሠረታዊ ናቸው:: ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን ከሰጠን መከራ ወደ ክብር ይመራናል፤ እምነት ኃይልን ያፈራል፤ የመሥዋዕትነት አገልግሎታችንም ወደ ክብር ይወስደናል:: ችኩልና በተደጋጋሚ ይሳሳት የነበረው ጴጥሮስ ከጌታ በመማሩ፣ «በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል» ሲል ጽፏል (1ኛ ጴጥ. 5:10)::

# 8

# የባሪያው አያዎዎች

## ማርቆስ 10

ታላቅ መምህር እንደ መሆኑ፣ ጌታችን የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል:: ከእነዚህም መካከል ተምሳሌቶች፣ ተአምራት፣ አምሳያዎች፣ ምሳሌዎችና አያዎዎች ይገኙባቸዋል:: አያዎ (Paradox) ከራሱ ጋር የሚቃረን እየመሰለ ጠቃሚ እውነትን ወይም መርህን የሚያስተላልፍ አገላለጽ ነው:: «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ» የሚለው ዓረፍተ ነገር አያዎ ነው (2ኛ ቆሮ. 12:10፤ 6:8--10ን አንብብ):: እውነትን ለመግለጽ ከሁሉም የሚሻለው መንገድ አያዎ የሚሆንባቸው ጊዜያት አሉ:: ይህም ምዕራፍ የሚያሳየው ጌታችን ይህንን ሲያደርግ ነው:: ጌታ ረዣዥም ስብከቶችን ማቅረብ ሲችል፣ እነዚህን እጥር ምጥን ባሉ አያዎዎች የሚገለጡ አምስት ጠቃሚ ትምህርቶችን ሰጥቶናል::

## 1. ሁለቱ አንድ ይሆናሉ (ማርቆስ 10:1-12)

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ሳለ እግረ መንገዱን የገሊላ አገልግሎቱን ፈጽሞ ከቅፍርናሆም ወጣ:: ከዚያም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ መጣ (ቍ. 32):: ይህንን አካባቢ የሚያስተዳድረው ሄሮድስ አንቲጳስ ነበር:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ፈሪሳውያኑ ስለ ፍቺ በመጠየቅ ሊያጠምዱት የሞከሩት:: ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ የተገደለው የሄሮድስን የዘማዊነት ጋብቻ በመቃወሙ ነበር (6:14-29)::

ነገር ግን የማሳሳቻ ጥያቄያቸው ከፖለቲካዊ ጉዳይም ያለፈ መልእክት ነበረው:: ምክንያቱም ፍቺ በአይሁድ የሃይማኖት መምህራን ዘንድ በጣም አወዛጋቢ ጉዳይ ነበር:: ኢየሱስ የሚሰጠው ማንኛውም መልስ የተወሰኑ ወገኖችን በማስቀየም ለእስራት ሊዳርገው እንደሚችል እርግጠኛ ነበር:: ግሦቹ እንደሚያመለክቱት ፈሪሳውያኑ ኢየሱስን ለመወንጀል የሚያስችል ምክንያት ያገኙ ዘንድ ደጋግመው ጠየቁት::

በዚያን ዘመን በፍቺ ጉዳይ ላይ ሁለት እርስ በርሳቸው የሚጋጩ አመለካከቶች ይሰነዘሩ ነበር:: መምህራኑ የሚይዙት አቋም የተመሠረተው በዘዳግም 24:1-4 «የእፍረት ነገር» የሚለውን ሐረግ በሚተረጉምበት መንገድ ላይ ነበር:: የመምህር (ረባይ) ሂለል ተከታዮች ለዘብተኛ አተረጓጎም ስለሚከተሉ አንድ ሰው ሚስቱን በማንኛውም ምክንያት (ምግብ ማሳረርን ጨምሮ) ሊፈታት እንደሚችል ያስተምሩ ነበር:: የመምህር ሺማይን አስተሳሰብ የሚከተሉ ወገኖች ግን ጥብቅ አተረጓጎምን ስለሚከተሉ «የእፍረት ነገር» የሚለው ሐረግ ከጋብቻ በፊት የተፈጸመን ኃጢአት እንደሚያመለክት ያስተምሩ ነበር:: አንድ ሰው ሚስቱ ልጃገረድ ካልሆነች ሊፈታት ይችል ነበር::

ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ እንደሚያደርገው፣ ክርክሩን ችላ ብሎ ትኩረታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ አሳረፈ:: ይህም በዘዳግም 24:1-4 የተገለጸው የሙሴ ሕግ ነበር:: ይህንን ምንባብ በምታጠናበት ጊዜ፣ ሁለት ነገሮችን ማጤኑ ጠቃሚ ነው:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ ሚስቱን የሚፈታው ባሏ ነበር እንጂ ሚስት ባሏን ልትፈታ አትችልም ነበር:: ሴቶች በእስራኤል አገር እንዲህ ዓይነት መብት አልነበራቸውም:: የሮማውያን ሴቶች ግን እንዲህ ዓይነት መብቶች ነበሯቸው:: <u>ሁለተኛ</u>፣ የሴቲቱን የጋብቻ ሁኔታና ለዳግም ጋብቻ ዝግጁ መሆኗን የሚያሳይ ሕጋዊ «የፍቺ ወረቀት» ይሰጣት ነበር:: ከፍቺው ወረቀት በተጨማሪ የሚፈለገው ነገር ቢኖር ሴቲቱ ሁለተኛው ባሏ ቢፈታት ወደ መጀመሪያው ባሏ ለመመለስ አለመቻሏን ማረጋገጥ ነበር:: እንደገና ማግባት የተፈቀደ በመሆኑ በአይሁዶች መካከል የሚነሣው ጥያቄ «የተፋታች ሴት እንደገና ልታገባ ትችላለች ወይ?» የሚል አልነበረም:: ትልቁ ጥያቄ፣ « አንድ ሰው ሚስቱን የሚፈታበት ሕጋዊ መስፈርት ምንድን ነው?» የሚለው ነበር::

የሙሴ ሕግ ዝሙት የፍቺ መስፈርት እንደሚሆን አላመለከተም:: ምክንያቱም በእስራኤል አገር ዝሙት የፈጸመች ሴትና የተባበራት ወንድ በድንጋይ ተወግረው ይሞቱ ነበር (ዘዳግ. 22:22፤ ዘሌዋ. 20:10፤ በተጨማሪም ዮሐ. 8:1--11ን አንብብ):: ሙሴ በዘዳግም 24:1 «የእፍረት ነገር» ሲል ዝሙትን ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው::

ኢየሱስ ሙሴ የፍቺን ሕግ የሰጠው በሰዎች ልብ ኃጢአተኝነት ምክንያት መሆኑን ገልጿል:: ሕጉ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደ ሰብአዊ ፍጡር ከመንከባከብ ይልቅ እንደ ፈቀዱ በመፍታት እንደማይረባ ዕቃ እንዳያንገላቷቸው ለመከላከል ነበር የሞከረው:: የፍቺ ወረቀት ካልተሰጣት የተፈታች ሴት በቀላሉ በኅብረተሰቡ ልትተፋና እንደ ጋለሞታ ልትቆጠር ትችል ነበር:: ማንም ሰው ሊያገባት ስለማይፈልግ፣ መከላከያ አጥታ ልትሠቃይ ትችል ነበር::

እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ ለእስራኤል ሲሰጥ ፍቺን መደገፉ ወይም ማበረታታቱ አልነበረም:: ነገር ግን ባሎች ሚስቶቻቸውን የሚፈቱበትን መንገድ በማጣበብ ፍቺን ለመከላከል እየሞከረ ነበር:: ሚስቶች የባሎቻቸው ፍላጐቶች ሰለባዎች እንዳይሆኑ ለመከላከል በፍቺ አካባቢ ብዙ ደንቦችን አስቀምጧል::

ከዚያም ጌታ ከሙሴ ባሻገር ወዳለው ወደ መጀመሪያው የፍጥረት ታሪክ ወሰዳቸው (ዘፍጥ.1:27፤ 2:21-25):: ምክንያቱም መጀመሪያ ጋብቻን የመሠረተው እግዚአብሔር እንደ መሆኑ፣ የጋብቻ ደንቦችን የማውጣት መብት አለው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣ ጋብቻ በሁለት ወንዶች ወይም በሁለት ሴቶች መካከል ሳይሆን በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም ግንኙነት ነው:: ግንኙነቱም የተቀደሰና ዘላቂ ነው:: ይህ ሁለቱ አንድ የሚሆኑበት በሰው ዘር ውስጥ የሚከሰት እጅግ የቀረበ ግንኙነት ነው:: አባትና ልጅ፣ እናትና ሴት ልጇ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት ሊመሠርቱ አይችሉም:: ባልና ሚስት ግን በዚህ ግንኙነት ደስ ሊሰኙ ይችላሉ::

በጋብቻ ውስጥ መንፈሳዊው ክፍል እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ቢታወቅም፣ በዚህ ስፍራ ትኩረት የተሰጠው በሥጋዊ ጥምረት ላይ ነው:: ሁለቱ አንድ መንፈስ ሳይሆን አንድ ሥጋ ይሆናሉ:: ጋብቻ ሥጋዊ ጥምረት ስለሆነ፣ ሊፈርስ የሚችለውም እንደ ሞት (ሮሜ 7:1-3) ወይም ዝሙት (ማቴ. 5:32፤ 19:9) ባሉት ሥጋዊ ምክንያቶች ነው:: ማርቆስ በማቴዎስ ውስጥ የተጠቀሰውን የጋብቻ ማፍረሻ ምክንያትም ሆነ ሞትን አልጠቀሰም::

ጌታ መጠየቅ ለማይታክታቸው ደቀ መዛሙርቱ ጉዳዩን ለብቻቸው አብራርቶላቸዋል:: በዚህ ጊዜ ማግባት አደገኛ ነው እያሉ ሳያስቡ አይቀሩም:: በዝሙት ምክንያት ከተፈቀደው ውጭ ፈትቶ ሌላ ማግባት ወንዱን ዘማዊ ያደርገዋል:: ይህ ደግሞ አደገኛ ነገር ነው:: ኢየሱስ በማስጠንቀቂያው ውስጥ ሴቶችንም እንዳካተተ ልብ በል:: ይህም በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበራቸውን ደረጃ በማሳደግ ከወንዶች ጋር እኩል ኃላፊነት እንዳላቸው አመልክቷል:: የአይሁድ መምህራን ይህን ያህል ለሴቶች ክብር አይሰጡም ነበር::

ማርቆስ 10:9 ሰው በጋብቻ የተጣመሩትን ሰዎች ሊያለያይ እንደማይችል ያስጠነቅቀናል:: እግዚአብሔር ግን ይህንን ሊያደርግ ይችላል:: እግዚአብሔር ጋብቻን ስለመሠረተ፣ ሕግ የመደንገግ መብት አለው:: ጋብቻ በእኛ ሕግ መሠረት ትክክል ሊሆንና በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት የተሳሳተ ሊሆን ይችላል:: ያገቡ ሰዎች ለትዳር ጓደኞቻቸው ራሳቸውን አሳልፈው ሊሰጡ (ቍ. 7) እና በታማኝነት አብረዋቸው ሊኖሩ ይገባል:: ብዙ ሰዎች ፍቺን ከትዳር ኃላፊነት ለማምለጥ የሚቻልበት «ቀላል አማራጭ» አድርገው ስለሚወስዱ ለትዳር ጓደኞቻቸውና ለእግዚአብሔር የገቡትን ቃል ኪዳን አያስታውሱም::

## 2. አዋቂዎች እንደ ልጆች ይሆናሉ (ማርቆስ 10:13-16)

መጀመሪያ ጋብቻ ይመሠረታል:: ከዚያም ልጆች ይወለዳሉ:: ቅደም ተከተሉ አመክንዮአዊ ነው:: ከዛሬዎቹ «ዘመነኞች» በተቃራኒ፣ በኢየሱስ ዘመን የነበሩት ሰዎች ልጆችን እንደ ሸክም ሳይሆን እንደ በረከት፣ እንደ ዕዳ ሳይሆን እንደ ትልቅ ሀብት ይቆጥሩ ነበር (መዝ. 127-128):: ልጅን አለመውለድ ለባለትዳሮች የኃዘንና የእፍረት ምክንያት ነበር::

ወላጆች ልጆቻቸውን ይባርኩላቸው ዘንድ ወደ አይሁድ መምህራን የማምጣት ልማድ ነበራቸው:: ስለሆነም፣ ልጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ ማምጣታቸው ተገቢ ነበር:: አንዳንዶች ገና በወላጆቻቸው ጀርባ ላይ የታዘሉ (ሉቃስ 18:15) ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በእግራቸው የሚራመዱ ነበሩ:: ኢየሱስ ሁሉንም ተቀብሎ ባረካቸው::

ደቀ መዛሙርቱ ሕዝቡን የገሠጹትና ልጆች ወደ ኢየሱስ እንዳይመጡ ለመከልከል የሞከሩት ለምን ነበር? (ማቴ. 15:23፤ ማር. 6:36 ደቀ መዛሙርቱ ጠንካራ ልብ እንዳላቸው የሚያሳዩ ይመስላል::) ምናልባት ይህንን የሚያደርጉት ጊዜውንና ጉልበቱን እንዲቆጥብ የረዱት እየመሰላቸው ይሆናል:: በሌላ አገላለጽ፣ ልጆች አስፈላጊ ናቸው የሚል ግምት አልነበራቸውም! ኢየሱስ ቀደም ሲል ልጆችን በስሙ እንዲቀበሉና ማናቸውንም ላለማሰናከል እንዲጠነቀቁ ካስተማራቸው በኋላ እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰዳቸው አስገራሚ ነው:: ባሕርያቸው የተለየ ነበር (9:ከ36 ጀምሮ):: ድጋሚ ያስተማራቸውን ረስተው ተገኙ::

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ዕንቅፋት በመሆናቸው በጣም በመቆጣቱ በይፋ ገሠጻቸው:: ከዚያም ልጆች ከአዋቂዎች የተሻለ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች መሆናቸውን ገለጸ:: እኛ ልጆች አዋቂዎችን እንዲመስሉ እንመክራለን:: ኢየሱስ ግን አዋቂዎች ልጆችን እንዲመስሉ መከሯቸዋል!

ልጆች ምሳሌዎች የሚሆኑት እንዴት ነው? በሌሎች ላይ በትሕትና ስለሚደገፉ፣ የተሰጣቸውን ትምህርት ስለሚቀበሉ፣ ራሳቸውንና በሕይወት ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ስለሚቀበሉ ልጆች መልካም ምሳሌዎች ናቸው:: ኢየሱስ የሚናገረው ምግባረ ብልሹ ስላልሆኑት ልጆች እንጂ አዋቂን ለመምሰል ስለሚሞክሩት አይደለም:: ልጆች እምብዛም መግለጽ ባይችሉም በጣም ይደሰታሉ:: ልጆች በእምነት ይኖራሉ:: ልጆች ሌሎች እንደሚንከባከቧቸው በማሰብ በእምነት ይኖራሉ::

እኛም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው እንደ ልጆች ራሳችንን ለመርዳት የማንችልና በእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ነው:: በእግዚአብሔር መንግሥትም ደስ የምንሰኘው አባታችን እንደሚወድደንና ዕለታዊ ፍላጐታችንን እንደሚያሟላ በማመን ነው:: አንድ ልጅ ችግር ሲገጥመው ምን ያደርጋል? ችግሩን ወደ አባቱና እናቱ ይወስዳል:: ይህ ከሰማያዊ አባታችን ጋር ለምናደርገው ግንኙነት ምን ዓይነት መልካም ምሳሌነት ነው! አዎ፣ እግዚአብሔር ልጆችን እንድንመስል ይፈልጋል!

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ልጆችን እንዳጠመቀ የሚያሳይ መረጃ አልተጠቀሰም:: ኢየሱስ አዋቂዎችንም አላጠመቀም ነበርና (ዮሐ. 4:1-2):: ደቀ መዛሙርቱ ልጆችን የማጥመቅ ልማድ ቢኖራቸው ኖሮ ሕዝቡን ለመመለስ አይጥሩም ነበር:: ኢየሱስ እነዚህን ብርቅዬ ልጆች በተወደደ ክንዱ አቅፎ ባረካቸው:: ይህ ምንኛ የከበረ በረከት ኖሯል!

## 3. ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ (ማርቆስ 10:17-31)

ከኢየሱስ እግር ሥር ከወደቁት ሰዎች ሁሉ ከመጣበት ሁኔታ ብሶበት የተመለሰው ይኼ ሰውዬ ብቻ ነው:: ይህ ሰው ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ነበሩት! ትልቅ እምቅ ኃይል ያለው ወጣት ነበር (ማቴ. 19:22):: ምናልባት በአካባቢው ፍርድ ቤት ውስጥ የሆነ ሥልጣን ስለነበረው (ሉቃስ 18:18)፣ ሰዎች ያከብሩት ነበር:: መልካም ባሕርይና ሥነ ምግባር የነበረው ከመሆኑም በላይ፣ ከኢየሱስ እግር ሥር መንበርከኩ በልቡ ውስጥ ለመንፈሳዊ ነገሮች ትልቅ ረሃብ እንደነበረው ያሳያል:: በሁሉም ነገር ፍጹም የተዋጣለት ወጣት ሲሆን፣ ኢየሱስም ወድዶት ነበር::

ይህ ሁሉ ብቃት የነበረው ወጣት ለመንፈሳዊ ነገሮች የነበረው አመለካከት ግልብ ነበር:: የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት አንድን ነገር ለማድረግ የሚችል ይመስለው ስለነበር፣ ስለ ደኅንነት ትልቅ ግምት አልነበረውም:: ይህ በዚያን ጊዜ አይሁዶች በብዛት የያዙት አቋም ነበር (ዮሐ. 6:28):: ዛሬም ብዙ ሰዎች በራሳቸው ጥረት ደኅንነትን ሊያገኙ የሚችሉ ይመስላቸዋል:: አብዛኞቹ ያልዳኑ ሰዎች አንድ ቀን እግዚአብሔር መልካምና ክፉ ሥራዎቻቸውን እንደሚደምርና መልካም ሥራቸው ከክፉ ሥራቸው በልጦ ከተገኘ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚያስገባቸው ያስባሉ::

ከዚህ በመልካም ሥራ የመዳን ስልት በስተጀርባ ስለ ኃጢአት፣ ሰው፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስና ደኅንነት ግልብ አመለካከት መኖሩ ግልጽ ነው:: ኃጢአት በቅዱስ አምላክ ላይ የሚፈጸም ዓመፅ ነው:: ይህ ተግባር ብቻ ሳይሆን ሰውን አልፎ እግዚአብሔርን የሚያንኳስስ ውስጣዊ አመለካከት ጭምር ነው:: ይህ ወጣት የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመፈጸም

መዝገቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማወራረድ የሚችል መስሎት ነበር?

ወጣቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠለቀ አመለካከት አልነበረውም:: «ቸር መምህር ሆይ» ብሎ ቢጠራውም ምፀት የቃጣው ይመስላል:: ምክንያቱም የአይሁድ መምህራን ሰው «ቸር» ብሎ እንዲጠራቸው አይፈቅዱም ነበር:: ቸር እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ቃሉም የሚያገለግለው ለእርሱ ብቻ ነበር:: ኢየሱስ ቸርነቱን እያረጋገጠ እንጂ እየካደ አልነበረም:: እርሱ የፈለገው ወጣቱ እየተናገረ ያለውን በትክክል እንዲገነዘብና ንግግሩ የሚያካትታቸውን ኃላፊነቶች ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑን ማረጋገጥ ነበር::

ይህም ኢየሱስ ስለ ሙሴ ሕግ ያነሣበትን ምክንያት ያስረዳል:: የፈለገውም ወጣቱ ራሱን በቅዱስ አምላክ ፊት እንደተንበረከከ ኃጢአተኛ አድርጐ እንዲያይ ነበር:: ሕግን በመጠበቅ ከኃጢአት ልንድን አንችልም (ኤፌ. 2:8-10፤ ገላ. 2:16-21):: ሕጉ መቆሸሻችንን የሚያሳይ መስተዋት ነው:: ነገር ግን መስተዋቱ ኃጢአታችንን አያጥብም:: ሕጉ ከተሰጠባቸው ምክንያቶች አንዱ ኃጢአተኛውን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነበር (ገላ. 3:24):: በዚህ ወጣት ላይ የፈጸመውም ይህንኑ ነው:: ሕጉ ኃጢአተኛውን ወደ ክርስቶስ ሊያመጣ ቢችልም፣ ኃጢአተኛው ክርስቶስን እንዲመስል ሊያደርግ አይችልም:: ይህንን ሊያደርግ የሚችለው ጸጋ ብቻ ነው::

ወጣቱ ሹም ራሱን በቅዱስ አምላክ ፊት እንደ ተኮነነ ሰው አድርጐ አልተመለከተም:: መታዘዝን በውስጣዊ ባሕርይ ሳይሆን በውጫዊ ተግባራት መለካቱ ስለ እግዚአብሔር ሕግ የጠለቀ አመለካከት እንዳልነበረው ያስረዳል:: ተግባራቱን በተመለከተ እንከን የለሽ መሆኑን ገልጿል (ፊልጵ. 3:6 አንብብ):: ነገር ግን ምኞት ስለነገሠበት ውስጣዊ አመለካከቱ ንጹሕ አልነበረም:: ሁሉንም ትእዛዛት የጠበቀ ቢመስልም፣ የመጨረሻው ትእዛዝ ግን አንቆ ያዘው:: «አትመኝ»! ምኞት አስከፊ ነገር ነው:: ምኞት ስውርና ለመለየት የሚያስቸግር ቢሆንም፣ አንድ ሰው ሌሎችን ትእዛዛት ሁሉ እንዲጥስ ሊያደርግ ይችላል:: «ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና» (1ኛ ጢሞ. 6:10)::

ይህንን የሚመለከት ሰው ሁሉም ነገር አለው ብሎ ሊያስብ ይችል ነበር። ኢየሱስ ግን አንድ ነገር እንደ ጐደለው ተመለከተ። ይኸውም በሕያው እግዚአብሔር ላይ የሚጣል እምነት ነበር። ገንዘብ የእርሱ አምላክ ስለሆነበት፣ ይተማመንበት፣ ያመልከውና ይረካበት ነበር። ግብረገብነቱና መልካም ባሕርዩ ምኞት የነገሠበት ልቡን ይሸፋፍኑ ነበር።

በማርቆስ 10:21 ጌታችን የሰጠው ትእዛዝ ደቀ መዝሙር ለመሆን ለሚፈልግ ሰው ሁሉ የሚሠራ አይደለም። ምክንያቱም ኢየሱስ ለሀብታሙ ወጣት ሹም ሆን ብሎ ያስተላለፈው መልእክት ነበር። ሰውዬው ሀብታም ስለነበር፣ ኢየሱስ ንብረቱን ሸጦ ለድሆች እንዲሰጥ አዘዘው። ሰውዬው ሹም ስለነበር፣ ኢየሱስ መስቀሉን ይዞ እንዲከተለው ጠየቀው። ይህ ለእርሱ የውርደት ተግባር ነበር። ኢየሱስ ለዚህ ሰውዬ የዘላለምን ሕይወት ቢሰጠውም፣ እርሱ ግን ሊቀበለው አልፈለገም። ጣቶችህ ለገንዘብና ገንዘብ ለሚገዛቸው ነገሮች በሚስገበገቡበት ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ስጦታ መቀበሉ አስቸጋሪ ነው። «አዘነ» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል የደመና ማዕበልን ስብስብ ያመለክታል። ሰውዬው ከፀሐይ ወጥቶ ወደ ማዕበሉ ገባ። ደኅንነትን በሩቀ መንገድ ለማግኘት በመፈለጉ አዝኖ ሄደ።

ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ስለ ሀብት በተናገረው ቃል ደነገጡ። ምክንያቱም አብዛኞቹ አይሁዶች ትልቅ ሀብት ከእግዚአብሔር ብዙ በረከት ማግኘትን ያመለክታል ብለው ያስቡ ነበር። ከኢዮብ መልእክት፣ ከክርስቶስና ከሐዋርያት ምሳሌነት ባሻገር፣ ዛሬም ሰዎች ይህንኑ ስሕተት የሙጥኝ ይላሉ። ይህን ወጣት በተመለከተ ግን ሀብቱ የእግዚአብሔር ታላቅ በረከት የሆነውን ዘላለማዊ ሕይወት አስቀርቶበታል። ዛሬም ገንዘብ ሀብታሞች ድሆች፣ ፈተኞች ኋለኞች እንዲሆኑ የማድረግ ተግባሩን ቀጥሏል (1ኛ ቆሮ. 1:26-31 አንብብ)።

ገንዘብ ግሩም ባሪያ ቢሆንም፣ መጥፎ ጌታ ነው። ገንዘብ በሚኖርህ ጊዜ የአመስጋኝነት ልብ ሊኖርህና ለእግዚአብሔር ክብር ልትጠቀምበት ይገባል። ነገር ግን ገንዘብ ጌታህ ከሆነ፣ ተጠንቀቅ! ገንዘብ የማይገዛቸውን ነገሮች ሳታጣ፣ ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ማግኘትህ ክፋት የለውም። የገንዘብ

አሳሳችነት የዚህን ወጣት ልብ በማነቁ የቃሉን መልካም ዘር አግኝቶ ደኅንነትን ሊቀበል አልቻለም (ማቴ. 13:22):: ይህ ሰው አንድ ቀን የሚያጭደው መከራ ምንኛ የከፋ ይሆን!

የጴጥሮስ ምላሽ በልቡ ውስጥ መጠነኛ ችግሮች መኖራቸውን ያመለክታል:: «ምን እናገኝ ይሆን?» (ማቴ. 19:27):: ይህ አሳብ የክርስትና ሕይወትን የንግድ አመለካከት ያንጸባርቃል:: «ሁሉንም ነገር ለጌታ ትተናልና በምላሹ ምን እናገኝ ይሆን?» ይህን የጴጥሮስን አባባል ከሦስቱ የዕብራውያን ሰዎች (ዳን. 3:16-18) እና በኋላ ራሱ ጴጥሮስ ከሰጠው ምስክርነት ጋር አነጻጽር (የሐዋ. 3:6):: «ምን አገኝ ይሆን?» ከማለት «ይህን ያለኝን እሰጥሃለሁ!» እስከ ማለት የተጓዘው ብዙ ርቀት ነው::

ኢየሱስ እርሱን የሚከተል ማንም ሰው በዚህም ሆነ በሚመጣው ሕይወት ጠቃሚ ከሆነው ነገር ምንም እንደማያጣ ለደቀ መዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል:: እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የሚገባውን ሽልማት ይሰጠዋል:: ነገር ግን ልባችን ንጹሕ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን:: የምንኖረው ለክርስቶስና ለወንጌሉ መሆን አለበት (ማር. 8:35 አንብብ):: ከአሥር ዓመታት በፊት የነበረው እውቅ ክርስቲያን አገልጋይ አር. ጂ. ሊቱርኑ፣ «የምትሰጡት አገኛለሁ በሚል አሳብ ከሆነ፣ አታገኙም!» ይል ነበር:: የምንሠዋው ሽልማት ለማግኘት ከሆነ፣ ሽልማቱ ከቶውንም ሊገኝ አይችልም::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንደሚሰደዱ መናገሩንም አስተውለህ አጢን:: ቀደም ሲል በኢየሩሳሌም አይሁዶችና አሕዛብ ምን እንደሚያደርጉበት የተናገረ ሲሆን፣ እነርሱም የድርሻቸውን እንደሚሰደዱ አረጋገጠላቸው:: እግዚአብሔር በረከትን ከስደት ጋር በማመጣጠን በሳል ልጆችን ያፈራል::

ከጠቅላላው ሕዝብ፣ ሀብታሙ ሹም የመጀመሪያውን ስፍራ ሲይዝ፣ ምስኪን ደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻውን ስፍራ ይዘዋል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ነገሮችን የሚመለከተው ከዘላለም እይታ አንጻር ነበር:: ስለሆነም፣ ፊተኞቹ ኋለኞች፣ ኋለኞቹ ፊተኞች ሆኑ:: በራሳቸው እይታ የመጀመሪያ የሆኑት በእግዚአብሔር ዓይኖች ኋለኞች ይሆናሉ:: በራሳቸው ዓይን የመጨረሻ የሆኑት

እንደ ሠራተኞች ይሸለማሉ:: ይህ ለእውነተኛ ደቀ መዛሙርት ምንኛ ታላቅ ማበረታቻ ነው!

## 4. ባሮች ገዥዎች ይሆናሉ (ማርቆስ 10:32-45)

አሁንም ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ነበር:: ማርቆስ ጌታችን ወደ ጎልጎታ የሚያደርገውን ጉዞ በሚተርክበት ጊዜ ከኢሳይያስ 42-53 ስለተጠቀሱት «የባሪያው መዝሙሮች» በሰፊው ለማሰላሰል ተገድዶ ነበር:: «ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛልና ስለዚህ አልታወክሁም ስለዚህም ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ አድርጌዋለሁ፣ እንዳላፍርም አውቃለሁ» (ኢሳ. 50:7):: ጌታችን ወደ ጎልጎታ የሚያደርገውን ጉዞ ስንመለከትና ይህንንም ያደረገው ለእኛ መሆኑን ስንገነዘብ፣ ልባችን ለምስጋና ሊነሣሣ ይገባል::

ተከታዮቹ እንዲህ ዓይነት ዱብዕዳ በድንገት ስለደረሰባቸው በፍርሃትና ግራ መጋባት መዋጣቸው ሊያስደንቀን አይገባም:: ስለ ሞቱ በተናገረ ቁጥር ግራ መጋባታቸው ይጨምራል:: በመጀመሪያ ሁለት ማስታወቂያዎች (ማር. 8:31፤ 9:31) ኢየሱስ ስለሚከሰተው ነገር የተናገረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የመስቀል ላይ ሞቱ በቅድስቲቱ የኢየሩሳሌም ከተማ እንደሚፈጸም ይነግራቸዋል:: በዚህ በሦስተኛው እወጃ ወቅት አሕዛብ በምርመራውና በሞቱ ውስጥ ምን ዓይነት ሚና እንደሚጫወቱ ተናግሯል:: ለአራተኛ ጊዜ፣ ከሞት እንደሚነሣ ነግሯቸዋል (9:9ን አንብብ):: ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እውነቱን ቢነግራቸውም እነርሱ ግን ለመረዳት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም::

ጌታችን እንደሚሞት እየነገራቸው ያዕቆብና ዮሐንስ ከዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ መጠየቃቸው አሳፋሪ ነገር ነው:: እነ ያዕቆብና እናታቸው እንዴት ስሜተ ደንዳናና ራስ ወዳዶች ሊሆኑ ቻሉ? ጴጥሮስ መጀመሪያ ጌታ እንደሚሞት ሲናገር ክርክር ገጥሞ ነበር:: ከሁለተኛው ጊዜ ጀምሮ ደቀ መዛሙርቱ ከመካከላቸው ማን ታላቅ እንደሆነ በመከራከር ነበር ምላሽ የሰጡት (ማር. 9:30-34):: እነዚህ ሰዎች የመስቀሉን ትርጉም ለማየት የታወሩ ይመስላል::

በመሠረቱ፣ ሰሎሜና ሁለት ልጆቿ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በወደፊት መንግሥቱ ውስጥ በአሥራ ሁለት ዙፋናት ላይ እንደሚቀመጡ በመግለጽ የሰጠውን የተስፋ ቃል ከእጃቸው ለማስገባት እየሞከሩ ነበር:: (ማቴ. 19:28ን አንብብ:: ማርቆስ በቀዳሚነት የጻፈው ለሮማውያን በመሆኑ ይህንን የተስፋ ቃል አላካተተውም::) ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚሞት ስለተናገረ፣ ተስፋውን ለመቀበል ብዙ እምነት ጠየቃቸው:: ሦስቱ ተስማምተው ስለጠየቁት (ማቴ. 18:19) እና ጌታም የማበረታቻ ቃል ስለሰጣቸው፣ ጥያቄያቸውን የማይቀበልበት ምክንያት አልነበረም::

ነገር ግን አንድ ችግር ነበር:: የሚጸልዩት የራስ ወዳድነት ጸሎት ነበር:: እግዚአብሔር ደግሞ የራስ ወዳድነትን ጸሎት አይመልስም (ያዕ. 4:2-3):: ይህን ቢያደርግ እንኳ ዓላማው እኛን ሥርዓት ማስያዝና እንዴት እንደ ፈቃዱ እንደምንጸልይ ማስተማር ነው የሚሆነው [መዝ. (106):15፤ 1ኛ ዮሐ. 5:14-15]:: ያዕቆብ፣ ዮሐንስና ሰሎሜ የጸሎትን መልስ ለማግኘት ዋጋ መክፈል እንደሚያስፈልግ አልተገነዘቡም ነበር:: ኢየሱስ ጥያቄያቸውን ለማሟላት መከራ መቀበልና መሞት ያስፈልገው ነበር:: ዙፋኖችን በነፃ እንዲያገኙ ለማስቻል እንዲህ ዓይነት ታላቅ ዋጋ መክፈል ያለበት ለምንድን ነው? እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚቻለው በዚህ መንገድ ነውን?

ኢየሱስ መጭ መከራውንና ሞቱን ጽዋን ከመጠጣት (ማር. 14:32-36) እና ጥምቀትን ከመጠመቅ ጋር አነጻጽሯል [ሉቃስ 12:50፤ በተጨማሪም መዝ. (41):7፤ (69):2፣15 አንብብ]:: ይህ እጅግ ከባድ ተሞክሮ ቢሆንም፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር መከራውንና ሞቱን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል! በኋላ የድርሻቸውን ጥምቀትና ጽዋ ስለተቀበሉ፣ በዚህ ጊዜ የሚናገሩትን አያውቁም ነበር:: ያዕቆብ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል በቀዳሚነት ሲሠዋ (የሐዋ. 12:1-2)፣ ዮሐንስም ከባድ ስደትን ቀምሷል::

ጸሎታቸው ከሰማያዊ ሳይሆን ከምድራዊ ጥበብ የመጣ በመሆኑ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት በማስቆጣት በቡድኑ ውስጥ አለመስማማትን ፈጥረዋል (ያዕ. 3:13-4:1

አንብብ):: ስለ ጉዳዩ ሳያስቡ ጌታን በመጠየቃቸው እንዳዘኑ የሚያጠራጥር አይሆንም:: አሁንም ኢየሱስ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ «ትልቅ ሰው» ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሊያስተምራቸው ሞከሯል (ማር. 9:33-37 አንብብ)::

እንደ ዛሬዎቹ ሰዎች ደቀ መዛሙርቱ የተሳሳቱ ምሳሌዎችን የመከተል ስሕተት ፈጽመው ነበር:: የኢየሱስን አርአያነት ከመከተል ይልቅ በሥልጣናቸውና በሹመታቸው የሚፈነጩትን የሮም ባለሥልጣናትን ክርክርና ሥልጣን ያደንቁ ነበር:: ታላቅነትን መሻት መጥፎ ባይሆንም፣ ለታላቅነት ለምንሰጠው ፍችና ታላቅነትን ለምንፈልግበት ዓላማ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል:: ኢየሱስ፣ «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፣ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን» ብሏል (10:43-44)::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተቀመጠው አሠራር አንድ ሰው ወደ ገዥነቱ ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት በመጀመሪያ በባርነት ማገልገል እንዳለበት የሚያስረዳ ነው:: ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ዳዊት፣ ጢሞቴዎስና ጌታችን ራሱ በዚህ ሂደት አልፈዋል (ፊልጵ. 2:1-11):: ትእዛዛትን መቀበል ካልተማርን፣ ትእዛዛትን የመስጠት መብት የለንም:: አንድ ሰው ባለሥልጣን ከመሆኑ በፊት፣ ከባለሥልጣናት ሥር መሥራት ምን እንደሚመስል ማወቅ አለበት:: ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ የደኅንነት ሥራውን ለማከናወን ይህንኑ አሠራር ከተከተለ፣ እኛም ከዚህ የተለየ አሠራር ልንከተል አንችልም::

## 5. ድሆች ይበለጽጋሉ (ማርቆስ 10:46-52)

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሩሳሌም ሠላሳ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ወደምትገኘው ኢያሪኮ በሚሄዱበት ወቅት ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ ብዙ ሰዎች ተከተሏቸው:: ኢያሪኮ በመባል የሚታወቁት ሁለት ከተሞች ናቸው:: እነርሱም አሁን የፈራረሰችው አሮጌይቱ ኢያሪኮና ታላቁ ሄሮድስና ተተኪዎቹ እጅግ ውድ የክረምት ቤተ መንግሥት ከሠሩበት ስፍራ አንድ ተኩል ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኘ ው አዲሲቱ ከተማ ናቸው:: ይህ በማርቆስ 10:46 እና በሉቃስ

18:35 መካከል የተከሰተ የሚመስለውን ግጭት ለማብራራት ሊረዳ ይችላል።

ከመንገዱ ጥግ የሚቀመጡ ሁለት ዓይነ ስውራን ለማኞች ነበሩ (ማቴ. 20:30)። ከእነዚህም አንዱ በርጤሜዎስ ይባል ነበር። ከሁለቱ መካከል ጮክ ብሎ የሚናገረው እርሱ በመሆኑ ማርቆስም ሆነ ሉቃስ በእርሱ ላይ ትኩረት አድርገዋል። ለማኞቹ ፈዋሹ የናዝሬቱ ኢየሱስ እያለፈ መሆኑን ሲሰሙ የምሕረት ረድኤቱን አግኝተው ለመፈወስ ይችሉ ዘንድ በተቻላቸው ዓቅም ትኩረቱን ለመሳብ ጣሩ።

መጀመሪያ ሕዝቡ ዝም ሊያሰኟቸው ሞከሩ። ነገር ግን ኢየሱስ ቆሞ ካስጠራቸው በኋላ ግን ሕዝቡ ለማኞቹን ያበረታቷቸው ጀመር። ችግር የደረሰባቸው ሰዎች ሕዝቡ ከኢየሱስ እንዲያርቃቸው አይፈቅዱም (ማር. 5:25-34 አንብብ)። በርጤሜዎስ ጠልፎ እንዳይጥለው ልብሱን ወርውሮ ወደ ጌታ ሮጠ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ የበዓል ተጓዦች ወይም ደቀ መዛሙርት እንደረዱት አይጠረጠርም።

«ምን እንዳደረግልህ ትፈልጋለህ?» የሚል ጥያቄ ለዓይነ ስውር ሰው ማቅረብ እንግዳ ነገር ይመስላል። (ጌታ ለያዕቆብ፣ ለዮሐንስና ለሰሎሜም ያቀረበው ይህንኑ ጥያቄ ነበር። ቊ. 36)። ኢየሱስ በርጤሜዎስ ራሱንና እምነቱን እንዲገልጽ ዕድል ሊሰጠው ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ ምን ሊያደርግለት እንደሚችል ነበር ያመነው?

በርጤሜዎስ ኢየሱስን የጠራው «ጌታ» በማለት ነበር። በርጤሜዎስ የተጠቀመው «ረቡኒ» የሚለውን ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም፣ «የእኔ ጌታ፣ የእኔ መምህር» የሚል ነው። በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስን በዚህ ስም የጠራችው ሌላዋ ሴት ማርያም ብቻ ነች (ዮሐ. 20:16)። ለማኙ ኢየሱስን ሁለት ጊዜ «የዳዊት ልጅ» እያለ ጠርቶት ነበር። ይህ ብሔራዊ የመሢሕነት መጠሪያ ሲሆን፣ «ረቡኒ» የሚለው የግል እምነት መግለጫ ነው።

ማቴዎስ ኢየሱስ በርኅራኄ ተነሣሥቶ የለማኞቹን ዓይኖች ዳስሶ እንዳበራ ገልጿል (20:34)። ለማኞቹ ከተፈወሱ በኋላ

ለኢየሱስ ምስጋናቸውን ለመግለጽ ለበዓል ከሚሄደው ሕዝብ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዙ ጀመር:: በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የተመዘገበው የመጨረሻው ተአምር ይህ ሲሆን፣ ይህም ከማርቆስ «የባሪያ» ጭብጥ ጋር ይጣጣማል:: መከራን የሚቀበል የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መስቀሉ እየሄደ ሳለ ሁለት ዓይነ ስውር ለማኞችን ለማገልገል ከመንገድ ላይ ቆሟል:: አቤት ምን ዓይነት ፍቅር፣ ምን ዓይነት ምሕረትና ምን ዓይነት ጸጋ ነው !

# 9

# የእግዚአብሔር ባሪያ በኢየሩሳሌም

## ማርቆስ 11:1-12:44

በፋሲካ ወቅት ኢየሩሳሌም ለአይሁዶች የደስታ ከተማ ለሮማውያን ግን የስጋት ከተማ ነበረች። በሺዎች የሚቆጠሩ አገር ወዳድ አይሁዶች ከዓለም ዙሪያ ሁሉ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ይገባሉ። በዚህ ጊዜ ልባቸው በደስታና በብሔራዊ ፈንጠዚያ ይሞላል። በዚህ የበዓል ወቅት የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ቊጥር ከሦስት እጥፍ በላይ ስለሚያድግ የሮም ወታደራዊ ክፍሎች በተጠንቀቅ ላይ ይሆናሉ። በዚህ ወቅት አንዳንድ ቀናዒ አይሁዳውያን የሮም ባለሥልጣናትን ለመግደል ሊሞክሩ ወይም ሁከት ሊያነሣሡ ይችላሉ። በተለያዩ የአይሁድ ሃይማኖት ቡድኖች መካከልም ክርክሮች ይነሡ ነበር።

ከከተማዪቱ ቅጥር ውጭ ሊሰቀል አንድ ሳምንት ያህል የቀረው የእግዚአብሔር ባሪያ የመጣው ወደዚሁ ሁኔታ ነበር። በዚህ ክፍል፣ የእግዚአብሔር ባሪያ በሦስት የተለያዩ የሥልጣን ሚናዎች ውስጥ ሲያገለግል እንመለከታለን።

## 1. ባሪያው - ንጉሥ (ማርቆስ 11:1-11)

ኢየሱስ በሄደበት መንገድ አንድ መንገደኛ መጀመሪያ ወደ ቢታንያ መድረስና ከዚያም ከኢየሩሳሌም ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ወደምትርቀው ቤተፋጌ መድረስ ይችል ነበር። ይህ ስፍራ ከባሕር ወለል ወደ 792 ሜትር ከፍ ብሎ የሚገኝ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ሆኖ ቅድስቲቱን ከተማ በግሩም ሁኔታ መመልከት ይቻላል። በዚህ ሰዓት ጌታችን ከዚህ በፊት ያላደረገውንና ሌሎችም እንዳያደርጉት ያስጠነቅቅ የነበረውን ነገር ለማድረግ ተዘጋጅቶ ነበር። ይኸውም ተከታዮቹ እርሱን በአደባባይ እንዲያከብሩት ማድረግ ነበር።

ኢየሱስ ለዚሁ ዝግጅት የፈለገውን ውርንጫ እንዲያመጡለት ሁለት ደቀ መዛሙርቱን ወደ ቤተ ፋጌ ላከ። ዛሬ አብዛኞቹ ሰዎች አህያን የተዋረደች ጭነት ተሸካሚ እንስሳ አድርገው

ይመለከቷታል፡፡ በዚያን ዘመን ግን ለንጉሥ መቀመጫ እንደምትመች እንስሳ ትታይ ነበር (1ኛ ነገ. 1:33)፡፡ ጌታችን በዘካርያስ 9:9 የሚገኘውን መሢሐዊ ትንቢት ለመፈጸም ይህችን ውርንጫ ማግኘት ያስፈልገው ነበር፡፡ ማርቆስ በቀዳሚነት የሚጽፈው ለአሕዛብ አንባብያን በመሆኑ ይህን ጥቅስ አልጠቀሰውም፡፡

ኢየሱስ ይህን ትንቢት በመፈጸሙ ሁለት ነገሮችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ (1) የእስራኤል ንጉሥና መሢሕ መሆኑን አውጇል፡፡ እንዲሁም፣ (2) ሃይማኖታዊ መሪዎችን ሆን ብሎ ተፋልሟቸዋል፡፡ ይህም ለእርሱ መያዝ፣ መመርመርና መሰቀል ምክንያት የሆነውን ሤራ ጠነሰሰ፡፡ የአይሁድ መሪዎች በበዓል ሰሞን ላያስሩት ቢወስኑም፣ እግዚአብሔር ግን ያቀደውን ፈጸመ፡፡ የእግዚአብሔር በግ በፋሲካ ዕለት መሞት ነበረበት፡፡

በዓሉን ለማክበር ከመጡት አይሁዶች በርካታ አገር ወዳድ ዜጎች በጌታ ስም የመጣውን የዳዊት ልጅ ንጉሥነት በሚያውጀው የአደባባይ ትዕይንት ላይ በተሟሟቀ ስሜት ተሳተፉ፡፡ ከገሊላ የመጡትና የአልዓዛርን ከሞት መነሣት የተመለከቱት ሰዎች በትዕይንቱ ላይ ዋንኛ ተዋንያን ነበሩ (ዮሐ. 12:12-18)፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ ሳምንት በፊት «ሆሣዕና!» ሲሉ የነበሩት እነዚያው ሰዎች በስቅለት ዕለት «ስቀለው!» ሲሉ ጮኹ ሲባል ሰምተህ ይሆናል፡፡ ይህ ግን እውነት አይደለም፡፡ ኢየሱስ እንዲሰቀል የገፋፉት ሰዎች በአመዛኙ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ የገሊላ ሰዎች ግን ለኢየሱስ አገልግሎት ፍቅር ነበራቸው፡፡

በእስራኤል አገር ለንጉሥ አቀባበል በሚደረግበት ጊዜ፣ ሰዎች ልብሶቻቸውንና የዘንባባ ዝንጣፊዎችን ከመንገድ ላይ የማንጠፍ ልማድ ነበራቸው (2ኛ ነገ. 9:13)፡፡ «ሆሣዕና» የሚለው ቃል «አሁን አድን» የሚል ፍች ያለው ሲሆን፣ ምንጩም መዝሙር (118):25-26 ነው፡፡ ኢየሱስ ከመዝሙረ ዳዊት መሢሐዊ ክፍል እየጠቀሱ መሆናቸውን እያወቀ [መዝ. (118):22-23ን ከማቴ. 21:42-44 እና የሐዋ. 4:11 ጋር አስተያይ]፣ ትክክለኛ የሆነውን ጩኸታቸውን እንዲቀጥሉ ፈቀደላቸው፡፡ ይህን በማድረጉም የዳዊት ልጅና የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን አረጋግጦላቸዋል፡፡

ሮማውያን ይህንን የአደባባይ ትርኢት በሚመለከቱበት ጊዜ ምን ያስቡ ነበር? ሮማውያን እኮ በዛን ዘመን በበዓላትና በአደባባይ ትዕይንቶች በአሰላለፍ የተካኑ ነበሩ:: እኛ ይህንን ክስተት «በድል የመግባት ትዕይንት» እንላለን:: ሮማውያን ግን በፍጹም እንደዚያ አይሉም:: መንግሥታዊ የሮማውያን ድል በዓል ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነበር:: አንድ የሮም ጄኔራል ጠላቱን ደምስሶ በሚመለስበት ጊዜ ታላቅ መንግሥታዊ የአቀባበል በዓል ይደረግለት ነበር:: በበዓሉም ላይ ድሉን የሚያረጋግጡለትን ምርኮኞችና የሚዳይ ሽልማቶቹን ያሳያል:: ድል ነሺው ጄኔራል በወርቃማ ሰረገላ ላይ ተቀምጦ በከተማ በሚያልፍበት ጊዜ ካህናት ለክብሩ ዕጣን ያጥናሉ፤ ሰዎች ስሙን እየጠሩ ያመሰግኑታል:: ትዕይንቱ ከፍጻሜ የሚደርሰው ሕዝቡ የጦር ምርኮኞቹ ከአራዊት ጋር ሲፋለሙ እየተመለከቱ በሚዝናኑበት ስፍራ ነበር:: «የሮማውያን ድል» እንዲህ ያለ ነበር::

የጌታችን «ድል» የሮማውያንን ባይመስልም፣ ድልነቱ ግን ያው ነበር:: ድሉ መንፈሳዊ በመሆኑ ቢለይም፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቅቡዕ ንጉሥና አዳኝ ነበር:: አንድ የሮም ጄኔራል የድል አድራጊነትን ደረጃ ለማግኘት ቢያንስ 5,000 ጠላቶችን መግደል ነበረበት:: የጌታ ወንጌል ደግሞ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ 5,000 ያህል አይሁዶችን «ማርኮ» ሕይወታቸውን የለወጠ ነበር (የሐዋ. 4:4):: የክርስቶስ ድል ፍቅር በጥላቻ ላይ፣ እውነት በስሕተት ላይና ሕይወት በሞት ላይ የነገሠበት ክስተት ነበር::

ኢየሱስ በቀጣዩ ዕለት የሚመለስበትን ቤተ መቅደስ ከተመለከተ በኋላ፣ ከከተማዪቱ ወጥቶ በቢታንያ አደረ:: ቢታንያ የተረጋጋችና ጸጥ ያለች ከተማ ነበረች:: ከፊታቸው ለሚጠብቃቸው ከባድ ሳምንት ያዘጋጃቸው ዘንድ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲጸልይ ያደረው አለምክንያት አልነበረም::

## 2. ባሪያው - ፈራጅ (ማርቆስ 11:12-26)

ጌታ በለሲቱን መርገሙና ቤተ መቅደሱን ማንጻቱ የእስራኤልን ሕዝብ አሳዛኝ መንፈሳዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ተምሳሌቶች ነበሩ:: እስራኤል ብዙ ዕድሎች የተሰጧት አገር ብትሆንም፣ ከውጭ

ፍሬ አልባ (በለሲቱ)፣ ከውስጥ ደግሞ ምግባረ ብልሹ (ቤተ መቅደሱ) ነበረች። ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ የፍርድ እርምጃ ባይወስድም (ዮሐ. 3:17)፣ እግዚአብሔር ከዚህ ውጭ አማራጭ የሚያጣባቸው ጊዜ ግን ይመጣል (ዮሐ. 12:35-41)።

*የበለስ ዛፍ መረገም* (11:12-14፣ 20-26)። የበለስ ዛፍ በመጋቢት ወይም ሚያዝያ ቅጠሉን ያቈጠቍጥና በሰኔ ፍሬ ያፈራል። ከዚያም በነሐሴ ሁለተኛውን ሌላ ፍሬ፣ በመስከረም ደግሞ የሦስተኛውን ዙር ፍሬ ይሰጣል። ስለሆነም፣ ቅጠል ያለው በለስ ፍሬ እንዳለው ይታወቃል። ምንም እንኳ ፍሬው ካለፈው ወቅት «የተረፈ» ሊሆን ቢችልም። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ በልዩ እውቀት አለመመራቱ አስገራሚ ነው። ወደ ዛፏ ሄዶ ፍሬ እንዳላት ወይም እንደሌላት ማረጋገጥ አስፈልጐት ነበር።

ዛፍ የማጠውለግ ኃይል ካለው በዚያው ኃይል ለምን ፍሬ እንድታፈራ ለማድረግ አልፈለገም? እሪያዎቹን ከማስመጡ በተጨማሪ (5:13)፣ ጌታችን ተፈጥሮን የሚጐዳ ተአምር ሲሠራ ይህ ሁለተኛው ነው። ይህንንም ያደረገው ለእኛ ሁለት ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማስተማር ነው።

በመጀመሪያ፣ ስለ *ውድቀት* ሊያስተምረን ፈልጓል። እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን አልቻለችም ነበር። በብሉይ ኪዳን የበለስ ዛፍ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የተያያዘች ናት (ኤር. 8:13፤ ናሆም 3:12፤ ሆሴዕ 9:10)። ጌታችን እንደ ረገማት የበለስ ዛፍ ሁሉ እስራኤል «ከቅጠል ሌላ ምንም» አልነበራትም። በለሲቱ «ከሥሯ» ጀምሮ እንደ ደረቀች አጢን (ማር. 11:20)። ከሦስት ዓመታት በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ከዛፏ ሥር ምሳር ቢያስቀምጥም (ማቴ. 3:10)፣ የሃይማኖት መሪዎች ሊሰሙት አልፈለጉም ነበር። አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በመንፈሳዊ ሕይወቱ «መድረቅ» የሚጀምረው ከሥሩ ነው። ሰዎች የሚያደንቁትን ብዙ ቅጠል ሊመለከቱ ቢችሉም፣ ደስ የሚሰኙ ባቸውን ፍሬዎች ሊያገኙባቸው አይችሉም።

ምናልባትም ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ተአምር ኢየሱስ ከጥቂት ወራት በፊት ከሰጠው ምሳሌ ጋር በማያያዝ (ሉቃስ 13:1-9)፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሚያወርደውን ፍርድ

በግልጽ ሳይመለከቱ አልቀሩም:: በተጨማሪም እግዚአብሔር ከሕዝቡ «በኩራቱን» እንደሚፈልግ የሚናገረውን የትንቢተ ሚክያስ 7:1-6 ትንቢት ይሆናል:: ክርስቶስ አሁንም ከሕዝቡ ፍሬ ይፈልጋል:: ፍሬ አልባ ሆኖ መገኘቱ ኃጢአት ነው (ዮሐ. 15:16):: ቅጠል ብቻ ይዘን ስንቀመጥ መንፈሳዊ ሥሮቻችንን በጥንቃቄ መኰትኰት አለብን::

ኢየሱስ ስለ እምነት ሊያስተምረን በመፈለጉ ጭምር ነበር ይህን ተአምር የፈጸመው:: በማግሥቱ ደቀ መዛሙርቱ የጠወለገችውን ዛፍ ሲመለከቱ፣ ኢየሱስ «በእግዚአብሔር እመኑ» ሲል ተናግሯል:: ይህም «ባለማቋረጥ በእግዚአብሔር ተማመኑ፤ በእርሱ ላይ የመደገፍ ባሕርይ ይኑራችሁ» ማለት ነው:: በአይሁዶች ንጽጽራዊ ምሳሌ፣ ተራራ ከሰው መንገድ ላይ የቆመውን ጠንካራና የማይነቃነቅ ነገር ያመለክታል (ዘካ. 4:7):: እንዲህ ዓይነቱን ተራራ መናድ የሚቻለው በእግዚአብሔር በመተማመን ነው::

ኢየሱስ ስለ ጸሎት የሰጠው ትምህርት ይኼ ብቻ ስላልሆነ፣ ከተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ነጥለን ልናወጣው አይገባም:: ጸሎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ሊጸለይ ይገባል (1ኛ ዮሐ. 5:14-15)፤ የሚጸልየው ግለሰብ ደግሞ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መሆን አለበት (ዮሐ. 15:7-14):: ጸሎት ችግር በሚደርስብን ጊዜ የምንወስደው የድንገተኛ አደጋ እርምጃ አይደለም:: እውነተኛ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው የማያቋርጥ ተግባቦትና አምልኮ አካል ነው::

ማርቆስ 11:24ን፣ «በብዙ ትጋትና በእምነት ብትጸልዩ፣ እግዚአብሔር የምትጠይቁትን ሁሉ ለመስጠት ይገደዳል» ብለን ልንተረጉመው አይገባም:: እንዲህ ዓይነቱ እምነት በእግዚአብሔር ላይ የሚጣል እምነት ሳይሆን፣ በእምነት ላይ የሚጣል እምነት ወይም በስሜት ላይ የሚጣል እምነት ነው:: እውነተኛ እምነት በቃሉ ላይ የተመሠረተ ነው (ሮሜ 10:17፤ ዮሐ. 15:7):: ቃሉ ደግሞ ፈቃዱን ይገልጽልናል:: የጸሎት ዓላማ የሰውን ፈቃድ በሰማይ ላይ መፈጸም ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ መፈጸም ነው የሚለው አባባል ትክክል ነው::

እውነተኛ ጸሎት ይቅርታንና እምነትን ያካትታል:: እግዚአብሔር ጸሎቴን እንዲመልስ ከፈለግሁ በሰማይ ከሚኖረው አምላኬና በምድር ከሚኖሩ ወንድሞቼ ጋር ኅብረት ሊኖረኝ ይገባል (ማቴ. 5:21-26፤ 6:14-15፤ 18:15-35 አንብብ):: «በአቡነ ዘበሰማያት» ጸሎት ውስጥ የመጀመሪያው ሐረግ፣ «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ» እንጂ፣ «አባቴ ሆይ» አይልም:: ክርስቲያኖች የግል ጸሎት ሊያደርጉ ቢችሉም፣ ብቻውን የሚጸልይ ክርስቲያን አይኖርም:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ በረከቱን ለመሻት የሚጣመረው ዓለም አቀፋዊ ቤተሰብ አካል ናቸውና (ኤፌ. 3:14-15):: ጸሎት ሁላችንንም በአንድ ላይ ያስተሳስረናል::

የእግዚአብሔርን በረከት የምናገኘው እርስ በርሳችን ይቅር በመባባላችን አይደለም:: ይቀር ባይው መንፈሳችን ልባችን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል መሆኑንና ፈቃዱን ለመፈጸም መፈለጋችንን ያሳያል:: ይህም እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ እንዲመልስ ያስችለዋል [መዝ. (66):18]:: እምነት የሚሠራው በፍቅር ነው (ገላ. 5:6):: በእግዚአብሔር ላይ እምነት ካለኝ፣ ለወንድሜ ፍቅር ይኖረኛል::

*ቤተ መቅደሱን ማጽዳት* (11:15-19):: ኢየሱስ በመጀመሪያው የፋሲካ ዕለት ጉብኝቱ ቤተ መቅደሱን ያጸዳ ሲሆን (ዮሐ. 2:13-22)፣ ውጤቱ ዘላቂ አልሆነም:: ብዙም ሳይቆይ የሃይማኖት መሪዎቹ ገንዘብ ለዋጮችና ነጋዴዎች ተመልሰው እንዲሠሩ ፈቀዱ:: ካህናትም ከትርፉ የድርሻቸውን ይቀበሉ ነበር:: እነዚህ የንግድ አገልግሎቶች ደግሞ ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም ለሚመጡት አይሁዶች አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የታሰቡ ነበሩ:: ከሩቅ ስፍራ የሚመጣ አይሁዳዊ መሥዋዕቱን ይዞ ቢመጣና የሆነ ግድፈት ቢገኝበትስ? የገንዘብ ለውጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለዋወጥ ነበር:: ስለሆነም የውጭ አገር ገንዘብ የሚለውጡ ነጋዴዎች ለራሳቸው ብዙ ትርፍ ቢያገኙም፣ ከውጭ ለሚመጡ ሰዎች እገዛ እያደረጉላቸው ነበር:: ለእነርሱ ስለ ንግዱ እንቅስቃሴ ምክንያት መስጠቱ ቀላል ነበር::

«የሃይማኖት ገበያው» የሚደራው በአሕዛብ አደባባይ ነበር:: ይህም አይሁዶች ተግተው ስለ እግዚአብሔር ሊመሰክሩ

የሚገባቸው ስፍራ ነበር። አንድ አሕዛብ ወደዚያ አደባባይ ደርሶ በእውነተኛ ሃይማኖት ስም የሚካሄደውን ንግድ ቢመለከት፣ የሚያስተምሩትን ለማመን የሚፈልግበት ምክንያት አይኖረውም። አይሁዶች በቤተ መቅደሳቸው ውስጥ የእንጨትና የድንጋይ ጣዖታት እንዲኖሩ አይፈቅዱም ነበር። ነገር ግን ተመሳሳይ ጣዖታትን በዚሁ ስፍራ እያካሄዱ ነበር። የአሕዛብ አደባባይ የጸሎት ስፍራ ሲሆን ሲገባው፣ የንግድ ቦታ ሆነ።

ማርቆስ ርግብ ሻጮችን ሆን ብሎ ጠቅሷቸዋል። ርግብ ድሆች ከሚያቀርቧቸው መሥዋዕቶች አንዱ ነበር (ዘሌዋ. 14:22)። ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን በቤተ መቅደስ ለእግዚአብሔር አሳልፈው በሰጡት ጊዜ ያቀረቡት የርግብ መሥዋዕት ነበር (ሉቃስ 2:24)። በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚካሄደው ንግድ በድሆች ላይ ጫና ፈጥሮባቸው ነበር። ይህ ራሱ ለድሆች የሚራራውን የጌታ ኢየሱስን ልብ ሊያሳዝን ይችል ነበር (ማር. 12:41-44 አንብብ)።

ኢየሱስ ያከናወነውን ተግባር ለመደገፍ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጠቅሷል ኢሳ. 56:7 እና ኤር. 7:11። በተመሳሳይ ጊዜ፣ የሃይማኖት መሪዎችን ኃጢአት አጋልጧል። አይሁዶች ቤተ መቅደሱ በቀዳሚነት የመሥዋዕት ማቅረቢያ ስፍራ እንደሆነ ሲያስቡ፣ ኢየሱስ ግን የጸሎት ስፍራ መሆኑን አመልክቷል። እውነተኛ ጸሎት በራሱ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው [መዝ. 141):1-2]። መሪዎቹ በሕጐችና ደንቦች የተሞሉትን ልማዳዊ አመለካከቶች ሲያስፋፉ፣ ኢየሱስ ግን የአይሁድን ሃይማኖት በመንፈሳዊ እይታ አጕልቷል።

ካምፕቤል ሞርጋን እንደሚሉት፣ «የሌቦች ዋሻ» ሌቦች ለመደበቅ የሚሮጡበት ስፍራ ነው። የካህናት አለቆችና ጸሐፍት ኃጢአታቸውንና ግብዝነታቸውን «ለመሸፋፈን» ቤተ መቅደሱን ይጠቀሙ ነበር። ኢሳይያስም (1:10-17) ሆነ ኤርምያስ (7:1-16) የአካላዊ ቤተ መቅደስ መኖር ለእግዚአብሔር በረከት ዋስትና እንደማይሰጥ ገልጸዋል። ዋናው ነገር ሕዝቡ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከልባቸው የሚፈጽሙት ተግባር ነበር። ሕዝቡ ለነቢያቱ ማስጠንቀቂያ ጆሮ ያልሰጡ ሲሆን፣ የጌታንም ማስጠንቀቂያ እንዲሁ በቸልታ ያልፉታል።

የካህናት አለቆችና ጸሐፍት ጌታችን ስላከናወናቸው ተግባራት በሰሙ ጊዜ እንዴት አድርገው እንደሚያስሩት ምክንያት ይፈልጉ ጀመር (ማር. 14:1-2 አንብብ):: ይሁዳ ደግሞ በዚህ በኩል ሊተባበራቸው ፈቀደ:: የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችን ኃጢአት ለመኮነን ከመጣደፋችን በፊት ምናልባት ወንጌሉን እየሸቃቀጥን እንደሆነ ለማመልከት የራሳችንን አገልግሎት ልንገመግም ይገባል:: በማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉ የማያምኑ ሰዎች ሕንጻዎቻችንን እንደ ጸሎት ቤቶች ይመለከቷቸዋልን? ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ተቀባይነት ያገኛ ሉን? አባሎቻችን እሑድ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጐርፉት ኃጢአታቸውን ለመሸፈን ነውን? ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንሄደው ዝናችንን ለመጠበቅ ነው ወይስ እግዚአብሔርን ለማምለክና ከፍ ከፍ ለማድረግ? ጌታ ኢየሱስ ወደ ጸሎት ቤታችን ቢመጣ ዛሬ ምን ዓይነት ለውጦችን ያደርግ ይሆን?

## 3. ባሪያው - ነቢይ (ማርቆስ 11:27-12:44)

ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲያገለግል የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች በብዙ ጥያቄዎች ሊያጠምዱት ሞከሩ:: ከጥያቄዎቻቸው አራቱን ከመለሰ በኋላ ለዘለቄታው ዝም የሚያሰኛቸውን አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው::

*የሥልጣን ጥያቄ* (11:27-12:12):: የሕግ ጠባቂዎች በመሆናቸው የአይሁድ ሸንጐ አባላት ከእግዚአብሔር ተልኬአለሁ የሚል ሰው ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ ሁኔታውን የመመርመር መብትና ኃላፊነት ነበራቸው:: በኢየሱስም ላይ ያደረጉት ይህንኑ ነበር (ዘዳግ. 18:15-22):: ይሁንና፣ እነዚህ ሰዎች የተከፈተ አእምሮና ቀና ልብ አልነበራቸውም:: እውነትን ከመፈለግ ይልቅ እርሱን ለማጥፋት የሚያስችላቸውን መረጃ ነበር የሚሹት (ማር. 11:18):: ኢየሱስ ምን እንደሚፈልጉ ስለሚያውቅ ጥያቄያቸውን በጥያቄ በመመለስ ግብዝነታቸውን ይፋ አወጣ::

ለምን ይሆን ወደ መጥምቁ ዮሐንስ የመለሳቸው? ለአንድ በጣም ጠቃሚ ምክንያት:: ይኸውም እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠንን እውነት ካልተቀበልን ሌላ አዲስ እውነት

እንደማይገልጥልን ለማሳየት ነው። ዮሐንስ 7፡17 ይህንን መሠረታዊ እውነት፣ «ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፣ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል» ሲል ገልጿል። የብሪታኒያ ሰባኪ የሆኑት ኤፍ. ደብልዩ. ሮበርትሰን እንደሚሉት፣ «መታዘዝ የመንፈሳዊ እውቀት ምንጭ ነው»። የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ዮሐንስ ያስተማራቸውን እውነት አልተቀበሉም ነበር። እንግዲህ እግዚአብሔር ተጨማሪ ቃል የሚልክላቸው ለምን ይሆን? ዮሐንስ የመጣው መሢሑን ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ ስለነበር፣ የዮሐንስን መልእክት ተቀብለው ቢሆን ኖሮ፣ ክርስቶስን በደስታ በተቀበሉት ነበር።

የአይሁድ መሪዎች በገዛ እጃቸው አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። የሚፈልጉት «እውነተኛውን ወይም ትክክለኛውን ነገር ሳይሆን፣ መከላከያ የሚሆናቸውን አሳብ ብቻ ነበር። ይህ ሁልጊዜም ግብዞችና ብዙኃኑን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች የሚይዙት አቋም ነው። መጥምቁ ዮሐንስም ሆነ (ማቴ. 11፡7-10) ጌታ ኢየሱስ (ማር. 12፡14) ይህንን አቋም አልያዙም። ኢየሱስ ግብዝነታቸውን ለመደገፍና ለመቀበል ባይፈልግም፣ ጥያቄያቸውን መልሶላቸዋል። እውነተኛ ለመሆን ፈለገ እንጂ፣ ጥያቄያቸውን ቸል ለማለት አልሞከረም።

የማምለጫ ቀዳዳ ከማግኘታቸው በፊት *ኃጢአቶቻቸው ወዴት እንደሚመሯቸው የሚያሳይ* አንድ ምሳሌ ነገራቸው። ቀደም ሲል መጥምቁ ዮሐንስን ያስገደሉ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሰቀል ሊጠይቁ ተዘጋጅተው ነበር!

የወይን ቦታ ለአይሁዶች የተለመደ የማነጻጸሪያ ምሳሌ ነበር [ኢሳ. 5፡1-7፤ መዝ. (80)፡8-16]። ዘሌዋውያን 19፡23-25 እንደሚለው፣ አንድ ገበሬ እስከ አምስተኛው ዓመት ድረስ የሥራውን ፍሬ መጠቀም አይችልም ነበር። (በርግጥ በዘመኑ የነበሩት አይሁዶች ይህን ትእዛዝ ስለመታዘዛቸው የምናውቀው ነገር የለም።) ባለቤቱ ሕጋዊ መብቱን ለማስከበር፣ ጥቂትም ቢሆን ከጭሰኞቹ ምርት መውሰድ ነበረበት። የወይኑ ሠራተኞች ለባለቤቱ ምንም ነገር ላለመስጠት የፈለጉት የወይን ቦታውን የራሳቸው ለማድረግ ነበር። ባለቤቱም በተከታታይ

መልእክተኞችን የላከው፣ ሥልጣኑንና ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ ነበር።

ማርቆስ 12:2-5 ገበሬዎቹ ፍሬውን ያልበሉባቸውን ሦስት ዓመታት የሚሸፍን ከሆነ፣ ተወዳጁ ልጅ የተላከው በአራተኛው ዓመት ነበር። ይህ ፍሬው ለጌታ የሚሰጥበት ዓመት ነው (ዘሌዋ. 19:24)። ይህም የልጁን መላክ የበለጠ ትርጉም ያለው ያደርገዋል። የወይኑ ሠራተኞች ወራሹን ካስወገዱ፣ ንብረቱ የራሳቸው ይሆን ነበር። ስለሆነም፣ ወራሹን ልጅ ገደሉት (ዕብ. 13:12-13 አንብብ)። ክፉ ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ ነፍስን ለማጥፋት ፈቀዱ (ዮሐ. 11:47-53)።

ኢየሱስ ከዚያ በኋላ፣ «እንግዲህ የወይኑ ጌታ ምን ያደርግ ይሆን?» ሲል ጠየቃቸው። መሪዎቹ መጀመሪያ ጥያቄውን በመመለስ ራሳቸውን ከፋኛ ኮነኑ (ማቴ. 21:41)። ከዚያም ኢየሱስ መልሳቸውን በመድገም እንደማይሻር የዳኛ ውሳኔ አጸናው። ለፍርዱ ይግባኝ ከማለታቸው በፊት መሢሐዊ ምንባብ እንደሆነ የሚያውቁትን መዝሙር (118):22-23ን ጠቀሰላቸው። በድል ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ወቅት ይህንን ክፍል ተመልክተነዋል (ማር. 11:9-10)። «ዓለቱ» ስለ መሢሑ የሚናገር የታወቀ ተምሳሌት ነበር (ዘዳግ. 17:6፤ ዳን. 2:34፤ ዘካ. 4:7፤ ሮሜ 9:32-33፤ 1ኛ ቆሮ. 10:4፤ 1ኛ ጴጥ. 2:6-8)።

*የኃላፊነት ጥያቄ* (12:13-17)። ያጋጠማቸው የጋራ ችግር ጠላቶች የነበሩትን ፈሪሳውያንንና ሄሮዲያኖችን አስተባበራቸው። ሄሮዲያኖች የሄሮድስ ቤተሰቦችና የመግዛት ሥልጣን የሰጣቸውን የሮም መንግሥት ይደግፉ ነበር። ፈሪሳውያን ግን የሄሮድስ ነገድ በዳዊት ዙፋን ላይ ሊቀመጥ እንደማይገባ ያስቡ ነበር። ምክንያቱም ሄሮድስ ኤዶማዊ እንጂ አይሁዳዊ አልነበረም። በተጨማሪም፣ ሮማውያን በይሁዳ ላይ የጣሉትን ተጨማሪ ቀረጥና በአጠቃላይም የሮማውያንን በአገራቸው ውስጥ መኖር ይጠሉ ነበር።

ጊዜያዊው ትብብር ስውር ወጥመድ ለማጥመድ የተደረገ ጥረት ነበር። ኢየሱስ ለጥያቄው የትኛውንም መልስ ቢሰጥ ከሮማውያን ወይም ከሄሮድስ ደጋፊዎች ጋር መጋጨቱ

አይቀርም ነበር:: ኢየሱስ ግን ውይይቱን ከፖለቲካ ወደ መርሕ በመውሰድ ግብዞቹን በራሳቸው ወጥመድ አጠመዳቸው:: የጌታን ምላሽ እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል:--

«የቄሣር ምስል በሣንቲሞቹ ላይ ስላለ ሣንቲሞቹ የሚሠሩት በእርሱ ሥልጣን መሆን አለበት:: እነዚህን ሣንቲሞች የምትይዙትና የምትጠቀሙት ዋጋ አላቸው ብላችሁ ስለምታስቡ ነው:: ይህም የቄሣርን ሥልጣን መቀበላችሁን ያሳያል:: አለዚያ ገንዘቡን አትጠቀሙም ነበር:: ነገር ግን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችሁን አትርሱ:: ስለሆነም፣ ለእርሱም መገዛት ይኖርባችኋል::»

በአንድ ወቅት የሮሜ 13 አተረጓጐሜን ከተቃወመ ግለሰብ ጋር የደብዳቤ ልውውጥ አደርግ ነበር:: ይህ ሰው መንግሥት ሁሉ ከዲያብሎስ ስለሆነ፣ ክርስቲያኖች ለመንግሥት መገዛት የለባቸውም የሚል አሳብ ነበረው:: እኔም በአሜሪካ ፖስታ ቤት መጠቀም እንኳ መንግሥትን እንደ ተቀበለ የሚያመለክት መሆኑን ገለጽሁለት:: ወረቀትና ቴምብር ለመግዛት የሚጠቀምበት ገንዘብም የሚመጣው ከመንግሥት ሥልጣን ነው:: ራሱን ለመግለጽ የሚጠቀምበት ነጻነትም ከመንግሥት ዋስትና የተገባለት ነው::

በማርቆስ 12:17 «አስረክቡ» ተብሎ የተተረጐመው ቃል «ዕዳን መክፈል፣ የወሰዱትን መልሶ ማስረከብ» የሚል ፍች ይሰጣል:: ይህም ቀረጥ ዜጐች መንግሥት ላበረከተላቸው አገልግሎት ሊከፍሉ የሚገባቸው ዕዳ እንደሆነ ኢየሱስ ማመልከቱን ያስረዳል:: በአሁኑ ዘመን መንግሥት ለዜጐች ከሚያበረክታቸው ከእነዚህ አገልግሎቶች መካከል የእሳት አደጋ መካለከያና የፖሊስ ጥበቃ፣ ብሔራዊ መከላከያ፣ የመንግሥትን ጉዳይ ለሚያስተዳድሩ የሥራ ኃላፊዎች ደመወዝ፣ ለድሆችና ለችግረኞች የሚሰጡ ድጋፎች፣ ወዘተ. . . ይገኙባቸዋል:: አንድ ክርስቲያን ዜጋ በቀረጥ መልኩ የሚከፈለውን ገንዘብ መንግሥት በሚጠቀምበት መንገድ ላይ ተቃውሞ ሊኖረው ይችላል:: ይህንንም ድምፁን አሰምቶ ሊቃወምና በምርጫ መብቱ የሚፈልገውን ባለሥልጣን ሊመርጥ ይችላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር መንግሥትን ለመልካም ዓላማ እንደ መሠረተ

መቀበል ይኖርበታል (ሮሜ 13፤ 1ኛ ጢሞ. 2:1-6፤ 1ኛ ጴጥ. 2:13-17)። ባለሥልጣናቱን ባናከብር እንኳ፣ ሥልጣናቸውን ማክበር አለብን።

*ስለ ዘላለማዊ ሕይወት የተነሣ ጥያቄ* (12:18-27)። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሰዱቃውያን የተጠቀሱት በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ሃይማኖታዊ ሥልጣናቸው አድርገው የተቀበሉት የሙሴን ሕግ ብቻ ነበር። ስለሆነም፣ በመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያልተደገፈን አስተምህሮ (ዶክትሪን) አይቀበሉም ነበር። በነፍስ ህልውና፣ ከሞት በኋላ ሕይወት፣ በትንሣኤ፣ በመጨረሻው ፍርድ፣ በመላእክት፣ ወይም በአጋንንት መኖር አያምኑም ነበር (የሐዋ. 23:8 አንብብ)። አብዛኞቹ ሰዱቃውያን ካህናትና ሀብታሞች ነበሩ። ራሳቸውን የአይሁዳዊ «ሃይማኖታዊ አምባገነኖች» አድርገው በመቁጠር ሌሎች ሰዎችን ሁሉ ዝቅ አድርገው ይመለከቱ ነበር።

ሰዱቃውያን በዘዳግም 25:7-10 በተሰጠው የጋብቻ ሕግ ላይ ተመሥርተው ለኢየሱስ የሚከተለውን መላምታዊ ጥያቄ አቀረቡለት። አንዲት ሴት በሕይወት ዘመኗ ሰባት ወንድማማቾችን አግብታ ሁሉም ሞቱባት። «እንግዲህ ወደፊት ትንሣኤ የሚባል ነገር ካለ፣ የዘላለምን ሕይወት የምትኖረው ሰባት ባሎቿን አግብታ ነው ማለት ነው?» አሉ። ይህ እንደ ብዙዎቹ መላምታዊ ክርክሮች ጠንካራ መሠረት ያለው ክርክር ይመስላል።

ሰዱቃውያኑ ምላሽ የሌለው ጥያቄ ያቀረቡ ቢመስላቸውም፣ ኢየሱስ ግን ቶሎ ብሎ ሁለት ነገሮችን አለማወቃቸውን ገልጧል፤ እነርሱም፡- የእግዚአብሔርን ኃይልና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ስተው ነበር። የትንሣኤ ሕይወት አሁን የምናውቀው ዓይነት ሕይወት አይሆንም። ትንሣኤ ወደ ተለየ ሕይወት የምንገባበት ነው። መላእክትን ፈጥሮ ባሕርያቸውን የወሰነው አምላክ ለሰማዩ ሕይወት የሚያስፈልገንን አዲስ አካል ሊሰጠን ይችላል (1ኛ ቆሮ. 15: ከ38 ጀምሮ)። ኢየሱስ መላእክት እንደምንሆን ወይም በሁሉም ነገር መላእክትን እንደምንመስል አልተናገረም። የእግዚአብሔር ልጆች ከመላእክት ይልቃሉና (ዮሐ. 17:22-24፤ 1ኛ ዮሐ. 3:1-2)። ኢየሱስ የተናገረው

በትንሣኤ አካላችን እንደ መላእክት ፆታ- አልባ እንደምንሆን ነው። ስለሆነም፣ በመንግሥተ ሰማይ ጋብቻ አይኖርም። ፍጹም አዲስ አካል በምንለብስበትና ሞት በማይታሰብበት የዘላለም መንግሥት፣ ጋብቻ ልጅ መውለድና ዘርን መቀጠል አስፈላጊ አይሆንም።

ሰዱቃውያን ስለ መጽሐፍ ቅዱስም እውቀት አልነበራቸውም። የሙሴን መጻሕፍት እንቀበላለን ቢሉም፣ ሙሴ ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ ማስተማሩን አልተገነዘቡም ነበር። አሁንም ጌታችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልሶ (ማር. 2:25፤ 10:19፤ 12:10)፣ የሚቃጠል ቍጥቋጦን ታሪክ አስታውሷቸዋል። እግዚአብሔር ለሙሴ በኃላፊ ጊዜ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ «ነበርሁ» አላለም። ይልቁንም፤ «የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ እኔ ነኝ» ነው ያለው። እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት በሚናገርበት ጊዜ እነዚህ የእምነት አባቶች (አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ) ሕያዋን ነበሩ። ስለሆነም፣ ሙሴ ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ በሚገባ አስተምሯል።

*የቀዳሚነት ጥያቄ* (12:28-34)። ቀጣዩ ተፈታታኝ አንድ ፈሪሳዊ የሆነ ጸሐፊ ነበር (ማቴ. 22:34-35)። ጸሐፍት አይሁዶች ከሕጉ 613 (365 አሉታዊና 248 አዎንታዊ) ድንጋጌዎችን እንዲታዘዙ ወስነው ነበር። ጸሐፍት ከሚነጋገሩባቸው ጉዳዮች አንዱ ከእነዚህ መለኮታዊ ትእዛዛት የትኛው ይበልጣል? የሚለው ነበር።

ጌታም ዛሬም እንኳ ሳይቀር አጥባቂ አይሁዶች ጠዋትና ማታ የሚደግሙትን የዘዳግም 6:4-5 ታላቅ የእምነት መግለጫ በመጥቀስ ምላሽ ሰጥቷል። ይህም «ሺማ» ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፣ «እስራኤል ሆይ፣ ስማ» ከሚለው የእምነት መግለጫ የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር የተወሰደ ነው። (ሺማ ማለት ስማ የሚል ፍች አለው)። ከዚያም ባልንጀራችንን እንድንወድ የሚያደፋፍረውን ዘሌዋውያን 19:18ን ጠቅሷል። ኢየሱስ ፍቅር በሕይወት ውስጥ ትልቁ ጉዳይ እንደሆነ ገልጿል። ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነውና (ሮሜ 13:8-10)። እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆነ፣ ፍቅሩ በልባችን ውስጥ ይቀጣጠላል። በተጨማሪም፣ ይህንኑ ፍቅር ለሌሎች መግለጽ አለብን። የምንኖረው በደንቦች ሳይሆን

በግንኙነቶች ነው። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን የፍቅር ግንኙነት ከሌሎች ሰዎች ጋር የፍቅር ግንኙነት እንድንመሠርት ያስችለናል።

ጸሐፊው ይህንን ክርክር ያስነሣው ኢየሱስን ለማሰር የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሚጥሩት ፈሪሳውያን መሣሪያ በመሆን ነበር (ማቴ. 22:35 አንብብ)። የጌታን ምላሽ ከሰማ በኋላ ግን አመስግኖታል። የጌታ ቃል ወደ ልቡ ስለ ዘለቀ አውቃለሁ እያለ የሚያስበውን እምነት በጥልቀት መረዳት ጀመረ። የአይሁድ ሃይማኖት መሥዋዕቶችን ከማቅረብና ሕግጋትን ከመጠበቅ የበለጠ መሆኑን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንኳ ያስተምሩ ነበር [1ኛ ሳሙ. 15:22፤ መዝ. (51):16-17፤ (141): 1-2፤ ኤር. 7:22-23፤ ሆሴዕ 6:6፤ ሚክ. 6:6-8]።

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መንግሥት አልራቀም ማለት ምን ማለት ነው? ይህ አንድ ሰው «የፓርቲ መስመር» ለመከተል ወይም ግላዊ አድልዎን ለማስተናገድ ሳይፈልግ እውነትን እንደሚሻ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። አንድ ሰው የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ቡድኖች በሚሉት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል በሚናገረው መንገድ እምነቱን እንደሚመረምር ያሳያል። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የቀረቡ ሰዎች አንዳንድ ወዳጆቻቸውን ለማጣትና አዳዲስ ጠላቶችን ለማፍራት ቢገደዱም እንኳ ለእውነት የመቆም ብርታት አላቸው።

*የማንነት ጥያቄ* (ማር. 12:35-37)። አሁን ጥያቄ ማቅረቡ የጌታችን ተራ ስለነበር፣ ከሁሉም በሚበልጠው የመሢሑ ማንነት ላይ አተኮረ። «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?» (ማቴ. 22:42)። ይህ ጠላቶቹ ከጠየቋቸው ጥያቄዎች ሁሉ የበለጠ ጠቃሚ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሳሳተ አስተሳሰብ ካለን፣ ስለ ደኅንነትም ትክክለኛ አስተሳሰብ ሊኖረን አይችልም። ይህም ነፍሳችንን ለኩነኔ ያጋልጣታል (ዮሐ. 3:16-21፤ 8:24፤ 1ኛ ዮሐ. 2: 18-23)።

ኢየሱስ መዝሙር (110):1ን በመጥቀስ የዳዊት ልጅ እንዴት የዳዊት ጌታ ሊሆን እንደሚችል ጠየቃቸው። አይሁዶች መሢሑ የዳዊት ልጅ እንደሚሆን ያምኑ ነበር (ዮሐ. 7:41-42)። ነገር ግን

የዳዊት ልጅ የዳዊት ጌታም ሊሆን የሚችለው መሢሕ *በሰብአዊ ሥጋ የተገለጠ አምላክ* ከሆነ ብቻ ነበር:: መልሱ ጌታችን በተአምራዊ መንገድ መረገዙና ከድንግል መወለዱ ነው (ኢሳ. 7:14፤ ማቴ. 1:18-25፤ ሉቃስ 1:26-38)::

ይህ ክፍል የተጠናቀቀው ጌታችን ባስተላለፋቸው ሁለት ማስጠንቀቂያዎች ነበር:: እነዚህም በጸሐፍት (ማር. 12:38-40) እና በሀብታሞች (ቍ. 41-44) ትንቢት ላይ የተሰነዘሩ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው:: የአንድ ሰው «አስፈላጊነት» የሚለካው በለበሰው ልብስ፣ በያዘው ሥልጣን፣ ወይም ማዕረግ ከሆነ አስፈላጊነቱ የውሸት ነው:: ሰውን ጠቃሚ ሰው የሚያደርገው ባሕርይ ነው:: ባሕርይ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በመመላለስ የምታሳድገው እንጂ ከሰው የምትቀበለው አይደለም::

በሴቶች አደባባይ አካባቢ ባሉት ግድግዳዎች ላይ ሰዎች መባዎቻቸውን የሚያስቀምጡባቸው አሥራ ሁለት የመለከት ቅርጽ ያላቸው ሰንዱቆች ነበሩ:: ሀብታሞች ብዙ ገንዘብ ይሰጡ ነበር (ማቴ. 6:1-4)፣ ኢየሱስ ግን እነርሱንም ሆነ ስጦታቸውን አልተቀበለም:: ዋናው ነገር ብዛቱ ሳይሆን ተመጣጣኝነቱ ነበር:: ሀብታሞቹ የሚሰጡት ከተትረፈረፈው ሀብታቸው ሲሆን፣ ደሀዋ መበለት ግን ያላትን ሁሉ ነበር የሰጠችው:: ለሀብታሞቹ ስጦታቸው አነስተኛ ምጽዋት ሲሆን፣ ለእርሷ ግን ሕይወቷን በሙሉ የሚጠይቅ ነበር::

የአኗኗርና የአሰጣጥ ትዕቢቶች ሙሉ ለሙሉ ልናስወግዳቸው የሚገቡ ናቸው:: መሪዎቹ አላፊ በሆነው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ላይ መደገፋቸው ምንኛ አሳዛኝ ነው:: ተራ ሰዎች የኢየሱስን ቃል በደስታ ሰምተው መታዘዛቸው ምንኛ ግሩም ነው::

አንተስ ከየትኛው ወገን ነህ?

# 10

# የእግዚአብሔር ባሪያ ወደፊት የሚሆነውን ገለጠ

## ማርቆስ 13

የሄሮድስ ቤተሰቦች አይሁዶችን ለማባበል ቤተ መቅደሱን ቢሠሩትም፣ አይሁዶች በቤተ መቅደሳቸው ይኩራሩ ነበር። ምንም እንኳ ኢየሱስ ቀደም ሲል ስለ ቤተ መቅደሱ የራሱን ግምት የሰጠ ቢሆንም (11:15-17)፣ ደቀ መዛሙርቱ አሁንም በቤተ መቅደሱ ማማር ይደነቁ ነበር። ይህ እጅግ የሚያደንቁት ሕንጻ አንድ ቀን እንደሚፈርስ በነገራቸው ጊዜ ምን ያህል እንደ ደነገጡ መገመት ይቻላል። የአይሁድ መሪዎች ስላረከሱት፣ ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን በመተው እንዲደመሰስ ያደርገው ነበር (ማቴ. 23:38)፤ ሮማውያን ሕንጻውን ይደመስሱታል።

ኢየሱስ ከሕዝቡ ገለል ሲል፣ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ይህ ታላቅ ክስተት መቼ እንደሚፈጸምና ምልክቶቹ ምን ምን እንደሚሆኑ ጠየቁት። ጥያቄያቸው ስለ ትንቢት የጠራ ግንዛቤ እንዳልነበራቸው ያሳያል። ቤተ መቅደሱ የሚፈርሰው በዘመን መጨረሻ ጌታ በሚመለስበት ወቅት መስሏቸው ነበር (ማቴ. 24:3)። ጥያቄያቸው ግን ኢየሱስ «የደብረ ዘይት ስብከት» የሚባለውን ትንቢታዊ መልእክት እንዲያስተላልፍ አነሣሥቶታል (ማቴ. 24-25፤ ሉቃስ 21:5-36)።

ይህንን ጠቃሚ ስብከት በምናጠናበት ጊዜ፣ አንዳንድ ተግባራዊ መምሪያዎችን መከተል ይኖርብናል። *በመጀመሪያ፣* ይህንን ስብከት ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ በተለይም ከትንቢተ ዳንኤል ጋር እያስተያየን ማጥናት አለብን። ትንቢታዊ ጽሑፎች የሚጣጣሙት እግዚአብሔር የገለጠውን ሁሉ አንድ ላይ ስናስተያይ ነው።

*ሁለተኛ፣* የስብከቱን ተግባራዊ ተዛምዶ መመልከት አለብን። ኢየሱስ ይህንን ስብከት ያቀረበው የደቀ መዛሙርቱን ጉጉት

ለማርካት ወይም የተዛባ አስተሳሰባቸውን ለማቅናት አልነበረም። ቢያንስ አራት ጊዜ ያህል «ተጠንቀቁ » (ማር. 13:5፣9፣23፣33) ሲል የተናገረ ሲሆን፣ ስብከቱንም የቋጨው «ተጠበቁ» በሚል ምክር ነው። ይህንን ስብከት ማጥናት የወደፊት ክስተቶችን በተሻለ መንገድ እንድንረዳ ሊያግዘን ቢችልም፣ ቀናትን የመቁረጥ ስሕተት መፈጸም የለብንም (ቍ. 32)።

<u>ሦስተኛ፣</u> «የአይሁዶችን ድባብ» ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን። የደብረ ዘይቱ ስብከት አራት አይሁዶች ስለ ወደፊቱ የአይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ለአይሁዳዊ መምህር ያቀረቡት ጥያቄ ውጤት ነው። በተለይ ስለ «ሐሰተኛ ክርስቶሶች» (ቍ. 5-6፣21-22)፣ ስለ አይሁድ ችሎቶችና መከራዎች (ቍ. 9) የተነገሩ አሳቦች አይሁዶችን የሚመለከቱ ናቸው። ስለ «ነቢዩ ዳንኤል» እና ከይሁዳ ስለ መሸሽ የተነገረው አይሁዶች በተለይ የሚደሰቱበት ነው (ቍ. 14)።

<u>በመጨረሻም፣</u> ይህ ጊዜ «ታላቁ መከራ» የተባለውን ክፍለ ጊዜ እንደሚያመለክት ማስታወስ አለብን (ቍ.19፣24፣ በተጨማሪም፣ ማቴ. 24:21፣ 29 አንብብ)። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህንን ክፍለ ጊዜ የገለጹት የያዕቆብ መከራ ጊዜ (ኤር. 30:7)፣ የቁጣ ጊዜ (ሶፎ. 1:15-18)፣ እንዲሁም የቁጣና የቅጣት ጊዜ (ኢሳ. 26:20-21) በማለት ነበር። ቀጥለን እንደምንመለከተው፣ የነገሮችን ቅደም ተከተል በተሻለ መንገድ የምንረዳበትን «ቁልፍ» የሚሰጠን ነቢዩ ዳንኤል ነው።

በማርቆስ 13፣ ኢየሱስ ስለዚህ የታላቁ መከራ ሦስት ደረጃዎችን ገልጿል። እነዚህም (1) መጀመሪያ (ቍ. 5-13)፣ (2) አጋማሽ (ቍ. 14-18) እና (3) ወደ ፍጻሜው የሚመሩ ክስተቶች ናቸው (ቍ. 19-27)። ከዚያም አማኞች እንዲጠነቀቁና እንዲጠበቁ የሚያሳስቡትን ሁለት ምሳሌዎች በመስጠት አጠቃልሏል (ቍ. 28-37)። የማቴዎስ ወንጌል ከማርቆስ በበለጠ ዝርዝር ጉዳዮችን ቢያቀርብም፣ መሠረታዊ አስተዋጽኦው ተመሳሳይ ነው። ይኸውም የኃዘን መጀመር (24:4-14)፣ የመከራው አጋማሽ (24:15-28)፣ ፍጻሜ (24:29-31)፣ እና የመዝጊያ ምሳሌያዊ ተዛምዶ (24:32-44)።

ታላቁ መከራ ከመጀመሩ በፊት በአሁኑ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ የሚገኙ አማኞች በክርስቶስ ተነጥቀው ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄዱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ያምናሉ (1ኛ ተሰ. 4:13-5:11፤ ራእይ 3:10-11)። በመከራው መዝጊያ ላይ፣ ከክርስቶስ ጋር ወደ ምድር ተመልሰው ከእርሱ ጋር ይነግሣሉ (ራእይ 19:11-20:6)። እኔም ይህንን አተረጓጎም እጋራለሁ። ነገር ግን የመንፈሳዊነት ወይም የጤናማ አስተምህሮ መለኪያ አድርጌ አልወስደውም።

## 1. የመከራው የመጀመሪያ አጋማሽ (ማርቆስ 13:5-13)

ቁልፍ ዓረፍተ ነገር የሚገኘው ከቊ. 8 መጨረሻ ላይ ነው። «እነዚህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።» በዚያን ጊዜ ዓለም ለመውለድ እንደምታምጥ ሴት ትጨነቃለች (ኢሳ. 13:6-8፤ ኤር. 4:31፤ 6:24፤ 13:21፤ 22:20-23፤ 1ኛ ተሰ. 5:3)። የምጥ ጣሮች በድንገት ብቅ ካሉ በኋላ፣ ቀስ በቀስ ተደራጅተው ዓለምን ለታላቅ ኃዘንና መከራ ይዳርጋሉ።

(ሀ) *«አትሳቱ።»* ኢየሱስ የምጽአቱ «ምልክቶች» የማይሆኑትን ነገሮች ዘርዝሯል። እነዚህ ነገሮች የመከራው «የምጥ ጣር» መጀመሩን ያመለክታሉ። እነዚህም ምልክቶች የሐሰተኛ ክርስቶሶች ስኬት (ቊ. 5-6)፣ የመንግሥታት ግጭት (ቊ. 7-8)፣ የተፈጥሮ ነውጦች (ቊ.8) እና የሃይማኖት ስደቶች ናቸው (ቊ. 9-13)። ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች ሁል ጊዜም ከሰው ልጅ ተለይተው የማያውቁ ቢሆኑም ከምጥ ጣሮቹ ጋር ስለተነጻጸሩ፣ ምናልባትም ጌታ ፍጥነታቸው በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር መግለጹ ይሆናል።

*ሐሰተኛ ክርስቶሶች።* የታሪክ ገጾች ስለ ሐሰተኛ መሲሖች፣ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና እውነትን ሳይጨብጡ በስሜት ስለተነሣሡ ደቀ መዝሙሮቻቸው በሚያትቱ አሳዛኝ ታሪኮች የተሞሉ ናቸው። ኢየሱስ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ለሕዝቡ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል (ማቴ. 7:15-20)፤ ጳውሎስ (የሐዋ. 20:28-31) እና ዮሐንስም (1ኛ ዮሐ. 4:1-6) እንዲሁ። ከሰው ባሕርይ ውስጥ ውሸትን ለማመን የሚወድና የቀድሞዎቹን ውድ ትምህርቶች ለመቀበል የማይሻ አንድ ነገር አለ። ማርክ ትዌይን እንዳሉት፣

እውነት ገና ጫማዋን በማድረግ ላይ ሳለች ውሸት ዓለምን ትዞራለች! መንፈሳዊ ዕውርነት የሚያጠቃቸው ሰዎች ታዋቂ መሪዎችን በመከተል ቀላልና የተሳሳቱ የሕይወት መፍትሔዎቻቸውን በምኝነት ሊቀበሉ ይችላሉ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በእነዚህ አጭበርባሪዎች እንዳይታለሉ አስጠንቅቋቸዋል። ይህ ማስጠንቀቂያ ዛሬም ይሠራል።

*ፖለቲካዊ ግጭቶች።* በአገሮች መካከል በሚከሰቱ ፖለቲካዊ ግጭቶች እንዳይረበሹም አስጠንቅቋቸዋል። የሮም መንግሥት ለረዥም ጊዜ በሰላም የኖረ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ ቀጣይነት ያለው አልነበረም። ግዛቱ እየበሰበሰ ሲሄድና ብሔርተኝነት ሲጎለብት፣ አገሮች መጋጨታቸው አይቀርም ነበር። የሮም መንግሥት ለዘላለሙ ይደመሰሳል።

*የተፈጥሮ አደጋዎች።* ብዙውን ጊዜ ጦርነት ረሃብን ያስከትላል (2ኛ ነገ. 25:2-3፤ ሕዝ. 6:11)። ረሃብ ሰው አካባቢውን በአግባቡ ባለመጠበቁ ወይም የእግዚአብሔር የፍርድ ማስፈጸሚያ በመሆን ሊከሰት ይችላል (1ኛ ነገ. 17:1)። በምድር ላይ ሁልጊዜም የምድር መንቀጥቀጥ ሲፈጸም ኖሯል። አንዳንዶች ይህ የእግዚአብሔር ቍጣ ምልክት እንደሆነ ይናገራሉ (ራእይ 6:12፤ 8:5፤ 11:13፤ 16:18)። የተፈጥሮ አደጋዎች የሚከሰቱባቸው ብዙ ምክንያቶች ስላሉ፣ በግትርነት «የምጽአቱ ምልክቶች» ናቸው ማለቱ አደገኛ ነው።

ለ) *«አይዟችሁ!»* አማኞቹ ጥንቃቄ በማድረግ ከአሳቾች መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ለራሳቸውም መጠንቀቅ ያስፈልጋቸው ነበር (ማር. 13:9-13)። ለምን? ምክንያቱም መንግሥታዊም ሆነ (ቍ. 9-11) ግላዊ (ቍ. 12-13) ስደቶች ያጋጥሟቸዋል። አማኞች እነዚህን አጋጣሚዎች ተጠቅመው ለኢየሱስ ክርስቶስ መመስከራቸው በጣም አስፈላጊ ነበር። ስደቱ ከአካባቢው የአይሁዶች ችሎት ተነሥቶ፣ ገዥዎችና ነገሥታት ወደሚሳተፉባቸው ታላላቅ ችሎቶች ይደርስ ነበር። በሐዋርያት ሥራ ውስጥም ተመሳሳይ የስደት የዕድገት ሂደት ተመዝግቧል (ምዕ. 4-5፤ 7፤ 12፤ 16፤21-28)።

ይሁንና፣ ስደት ወንጌሉን ለማስራጨት ጠቃሚ ሚና ይጫወታል:: አማኞቹ ለስሙ እየተሰደዱ ወንጌሉን ይሰብካሉ:: ተርቱሊያን ለአሳዳጆቹ፣ «በገደላችሁን ቁጥር እንበዛለን:: የክርስቲያኖች ደም ዘር ነው!» ብሏል:: ወንጌሉን ወደ ሁሉም ብሔሮች እስክናዳርስ ድረስ ክርስቶስ ደግሞ አይመለስም የሚል እምነት ባይኖረኝም (ማር. 13:10)፣ ወንጌሉን ማስራጨት ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ተልዕኮ መሆኑ ግልጽ ነው (ማቴ. 28:19-20):: በዚህ ስፍራ «መጨረሻ» የሚያመለክተው «የዘመን ፍጻሜ» የሆነውን የታላቁን መከራ ጊዜ ነው::

ለእነዚህ «ተራ ሰዎች» ወደ ፍርድ ችሎቶች፣ ገዥዎችና ነገሥታት መጕተቱ ቀላል አይሆንም:: ነገር ግን ኢየሱስ የመመስከር ዕድል በሚያጋጥማቸው ጊዜ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ በኩል እንደሚያገለግል አረጋግጦላቸዋል (ማር. 13:11):: በሚገባ የማይዘጋጁ ሰባክያን ይህንን ምንባብ ለማመኻኛነት ሊጠቀሙ አይገባም:: ይህ ለክርስቶስ ከልባቸው ለመመስከርና እርሱን ለማስከበር ለሚፈልጉ አማኞች የተሰጠ ማበረታቻ ነው (ዮሐ. 14:26፤ የሐዋ. 4:8):: በመንፈስ የምንመላለስ ከሆነ፣ ዕድሉ በሚያጋጥመን ጊዜ ለክርስቶስ ለመመስከር አንቸገርም (ዮሐ. 15:26-27)::

ከመንግሥታዊ ምንጮች የሚመጡ ስደቶች የሚከሰቱባቸውን ምክንያቶች መረዳቱ ባይቸግረንም፣ ጓደኞቻቸውና የቤተሰብ አባሎቻቸው በክርስቲያኖች ላይ ለምን ችግሮችን እንደሚፈጥሩ መገንዘቡ አዳጋች ነው (ሚክ. 7:ከ4 ጀምሮ፤ ዮሐ. 15:18-27 አንብብ):: በተለይ የአይሁድ ቤተሰቦች እርስ በርሳቸው ይደጋገፋሉ ብለን እናስብ ይሆናል:: ነገር ግን አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ የክርስትናን እምነት እንደ ኑፋቄና ስድብ ይመለከቱ ነበር:: አይሁዳውያን አማኞች፣ «እስራኤል ሆይ፣ ስማ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው!» እያሉ በቀን ሁለት ጊዜ ይደግሙ ነበር (ዘዳግ. 6:4):: «ኢየሱስ ጌታ ነው!» የሚሉ አይሁዶች በእግዚአብሔር ላይ እንደ ተሳደቡና ሞት እንደሚገባቸው ይታመን ነበር:: ሮምም ብትሆን «ቄሣር ጌታ ነው!» የማይል ዜጋዋን ለመቅጣት ዝግጁ ነበረች:: ስለሆነም፣ ቤተሰቦችና ወዳጆች ለጥንታዊ እምነታቸውና ለአገራቸው፣ በሌላ

በኩል ደግሞ ለወዳጆቻቸው ባላቸው ፍቅር ሳቢያ ለሁለት እንዲሰነጠቁ ተደርጓል፡፡

እውነተኛው የስደት ምክንያት በማርቆስ 13:13፣ «ስለ ስሜ» ተብሎ ተገልጿል፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በምንተባበርበት ጊዜ ዓለም እርሱን ባስተናገደችበት መንገድ ልታስተናግደን እንደምትችል እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን (ዮሐ. 15:ከ20 ጀምሮ)፡፡ ዛሬ በተለያዩ የሃይማኖት ቡድኖች ውስጥ አባል በመሆን ሳትሰደድ ልትኖር ትችላለህ፡፡ ነገር ግን የኢየሱስን ስም መጥራትና ወንጌሉን ማካፈል ስትጀምር፣ ተቃዋሚ ይነሣብሃል፡፡ የጌታ ስም ዛሬም ቢሆን እንደተጠላ ነው፡፡

ቊጥር 13 በቀዳሚነት በታላቁ መከራ ወቅት ስለሚመሰክሩ ሰዎች የሚናገር ስለሆነ፣ ለደኅንነት እንደ ተሰጠ ቅድመ - ሁኔታ አድርገን ልንወስደው አይገባም፡፡ አንድ ሰው እውነተኛ ዳግም ልደት ካገኘ እግዚአብሔር በየትኛውም ዘመን ውስጥ ቢኖር ፍቅሩን ይገልጽለታል (ዮሐ. 13:1፤ ሮሜ 8:35-38)፤ ይጠብቀዋልም (ዮሐ. 10:27-29፤ ሮሜ 8:29-34)፡፡ በማርቆስ 13:7 «መጨረሻው» የሚያመለክተው «የዘመንን ፍጻሜ» ስለሆነ፣ የቊጥር 13 ፍችውም ይኸው ሳይሆን አይቀርም፡፡ በታላቁ መከራ ጊዜ፣ እውነተኛ አማኞች እምነታቸውን በታማኝነታቸው ያረጋግጣሉ፡፡ መንፈሳዊነት ለጐደለው የሐሰተኛ ሃይማኖት ጫና እጅ አይሰጡም (ራእይ 13)፡፡

## 2. የመከራው አጋማሽ (ማርቆስ 13:14-18)

«የጥፋት ርኲሰት» የሚለው ሐረግ የተወሰደው ከትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ሲሆን፣ አሕዛብ የአይሁድን ቤተ መቅደስ በጣዖት ማርከሳቸውን ያመለክታል፡፡ ለአይሁዶች ጣዖት ሁሉ ርኲሰት ነው (ዘዳግ. 29:17፤ 2ኛ ነገ. 16:3)፡፡ አንቲዮከስ አራተኛ የተባለው የሶርያ ንጉሥ በ167 ዓ.ዓ የአይሁድን ቤተ መቅደስ አርክሷል፡፡ (ይህ ንጉሥ «ኤጵፋነስ»ም ተብሎ ይታወቃል፡፡ ፍችው ዝነኛ ማለት ነው፡፡) ይህንንም ያደረገው በቤተ መቅደሱ መሠዊያ ላይ የአሣማ ደም በማፍሰስ ነበር፡፡ ይህ በዳንኤል 11:31 የተተነበየ ክስተት ነበር፡፡ ሮማውያንም በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌምን በወረሩና ባወደሙ ጊዜ ቤተ መቅደሱን አርክሰዋል፡፡ ነገር ግን

እነዚህ ክስተቶች በዳንኤል 9:27 እና 12:11 ለተተነበየው የመጨረሻው የጥፋት ርኩሰት ማስታወሻ ነበሩ::

ዳንኤል 9:24-27ን በሚገባ ለመረዳት፣ የአይሁዶች የቀን መቊጠሪያ በተከታታይ ሰባቶች የተከፋፈለ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል:: ሰንበት በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ይውላል:: በዓለ ኀምሳ ደግሞ ከፋሲካ በኋላ በሰባተኛው ሳምንት ላይ ይውላል:: የመለከቶች በዓል፣ የስርየት ቀንና የዳስ በዓል የሚውለው በሰባተኛው ወር፣ ወዘተ. . .ነበር::

ዳንኤል ሰባ ሳምንታት (ሰባ ሱባዔ) ወይም የሰባት ዓመት ክፍለ ጊዜያትን ተመልክቷል:: እነዚህም እግዚአብሔር ለአይሁዶችና ለተቀደሰች የኢየሩሳሌም ከተማቸው የወሰነው ጊዜ ነበር:: ይህ የ490 ዓመታት ክፍለ ጊዜ የሚጀምረው ንጉሥ አርጤክስስ በ445 ዓ.ዓ አይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው ኢየሩሳሌምን እንደገና እንዲገነቡ አዋጅ ካወጣበት ጊዜ ነው (ዕዝራ 1:1-4):: ከተማዪቱ ለምን እንደገና መገንባት አስፈለጋት? ምክንያቱም ከ483 ዓመታት (7x69) በኋላ፣ መሢሑ ወደ ከተማዪቱ መጥቶ ሕይወቱን ለኃጢአተኞች አሳልፎ መስጠት ነበረበት::

እዚህ ላይ ትንሽ የሒሳብ ስሌት ማድረግ ይኖርብናል:: አብዛኞቹ የታሪክ ምሁራን ኢየሱስ በ5 ዓ.ዓ እንደ ተወለደ ያምናሉ:: ምክንያቱም ታላቁ ሄሮድስ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ገና አልሞተም ነበር:: የሞተው በመጋቢት ወር በ4 ዓ.ዓ ነበር:: ጌታችን የሞተው በ33 ዓመቱ አካባቢ ከሆነ፣ ጊዜው 27 ወይም 28 ዓ.ም ነው ማለት ነው:: ይህም አዋጁ ከወጣበት ከ445 ዓ.ዓ ጀምሮ 483 ዓመታት እንደተቈጠሩ ያሳያል::

ዳንኤል ከተነበየው የ490 ዓመታት ጊዜ ውስጥ 483ቱን አንሥተናል:: የቀረው ሰባት ዓመትስ? ዳንኤል 9:27 ይህንን የሰባት ዓመት ጊዜ አሁን እያጠናን ላለነው የታላቁ መከራ ዘመን ይሰጠዋል:: (የማብራሪያ ጸሐፊዎች ዳንኤል 9:26 ኢየሩሳሌም በሮማውያን እንደምትወድም እንደተነበየ ያስረዳሉ:: ነገር ግን እነዚህ ሁለት ነገሮች ሊደነጋገሩብህ አይገባም:) «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» ሰባት ዓመት ይወስዳል::

ለመሆኑ የዚህን አስከፊ የሰባት ዓመታት ክፍለ ጊዜ መጀመር የሚያመለክቱ ምልክቶች ምን ምንድን ናቸው? በእስራኤልና በሚመጣው ልዑል መካከል የሚፈጸም የስምምነት ፊርማ (ዳን. 9:26):: ይህ «ልዑል» በአመዛኙ «ጸረ ክርስቶስ ወይም መሢሕ» እያልን የምንጠራው የዓለም አምባገነን ይሆናል:: ይህ ልዑል በራእይ መጽሐፍ ውስጥ «አውሬው» ተብሎ ተጠርቷል (ምዕ.13-14):: አውሬው ለሰባት ዓመታት እስራኤልን ከብዙ ጠላቶቿ ለመጠበቅ ስምምነት ይፈራረማል:: አይሁዶች ቤተ መቅደሳቸውን እንደ ገና እንዲገነቡና የመሥዋዕት ሥርዓቶቻቸውን እንዲያካሂዱ ጭምር ይፈቅድላቸዋል:: አይሁዶች እውነተኛ መሢሐቸውን ለመቀበል ያልፈለጉ ሲሆን፣ ሐሰተኛውን መሢሕ ግን ይቀበሉታል (ዮሐ. 5:43):: ነገር ግን ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ሐሳዊው መሢሕ ቃሉን ያፈርስና ቤተ መቅደሱን ይወርራል፤ የራሱን ምስል ከመሠዊያው ላይ አኑሮ የዓለም ሕዝብ ሰይጣንን እንዲያመልክ ያስገድዳል (ራእይ 13፤2ኛ ተሰ. 2:1-12 አንብብ):: በዳንኤል የተተነበየው የጥፋት ርኩሰት ይኼ ሲሆን፣ የመጨረሻውን የመከራ ጊዜ ያስከትላል:: ይህም «ታላቁ መከራ» በመባል የሚታወቀው ክፍለ ጊዜ ነው (ማቴ. 24:21):: በ13:14 ማርቆስ ተጨማሪ ማብራሪያ የሰጠው ኢየሱስ መልእክቱን በሰጠበት ወቅት ለነበሩት አድማጮች ሳይሆን፣ ለወደፊት አንባብያን መሆኑን አስተውል:: እነዚህ ክስተቶች ሲፈጸሙ በሚመለከቱበት ጊዜ ይህ መልእክት ለእነርሱ የተለየ ትርጉም ይሰጣል::

ኢየሱስ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ለሚኖሩ አይሁዳውያን አማኞች ልዩ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸዋል:: ይህም፣ «ፈጥናችሁ ውጡ!» የሚል ነው:: ይኸው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ በ70 ዓ.ም ሮም ኢየሩሳሌምን በወረረች ጊዜ ተፈጻሚ ሆኗል (ሉቃስ 21:20-24ን አንብብና ወረራው በዳንኤል 9:26 ላይ እንደተተነበየ አስታውስ::) በ70 ዓ.ም የተከሰተው በታላቁ መከራ አጋማሽ ላይ ለሚሆነው ፍንጭ ሰጥቷል:: ዶ/ር ሐሪ ሪመር፣ «ነገሮች ከመከሰታቸው በፊት ጥላቸውን ያጠላሉ» ይሉ ነበር:: በማርቆስ 13:14-18 የተገለጹት ማስጠንቀቂያዎች ዛሬ ለአማኞች አይሠሩም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁልጊዜም

ትንቢታዊ ቃልን እንዲያውቁና በየትኛውም ጊዜ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንዲዘጋጁ ያሳስቡናል::

### 3. የታላቁ መከራ የመጨረሻው አጋማሽ (ማር. 13:19--27)

በራእይ መጽሐፍ ውስጥ የመከራው የመጨረሻው አጋማሽ «የእግዚአብሔር ቍጣ» ተብሏል (14:10፣ 19፤ 15:1፣ 7፤ 16:1 19፣ 19:15):: በዚህ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ይፈርዳል፤ እስራኤልንም ለመሢሑ ምጽአት ያዘጋጃታል:: ይህ ዓለም ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ አይቶ የማያውቀው ታላቅ ፍርድ ይሆናል:: በዚህም እግዚአብሔር ዓላማዎቹን በመፈጸም ለድል ነሺው መምጣት ሁኔታዎችን ያመቻቻል (ራእይ 19:ከ11 ጀምሮ)::

በፍርዱ መሀል ሳይቀር እግዚአብሔር ምሕረትን ያስታውሳል (ዕንባ. 3:2):: በመሆኑም፣ ለምርጦቹ ሲል የመከራውን ጊዜ ያሳጥራል:: (ምርጦቹ በመከራው ጊዜ የሚያምኑ አሕዛብና አይሁዶች ናቸው:: ራእይ 14ን አንብብ::) ቀናቱን የሚያሳጥረው ቀደም ሲል እንደወሰነው የመከራው ጊዜ በሦስት ዓመት ተኩል እንዲያበቃ በማድረግ ነው::

ሰይጣናዊ ማታለያ እስከ መጨረሻው ድረስ ይቀጥላል:: ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ሰዎችን ወደ ጥፋት ይመራሉ:: እንዲያውም፣ ተአምራትን ጭምር ይሠራሉ (ማቴ. 7:21-23፤ 2ኛ ተሰ. 2:9-12፤ ራእይ 13:13-14):: እነዚህ ተአምራት በጣም አሳሳቾች ከመሆናቸው የተነሣ የተመረጡት ሳይቀሩ ይህንን ውሸት ለማመን ይፈተናሉ:: ተአምራት በራሳቸው መለኮታዊ ጥሪና ድጋፍ መኖሩን አያረጋግጡም (ዘዳግ. 13:1-5):: የመጨረሻው መፈተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው::

በሰማይ በሚታዩ አስፈሪ ምልክቶችና በዓለም ሁሉ በሚከሰቱ ሁከቶች አማካኝነት የመከራው ጊዜ እየጦዘ ይሄዳል (ሉቃስ 21:25-26):: እነዚህ ነቢያት የተነበዩአቸው ምልክቶች (ኢሳ. 13:10፤ 34:4፤ ኢዩ. 2:10፤ 3:15)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የሚመጣበትን መንገድ ያዘጋጃሉ:: በምድር ላይ መንግሥቱን ለመመሥረት በሚመጣበት ጊዜ (የሐዋ. 1:11፤ ራእይ 1:7) ታላቅ ክብሩ ይገለጣል (ዳን. 7:13-14፤ ማር. 8:38 አንብብ)::

ማርቆስ 13:27 እስራኤላውያን ከተበተኑባቸው አገሮች ሁሉ እንደሚሰበሰቡ ይገልጻል (ዘዳግ. 30:3-6፤ ኢሳ. 11:12፤ ኤር. 31:7-9)። መሢሐቸውን አይተው ያምኑበታል። አገሪቱም በቅድስናና በክብር ትፈጠራለች (ዘካ. 12:9-13:1፤ 14:4-11)። እስራኤል የከበረ ተስፋ እንዳላት ጳውሎስ በሮሜ 11 ውስጥ አብራርቷል።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ የአሁኑ ኃላፊነቶቻቸውን እስኪዘነጉ ድረስ በወደፊት ትንቢቶች እንዲጠመዱ አልፈለገም። በመሆኑም፣ የደብረ ዘይቱን ስብከት በሁለት ምሳሌዎች አጠቃልሏል። (ማቴዎስ 25 ሦስት ሌሎች ምሳሌዎችን፣ ማለትም የቆነጃጅት፣ የመክሊትና የበጐችና የፍየሎችን ታሪኮች ጨምሯል።) የመጀመሪያው ምሳሌ የምጽአቱን መቅረብ በማወቅ ላይ ሲያተኩር፣ ሁለተኛው ምሳሌ የመምጫውን ጊዜ *ባለማወቅ* ላይ ያተኩራል። ይኼ እርስ በርስ *መቃረን* ነውን? ምሳሌዎቹ ስለ ሁለት የተለያዩ ቡድኖች የሚናገሩ በመሆናቸው፣ ይኼ እርስ በርስ *መቃረናቸውን* አያሳይም። የመጀመሪያው በታላቁ መከራ ውስጥ ስለሚገኙ ቅዱሳን፣ ሁለተኛው በሁሉም ዘመን ውስጥ ለሚኖሩ ሁሉም አማኞች የሚናገሩ ናቸው።

የበለስ ዛፍ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ልዩ ግንኙነት አላት (ማርቆስ 11:12-14ን አንብብ። ነገር ግን ሉቃስ 21:29 «ዛፎችን ሁሉ» እንደሚጨምር አጢን።) በፍልስጥኤም አገር የሚገኙ አብዛኞቹ ዛፎች ሁልጊዜም አረንጓዴ ሆነው የሚኖሩ በመሆናቸው፣ ከወቅቶች ጋር በፍጥነት አይለዋወጡም። የበለስ ዛፍ ግን እንዲህ አይደለችም። በፀደይ ወቅት ፈጥነው ከሚያቈጠቊጡ ዛፎች አንዷ በመሆኗ፣ የበጋው ወራት መቃረቡን ታመለክታለች።

ዛሬ ክርስቲያን አማኞች እንደ መሆናችን፣ ለምጽአቱ «ምልክቶችን» እየተጠባበቅን አይደለንም። ነገር ግን በታላቅ መከራ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች የእነዚህን ነገሮች መፈጸም አይተው ምጽአቱ እንደ ቀረበ ያውቃሉ። ይህም ማረጋገጫ በመከራ እንዲጸኑና (13:13) መልካም ምስክሮች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

«ትውልድ» በታሪክ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል ብለን እናስባለን:: ለመሆኑ ኢየሱስ በቁጥር 30 ላይ የጠቀሰው የትኛውን «ትውልድ» ነው? በዚያን ጊዜ በይሁዳ የነበረው ትውልድ «እነዚህ ነገሮች» ሲፈጸሙ እንዳልተመለከተ ግልጽ ነው:: ምናልባት በታላቅ መከራ ወቅት የሚኖረውን ትውልድ ማመልከቱ ይሆናል:: ነገር ግን ታላቁ ዘመን የሚሸፍነው ሰባት ዓመታትን ብቻ ሆኖ ሳለ ትውልድን መጥቀሱ ለምን አስፈለገው? በዚያ ላይ ደግሞ በሁሉም የታሪክ ወቅት የተለያዩ ትውልዶች እንደሚኖሩ ይታወቃል::

«ትውልድ» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል «ዘር፣ ቤተሰብ» ተብሎ ሊፈታ ይችላል:: ኢየሱስ የእስራኤልን ሕዝብ ለማመልከት ይህንን ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሟል (ማር. 8:12፣ 38፤ 9:19)፤ በማርቆስ 13:30ም በዚያ መልኩ ይሆናል የተጠቀመበት:: የተመረጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ እስከ መጨረሻው ድረስ ከምድር ላይ አይጠፋም:: እግዚአብሔርም ለእነርሱ የገባላቸውን የተስፋ ቃል ይፈጽምላቸዋል:: ቃሉ በፍጹም ሳይፈጸም አይቀርም (ኢያሱ 21:45፤ 1ኛ ነገ. 8:56፤ ማቴ. 24:35):: አማኞች እንደ መሆናችን፣ በምልክቶች ላይ አንደገፍም:: ነገር ግን በማይለወጥና ጽኑ በሆነው የትንቢት ቃሉ ላይ እንደገፋለን (2ኛ ጴጥ. 1:19-21)::

የበለስ ዛፍ ምሳሌ በታላቁ መከራ ጊዜ የሚኖሩ ቅዱሳን «የዘመኑን ምልክቶች» እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: ነገር ግን የባለቤቱ ምሳሌ ዛሬ ሁላችንንም ያስጠነቅቀናል (ማር. 13:37):: ምክንያቱም ወደ ሰማይ ሊወስደን መቼ እንደሚመጣ አናውቅምና (1ኛ ቆሮ. 15:51-52):: በታሪኩ ውስጥ እንደተጠቀሰው ባለቤት ሁሉ፣ ጌታችንም ወደ ሰማይ ከመሄዱ በፊት ለእያንዳንዳችን ሥራ ሰጥቶናል:: እርሱ ከሄደ በኋላ ታማኞች እንድንሆንና በሚመለስበትም ጊዜ በሥራ ላይ እንድንገኝ ይጠብቅብናል:: የሰጠንም ምክር፣ «ነቅታችሁ ጸልዩ» የሚል ነው::

«መንቃት» ከእንቅልፍ ርቆ መትጋትን ያመለክታል:: የምንነቃው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለስበትን ጊዜ የሚያውቅ ማንም የለምና ነው:: ኢየሱስ በተዋረደ ሥጋዊ ሕይወቱ የመምጫውን ቀንና ሰዓት አያውቅም

ነበር። መላእክትም ይህንን ቀንና ሰዓት አያውቁም። ይህን «የተባረከ ተስፋ» የሙጥኝ በማለታችን ደኅንነትን ያላገኘው ዓለም ይሳለቅብናል (2ኛ ጴጥ. 3)። ሥራችን በታማኝነት ተግቶ መሥራት እንጂ የትንቢትን ድብቅ ዝርዝሮች እያነሡ መከራከር ወይም መላ መምታት አይደለም።

ንቁነት ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመሄድ ጋር አይገናኝም። ይህ እርሱን የማስደሰት፣ አስደሳች ምስጋናውን የመስማትና ሽልማቱን የመቀበል ጉዳይ ነው (ማቴ. 25:14-30)። ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ አንዳንዶችን ወደ ሰማይ እንደሚወስድና ሌሎችን ለታላቁ መከራ አጋልጦ እንደሚተው የሚያመለክት አሳብ በዚህ ክፍል አልተጠቀሰም። ቤተሰቡ አንድ ስለሆነ፣ ለሁሉም ስፍራ እያዘጋጀላቸው ነው– ከሁሉ ለሚያንሱት ሳይቀር (ዮሐ. 14:1-6)። ወደ መንግሥተ ሰማይ የምንሄደው በጸጋው እንጂ በታማኝነታችን ወይም በበጐ ሥራችን አይደለም (ኤፌ. 2:8-10)።

የማርቆስን ወንጌል የሚያነብቡ ክርስቲያኖች የኋላ ኋላ በሮም ይሰደዱ ስለነበር (1ኛ ጴጥ. 4:ከ12 ጀምሮ)፣ ይህ መልእክት ከፍተኛ መጽናናትና ብርታት ሳይሆናቸው አይቀርም። ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር ሕዝቡ እጅግ በከፋው በታላቁ የመከራ ጊዜ ስደት ውስጥ እንዲመሰክሩለት ማድረግ ከቻለ፣ ቅዱሳኑ የሮምን መከራ በሚቀበሉበት ጊዜም ሊያጠነክራቸው ይችል ነበር።

ዛሬ ክርስቲያኖች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተገለጸውን አስከፊ መከራ ባይቀበሉም፣ ጌታችን ከመመለሱ በፊት የድርሻችንን ስደትና መከራ በዚህ ምድር ላይ መቀበላችን የማይቀር ነው (ዮሐ. 16:33፤ የሐዋ. 14:22)። ነገር ግን በማርቆስ 13 ውስጥ የተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ከራሳችን ሕይወት ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ። «እንዳትሳሳቱ ተጠንቀቁ» (ቍ. 5፣23)፤ «ተስፋ እንዳትቈርጡ ተጠንቀቁ» (ቍ. 9)፤ «ነቅታችሁ ጸልዩ» (ቍ. 33)።

«ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ፤ ትጉ» (ቍ. 37)።

# 11

# የእግዚአብሔር ባሪያ ሲሠቃይ

## ማርቆስ 14:1-15:20

በሺዎች የሚቈጠሩ የፋሲካ ታዳሚዎች ለበዓሉ ደስታ በሚዘጋጁበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ለመከራና ስቅለት እየተዘጋጀ ነበር:: ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንደ ቈረጠ ሁሉ (ሉቃስ 9:51)፣ የአብን ፈቃድ ለመፈጸም ልቡን አጸና:: የእግዚአብሔር ባሪያ «ለሞት፣ ያውም ለመስቀል ሞት እንኳ ታዘዘ» (ፊልጵ. 2:8)::

የመጨረሻ ሳምንት ታሪኩን በምታጠናበት ጊዜ የተለያዩ ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጧቸውን ምላሾች በመመልከት ትደነቃለህ::

## 1. በቢታንያ- ተመሰገነ (ማርቆስ 14:1-11)

ይህ ክስተት የተፈጸመው ከፋሲካ ስድስት ቀናት ቀደም ብሎ ነበር:: ይህም ጌታ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ከመግባቱ በፊት በዋለው ዓርብ ዕለት የተፈጸመ መሆኑን ያስገነዝበናል (ዮሐ. 12:1):: ማርቆስ ይህንን ታሪክ ኢየሱስን ለማሰር በሚደረጉት የሤራ ውጥኖች መካከል በማስፈሩ፣ የይሁዳንና የአይሁድ መሪዎችን የማሳሳቻ ተግባራት ከማርያም ፍቅርና ታማኝነት ጋር አነጻጽሯል:: የእነዚህ ሰዎች ተግባራት አስቀያሚነት የመሥዋዕቷን ውበት ይበልጥ አፍክቶታል::

ማርቆስና ማቴዎስ የሴትየዋን ስም አይጠቅሱም:: ዮሐንስ ግን ይህች ሴት የማርታና የአልዓዛር እኅት የሆነችው የቢታንያዋ ማርያም እንደሆነች ገልጿል (ዮሐ. 11:1-2):: ማርያም በወንጌላት ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሳለች:: በተጠቀሰችባቸው ጊዜያት ሁሉ ከኢየሱስ እግር ሥር እናገኛታለን (ሉቃስ 10:38-42፤ ዮሐ. 11:31-32፤ 12:1-8):: ማርያም ከእግሩ ሥር ተቀምጣ ቃሉን በመስማት ከጌታ ጋር የቅርብ ኅብረት መሥርታ ነበር:: ስለሆነም፣ ሁላችንም ልንከተላት የሚገባ መልካም ምሳሌ ናት::

ማርያም ጌታን ሽቶ የቀባችበት ክስተት በሉቃስ 7:36-50 ከተጠቀሰው ተመሳሳይ ተግባር የተለየ ነው:: በፈሪሳዊው ስምዖን

ቤት ውስጥ ጌታን ሽቱ የቀባችው የቀድሞዋ ጋለሞታ ብዙ ኃጢአቷን ይቅር ስላለላት ፍቅሯን በዚህ መልክ ገልጻለች:: ለምጹ በተፈወሰለት ስምዖን ቤት ማርያም ጌታ ወደ መስቀል ሞቱ ከመሄዱ በፊት ፍቅሯን ገልጻለች:: ራሱን (ማር. 14:3) እና እግሮቹን (ዮሐ.12:3) በመቀባት ሥጋውን ለቀብር አዘጋጀች:: በዚህም ገና በሕይወት ሳለ ፍቅሯን ገለጸችለት::

ለጌታ ያበረከተችው ውድ ስጦታ ነበር:: ይህ ከሕንድ የሚገባ ሽቶ በመሆኑ፣ አንድ ጠርሙስ ሙሉ ሽቶ የአንድ ተራ ሠራተኛ ዓመታዊ ገቢ ያህል ነበር:: ማርያም ስጦታውን ያበረከተችለት በልግስናና በፍቅር ነበር:: ፍቅሯን ለክርስቶስ በይፋ ለማሳየት አላፈረችም::

ይህ የአምልኮት ተግባሯ ሦስት ውጤቶችን አስከትሏል:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ ቤቱ በሽቶው ውብ መዓዛ ታወደ (ዮሐ. 12:3፤ በተጨማሪም፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 2:15-16ን አንብብ):: ኢየሱስ ክርስቶስ በሚወደድበትና በሚመለክበት ቤት ውስጥ ሁሉ ሁልጊዜም «መንፈሳዊ መዓዛ» አለ::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ደቀ መዛሙርቱ በይሁዳ መሪነት ተነሣሥተው ማርያም ገንዘቡን በማባከኗ ተቿት:: ይሁዳ ገንዘቡን ለራሱ ለመውሰድ እየፈለገ (ዮሐ. 12:4-6)፣ ለድሆች ግድ ያለው ይመስል የተቃውሞ አሳብ አቀረበ:: ከስድስት ቀናት በኋላ እንኳ በሰገነቱ ላይ ሳሉ ደቀ መዛሙርቱ አሁንም ይሁዳ ለድሆች ያስበ መስሏቸው ነበር (ዮሐ. 13:21-30):: በማርቆስ 14:4 «ማባከን» ተብሎ የተተረጐመው ቃል በዮሐንስ 17:12 *ይሁዳ* ሕይወቱን እንዳባከነ ለማመልከት *ማገልገሉ* አስገራሚ ነው:: ይሁዳ ማርያም «ገንዘብ አባክናለች» እያለ ቢወቅሳትም፣ የራሱን ሕይወት ከማባከን አልተቈጠበም

<u>ሦስተኛ</u>፣ ኢየሱስ ማርያምን አመስግኖ ውድ ስጦታዋን ተቀበለ:: የይሁዳን ልብ ስለሚያውቅ፣ ሌሎች ደቀ መዛሙርት መጥፎ ምሳሌነቱን ለምን እንደ ተከተሉ ተረድቷል:: የማርያምንም ልብ ያውቅ ስለነበር ፈጥኖ ከትችት ተከላከላት (ሮሜ 8:33-39):: ስለ አምልኳችንና አገልግሎታችን ሌሎች የፈለጉትን ቢሉም፣ ዋናው ነገር ጌታን ደስ ማሰኘታችን ነው::

ሌሎች ሥራችንን በተሳሳተ መንገድ መረዳታቸውና መተቸታቸው ለክርስቶስ ፍቅራችንን እንዳናሳይ ሊያቅበን አይገባም:: የሚያሳስበን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታችን ብቻ ሊሆን ይገባል::

ማርያም በኢየሱስ ፊት ከሁሉም የሚሻል ስጦታዋን በማበርከቷ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚቀጥል «የበረከት ሞገድ» ጠንስሳለች:: ፍቅሯን በማካፈሏ ለኢየሱስ በረከት ሆናለች:: መልካም መዓዛ በመርጨቷ ለቤቱም በረከት ሆናለች:: ይህ የማርያም መልካም ተግባር ባይኖር ኖሮ መንደሯ ቢታንያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ላይኖራት ይችል ነበር:: የሥራዋ ታሪክ በተሰማ ጊዜ ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ በረከት ሆኗል:: ለዓለምም ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ ማርያም በረከት ሆናለች! ይህም የጌታ ትንቢት በትክክል መፈጸሙን ያመለክታል::

ማርያም ያላትን ከሁሉም የላቀ ስጦታዋን በፍቅርና በእምነት ነበር የሰጠችው፤ ይሁዳ ግን ከሁሉም የከፋ ስጦታውን ባለማመንና በጥላቻ ሰጠ:: ይህን በማድረጉም የአይሁድ መሪዎች በበዓል ሰሞን ምንም ሁከት ሳይፈጥሩ ኢየሱስን ለማሰር የሚችሉበትን መንገድ አመቻቸ:: ጌታውን በባሪያ ዋጋ ሸጠው (ዘጸ. 21:32 አንብቡ):: ይህም በታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ወራዳ የክሕደት ተግባር ነው::

## 2. በሰገነት ውስጥ- ተካደ (ማርቆስ 14:12-26)

የፋሲካ በግ የሚታረደው በኒሳን ወር (መጋቢት- ሚያዝያ) ሲሆን፣ በወሩ በአሥረኛው ቀን ተመርጦ ነውር እንዳይገኝበት ይመረመራል (ዘጸ. 12:3-6):: በጉ በቤተ መቅደሱ ክልል ታርዶ በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ እራት መበላት ነበረበት:: ለአይሁዶች፣ የፋሲካ በዓል የድሮ ድል ማስታወሻ ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን የሞቱ መታሰቢያ የሚሆን አዲስ እራት ይመሠርት ነበር::

ጴጥሮስና ዮሐንስ የእራቱን መዘጋጀት ሲከታተሉ አመሹ (ሉቃስ 22:8):: ይህ ብዙውን ጊዜ የሴቶች ሥራ በመሆኑ፣ ውኃ በማሰሮ የተሸከመ ወንድ ለይቶ ማግኘቱ ከባድ አልነበረም:: ይህ

ሰው የዮሐንስ ማርቆስ አባት ይሆን? ኢየሱስ የፋሲካን እራት የበላው በሰገነቱ ውስጥ በዮሐንስ ማርቆስ ቤት ይሆን? እነዚህ ጉጉት የሚጭሩ መላምቶች ቢሆኑም፣ እውነትነታቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ የለንም:: ነገር ግን የዮሐንስ ማርቆስ ቤት በኢየሩሳሌም የክርስቲያኖች መገናኛ ማዕከል እንደነበር እናውቃለን (የሐዋ. 12:12)::

የድሮው የፋሲካ ምግብ የበግ ጥብስ፣ ካልቦካ ሊጥ የተጋገረ ዳቦና መራራ ቅጠል ያለበት ነበር (ዘጸ. 12:8-20):: በጉ አይሁዶች የሞት መልአክ የበኩር ልጆቻቸውን እንዳይገድል ከመቃኖቻቸው ላይ የረጩትን ደም ያስታውሳቸዋል:: ካልቦካ ሊጥ የተጋገረው ዳቦ ከግብጽ በችኮላ መውጣታቸውን (ዘጸ. 12:39)፣ መራራ ቅጠል ደግሞ በግብጽ የፈርዖን ባሪያዎች ሆነው መሠቃየታቸውን ያመለክታል:: አይሁዶች በሆነ ወቅት ላይ በውኃ የቀጠኑ አራት ብርጭቆ ወይን መጠጣትን አክለዋል::

ለአይሁዶች አዲስ ቀን የሚጀምረው ከፀሐይ መጥለቅ ጀምሮ ስለሆነ፣ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በሰገነቱ ላይ የተቀመጡበት ቀን ዓርብ ዕለት ይሆናል:: ይህ የመጨረሻ ፋሲካው ነበር:: በዚያን ዕለት ነውር እንደሌለው የእግዚአብሔር በግ በመስቀል ላይ በመሞት ፋሲካው ይፈጸም ነበር (ዮሐ. 1:29፤ 1ኛ ቆሮ. 5:7፤ 1ኛ ጴጥ. 2:21-24)::

በማርቆስ 14:17 እና 18 መካከል ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበትና ራስን ዝቅ ስለማድረግ ያቀረበው ትምህርት አለ (ዮሐ. 13:1-20):: ኢየሱስ ይህንን ትምህርት ካስተማረ በኋላ፣ በመንፈሱ ታወከ:: ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ተናገረ:: ይህም ንግርት ስለ እርሱ የተነገረ መሆኑን ከሚያውቀው ይሁዳ በቀር ለደቀ መዛሙርቱ በሙሉ አስደነገጣቸው:: ኢየሱስ እስከ መጨረሻው ድረስ አሳልፎ የሚሰጠው ደቀ መዝሙር ማን እንደሆነ ለሌሎች ደቀ መዛሙርት አልተናገረም:: ይህንንም ያደረገው ይሁዳ ከኃጢአቱ ይመለስ ዘንድ ሰፊ ዕድል ለመስጠት ነበር:: እግሩን ሳይቀር አጠበለት:: ይሁዳ ጌታን አሳልፎ እንደሚሰጥ ጴጥሮስ ቢያውቅ ኖሮ፣ ምናልባትም ካልገደልሁት ሳይል አይቀርም ነበር::

አንዳንድ ሰዎች ይሁዳ ጌታን አሳልፎ የሰጠው ኃይሉን እንዲገልጥና የአይሁድን መንግሥት እንዲመሠርት ለመገፋፋት ነበር ሲሉ ይሁዳን ለመደገፍ ይጥራሉ:: ሌሎች ደግሞ ይሁዳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በታዛዥነት የፈጸመ አገልጋይ ነበር ይላሉ:: ነገር ግን ይሁዳ ሰማዕትም አገልጋይም አልነበረም:: ይሁዳ የራሱን ውሳኔ የወሰነ ተጠያቂ ግለሰብ ነው:: ይህንን በማድረጉ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሟል::) «አንድ ሰው ኢየሱስን አሳልፎ መስጠት ስለነበረበት!» (ይሁዳም ይህንን በመፈጸሙ ጀግና ነው ወይም ምሕረት የማይሰጠውና የቅድመ ውሳኔ ሰለባ ነበር ተብሎ መወሰድ የለበትም:: ይሁዳ የጠፋው ዛሬ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች በሚጠፉበት ዓይነት መንገድ ነው:: ይኸውም ኃጢአቱን ተናዝዞ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለማመኑ ነው (ዮሐ. 6:64-71፤ 13:10-11):: ዳግም ካልተወለድህ፣ አንድ ቀን ከእናቴ ማኅፀን ባልወጣሁ ብለህ ትማረራለህ::

ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ጌታን አሳልፈው እንደማይሰጡት ያውቁ ነበር:: «እኔ እሆንን?» የሚለው ጥያቄያቸው አሉታዊ ምላሽን የሚያመለክት መሆኑ ይህንን እውነት ያሳያል:: ብዙውን ጊዜ ከመካከላችን ታላቁ ማን ይሆን? እያሉ ሲከራከሩ የነበሩት ሰዎች አሁን ከመካከላችን ወራዳ ተግባር የሚፈጽመው ሰው ማን ይሆን? ይሉ ጀመር:: ኢየሱስ ይባስ ብሎ አሳልፎ የሰጠው ከእርሱ ጋር አብሮ እንደ ተመገበ ገለጸ:: በምሥራቃውያን ባሕል፣ ከአንድ ሰው ጋር አብሮ መብላት የወዳጅነትና የመተማመን ቃል ኪዳን ነበር:: አብረህ ከተመገብህ በኋላ ጋባዥህን አሳልፎ መስጠት እጅግ የከፋ የክፋት ተግባር ነበር:: ነገር ግን ይህም እንኳ የእግዚአብሔር ቃል ፍጻሜ ነበር [መዝ. (41):9]::

ዮሐንስ በቀኝ በኩል ወደ ጌታ ደረት ሲጠጋ፣ ይሁዳ ከበስተግራው የክብርን ስፍራ ይዞ ነበር (ዮሐ. 13:23):: ኢየሱስ ለይሁዳ እንጀራ አጥቅሶ መስጠቱ ይሁዳን እንደ ልዩ እንግዳው እንዳከበረው ያሳያል:: ይህም እንኳ የይሁዳን ልብ አልሰበረውም:: ምክንያቱም ጉርሻውን ከተቀበለ በኋላ ሰይጣን ገብቶበታል:: ይሁዳ ጌታን ለማስያዝ የሚችልበትን የመጨረሻ ዝግጅት ለማድረግ ከሰገነቱ ወጥቶ ሄደ:: በዚህ ጊዜም ሳይቀር ደቀ

መዛሙርቱ ይሁዳ ጌታን አሳልፎ እንደሚሰጥ አላወቁም ነበር (ዮሐ. 13:27-30):: በኋላ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ እስኪያዩት ድረስ በጭራሽ አልጠረጠሩትም ነበር::

ይሁዳ ከወጣ በኋላ፣ ኢየሱስ «ቅዱስ ቊርባን» ወይም «የጌታ እራት» የምንለውን ሥርዓት ጀመረ:: የጌታ እራት በግሪኩ «ማመስገን» ከሚል ቃል የመጣ ነው:: ከሦስተኛው የፋሲካ ጽዋ በኋላ፣ ኢየሱስ ካልቦካ ሊጥ ከተጋገሩት ዳቦዎች አንዱን አንሥቶ በመባረክ ለደቀ መዛሙርቱ ቁርሶ ሰጠ:: ከዚያም «ይህ ሥጋዬ ነው» አላቸው:: ከዚያም አራተኛውና የመጨረሻውን የፋሲካ ጽዋ በመባረክ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው:: ከዚያም «ይህ ደሜ ነው» አላቸው (1ኛ ቆሮ. 11:23-26 አንብብ)::

ዳቦና ወይን በእያንዳንዱ የምግብ ሰዓት ላይ የሚገኙ ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ነበሩ፣ ኢየሱስ ግን አዲስ ትርጒም ሰጥቷቸዋል:: ኢየሱስ «ይህ ሥጋዬ ነው» እና «ይህ ደሜ ነው» በሚልበት ጊዜ ዳቦውንም ሆነ ወይኑን ወደ አንድ ልዩ ነገር አልለወጠውም:: ደቀ መዛሙርቱ ዳቦውን በበሉት ጊዜ፣ ያው የለመዱት ዳቦ ነበር፤ ወይኑም ያው ወይን ነበር:: ነገር ግን ጌታ ለዳቦውና ለወይኑ አዲስ ትርጒም ስለሰጠ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሞቱ መታሰቢያዎች ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

እንግዲህ፣ ኢየሱስ በሞቱ የፈጸመው ተግባር ምንድን ነው? ኢየሱስ በመስቀል ላይ አሮጌውን ኪዳን ፈጽሞ አዲሱን መሥርቷል (ዕብ. 9-10):: አሮጌው ኪዳን የሚጸናው በእንስሳት ደም ሲሆን፣ አዲሱ ኪዳን በእግዚአብሔር ልጅ ደም ጸንቷል:: በደሙ የተመሠረተው አዲሱ ኪዳን አሮጌው ኪዳን ያልቻለውን ተግባር ፈጽሞታል:: ይኸውም ኃጢአትን ማስወገድና የአማኙን ልብና ሕይወት ማንጻት ነው:: ከኃጢአቶቻችን የዳንነው ሃይማኖታዊ ሥርዓትን በመካፈል ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችን በማመን ነው::

የጌታችን ትእዛዝም «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉ» የሚል ነበር (1ኛ ቆሮ. 11:24-25):: «መታሰቢያ» የሚለው ቃል «ማስታወሻ» ከሚለው የላቀ ነው:: አንድን ሰው ለማስታወስ አንድ ነገር ማድረግ ይቻላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕያው

ነው:: መታሰቢያ የሚለው ቃል ቀደም ሲል በተፈጸመ ክስተት ውስጥ የሚደረገውን የአሁን ጊዜ ተሳትፎ ያመለክታል:: ኢየሱስ ሕያው ስለሆነ፣ ቅዱስ ቊርባን በምንወስድበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ኅብረትን እናደርጋለን (1ኛ ቆሮ. 10:16-17):: ይህ ዳቦውና ወይኑ የሚያመጣው የሆነ «ምትሐታዊ» ልምምድ ሳይሆን፣ ክርስቶስንና የቅዱስ ቊርባንን ትርጉም በምንመረምርበት ጊዜ የምናገኘው መንፈሳዊ ልምምድ ነው (1ኛ ቆሮ. 11:27-34)::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በሰገነቱ ውስጥ ያደረጉት የመጨረሻው ነገር በመዝሙር 115-118 ላይ የተመሠረተውን ባሕላዊ የፋሲካ መዝሙር መዘመር ነበር:: ጌታችን በመስቀል ላይ ለመሞት ጥቂት ሰዓታት ብቻ ቀርተውት እያለ ሲዘምር ይታይህ!

## 3. በአትክልት ስፍራ - ተተወ (ማርቆስ 14:27-52)

ኢየሱስ ወደ ጌቴሴማኒ («የዘይት መጭመቂያ») ሲሄድ፣ ደቀ መዛሙርቱ እንደሚተዉት ተናገረ:: ነገር ግን ከትንሣኤው በኋላ በገሊላ እንደሚያገኛቸው አረጋገጠላቸው:: ቃሉን ለማስደገፍም፣ «እረኛውን ምታ፣ በጐቹም ይበተናሉ» የሚለውን ትንቢት ከዘካርያስ 13:7 ጠቀሰላቸው:: ነገር ግን አእምሮአቸውና ልባቸው ቃሉን ለመቀበልና ለማመን አልቻሉም ነበር:: ምክንያቱም ከሦስት ቀናት በኋላ የትንሣኤውን ዜና ለማመን ተቸግረው ነበር:: በዚህ ጊዜ መልአኩ በገሊላ እንገናኛለን የሚለውን የጌታ ቃል በመጥቀስ አስታውሷቸዋል (ማር. 16:6-7):: ቃሉን ሰምተው ቢያምኑ ኖሮ፣ ከብዙ ጭንቀት በተረፉና ጴጥሮስም ጌታን ባልከዳ ነበር::

ከዘካርያስ የተወሰደው ጥቅስ አይሁዶች ኢየሱስን በሚይዙበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መበተን እንዳለባቸው ያሳስባል:: እንዲያውም፣ ኢየሱስ ሊይዙት በቀረቡ ጊዜ፣ «እነዚህን (ደቀ መዛሙርት) ተዉአቸው!» ነበር ያለው (ዮሐ. 18:8):: ይህ በገሊላ አባባል፣ «በሉ፣ ከዚህ ውጡ» እንደ ማለት ነበር:: ጴጥሮስ በርቀት ጌታን መከተሉን የሚነቅፉ ጠንካራ ስብከቶች ሲሰበኩ ሰምቻለሁ:: እነዚህ ስብከቶች ግን ይህንን ክስተት ያልተገነዘቡ ናቸው:: በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ጭራሽ ኢየሱስን መከተል

አያስፈልገውም ነበር። ጴጥሮስ ጌታ የተናገረውን ቢሰማ ኖሮ፣ የሰውዬውን ጆሮ ከመቍረጥም ሆነ ጌታን ሦስት ጊዜ ከመካድ ይተርፍ ነበር።

ጴጥሮስ የኢየሱስን ትእዛዛት ከግል ሕይወቱ ጋር ለማዛመድ የሚቸገር ይመስላል። ጴጥሮስ ሌሎች ቢክዱህ እንኳ እስከ እስራት ወይም እስከ ሞት ድረስ አልለይህም ብሎ ነበር። ሌሎች ደቀ መዛሙርትም የጴጥሮስን ጕራ አስተጋቡ። በመሆኑም እርሱ ብቻ አልነበረም በቡድኑ አባላት መካከል በራስ መተማመን የተላበሰው። በመጨረሻው ግን ሁሉም በቃላቸው ሳይገኙ ቀሩ።

አብዛኞቹ ሰዎች ታላቅ መከራ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ሸክማቸውን ለመጋራት ከጐናቸው የሚቆም ሰው ይሻሉ። በመጋቢነት አገልግሎቴ፣ ብዙ ጊዜ በሆስፒታል ውስጥ ከተኙት ሕሙማን ጐን በመቀመጥ የሐኪሙን ሪፖርት አድምጫለሁ። ኢየሱስ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ መጠን፣ መስቀሉን በሚጋፈጥበት ጊዜ ሰዎች አብረውት እንዲሆኑ ፈለገ። ለዚህም ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን መረጠ። እነዚህ ሰዎች ወደ ኢያኢሮስ ቤት (ማር. 5:37) እና ኢየሱስ ወደ ተለወጠበት ተራራ (9:2) አብረውት የሄዱ ነበሩ። እነዚህ ሦስት ልምምዶች ከፊልጵስዩስ 3:10 ጋር ይስማማሉ። «እርሱን (ኢየሱስ የተለወጠበት ተራራ) እና የትንሣኤውን ኃይል (የኢያኢሮስ ቤት) እንዳውቅ፣ በመከራው እንድካፈል (የጌቴሴማኒ አትክልት ስፍራ)»።

ጌታችን በአትክልት ስፍራው ውስጥ ያጋጠመውን ትግል መረዳት የሚቻለው በመስቀል ላይ ከሚደርስበት ሁኔታ አንጻር ነው። ይኸውም ለእኛ ኃጢአት በመሆን (2ኛ ቆሮ. 5:21) የሕጉን መርገም የሚሸከም (ገላ. 3:13) መሆኑ ነው። ጌታን ያሠቃየውና ያሳዘነው ሥጋዊ መከራ ሳይሆን፣ በአባቱ የመተው አሳብ ነው(ማር. 15:34)። ይህ ኢየሱስ የሚጠጣው «ጽዋ» ነበር (ዮሐ. 18:11)። ዕብራውያን 5:7-9 እንደሚለው፣ እርሱ የጠየቀው ላለመሞት ሳይሆን ከሞት ለመዳን፣ ማለትም ሞቶ ለመነሣት ነበር። አብም ይህንኑ አድርጐለታል።

«አባ» የሚለው «አባቴ» የሚል ፍች የሚሰጥ የአረማይክ ቃል ነው። ይህ ቃል በጌታችንና በአባቱ መካከል ያለውን የቅርብ ግን ኙነት ያመለክታል። ይህ ቃል ለእኛም የሚሠራ ነው (ሮሜ 8:15፤ ገላ. 4:6)። ኢየሱስ አብ አንድን ነገር እንዲያደርግ እንዳልነገረው አስተውል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ጽኑ መተማመን ነበረው። ስለ ጉዳዩ በጸለየባቸው ሦስት ጊዜያት ለአብ ፈቃድ በፍቅር ራሱን አስገዝቷል።

በዚህ ጊዜ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ምን እያደረጉ ነበር? እያንቀላፉ ነበር? ከአንተ ጋር እሞታለሁ ያለው ጴጥሮስ አብሮት ሊቆይ እንኳ አልቻለም። ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን በመገሠጽ አስጠነቀቃቸው። «ንቁና ጸልዩ» የሚለው ምክር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ ይገኛል (ነህ. 4:9፤ ማር. 13:33፤ ኤፌ. 6:18፤ ቈላ. 4:2)። ይህም፣ «ነቅታችሁ ጸልዩ! ጠላት እየቀረበ ስለሆነ፣ መንፈሳዊ ዓይኖቻችሁን አትክደኑ!» ማለት ነው።

ጌታችን ለሦስተኛ ጊዜ ተኝተው ሲያገኛቸው፣ «እንግዲህስ ተ ኙ፣ ዕረፉም፤ ይበቃል ሰዓቲቱ ደርሳለች» ብሏል (ማር. 14:41)። ይህ ለዓለም ኃጢአት የሚሞትበት የመሠዊያው ጊዜ ነበር። በዚያች ሰዓት ይሁዳና የቤተ መቅደሱ ጠባቂ ኢየሱስን ለመያዝ መጡ። ይሁዳ ኢየሱስን ደጋግሞ በመሳም አሳልፎ ሰጠው። ምንኛ አሳዛኝ ግብዝነት ነው!

ይሁዳ ይህን ያህል የታጠቀ ሠራዊት አስከትሎ መምጣቱ እርሱም ሆነ የሃይማኖት መሪዎች የኢየሱስን ማንነት እንዳልተረዱ ያስረዳል። ኢየሱስ ለማምለጥ እንደሚሞክር፣ ወይም ደቀ መዛሙርቱ ለመዋጋት እንደሚሞክሩ ወይም ተአምር እንደሚሠራ አስበው ነበር። ጌታችን በማርቆስ 14:49 የተናገረው ቃል እርሱ ሁኔታውን በመቈጣጠር ላይ እንደነበረ ያረጋግጣል። ምክንያቱም ቀደም ሲል ያልያዙት ሰዓቱ ስላልደረሰ ነበርና።

ጴጥሮስ የማልኮስን ጆሮ መቍረጡ የሞኝነት ተግባር ነበር (ዮሐ. 18:10)። ምክንያቱም መንፈሳዊ ጦርነቶችን በሥጋዊ የጦር መሣሪያዎች ልንዋጋ አንችልም (2ኛ ቆሮ. 10:3-5)። ትክክል ባልሆነ ጊዜ፣ ትክክል ያልሆነውን መሣሪያ፣ ትክክል

ላልሆነ ዓላማ፣ ትክክል ባልሆነ ልብ ተጠቀመ። የማልኮስን ጆሮ ባይፈውስ ኖሮ፣ ጴጥሮስም ሊያዝ ይችል ነበር፤ በጎልጎታ ላይም አራት ሰዎች በተሰቀሉ ነበር።

በዚህች ነጥብ ላይ፣ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ትተው ሸሹ። ወደ አትክልት ስፍራው መጥቶ ኢየሱስ ሲያዝ የተመለከተ በስሙ ያልተጠቀሰው ወጣትም እንደዚሁ ሸሸ። ይህ ወጣት ዮሐንስ ማርቆስ ነበርን? የምናውቀው ነገር የለም። ነገር ግን ይህ ታሪክ የተገለጸው በዚህ ወንጌል ውስጥ ብቻ በመሆኑ፣ ምናልባትም ደራሲው ስለ ራሱ ይሆናል የጻፈው። ሰገነቱ የማርቆስ ቤት ከሆነ፣ ምናልባትም ይሁዳ ወታደሮቹን መጀመሪያ የወሰደው ወደዚያው ሳይሆን አይቀርም። ዮሐንስ ማርቆስ የሆነ ልብስ ጣል አድርጎ ወታደሮቹን ተከትሎ እስከ አትክልት ስፍራው ሄዶ ይሆናል። ወታደሮቹ ሊይዙት ሞክረው ሊሆን ይችላል። እናም ሸሸ።

ደቀ መዛሙርቱ ከተበታተኑ በኋላ የእግዚአብሔር ባሪያ ብቻውን ቀረ። «አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም» (ዮሐ. 16:32)። ብዙም ሳይቆይ አብም እንኳ ይተወዋል።

### 4. በሊቀ ካህናቱ ቢሮ- ተቀባይነት አጣ (ማርቆስ 14:53-72)

የአይሁድም ሆኑ የሮማውያን ምርመራዎች ሦስት ደረጃዎች ነበሯቸው። የአይሁድ ምርመራ የተጀመረው የቀድሞው ሊቀ ካህናት በነበረው በሐና ነበር (ዮሐ. 18:13-24)። ከዚያም የምስክሮችን ቃል ለመስማት ሸንጎው ተሰበሰበ (ማር. 14:53-65)። ማለዳ ደግሞ የመጨረሻው የኩነኔ ድምፅ ተሰጠ (15:1)። ከዚያም ኢየሱስ ወደ ጲላጦስ ተላከ (ማር. 15:1-5፤ ዮሐ. 18:28-38)። እርሱም ወደ ሄሮድስ ላከው (ሉቃስ 23:6-12)። ሄሮድስም መልሶ ወደ ጲላጦስ ላከው (ማር. 15:6-15፤ ዮሐ. 18:39-19:6)። ጲላጦስ የሕዝቡን ሁከት ለማርገብ ሲል ኢየሱስን ለስቅላት አሳልፎ ሰጠ።

ወታደሮቹ ከሊቀ ካህናቱ ቢሮ በደረሱ ጊዜ፣ የጌታን ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያዎች ልብ ያላሉት ዮሐንስና ጴጥሮስ ሕዝቡን ተከትለው ወደ ግቢ ገቡ። በዚያን ሌሊት ኢየሱስ የደም ጠብታ የሚመስል ላብ ይወጣው ነበር (ሉቃስ 22:44)፤ ጴጥሮስ

ግን ብርዱ አቆራምዶት የጠላትን እሳት ይሞቅ ነበር! ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ምርመራውን ሊመለከቱ ባይችሉም፣ በቂ በሆነ ቅርበት የፍርዱን ውሳኔ አይተዋል (ማቴ. 26:58፤ ዮሐ. 18:15)::

ሐና ኢየሱስን ከመረመረና ከሰደበ በኋላ አማቹ ወደ ሆነው ሊቀ ካህናት ቀያፋ አስሮ ላከው:: ሸንጎው ተሰብስቦ ምስክሮቹ ተዘጋጅተው ነበር:: ተከሳሹን በበደለኛነት ፈርጆ የሞት ቅጣት ለመፈጸም ቢያንስ የሁለት ምስክሮች መገኘት ወሳኝ ነበር (ዘዳግ. 17:6):: ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ላይ ቢመሰክሩም፣ ቃላቸው የተለያየ በመሆኑ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ:: ሃይማኖታዊ መሪዎች ሰዎች እንዲዋሹ ማበረታታቸው ምንኛ አሳዛኝ ነው! ለዚያውም በተቀደሰ ልዩ ሰሞን::

ይህ ሁሉ የውሸት ክስ ሲቀርብበት ጌታችን ትንፍሽ አላለም (ኢሳ. 53:7፤ 1ኛ ጴጥ. 2:23):: ነገር ግን ሊቀ ካህናቱ በእግዚአብሔር ስም እንዲመልስ በጠየቀው ጊዜ የግድ መናገር ነበረበት:: በዚህም ጊዜ በግልጽ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መሰከረ:: «የሰው ልጅ» የሚለው ሐረግ መሢሐዊ በመሆኑ (ዳን. 7:13)፣ የሸንጎው አባላት ኢየሱስ ምን እያለ እንደ ሆነ ተገንዝበው ነበር:: በሥጋ የተገለጥሁ አምላክ ነኝ እያለ ነበር! ይህ ለአይሁዶች ስድብ በመሆኑ፣ሞት የሚገባው ጥፋተኛ መሆኑን በየኑ:: ለሸንጎው በታላላቅ ጉዳዮች ላይ በሌሊት ድምፅ መስጠቱ ተገቢ ስላልሆነ፣ እንደገና በጠዋት ተሰብስበው ይፋዊ ፍርድ ሰጡ (ማር. 15:1)::

ሰዎች በጌታችን ላይ እየተሳለቁና እያጉላሉት ሳለ፣ ጴጥሮስ በታችኛው ግቢ ለይተው እንዳያውቁት ለማምለጥ እየጣረ ነበር:: የጌታን ማስጠንቀቂያ ቢሰማ ኖሮ፣ ወደ ፈተና ከመግባትና ጌታውን ሦስት ጊዜ ከመካድ በተቆጠበ ነበር:: የእርሱ ሕይወት ለሁላችንም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው:: ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር የነበረ ሐዋርያ ጌታውን ከካደ፣ እኛስ በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ብንገኝ ምን እናደርግ ይሆን? የማርቆስን ወንጌል ያነበቡት የሮም አማኞች ከዚህ ታሪክ ጠቃሚ ትምህርት ማግኘታቸው የማይቀር ነው:: ምክንያቱም በቅርቡ ከስደት እቶን ውስጥ ይገቡ ነበርና::

በመጀመሪያ፣ ከሊቀ ካህናቱ አገልጋይ ሴቶች አንዷ ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር መሆኑን ተናገረች:: እርሱ ግን ስለ ኢየሱስ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ገለጸ:: ወዲያውም ዶሮ ጮኸ:: ሌላዋ አገልጋይ እዚያው ለተቀመጡት ስለ ጴጥሮስ ተናገረች:: እርሱ ግን ካደ:: በመጨረሻም አንድ ሰው ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንዱ መሆኑን ተናገረ:: በዚያ የቆሙትም ሁሉ ይህንኑ ተናገሩ:: ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደማያውቅ ምሎ ተናገረ:: በዚህ ጊዜ ዶሮ ለሁለተኛ ጊዜ ጮኸ:: የጌታም ትንቢት ተፈጸመ (ማር. 14:30 አንብብ)::

ይሁንና፣ ጴጥሮስን የወቀሰው የጌታን ቃል ማስታወሱ እንጂ የዶሮው መጮኽ አልነበረም:: ሁልጊዜም ወደ ሰዎች ልብ ዘልቆ በመግባት እውነተኛ ንስሐን የሚያስከትለው ቃሉ ነው :: ጴጥሮስ ኢየሱስ የተናገረውንና እርሱ የፈጸመውን ተግባር አስታወሰ:: ከዚያም ኢየሱስ ወደ ጲላጦስ አዳራሽ እየተወሰደ ሳለ ዘወር ብሎ አየው:: ይህ የፍቅር እይታ ነበር የተጐዳ ፍቅር (ሉቃስ 22:61):: ጴጥሮስ ከልቡ አዘነና ቶሎ ወደ ውጭ ወጥቶ አምርሮ አለቀሰ::

በጴጥሮስ ላይ ከመፍረዳችን በፊት የራሳችንን ሕይወት መመርመር ይኖርብናል:: ስንት ጊዜ ጌታን በመካድ ለሌሎች ወንጌል የምንመሰክርባቸውን ዕድሎች ሳንጠቀም ቀርተናል? እኛ ም እንደ ጴጥሮስ ማዳመጥ ሲኖርብን በመናገር፣ መታዘዝ ሲኖርብን በመከራከር፣ መጸለይ ሲኖርብን በመተኛትና መገዛት ሲኖርብን በመዋጋት ጥፋትን እንፈጽማለን? ጴጥሮስ በኃጢአቱ በመጸጸት አልቅሷል፤ ጌታም ይቅር ብሎታል:: ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ከጴጥሮስ ጋር በግል ተነጋግሯል (ሉቃስ 24:34):: ከዚያም ኢየሱስ በገሊላ ደቀ መዛሙርቱን ባገኘ ጊዜ ጴጥሮስ በይፋ ኑዛዜ እንዲያደርግ ረድቶታል (ዮሐ. 21)::

## 5. በጲላጦስ አዳራሽ- ተፈረደበት (ማርቆስ 15:1-20)

የጠዋት ስብሰባቸው ተጠናቅቆ ውሳኔው በይፋ እንደ ተመዘገበ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን የሮም ገዥ ለነበረው ለጴንጤናዊው ጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት:: ጴንጤናዊው ጲላጦስ ብዙውን ጊዜ የሚሠራው በቂሣርያ ቢሆንም፣ በየዓመቱ ለበዓል ወደ

ኢየሩሳሌም የመምጣት ልማድ ነበረው:: ወደ ኢየሩሳሌም በሚጐርፍ እጅግ ብዙ ሰዎች መካከል ችግር ከተፈጠረ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ስለሚኖር፣ የእርሱ መገኘት አንዳንድ አይሁዶችን ደስ ያሰኝ ነበር:: የሮም ገዥዎች ፍርድ የሚሰጡት ጠዋት ስለሆነ፣ እስረኛውን ባመጡለት ጊዜ በሚገባ ተዘጋጅቶ ነበር::

የአይሁድ ሸንጐ ኢየሱስ ሞት የሚገባው ወንጀለኛ መሆኑን ለጲላጦስ አስረድቶ ማሳመን ነበረበት (ዮሐ. 18:31-32):: ከፖለቲካዊ ምግባረ ብልሹነታቸው ባሻገር፣ ብዙ የሮም ባለሥልጣናት ፍትሕን ይወዱና በእስረኞች ላይ ተገቢውን ፍርድ ለማስተላለፍ ይጥሩ ነበር:: በተጨማሪም፣ ጲላጦስ ለአይሁዶች ትልቅ ፍቅር ስላልነበረው የሚፈልጉትን የማድረግ ፍላጐት አልነበረውም:: የአይሁድ መሪዎች ፍትሕን የማስፈን ፍላጐት እንዳልነበራቸው ያውቅ ነበር:: እነርሱ የፈለጉት ነገር ቢኖር ብቀላን ነበር (ማር. 15:10)::

ዮሐንስ ስለ ሮም ምርመራ ሰፊ ዝርዝር ጽፏል:: የሁሉንም ወንጌላት ዝርዝር አንድ ላይ በምናዋህድበት ጊዜ፣ ጲላጦስ ከኢየሱስ ላይ ምንም ዓይነት ጥፋት አለማግኘቱን በተደጋጋሚ ሲገልጽ እንመለከታለን (ዮሐ. 18:38፤ ሉቃስ 23:14፤ ዮሐ. 19:4፤ ሉቃስ 23:22፤ ማቴ. 27:24):: ችግሩ ለሚያምንበት ነገር የመቆም ቆራጥነት አልነበረውም:: የሕዝቡን ሁከት ለማርገብ ስለፈለገ (ማቴ. 27:24)፣ ደስ የሚያሰኛቸውን እርምጃ ለመውሰድ ተገደደ (ማር. 15:15):: ጲላጦስ የፈለገው የእርምጃውን ትክክለኛነት ሳይሆን፣ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን ነበር::

የአይሁድ ሸንጐ ለጲላጦስ የሚያቀርበው አንድ ትልቅ ክስ ብቻ ነበር:: ይኸውም ኢየሱስ ንጉሥ ነኝ ብሎ ሕዝቡን እንዳነሣሣ የሚያስረዳ ነበር:: ኢየሱስ የሮምን ሥልጣን የሚጋፋ አደገኛና ዓመጸኛ ነው ብለው ከሰሱት:: ጲላጦስ የተለያዩ ጥያቄዎችን በሚያቀርብለት ወቅት፣ ጌታችን ምንም አልተናገረም:: ነገር ግን የካህናት አለቆች የገዥውን ተቃውሞ ለማርገብ በመጣር የተለያዩ ክሶችን ይደረድሩበት ጀመር::

ጲላጦስ ኢየሱስን የገሊላ ገዥ ወደሆነው ሄሮድስ በመላክ ውሳኔ ላለመስጠት ጣረ ( ሉቃስ 23፡6-12)፡፡ ሄሮድስ ግን በኢየሱስ ላይ ከተሳለቀ በኋላ ወደ ጲላጦስ መልሶ ላከው፡፡ ከዚያም ገዥው ለሕዝቡ ምርጫ ሰጣቸው-- ከናዝሬቱ ኢየሱስና ነፍሰ ገዳይ ወንበዴ ከነበረው በርባን አንዱን ሊፈታላቸው እንደሚችል ገለጸ፡፡ ይህንን ምርጫ ያቀረበው ሕዝቡ ኢየሱስ ይለቀቅልን እንደሚሉ በማሰብ ነበረ፡፡ ነገር ግን የካህናት አለቆች ሕዝቡን በጥንቃቄ ስላዘጋጁ (ማር. 15፡11)፣ በርባን እንዲለቀቅና ኢየሱስ እንዲሰቀል ጠየቁ፡፡

በመቀጠልም፣ ገዥው ሌላ ስልት ተለመ፡፡ እስረኛውን በመግረፍ ሕዝቡ ሥቃዩን አይተው እንደሚያዝኑለት አሰበ (ቊ. 15፤ ዮሐ. 19፡ ከ1 ጀምሮ)፡፡ ትልሙ ግን አልያዘለትም፡፡ ሕዝቡ ኢየሱስ እንዲሰቀል አብዝተው ጮኹ፡፡ በመሆኑም፣ ገዥው ኢየሱስ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው፡፡

ከዚያ በኋላ ወታደሮቹ በኢየሱስ ላይ በመሳለቅ፣ ምራቃቸውን በመትፋትና ከፊቱ እየተንበረከኩ በመስገድ ቀለዱበት፡፡ የሮም ወታደሮች ንጉሥ ነኝ ባለ አይሁዳዊ ላይ መቀለዳቸው ግልጽ ነው! «ከቄሣር ሌላ ንጉሥ የለንም!» (ዮሐ. 19፡12-15)፡፡ ጌታችን የተቃውሞ ምልክት ሳያሳይ በዝምታ ተሠቃየ፡፡ ይህም የማርቆስ አንባቢዎች መንግሥታዊ ስደትን ለመጋፈጥ የሚጠቀሙበት ትምህርት ነበር (1ኛ ጴጥ. 2፡21-24)፡፡

እስካሁን ሕዝቡ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ከሁሉ የከፋውን በደል ገና አልፈጸሙም፡፡ ከዚህ በኋላ ከከተማዪቱ ውጭ ወስደው በመስቀል ላይ ይቸነክሩታል፡፡ የእግዚአብሔርም ባሪያ ለእነዚሁ ለሚያሠቃዩት ሰዎች ኃጢአት ይሞታል፡፡

# 12

# የእግዚአብሔር ባሪያ ሥራውን ፈጸመ

## ማርቆስ 15:21-16:20

ሴሲል ሮዴስ ብሪታንያ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ለምታካሂደው የቅኝ ግዛት ተግባርና ለአልማዝ ሥራ ሕይወታቸውን ሰጥተው አገልግለዋል። ሮዴስ የሞቱት ገና ኀምሳ ዓመት ሳይሞላቸው ነበር። የመጨረሻ ቃላቸው፣ «ጥቂት ብቻ ሠርቻለሁ። ገና ብዙ ይቀረኛል» የሚል ነበር።

ኢየሱስ ለአባቱ፣ «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ብሏል (ዮሐ. 17:4)። ሁላችንም ከሕይወታችን መጨረሻ ላይ እንዲህ ዓይነት ሪፖርት ለመስጠት ብንችል ምንኛ መልካም ነው። ሥራውን ፈጽመን ስሙን እንዳከበርን ማወቃችን የኋላችንን በምስጋና፣ የፊታችንን ደግሞ በደስታና በመጠባበቅ ስሜት ለመመልከት ያስችለናል።

በዚህ የማርቆስ ወንጌል የማጠቃለያ ክፍል ውስጥ የተገለጹት አራት ነገሮች የወንጌሉን ታሪክ ጡዘትና ታሪካዊ መሠረት ያስጨብጡናል (1ኛ ቆሮ. 15:1-8)።

## 1. የእግዚአብሔር ባሪያ አሟሟት (ማርቆስ 15:21-41)

በዚህኛው የማርቆስ ወንጌል ውስጥ ሦስት ሰዓታት ተጠቅሰዋል-- ሦስተኛ (ቍ. 25)፣ ስድስተኛ (ቍ. 33) እና ዘጠነኛ ሰዓት (ቍ. 33-34)። አይሁዶች ቀን የሚቆጥሩት ከጠዋቱ 12 እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ነበር። ስለሆነም፣ ሦስተኛው ሰዓት 3 ሰዓት ጠዋት፣ ስድስተኛው ሰዓት ቀትር፣ ዘጠነኛው ሰዓት ከቀትር በኋላ 9 ሰዓት መሆኑን እንረዳለን። ማርቆስ የአይሁዶችን የሰዓት አቆጣጠር ሲከተል፣ ዮሐንስ የሮማውያንን የጊዜ አቆጣጠር ተጠቅሟል። በዮሐንስ 19:14 ስድስት ሰዓት የሚለው ከጠዋቱ 12 ሰዓት ነው።

*ሦስተኛው ሰዓት* (15:21-32)። ሕጉ ወንጀለኛው መስቀሉን ተሸክሞ ወደሚሰቀልበት ስፍራ እንዲሄድ ይደነግጋል። በኢየሱስም ላይ የተፈጸመው ይኸው ነበር። መስቀሉን ተሸክሞ ከጲላጦስ ቤት ቢወጣም (ዮሐ. 19:16-17)፣ ብዙ ርቀት

ተሸክሞት ሊሄድ አልቻለም:: ስለሆነም፣ ወታደሮች የቀሬናው ስምዖን መስቀሉን እንዲሸከምለት አስገደዱት:: የሮም ባለሥልጣናት ሰዎች የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ የማስገደድ መብት የነበራቸው ሲሆን፣ ይህን መብታቸውን የሚጠቀሙበት መንገድ አይሁዶችን ያበሳጭ ነበር (ማቴ. 5:41)::

ጌታችን ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የታገሣቸውን ነገሮች ሁሉ ስንመለከት፣ ዝም ብሎ እንዲሁ አይደለም:: 10,000 መላእክትን ሊጠራ ሲችል፣ መከራውን በፈቃደኛነት ተሸክሞልናል:: ከዚህ ተግባር በስተጀርባ ላቅ ያለ ዓላማ ነበረ:: ወንጀለኛው መስቀሉን እንዲሸከም ቢደረግም ጥፋተኛ በመሆኑ ነበር:: *ጌታችን ግን ጥፋተኛ አልነበረም::* እኛ ጥፋተኞች ስለሆንን፣ ስምዖን በእኛ ፋንታ መስቀሉን ተሸክሟል:: ስምዖን ጴጥሮስ ከጌታ ጋር ወደ እስራትና ሞት ለመሄድ ፎክሮ ነበር (ሉቃስ 22:33)፣ ነገር ግን ጌታን የረዳው የቀሬናው ስምዖን እንጂ ስምዖን ጴጥሮስ አልነበረም::

ሃሪ ትሩማን ለእናቱ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች በአንዱ ውስጥ፣ «ፕሬዚዳንቱን ለማየት ወደ ኋይት ሐውስ ሄጄ ፕሬዚዳንቱ እኔ መሆኔን አወቅሁ» ብሏል:: ስምዖን የፋሲካ በዓል በማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ (የሐዋ. 2:10፤ 6:9)፣ ከፋሲካው በግ ጋር ተገናኝቶ ዕርፍ! ስምዖን ጌታን አምኖ ወደ ቤቱ እንደሄደና ሁለት ልጆቹን ወደ ጌታ እንደ መራ ለማመን የሚያስችል ምክንያት አለን:: ወንጌሉን ማርቆስ ከጻፈላቸው ሮማውያን መካከል አለጥርጥር ብዙዎቹ አሌክሳንደርና ሩፎስን ያውቁ ነበር (ማቴ. 16:13)፤ ምናልባትም ስምዖንንም ሳይቀር ሳያውቁት አይቀርም::

*ጎልጎታ* «የራስ ቅል» የሚል ፍች ያለው የዕብራይስጥ ቃል ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስፍራው ለምን በዚህ ስም እንደ ተጠራ የሚያስረዳ ምንባብ አልተጠቀሰም:: ዛሬ ወደ እስራኤል የሚሄዱ ጐብኝዎች «የጐርደን ጎልጎታ» የተባለውን ስፍራ ይመለከታሉ:: ይህም የራስ ቅል ገጽታ ያለው ነው:: አስጐብኝዎቹ በቅዱስ መቃብሩ ውስጥ የሚገኘውን ሌላ ስፍራም ለጎብኝዎች ያሳያሉ:: የተሰቀለበትን ትክክለኛ ስፍራ ግን አናውቅም:: ስፍራውን ማወቁም አስፈላጊ አይደለም:: የተሰቀለው

ከከተማዪቱ ቅጥር ውጭ ነበር። ይህም የውርደት ስፍራ ነው (ዕብ. 13:12-13)። የሞተውም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ነው።

ለሚሞቱ ሰዎች ሥቃያቸውን የሚያስታግሥ ከምጣጤ መስጠት የተለመደ ተግባር ነበር (ምሳሌ 31:6)፣ ጌታችን ግን ሊጠጣው አልፈለገም። በአንድ በኩል፣ የአብ ፈቃድ እና የደኅንነትን ሥራ በሚፈጽምበት ጊዜ በሙሉ አእምሮው ለመሆን ፈልጕ ነበር። ምንም ዓይነት የማቋረጫ መንገድ ሳይጠቀም በእኛ ፋንታ ሊሠቃይ መረጠ። የበደልን ጽዋ ይጠጣ ዘንድ የኃዘኔታን ጽዋ ላለመጠጣት ወሰነ (ማቴ. 26:36-43)። ይህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንፈጽምና መከራውን ስንካፈል (ፊልጵ. 3:10)፣ ሁላችንም ልንከተለው የሚገባን ምንኛ ግሩም ምሳሌነት ነው!

ከወንጌላት ጸሐፊዎች ማናቸውም ስለ ስቅለቱ ዝርዝር አፈጻጸም አልጻፉም፣ መጻፉም አስፈላጊ አይደለም። ዓላማቸው ልባችንን ማራራት ሳይሆን፣ እምነታችንን ማረጋገጥ ነው። ከአንባቢዎቻቸው ብዙዎቹ ስቅለቱን በስፍራው ተገኝተው አይተው ሊሆን ይችላል። ስለሆነም፣ ዝርዝር ማብራሪያው አስፈላጊ አይሆንም። ስቅለት በጨዋ ማኅበረሰብ ውስጥ ለውይይት የማይቀርብ አስጨናቂ ክስተት ነበር። ይህም ዛሬ በጋስ ቻምበር ወይም በኤሌክትሪክ ወንበር የሚገደሉትን ሰዎች ጉዳይ እያነሡ እንደሚወያዩት ያለ አሰቃቂ ነገር ነበር። ስቅላት ሰዎች ከፈጠሯቸው የመግደያ ዘዴዎች ሁሉ የከፋ ነበር። የጌታችንን የመስቀል ላይ ሥቃይ የሚገልጸውን መዝሙር 22ን አንብብ።

ብዙውን ጊዜ አንድ ወንጀለኛ በሚሰቀልበት ጊዜ የተከሰሰበት ጽሑፍ ከመስቀሉ ላይ ተጽፎ ይሰቀል ነበር። ጲላጦስም ኢየሱስ የተከሰሰበትን ወንጀል ጽፎ ከመስቀሉ ላይ አኖረ። ጽሑፉም፣ «የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ» የሚል ነበር። የአይሁድ መሪዎች ተቃውሟቸውን ቢያሰሙም፣ ጲላጦስ አሳቡን ለመቀየር አልፈለገም (ዮሐ. 19:19-22)። ይህ የመጀመሪያው ምልክት ንስሐ የገባውን ሌባ ልብ ያነሣሣ ይመስላል (ሉቃስ 23:39-43)። ምናልባትም፣ «ስሙ ኢየሱስ ከሆነ፣ እርሱ አዳኝ ነው። አገሩ ናዝሬት ከሆነ፣ ከተናቁ ሰዎች ጋር መቆጠሩ አይቀርም (ዮሐ. 1:46)። መንግሥት ካለው ለእኔ ስፍራ ይኖረዋል!»

ኢየሱስን የሚሰቅሉ ወታደሮች የሥራ ግዴታቸውን ከመወጣት አልፈው በጌታ ልብስ ላይ ዕጣ በመጣጣላቸው የትንቢትን ቃል ፈጽመዋል [መዝ. (22):18]:: ንጹሕ የእግዚአብሔር ልጅ በሁለት ወንጀለኞች መካከል መሰቀሉም የትንቢትን ቃል ፈጽሟል (ኢሳ. 53:12፤ በተጨማሪም ሉቃስ 22:37ን አንብብ):: «ሌቦቹ»ን ለመግለጽ ያገለገለው ቃል በዮሐንስ 18:40 ወንበዴ ተብሏል:: ቃሉ በርባንን የሚያመለክት ስለሆነ፣ ምናልባት እነዚህም ሁለት ሰዎች የበርባን የዓማፅያን ቡድን አባላት ሳይሆኑ አይቀሩም::

የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን እጅግ በመጥላታቸው እስከ ጎልጎታ ተጉዘው በእርሱ ላይ መሳለቃቸው አስገራሚ ነው:: ቶማስ ካርላይል መሳለቅ «የዲያብሎስ ቋንቋ» ነው ብሎአል:: በተለይ በዚህ የሃይማኖት መሪዎች ሁኔታ ላይ የካርላይል አገላለጽ በትክክል ይሠራል:: በአካባቢው የሚተላለፉ ሥራ ፈት ተመልካቾች የመሪዎቻቸውን ምሳሌነት ተከትለው በጌታችን ሥቃይ ላይ ስላቅ ጨመሩ:: በነቢይነቱ (ማር. 15:29)፣ በአዳኝነቱ (ቍ. 31) እና በንጉሥነቱ (ቍ. 32) ላይ ተሳልቀዋል:: ምናልባትም «ሌሎችን አዳነ!» የሚለው ምፀታቸው አንደኛውን ሌባ ለእምነት ያነሣሣው ይመስላል:: ምናልባትም ሌባው፣ «ሌሎችን ካዳነ፣ እኔንም ሊያድን ይችላል!» ብሎ አስቦ ይሆናል:: ይህም እግዚአብሔር የሰውን ቍጣ ለምስጋናው ሊያውል እንደሚችል ያሳያል [መዝ. (76):10]::

*ስድስተኛው ሰዓት* (ማር. 15:33):: ከቀትር ላይ ታላቅ ጨለማ በምድር ላይ ነገሠ:: ፍጥረት ሁሉ ለጌታ ሥቃይ ኀዘኑን ገለጸ:: ይህ ተአምር እንጂ እንደ ፀሐይ ግርዶሽ ያለ ተፈጥሯዊ ክስተት አልነበረም:: ጨረቃ ሙሉ በምትሆንበት የፋሲካ ሰሞን የፀሐይ ግርዶሽ ሊከሰት አይችልም:: በዚህ ጨለማ አማካኝነት እግዚአብሔር ለሕዝቡ አንድ መልእክት እያስተላለፈ ነበር::

ይህም በአንድ በኩል አይሁዶች ስለ መጀመሪያው ፋሲካ እንዲያስቡ ያደርጋቸው ነበር:: በግብጽ ዘጠነኛው መቅሠፍት ለሦስት ቀናት በምድር ላይ ጨለማ መስፈኑ ነበር:: ይህን ተከትሎ የመጨረሻው መቅሠፍት፣ ማለትም የበኵር ልጆች ሞት ደረሰ (ዘጸ. 10:22-11:9):: የጎልጎታው መስቀል የተወደደው

የእግዚአብሔር በኵር ልጅ (የእግዚአብሔር በግ) ሕይወቱን ለዓለም ኃጢአት እየሰጠ መሆኑን አውጇል:: በተጨማሪም፣ ፍርድ እየመጣ ስለሆነ ሰዎች ሊዘጋጁ እንደሚገባ የሚያሳስብ ነበር::

*ዘጠነኛው ሰዓት* (ማር. 15:34-41):: ጌታችን በመስቀል ላይ ሰባት ዐረፍተ ነገሮችን ተናግሯል:: ከእነዚህም መካከል ሦስቱን የተናገረው ከጨለማው በፊት ነበር:: እነዚህም፣ «አባቴ ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃስ 23:34)፤ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» (ሉቃስ 23:43)፤ እና «እነሆ፣ ልጅሽ. . . እነሆ፣ እናትህ» (ዮሐ. 19:26-27) ናቸው:: ጨለማው በተከሰተ ጊዜ በመስቀሉ ላይ ዝምታ ሆነ:: በዚህ ጊዜ ነበር እርሱ ለእኛ ኃጢአት የሆነው (2ኛ ቆሮ. 5:21)::

በዘጠነኛው ሰዓት፣ ኢየሱስ፣ «አባት ሆይ፣ አባት ሆይ፣ ለምን ተውከኝ?» [መዝ. (22):1 አንብብ] በማለት የነፍሱን ጣር አሰምቷል:: ጨለማው ኢየሱስ አብ በተወው ጊዜ የተጋፈጠውን ፍርድ በተምሳሌታዊ መንገድ ገልጿል:: እንደ ወትሮው ሕዝቡ የተናገረውን አልተረዱም ነበር:: ነቢዩ ኤልያስን የሚጠራ ነበር የመሰላቸው:: ጨለማው በምድር ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሰዎች አእምሮና ልብም ውስጥ ሰፍኖ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4:3-6፤ ዮሐ. 3:16-21፤12:35-41)::

ከዚያም ኢየሱስ «ተጠማሁ» አለ (ዮሐ. 19:28):: ወታደሩ ሆምጣጤ በመስጠት የፈጸመው የደግነት ተግባር [መዝ. (69):21 አንብብ] ጌታ ሁለት ግሩም አሳቦችን እንዲናገር አስቻለው:: «ተፈጸመ» (ዮሐ. 19:30) እና «አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ እሰጣለሁ» [ሉቃስ (23):46 እና መዝ. (31):5ን አንብብ]:: ኢየሱስ በገዛ ፈቃዱ ነፍሱን ለእኛ አኖረ እንጂ አልተገደለም (ዮሐ. 10:11፣15፣17-18):: እርሱ ለዓለም በፈቃዱ ተሠዋ እንጂ፣ በሰማዕትነት አልተገደለም::

በሞቱ ወቅት ሁለት አስደናቂ ነገሮች ተከስተዋል– የምድር መንቀጥቀጥ (ማቴ. 27:51) እና የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መተርተር:: መጋረጃው ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶ ቆይቷል፤ አሁን ግን ኢየሱስ በሞቱ ለዓለም ሁሉ «አዲስና ሕያው መንገድ» ከፍቷል (ዕብ. 10:12–22፤ በተጨማሪም፣ ዮሐ. 14:6ን

አንብብ):: ሕግ በተሰጠ ጊዜ በሲና የምድር መንቀጥቀጥ ተከስቶ ነበር (ዘጸ. 19:16-18):: አሁን ግን ሕጉ በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል፤ መርገሙም ተነሥቷል (ሮሜ 10:4፤ ገላ. 3:10-14):: ኢየሱስ በመሥዋዕትነቱ አማካኝነት ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የመሥዋዕት ሥርዓት ነፃ አውጥቶናል::

የሮማዊውን መቶ አለቃ ምስክርነት ማንበቡ አስደሳች ነገር ነው:: በተለይም ምስክርነቱ ከሮማውያንም ሆነ ከአይሁዶች ጋር ሊያጋጨው እንደሚችል ስንገነዘብ፣ ለምስክርነቱ የሚኖረን አመለካከት ከፍተኛ ይሆናል:: ከማርቆስ ዐበይት ጭብጦች አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለው ነበር (1:1፣ 11፤ 3:11፤ 5:7፤ 9:7፤14:61-62):: ይህም የእግዚአብሔር ባሪያነቱን የበለጠ ግሩም ያደርገዋል (ፊልጵ. 2:1-11)::

እስከ መጨረሻው ድረስ ሴቶች ከመቃብሩ አጠገብ ቆመው መቆየታቸው ልብን የሚነካ ነገር ነው:: ዮሐንስም እዚያው ከቆየ በኋላ የጌታችን እናት የሆነችውን ማርያምን ወደ ቤቱ ወሰዳት (ዮሐ. 19:25-27):: ታማኝ ሴቶች ዓርብ ዕለት ከመስቀሉ የተመለሱት ሰዎች ሁሉ ሄደው ካለቁ በኋላ ሲሆን፣ እሑድ ዕለት ደግሞ ከሁሉም ቀድመው መቃብሩ ዘንድ ደረሱ:: ይህ እንሞትልሃለን ብለው ከፎከሩት ደቀ መዛሙርት ሁኔታ ምንኛ እጅግ የተለየ ነበር! የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የአማኝ ሴቶች መሥዋዕትና መሰጠት ባለውለታ ነች::

## 2. የእግዚአብሔር ባሪያ ቀብር (ማርቆስ 15:42-47)

አይሁዶች ሁለት ዓይነት ምሽቶች አሏቸው:: አንደኛው ከ9-12 ሰዓት ያለው «ማምሻ» ሲሆን፣ ሁለተኛው ከ12 ሰዓት በኋላ ያለው ምሽት አዲሱ ቀን የሚገባበት ነው:: ለዚህ ነበር ማርቆስና ማቴዎስ (27:57) ዓርብ ከሰዓት ገና ቀኑ ሳይመሽ «ምሽት» ያሉት:: የአይሁድ ሰንበት ሊገባ ስለተቃረበና ያም ሰንበት ከፋሲካው የተነሣ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስለሆነ፣ ኢየሱስ የተሰቀለበት ስፍራ በፍጥነት መጽዳት ነበረበት (ዮሐ. 19:31)::

እግዚአብሔርን የሚያምን አንድ ሀብታም የሸንጐ አባል ነበር:: እርሱም የአርማትያሱ ዮሴፍ ሲሆን፣ የጌታን አስከሬን ለመቅበር ተዘጋጅቶ ነበር (ማቴ. 27:57):: ሌላው የሸንጐ አባል የነበረው ኒቆዲሞስም ዮሴፍን ረድቶታል (ዮሐ. 19:38-42)::

እነዚህ ሁለት ሰዎች ጌታን ለመቅበር የወሰኑት በድንገት ነው ብለን ልናስብ አይገባም:: ምክንያቱም ያከናወኑት ተግባር ብዙ ዝግጅቶችን የሚጠይቅ ነበርና ነው::

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ዮሴፍ ኢየሱስ ከሞተበት አካባቢ ቀረብ ብሎ በሚገኝ አትክልት ስፍራ መቃብሩን ማዘጋጀት ነበረበት:: ይህም የመቃብር ቦታ የራሱ የዮሴፍ አይመስልም:: ምክንያቱም ሀብታም ሰው ስቅላት በሚፈጸምበት አካባቢ የመቃብር ስፍራ የሚመርጥ አይመስልም:: እነዚህ ሰዎች ብዙ ቅመማ ቅመምም ማግኘት ነበረባቸው (ዮሐ. 19:39):: ይህ ደግሞ ሱቆች ለፋሲካ በዓል ሲባል ከተዘጉ በኋላ ተፈልጐ የሚገኝ አይመስልም:: ይህ ሁሉ ከሸንጐው እውቅና ውጭ መፈጸም ነበረበት::

እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ሰዎች ያዘጋጀና የመራቸው ይመስላል:: ኒቆዲሞስ ቀደም ሲል ብቻውን ወደ ኢየሱስ የመጣ ሲሆን (ዮሐ. 3)፣ በሸንጐውም ፊት ኢየሱስን የሚደግፍ ንግግር አድርጓል (ዮሐ. 7:45-53):: ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ቅዱሳት መጻሕፍትን አብረው በመመርመር በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በጉ በፋሲካ ዕለት እንደሚሞት እንደተገነዘቡ አምናለሁ:: ኢየሱስ በሞተ ጊዜ እነርሱ በአዲሱ መቃብር ላይ ቆመው የነበሩ ይመስለኛል:: የኢየሱስን ሥጋ ይሰጠው ዘንድ ለዮሴፍ ወደ ጲላጦስ ሄዶ ማስፈቀዱ ቀላል ነበር:: ለኒቆዲሞስም ሕጋዊ ፈቃድ እስኪሰጥ ድረስ የኢየሱስን ሥጋ መጠበቅ ቀላል ነበር:: እነዚህ ሰዎች በድፍረት እርምጃ ባይወስዱ ኖሮ፣ የኢየሱስ አስከሬን እዚያው እንደ ቆሻሻ ነገር ሊተው ይችል ነበር::

የከፈን ልብሶቹ በመቃብሩ ውስጥ ተለይተው መቅረታቸው መነሣቱን ስለሚያረጋግጥ ሥጋው ለቀብር መዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር (ዮሐ. 20:1-10):: የተቀበረበት ሁኔታም ትንቢትን ፈጽሟል (ኢሳ. 53:9):: መቀበሩ ራሱ ለመሞቱ ማረጋገጫ ነበር:: ምክንያቱም የሮም ባለሥልጣናት የኢየሱስን መሞት ሳያረጋግጡ ሥጋውን አይሰጡም ነበርና::

## 3. የእግዚአብሔር ባሪያ መነሣት (ማርቆስ 16:1-18)

«ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን. . .» (ሮሜ 4:25):: ሙት አዳኝ ማንንም ሊያድን አይችልም:: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የመሥዋዕትነት ሞቱን ያህል የወንጌሉ አካል ነው (1ኛ ቆሮ.15:1-8):: እንዲያውም፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በቀዳሚነት ስለ ትንሣኤው ትመሰክር ነበር (የሐዋ. 1:22፤ 4:2፣33)::

ትንሣኤው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያረጋግጣል (ሮሜ 1:4):: ለደቀ መዛሙርቱ ከሞት እንደሚነሣ የነገራቸው ቢሆንም፣ የዚህን እውነት ትርጉም አልተረዱም ነበር (ማር. 9:9-10፣31፤ 10:34):: በማለዳም ወደ መቃብሩ የመጡት ሴቶች እንኳ ከሞት ይነሣል ብለው አላሰቡም ነበር:: እንዲያውም፣ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በችኮላ የጀመሩትን ተግባር ለመፈጸም ቅመማ ቅመሞችን ገዝተው ነበር::

በወንጌላት ውስጥ የቀረቡትን ታሪኮች አንድ ላይ በምናዋህድበት ጊዜ፣ በዕለተ እሑድ ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ ለሰዎች የታየው በሚከተለው ቅደም ተከተል ይሆናል:: (1) ለመግደላዊት ማርያም (ዮሐ. 20:11-18፤ ማር. 16:9-11)፣ (2) ለሌሎች ሴቶች (ማቴ. 28:9-10)፣ (3) ለጴጥሮስ (ሉቃስ 24:34፤ 1ኛ ቆሮ. 15:5)፣ (4) ወደ ኤማሁስ ለሚሄዱ ሁለት ሰዎች (ማር. 16:12፣ ሉቃስ 24:13-32)፣ እና (5) በሰገነቱ ውስጥ ለነበሩት አሥር ደቀ መዛሙርት (ማር. 16:14፤ ዮሐ. 20:19-25)::

መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያም፣ ሰሎሜና ዮሃና (ሉቃስ 24:10) ወደ መቃብሩ የሄዱት ገና ጨለማ ሳለ ነበር (ዮሐ. 20:1)፣ የደረሱትም ገና ጐሕ ሳይቀድ ነበር (ሉቃስ 24:1):: መጀመሪያ የተደነቁት ድንጋዩ ከመቃብሩ በር ላይ ተንከባልሎ በማግኘታቸው (ማቴ. 28:2-4) እና ወደ መቃብሩ ውስጥ ሊገቡ በመቻላቸው ነበር:: በሁለተኛ ደረጃ ሁለት መላእክት ከመቃብሩ ላይ ተቀምጠው በማየታቸው ተደነቁ (ሉቃስ 24:4፤ ማርቆስ ያተኮረው በአንደኛው መልአክ ላይ ነው)፣ በሦስተኛ ደረጃ የመላእክቱን ድምፅ በመስማታቸው ተገረሙ:: ለካ ሴቶቹ ካለ ምክንያት አልተገረሙም!

መልእክቱ ኢየሱስ በዚያ እንደሌለ የሚያስገነዝብ ነበረ:: ከሞት ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ይገናኝ ዘንድ ወደ ገሊላ እየሄደ ነበር:: የከበረውን የትንሣኤ መልእክት በቀዳሚነት ያደረሱት ሴቶች

ነበሩ! ለጴጥሮስ ልዩ የማበረታቻ ቃል መስጠቱን (ማር. 16:7) እና ማርቆስ ወንጌሉን በጴጥሮስ እገዛ መጻፉን ልብ በል።

መግደላዊት ማርያም ያጋጠማትን ለመናገር ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሮጠች (ዮሐ. 20:2-10)። ከዚህ በኋላም እነርሱ ከሄዱ በኋላ በመቃብሩ ስፍራ ቆማ ቀረች። በዚህ ጊዜ ነበር ኢየሱስ የተገለጠላት (ዮሐ. 20:11-18)። ከኢየሱስ ጋር ያካሄደችው ውይይት እንደሚያስረዳው፣ መላእክቱ የነገሯትን ሙሉ በሙሉ የተረዳች አይመስልም። ነገር ግን ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ያየችው የመጀመሪያዋ አማኝ እርሷ ነበረች። ማርቆስ 16:8 ሁሉም ሴቶች ሸሹ የሚል አሳብ የሚሰጥ ይመስላል፣ ነገር ግን ቊ. 9 ደግሞ ኢየሱስን ራሷ እንዳገኘችው ይናገራል።

ኢየሱስ ማርያምን አገኘት፣ ከዚያ በኋላ ሌሎቹን ሴቶች አገኛቸው። እነዚህ ሴቶች ከመላእክቱ የሰሙትን ለሌሎች ደቀ መዛሙርት ለመናገር እየገሠገሡ ነበር (ማቴ. 28:9-10)። መጀመሪያ ሴቶቹ ፈርተው ነበር። ከሞት የተነሣውን ጌታ ካገኙት በኋላ ግን ለሌሎች ደቀ መዛሙርት የምሥራቹን አጋሯቸው (ማቴ. 28:8)። የመነሣቱን ዜና መስማትና የተነሣውን ጌታ ማግኘት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እርሱን ባገኘህበት ጊዜ ለሌሎች የምታካፍለው አንድ ነገር ይኖርሃል።

ማርቆስ 16:9-14 ያተኰረው በሰሙት የምሥራች መደሰት ሲገባቸው እያለቀሱ በሚያዝኑ ደቀ መዛሙርት ላይ ነው። ያልተደሰቱት የሴቶቹን ምስክርነት ባለማመናቸው ነበርን? ሊሆን ይችላል። የሴቶች ምስክርነት በአይሁድ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት አልነበረውም። ነገር ግን ሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች ምስክርነታቸውን በሰጡ ጊዜም ሁሉም አላመኑም ነበር። ማርቆስ 16:13ን ከሉቃስ 24:33-35 ጋር አነጻጽር። ኢየሱስ እስከተገለጠበት ጊዜ ድረስ በሰገነቱ ውስጥ የአሳብ ልዩነት የተከሰተ ይመስላል።

እርሱ በተገለጠ ጊዜ ግን ባለማመናቸው ነቀፋቸው። ይህም ከልባቸው ደንዳናነት የመነጨ ነበር (ማር. 6:52፤ 8:17 አንብብ)። የትንሣኤውን ምስክሮች ማመን እንደሚያስፈልግ ግልጽ አድርጐላቸዋል። በ16:14 «አሥራ አንዱ» የሚለው ሐረግ

«ሐዋርያቱን» ማለቱ ነው፣ ምክንያቱም ሲገለጥላቸው ቶማስ በመካከላቸው ስላልነበረ፣ አሥሩ ብቻ ነበሩ (ዮሐ. 20:19-25)::

ጌታ ከማረጉ በፊት አርባ ቀን ቆይቶ ለተከታዮቹ ጥቂት ተልዕኮዎችን ሰጥቷቸዋል (ዮሐ. 20:21፤ 21:15-17፤ ማቴ. 28:18-20፤ ሉቃስ 24:47-49፤ የሐዋ. 1:4-8):: ማርቆስ የጠቀሰው ምናልባትም ኢየሱስ በገሊላ ተራራ ላይ የሰጠውን የታላቁን ተልዕኮ ክፍል ሳይሆን አይቀርም (ማቴ. 28:16-20)::

በዚህ ተልዕኮ ውስጥ፣ ኢየሱስ መልእክታችንና አገልግሎታችንን ከገለጸ በኋላ፣ እርሱ ብቻ በሚሰጠው ተአምር አስደግፎታል:: መልእክቱ ወንጌሉ ነው:: ይህም:- ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ስለሚያገኘው ደኅንነት የሚናገር የምሥራች ነው:: አገልግሎቱም ይህንኑ መልእክት ለዓለም ሁሉ ማካፈል ነው::

ማርቆስ 16:15-16ን ላይ ላዩን ሲመለከቱት፣ ኃጢአተኞች ደኅንነትን ለማግኘት መጠመቅ አለባቸው የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ ይመስላል:: ነገር ግን ትኩረት የተሰጠው በማመን ላይ መሆኑን ስትገነዘብ፣ ይህ የተሳሳተ አተረጓጎም ይወገዳል:: አንድ ሰው እስካላመነ ድረስ ቢጠመቅም እንኳ መኮነኑ የማይቀር ነው (ዮሐ. 3:16-18፣36 አንብብ):: በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይጠመቁ ነበር ተብሎ ይገመት ነበር (የሐዋ. 2:41፤ 10:44-48)::

እግዚአብሔር በግብጽ ፈርዖንን ለመገዳደር ሙሴን በላከ ጊዜ፣ ልዩ ተአምራት እንዲፈጽም አድርጓል:: እነዚህም ተአምራት ከእግዚአብሔር ተልኮ መምጣቱን የሚያረጋግጡ ነበሩ (ዘጸ. 4:1-9):: ይህ በአንዳንድ ነቢያትም አገልግሎት ውስጥ ተከስቷል (1ኛ ነገ. 18፤ 2ኛ ነገ. 2:14-25):: ለሐዋርያትም መልእክታቸውን የሚያጠናክሩ «ምልክቶች» ተሰጥተዋቸዋል ( ዕብ. 2:3-4፤ 2ኛ ቆሮ. 12:12፤ የሐዋ. 19:11-12):: ተአምራት በራሳቸው አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ተልኮ መምጣቱን አያረጋግጡም:: ምክንያቱም መልእክቱም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መጣጣም አለበትና (2ኛ ተሰ. 2፤ ራእይ 13 አንብብ)::

በዚህ ስፍራ የተዘረዘሩት አብዛኞቹ ምልክቶች በሐዋርያት ዘመን የተፈጸሙና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ

ናቸው:: እባብን ከመያዝ ጋር በጣም የሚቀራረበው ጳውሎስ በማልታ የታየው ገጠመኝ ነው (የሐዋ. 28:3-6):: ነገር ግን አንድ ሰው መርዝ ጠጥቶ አለመጐዳቱን የሚያሳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የለንም:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ እኛ የማናውቃቸውን ተአምራት መሥራቱ የሚያጠራጥር አይሆንም:: ስለ እነዚህ ነገሮች መንግሥተ ሰማይ ስንደርስ እናውቃለን::

መልካም አስተሳሰብ ያላቸው፣ ዳሩ ግን በቂ እውቀት የሌላቸው ክርስቲያኖች እነዚህ ምልክቶች ለእነርሱ እንደ ተሰጡ አድርገው በመውሰድ በመርዝ ወይም በእባብ ንድፊያ መሞታቸው አሳዛኝ ነገር ነው:: እንዲህ ዓይነት አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ በቂ እምነት ስለሌላቸው ነው ሲባል እንሰማለን:: ነገር ግን በእምነት ያልሆነ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው (ሮሜ 14:23):: ስለሆነም፣ ቀድሞውኑ ይህንን ማድረግ አይገባቸውም ነበር::

እምነት እንዳለ ለማሳየት እባብን የሚይዝ ሰው ሰይጣን በቤተ መቅደስ ጫፍ ለኢየሱስ ባቀረበለት ፈተና ውስጥ ራሱን እየከተተ ነው (ማቴ. 4:5-7):: ሰይጣን፣ «ከዚህ ከፍታ ላይ ራስህን ወርውርና እግዚአብሔር ያድንህ እንደሆነ ተመልከት» ነበር ያለው:: ሰይጣን በእምነታችን «እንድንኩራራ»ና እግዚአብሔር አላስፈላጊ ተአምራቶችን እንዲፈጽም እንድናስገድደው ይፈልጋል:: ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለመፈታተን አልፈለገም:: እኛም የእርሱን ምሳሌነት ልንከተል ይገባል:: በእርግጥ እግዚአብሔር ልጆቹ በፈቃዱ እየተመላለሱ እያለ አደገኛ ሁኔታ በሚገጥማቸው ጊዜ ይረዳቸዋል:: ነገር ግን በሞኝነት ከፈቃዱ በምንወጣበት ጊዜ እኛን የመርዳት ግዴታ የለበትም:: በእምነት እንጂ በዕድል እንድንመላለስ አልተጠራንም:: በእግዚአብሔር እንድንተማመን እንጂ እንድንፈታተነው አልተጠራንም::

## 4. የእግዚአብሔር ባሪያ ዕርገት (ማርቆስ 16:19-20)

የማርቆስ ወንጌል በሚያስደንቅ ሁኔታ ታላቁ «የእግዚአብሔር ባርያ ምንባብ»ን ከፊልጵስዩስ 2 ጋር ያመሳስለዋል::

ባሪያ ሆኖ መጣ (ፊልጵ. 2:1-7) – ማር. 1-13

በመስቀል ላይ ሞተ (ፊልጵ. 2:8) – ማር. 14-15

ወደ ክብር ዐረገ (ፊልጵ. 2:9) – ማር. 16

ጳውሎስም ሆነ ማርቆስ የእግዚአብሔር ሕዝብ መልእክቱን ለሕዝቦች ሁሉ ማድረስ እንዳለባቸው አስረግጠው አስረድተዋል (ፊልጵ. 2:10-11፤ ማር. 16:15-16):: እግዚአብሔር በሕዝቡ እንደሚሠራ የሚያመለክት ተጨማሪ ማረጋገጫም ተሰጥቷል (ፊልጵ. 2:12-13፤ ማር. 16:19-20)::

የጌታችን ዕርገት የምድራዊ አገልግሎቱን ፍጻሜና በሰማይ አዲስ አገልግሎት መጀመሩን ያመለክታል:: አዲስ አገልግሎት ለሕዝቡ እንደ ሊቀ ካህናትና ጠበቃ የሚያከናውነው ተግባር ነው (ዕብ. 7-10፤ 1ኛ ዮሐ. 2:1-3):: «የእግዚአብሔር ቀኝ» የክብርና የሥልጣን ስፍራ ነው [መዝ. (110):1፤ 1ኛ ጴጥ. 3:22]:: ጌታችን እንደ መልከ ጼዴቅ የጽድቅና የሰላም ንጉሥ ነው (ዘፍጥ. 14:17-19፤ ዕብ. 7:2)::

ከሰማያዊ አገልግሎቶቹ አንዱ ሕዝቡ ፈቃዱን እንዲፈጽም ማስቻል ነው (ዕብ. 13:20-21):: የንጉሥ ወንጌል የሆነው ማቴዎስ ታላቅ ሥልጣኑን በማመልከት እንደ ተጠናቀቀ ሁሉ፣ ይህ የባሪያ ወንጌል ሥራን በማመልከት መጠናቀቁ ተገቢ ነው:: ጌታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በእኛ ውስጥ (ፊልጵ. 2:12-13)፣ ከእኛ ጋር (ማር. 16:20) እና ለእኛ (ሮሜ 8:28) ለመሥራት ይተጋል::

ሐዋርያትና ነቢያት ለቤተ ክርስቲያን መሠረት ስለጣሉ (ኤፌ. 2:20)፣ ሥራቸው ተጠናቅቋል፤ ሐዋርያዊ ምልክቶችም አብቅተዋል:: የጌታ ሥራ ግን አላበቃም:: በሕዝቡ አማካኝነት ይህን የጠፋ ዓለም ለማዳን እየሠራ ነው:: ባሪያው ልጁ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ቢመለስም፣ ባሪያዎቹ ሊሆኑለት የሚችሉ ሕዝቦቹ በምድር ላይ አሁንም አሉለት::

ጌታ ከእኛ ጋር መሥራቱ ምንኛ ታላቅ ዕድል ነው!

ወንጌሉን ለዓለም ሁሉ ማዳረስ ምንኛ ታላቅ ዕድልና ግዴታም ነው!

«የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማር. 10:45)::

አንተ እያገለገልህ ነው -- ወይስ ሌሎች እንዲያገለግሉህ እየጠበቅህ ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ

## እነሆ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ

(ማርቆስ 1)

1. ከኢየሱስ ሕይወት የባርያነት መንፈሱን የሚያሳይህ ምንድን ነው?
2. ሮማውያን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመቀበል የነበረባቸው ችግር ምን እንደ ነበረ ግለጽ::
3. ከማርቆስ ወንጌል ስለ የምሥራቹ ሦስት ነጥቦችን ዘርዝር::
4. የኢየሱስ ጥምቀት የባርነት ሚናውን እንዴት ያንጸባርቃል?
5. የኢየሱስ መፈተን ባርነቱን የሚያንጸባርቀው እንዴት እንደሆነ አንዳንድ መንገዶችን ጥቀስ::
6. የአንድ ሰው የሥልጣን አስተሳሰብ ስለ ባርነቱ ምን ያስረዳል?
7. ኢየሱስ በአጋንንት ላይ ሥልጣኑን በገለጸ ጊዜ ሁኔታውን የሚመለከቱት ሰዎች ስለ እርሱ ምን ተማሩ?
8. ኢየሱስ የታመሙትን ሲፈውስ፣ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ባርያነቱ ምን ተረዱ?
9. የኢየሱስ ዓይነት ባሪያዎች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው?
10. በባርነት ውስጥ ርኅራኄ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሁለት

## የባሪያው ገጸ በረከት

(ማርቆስ 2:1-3:12)

1. የኢየሱስን ምሳሌነት ተከትለን ለጸሎት ጊዜ እንዳንወስድ የሚከለክሉን ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. በሕይወታችን የጸሎት ጊዜ የሚፈጽማቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር::
3. ጓደኛቸውን ኢየሱስ ይፈውሰው ዘንድ ጣሪያ ቀድደው ካወረዱት አራት ሰዎች ታሪክ በጣም ያስደነቀህ ምንድን ነው?
4. በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ ኢየሱስ የሰውዬውን ኃጢአት ይቅር ማለቱ ሰውነቱን ከመፈወሱ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
5. ኢየሱስ የማይወደዱ ሰዎች ጓደኛ ለመሆን መርጧል:: እኛስ በግንኙነቶቻችን ውስጥ ይህንን የምናዘወትረው እንዴት ነው?
6. ክርስቲያን መሆን በጋብቻ ሥርዓት ውስጥ «ቃል እገባለሁ» ከማለት ጋር የሚመሳሰልባቸውን መንገዶች ዘርዝር::
7. ክርስትና በዘመናችን ካሉ የዓለም ሃይማኖቶች የሚለየው እንዴት ነው?
8. ዌርዝቢ፣ «ክርስትና የሰውን ሕይወት በከፊል መጠገን ሳይሆን፣ ፍጹም አዲስ ጽድቅ ነው» ብለዋል:: ሕይወትን በከፊል መጠገን ምን እንደሚመስል ግለጽ::
9. ኢየሱስ በሰንበት ቀን እንዳለመሥራት ያሉትን ልማዶች አፍርሷል:: ይህንን ለማድረግ የቻለው ለምን ይመስልሃል?
10. በአንዳንድ መንገዶች ኢየሱስ በልማዳዊ ሃይማኖት ላይ ዓመፅን እየመራ ነበር:: የኢየሱስን ዓመፅ እንዴት ትገልጸዋለህ?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሦስት

## ባሪያው፣ ሕዝቡና መንግሥቱ

(ማርቆስ 3:13-4:34)

1. በዝነኝነትና በአገልጋይነት መካከል ያሉትን አንዳንድ ልዩነቶች ዘርዝር::
2. ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ላቀረበላቸው ግብዣ ምላሽ በመስጠት ኑሯቸውን ትተው እንዲከተሉ ያደረገው ምን ይመስልሃል?
3. ክርስቲያን መሆን የአዲስ ቤተሰብ አባል ከመሆን ጋር የሚመሳሰል ከሆነ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚሄዱ ኃላፊነቶች ምን ምን ናቸው?
4. በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁዶች ኢየሱስ አዲስ መንግሥት የሚመሠርት መስሏቸው ነበር:: ኢየሱስ ሊመሠርት የመጣው መንግሥት ምን ዓይነት ነበር? ግለጽ::
5. በኢየሱስ ዘመን የነበሩት የአይሁድ መሪዎች የኢየሱስን ታዋቂነት የፈሩት ለምን ነበር? አንዳንድ ምክንያቶችን ጻፍ::
6. ምሳሌዎች ለኢየሱስ ጠንካራ የማስተማሪያ መንገዶች የነበሩት ለምንድን ነው?
7. ዛሬ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ስትመለከት፣ በዘሪው ምሳሌ ውስጥ ከተጠቀሱት ከደንዳና ልቦች፣ ከጭንጫ ልቦች፣ ከተጣበቡ ልቦች፣ ወይም ከታመኑ ልቦች ጋር የምታነጻጽራቸው የትኞቹን ዘሮች/ልቦች ነው? ለምን?
8. ሕይወታችን ከብርሃን ጋር የሚመሳሰልባቸውን መንገዶች ዘርዝር (ማር. 3:21)::
9. በአካባቢህ ሲከሰት የተመለከትኸውንና ሰይጣን በክርስቶስ ሥራ ላይ ያነሣሣው ነው ብለህ ያሰብኸውን አንድ ክስተት ግለጽ::
10. ኢየሱስ ባዛሬው ዘመን ቋንቋ አንድን ሰው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እንዴት የሚጋብዝ ይመስልሃል?

# የማጥኛ ጥያቄዎች
## ምዕራፍ አራት

## ባሪያው ያሸንፋል!

(ማርቆስ 4:35-5:43)

1. ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ተአምራትን ሲሠራ እየተመለከቱና ትምህርቱን እያዳመጡ፣ ማዕበሉን ጸጥ በማሰኘቱ የተደነቁት ለምን ይመስልሃል?
2. ብዙውን ጊዜ ስለ አንድ ጉዳይ ጸልየን እግዚአብሔር ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ የምንደነቀው ለምንድን ነው?
3. አስቸጋሪ ሁኔታዎች እግዚአብሔር የሚያደርግልንን እንክብካቤ እንድንጠራጠር የሚያደርጉት ለምንድን ነው?
4. ችግር የሌለበት ቀለል ያለ ሕይወት ብንኖር እምነታችን የሚለመልም ይመስልሃል?
5. ቁርዝቢ ሰይጣን አጋንንቱ የያዟቸውን ሰዎች ሥራ፣ ቤተሰብ፣ ወዳጆችና ያሏቸውን ሁሉ እንደወሰደ አብራርተዋል:: ሰይጣን ዛሬ ተመሳሳይ ተግባር የሚፈጽመው እንዴት ነው?
6. ደም ይፈስሳት የነበረችው ሴት ኢየሱስ ይፈውሳት ዘንድ በሕዝቡ መካከል እየተጋፋች ማለፏ ምን ያህል ቆራጥነትና እምነት የጠየቃት ይመስልሃል?
7. ኢያኢሮስ ጌታ ልጁን እንዲፈውስለት ለመጠየቅ በሄደ ጊዜ፣ የዚህችን ሴት መፈወስ ተመልክቷል:: አንተ በኢያኢሮስ ቦታ ብትሆን ምን ዓይነት ስሜት ይሰማህ ነበር?
8. ኢያኢሮስ ልጁ እንደ ሞተች ከሰማ በኋላ እንኳ ተስፋ ላለመቁረጥ ምን ዓይነት እምነት ጠይቆታል?
9. ኢየሱስ በድሆች መካከል ሲመላለስ፣ ማንን እንደሚረዳ የሚወስነው እንዴት ነበር?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አምስት

## የእግዚአብሔርን ባሪያ የሚያምን ሰው ይኖር ይሆን? (ማርቆስ 6:1-56)

1. በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ማመን ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከኢየሱስ ሕይወት በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንድታምን የሚያደርግህ ነገር ምንድን ነው?
3. የናዝሬት ሰዎች ለኢየሱስ ትኩረት እንዳይሰጡ ያደረገው «የአገር ልጅነት» መስፈርት ምን ነበር?
4. የናዝሬት ሰው ብትሆን ኖሮ ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለመቀበል ከሁሉም በላይ የሚፈታተንህ ምን ሊሆን ይችል ነበር?
5. የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ትልቁ ችግር ምን ይመስልሃል?
6. የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን የሚያስከትለው ትልቁ ደስታ ምን ይመስልሃል?
7. የመጥምቁ ዮሐንስ ራስ ተቆርጦ በወጭት እንዲመጣ የጠየቀችውን የሄሮድስ ሚስት ዛሬ ከየትኛው ዓይነት ክፋት ወይም መጥፎ ባሕርይ ጋር ታዛምዳለህ? አብራራ።
8. ኢየሱስ ከትንሽ ምሳ የተራቡትን 5,000 ሰዎች በመገበ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያስተማራቸውን ነገሮች ዘርዝር።
9. ማዕበል እየተነሣ ሳለ ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ጀልባ በመጣ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን አስተማረ?
10. በጴጥሮስ እምነትና ውኃ ላይ ለመራመድ በመቻሉ መካከል የነበረው ግንኙነት ምንድን ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች
## ምዕራፍ ስድስት

## ባሪያው - አስተማሪ
(ማርቆስ 7:1-8:26)

1. የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይነት በሥልጣናቸው ከሕዝቡ ጥቅም ለማግኘት ከሚፈልጉት የዘመኑ የሃይማኖት መሪዎች የሚቃረን ነበር:: ዛሬ ይህንኑ ተመሳሳይ ችግር የምንመለከተው እንዴት ነው?
2. እግዚአብሔርን በውጫዊ ሥርዓቶች መታዘዝ ምን ያህል እንደሚቀልህ ውጤቱን ከ 10 ጻፍ (1. በጣም ከባድ፣ 10. በጣም ቀላል) እና በልብህ ባሕርይ አለመታዘዙ ምን ያህል እንደሚከብድህ ግለጽ:: ይህ ምን ዓይነት መንፈሳዊ ችግር ይፈጥራል?
3. የረዥም ዘመን ልማዶች አዎንታዊ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?
4. የረዥም ዘመን ልማዶች አሉታዊ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?
5. በአካባቢህ የምትመለከታቸውና ኢየሱስ ይገሥጻቸው ነበር ብለህ የምታስባቸው ግብዝነቶች ምን ምን ናቸው?
6. የእግዚአብሔር እውነት ከቤተ ክርስቲያን ባህል ጋር ምን ያህል ጊዜ በተደጋጋሚ የሚጋጭ ይመስልሃል?
7. ዌርዝቢ፣ «ታላቅ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚያርፍና እግዚአብሔር ምላሽ እስኪሰጥ ድረስ የማይተው ነው» ብለዋል:: ያየኸውን፣ የሰማኸውን ወይም በሕይወትህ የተለማመድኸውን አንድ የታላቅ እምነት ተግባር ግለጽ::
8. ኢየሱስ በተአምራቱ የሰዎችን ችግሮች አቃልሏል:: ይህ እግዚአብሔር ችግሮቻችንን ስለሚፈታበት መንገድ ምን ያስተምረናል?
9. ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ተአምራት ቢመለከቱም፣ ችግሮች በሚገጥሟቸው ጊዜያት መፍራታቸው አልቀረም ነበር:: እግዚአብሔር በችግራችን ከረዳን በኋላ፣ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ አሁንም የምንፈራው ለምንድን ነው?
10. የሐሰት አስተምህሮ እንደ እርሾ የሚሆነው እንዴት ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሰባት

## የባሪያው ምሥጢራት

(ማርቆስ 8:27-9:50)

1. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በሚያስተምርበት አንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ብትገኝ፣ ምን ዓይነት ጥያቄ ታቀርብለት ነበር?
2. ብዙ ሰዎች ተአምራቱን እየተመለከቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመረዳት ያልቻሉት ለምንድን ነው?
3. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መጭው ሞቱ በተናገረበት ስብሰባ ላይ ብትገኝ ኖሮ፣ በአእምሮህ ምን ዓይነት አሳቦች ይመጡብህ ነበር?
4. በኢየሱስ ሕይወት በ«መከራ» እና «ክብር» መካከል የነበረው ግንኙነት ምንድን ነው?
5. ዌርዝቢ እንደሚሉት፣ ኢየሱስ ሕዝቡ ተአምራቱን ለማየት እንደሚከተሉት ያውቅ ነበር:: ኢየሱስ ለምን ምክንያት ቢከተሉት ይወድ ነበር?
6. የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የመሆን ዋጋ ምንድን ነው?
7. እንደ ጴጥሮስ ለዘለቄታው እዚያው ለመቆየት የፈለግህበት የተራራ ጫፍ ገጠመኝ አጋጥሞህ ያውቃል? አጋጥሞህ ከሆነ፣ አብራራ::
8. ማርቆስ 9:24ን አንብብና እንደዚህ አባት ችግር ገጥሞህ ወደ እግዚአብሔር የመጣህበትን ጊዜ ግለጽ::
9. ኢየሱስ ስለ ትሕትና ለማስተማር ሕፃን ልጅ ተጠቅሟል:: ሕፃን ልጅ በምትመለከትበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ስላስተማረው ትሑት ባሪያ ምን ተንጸባርቆበት ታያለህ?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ስምንት

## የባሪያው አያዎዎች

(ማርቆስ 10)

1. በአሁኑ ወቅት ማኅበረሰባችን ስለ ፍቺ ያለውን አመለካከት እንዴት ትገልጸዋለህ?
2. ኢየሱስ ስለ ፍቺ ባስተማረ ጊዜ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሴቶችን ደረጃ ካሉበት ከፍ ያደረገው እንዴት ነው?
3. ልጆች እግዚአብሔርን ስለ መከተል ምን አስተምረውሃል?
4. በኢየሱስ ዘመን መካንነት እንደ መርገም፣ ልጅን መውለድ ግን እንደ በረከት ይቈጠር ነበር:: ይህ ዛሬ ስለ ልጆች ከምንመለከተው አስተሳሰብ ጋር እንዴት ይነጻጸራል?
5. ቄርዝቢ በማርቆስ 10 ውስጥ የተጠቀሰው ወጣት ሹም መታዘዝን በውስጣዊ ባሕርያት ሳይሆን በውጫዊ ተግባራት እንደ መዘነ ገልጸዋል:: መታዘዝን መለካት የሚገባን ተገቢው መንገድ ምንድን ነው?
6. በሕይወትህ ስለ ገንዘብና ቀዳሚነቱ ምን ተምረሃል?
7. ከክርስቶስ የአገልጋይነት አመራር አንጻር፣ ደቀ መዛሙርቱ ከመካከላችን ታላቁ ማን ነው? በሚል አሳብ መወዛገባቸው የማይታመን ይመስላል:: ከሰው ልጅ ባሕርይ አንጻር ግን ይህ እንዴት የተከሰተ ይመስልሃል?
8. የአገልጋይነት ልብ ያለው ሰው ግሩም መሪ የሚሆነው ለምንድን ነው?
9. ኢየሱስ በርጤሜዎስን እንደጠየቀው፣ «ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?» ቢልህ ምን ምላሽ ትሰጠዋለህ?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የእግዚአብሔር ባሪያ በኢየሩሳሌም
## (ማርቆስ 11:1-12:44)

1. የኢየሱስ መልእክትም ሆነ መገኘት በዘመኑ ከነበሩት ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ መሪዎች ተጋጭቷል። ይህ ዛሬም እውነት የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በድል ሲገባ አቀባበል ያደረጉለት ሰዎች ምን ሊያደርግ እንደ መጣ በትክክል አልተረዱም ነበር። ሲያከብሩ የነበሩት ምንን ነበር?
3. በኢየሱስ ዘመን የነበረችው እስራኤል «ፍሬያማ» ያልነበረችው እንዴት ነበር?
4. የበለስ ዛፏ በተአምር መጠውለጓ ለደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔር ለእስራኤል ስላለው ፍላጎት ምን አስተማራቸው?
5. ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ ከጸሎትና አምልኮ ይልቅ ለንግድ አገልግሎት በመዋሉ ተቆጥቷል። ዛሬ በባሕላችን ውስጥ ያንን የሚመስል ነገር ይፈጸማል? እንዴት?
6. ዊርዝቢ፣ «ጌታ ኢየሱስ በጸሎት ቤቶቻችን ውስጥ ቢገኝ፣ ምን ይለውጥ ይሆን?» ሲሉ ጠይቀዋል። ምን የሚለውጥ ይመስልሃል?
7. በማርቆስ 12:1-9 የተሰጠውን ምሳሌ ድምፅህን ከፍ አድርገህ አንብብ። ልጁ ኢየሱስን፣ ሠራተኞቹ የሃይማኖት መሪዎችን ከወከሉ፣ ሊሰርቁ የፈለጉት ውርስ ምን ነበር?
8. መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሾማቸው ቢናገርም እንኳ ለመንግሥት ባለሥልጣናት መገዛት አስቸጋሪ የሚሆንባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
9. ምድር ላይ ባልና ሚስት ወይም ፍቅረኛሞች የነበርን ሰዎች በመንግሥተ ሰማያት ስንተያይ የነበረን ተዛምዶ እንዴት ይሆናል ብለህ ታስባለህ?
10. ያላትን ሁሉ እንደሰጠችው ችግረኛ መበለት ለእግዚአብሔር ልንሰጥ የምንችለው እንዴት ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥር

## የእግዚአብሔር ባሪያ ወደፊት የሚሆነውን ገለጠ

(ማርቆስ 13)

1. ኢየሱስ መቼ ወደ ምድር የሚመለስ ይመስልሃል?
2. የሚመለስበትን ትክክለኛ ጊዜ መመርመሩ ምን ያህል አስፈላጊ ይመስልሃል?
3. የመጨረሻው ምእተ ዓመት «ሐሰተኛ ክርስቶሶች» እነማን ነበሩ?
4. የክርስቶስን መመለስ ስንጠባበቅ ሳለ አንዳንድ ጊዜ ሕይወት ተስፋ አስቆራጭ የሚሆነው እንዴት ነው?
5. ሃይማኖታዊ ስደት የደረሰበት የምታውቀው ሰው ማን ነው?
6. በዛሬው ዓለም ውስጥ ሃይማኖታዊ ስደት ሲጨምር የምትመለከተው እንዴት ነው?
7. ስለ ኢየሱስ መመለስ የሚናገሩ የዓለማችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
8. ስለ ኢየሱስ መመለስ የሚያሳዩ የዓለማችን የአየር ንብረቶች ምን ምን ናቸው?
9. ከትንቢት ግንዛቤህ፣ የሚያስፈሩህ የመጨረሻው ዘመን ክፍሎች አሉን? ከሆነ፣ ምን?
10. በዕለት ተዕለት ሕይወታችን፣ ለክርስቶስ ምጽአት ንቁዎች ሆነን ልንጠብቅ የምንችለው እንዴት ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## የእግዚአብሔር ባሪያ ሲሠቃይ

(ማርቆስ 14:1-15:20)

1. ከኢየሱስ ጋር ለመሆንና እርሱን ለማክበር ጊዜ በመውሰድ እንደ ማርያም ለእርሱ ቀዳሚውን ስፍራ ልንሰጥ የምንችለው እንዴት ነው?
2. ማርያም ጌታን ሽቶ በቀባች ጊዜ መልካም መዓዛ ቤቱን አውዶታል። የራሳችን አምልኮ ቤታችንን በጣፋጭ ሽታ የሚሞላው እንዴት ነው?
3. አንተ በመጨረሻው እራት ላይ የተገኘህ ደቀ መዝሙር ብትሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ አሳልፎ የሚሰጠው ከመካከላችሁ አንዱ እንደሆነ በሚናገርበት ጊዜ ምን ታስብ ነበር?
4. ኢየሱስ በአትክልቱ ስፍራ ሲጸልይ ደቀ መዛሙርቱ ተኝተው ነበር። ግድየለሾች እንዲሆኑ ባደረጋቸው ሁኔታ ላይ የነበራቸው እይታ ምን ይመስልሃል?
5. ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ለመያዝ ተንጋግተው መምጣታቸው የኢየሱስን ባሕርይ ስለመረዳታቸው ወይም ስላለመረዳታቸው ምን ያሳይሃል?
6. ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ከካደ በኋላ ዶሮ ጮኸአል። አንተ ራስህ ጴጥሮስ ብትሆን ኖሮ ምን ይሰማህ ነበር?
7. ዛሬ አንዳንድ ጊዜ ክርስቶስን የምንክደው እንዴት ነው?
8. ሕዝቡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በድል አድራጊነት በገባ ጊዜ መልካም አቀባበል ካደረጉለት በኋላ፣ ተይዞ ሲመረመርና ሲሰቀል ጥላቻቸውን ገልጸውለታል። ይህንን የባሕርይ ለውጥ እንዴት ታብራራዋለህ?
9. በኢየሱስ ላይ የቀረበው ክስ «ንጉሥ ነኝ ብሏል። ሕዝቡን ለዓመፅ ቀስቅሷል» የሚል ነበር። እነዚህ ክሶች እውነት ወይም ሐሰት የሚሆኑት እንዴት ነው?

# የማጥኛ ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የእግዚአብሔር ባሪያ ሥራውን ፈጸመ

(ማርቆስ 15:21-16:20)

1. ኢየሱስ ለማሸነፍ የሚያስችል ኃይል እንዳለው እያወቀ ሥቃይና ሞትን ተጋፍጧል:: እንዲህ ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ምን ያህል ቈራጥነት እንደሚጠይቅ ግለጽ::
2. ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉት ሌቦች አንዱ የኢየሱስን እርዳታ እንዲጠይቅ ያነሣሣው ምን ይመስልሃል?
3. በኢየሱስ ዘመን የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች በሚሰቀልበት ስፍራ ቆመው መሳለቃቸው ምን ጥላቻ እንዳደረባቸው ያሳያል?
4. ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት እንደ በር የሚያገለግለው መጋረጃ ተቀድዷል:: ይህ ወደ እግዚአብሔር ስለ መቅረብህ ምን ዓይነት ተምሳሌታዊ መልእክት ያስተላልፍልሃል?
5. በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ መሃከል ባለው ጊዜ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ ምን ዓይነት ውይይቶችን ሲያካሂዱ የቆዩ ይመስልሃል?
6. ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልሞተና ዳኑ ግን አምልጦ ከሄደ በኋላ እንደ ተመለሰ በመግለጽ ለሚከራከሩት ሰዎች ምን ምላሽ ትሰጣለህ?
7. ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ እስካረገበት ጊዜ ድረስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምን ዓይነት ትዝታዎችን የተጋሩ ይመስልሃል?
8. የኢየሱስ ትንሣኤ በዕለት ተዕለት ኑሮህ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድርብህ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?
9. ኢየሱስ ወደ ሰማይ በዐረገ ጊዜ ተልዕኮና ኃላፊነት ሰጥቶናል:: ይህንኑ ተልዕኮ የምትወጣው እንዴት ነው?

# «... ሁን» በሚል ርእስ ታትመው በስርጭት ላይ የሚገኙ መጻሕፍት

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ተግተህ አገልግል (የማርቆስ ወንጌል)
3. ርኅሩኅ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 1–13)
4. የበረታህ ሁን (የሉቃስ ወንጌል 14–24)
5. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋ. ሥራ 1–12)
6. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13–28)
7. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
8. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
9. አርነት መውጣት (ገላትያ)
10. ፍለጋ የሌለውን ባለጸግነት ውረስ (ኤፌሶን)
11. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
12. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
13. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ)
14. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶና ፊልሞና)
15. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
16. ተስፋ አድርግ (1ኛ ጴጥሮስ)
17. ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
18. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
19. በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)
20. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)

## ከ 60 ሺህ በላይ የ«... ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት ታትመዋል!

*እግዚአብሔርንና ሌሎችንም እንዴት በጽናት እንደምታገለግል!*

የማርቆስ ወንጌል በዘመናችን ጥድፊያ ለበዛባቸው ሰዎች የሚሆን ትክክለኛ ወንጌል ነው:: በዚህ ጥናት፣ ዶ/ር ዌርዝቢ የሚያተኩሩት በአገልጋዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው:: እርሱ ሁልጊዜ በጉዞ ላይ ሲሆን፣ ሁልጊዜም የአባቱን ፈቃድ ያደርግና ሌሎችን ያገለግል ነበር:: ማርቆስ ሥራ ለሚበዛባቸውና ሕይወታቸው እግዚአብሔርን የሚያስከብር እንዲሆን ለሚፈልጉ ሰዎች ተስማሚ ወንጌል ነው::

ማርቆስ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ላይ ያቀረበውን ኃይለኛ ትዕይንታዊ ገለጻ ማጥናት ኢየሱስን እንደ እንከን የሌለው የእግዚአብሔር ባሪያ አድርገህ ለመቀበል ይረዳሃል:: ለጌታ በምታበረክተው አገልግሎትህ መበረታታትና መጽናናትን ታገኝበታለህ. . . በተጨማሪም

# ተግተህ እንድታገለግል

በጣም ይረዳሃል!

ዶ/ር ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ በግራንድ ራፒድስ፣ ሚሺጋን በሚገኘው ኮርነርስቶን ኮሌጅ ጸሐፊ፣ እና በግራንድ ራፒድስ ባፕቲስት ሴሚናሪ የስብከት ዘዴ ትምህርት ፕሮፌሰር ናቸው:: በቺካጎ የሚገኘውን የሙዲ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ሦስት ቤተ ክርስቲያናትን በመጋቢነት ያገለገሉ ሲሆን፣ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» ለተባለው የሬድዮ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተርና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ሆነው አገልግለዋል:: እነዚህን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማብራሪያዎችን ጨምሮ፣ ከ100 በላይ መጻሕፍትን ጽፈው ለንባብ አብቅተዋል::

*የግል እና የቡድን የጥናት መምሪያም ተካትቷል::*

**Be Diligent**

**Printed by SIM Press**